# ኦሪት ዘፀአት

| ምዕራፍ ፩ ። | | ምዕራፍ ፩ ። |
|---|---|---|
| ዝ ውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል እለ በኡ ብሔረ ግብጽ ምስለ ያዕቆብ አቡሆሙ ብእሲ ብእሲ ወቤቱ። | ፩ | አንዱም አንዱም ሰው ወገኑን ከአባታቸው ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብጽ አገር የገቡ የያዕቆብ ልጆች ስማቸው ይህ ነው፤ ዘፍ፡ ፵፮ ፳፫ ። ዘፀ፡ ፮ ፲፬ ። |
| ሮቤል ፡ ወስምዖን ፡ ወሌዊ ፡ ወይሁዳ ። | ፪ | ሮቤል ፡ ስምዖን ፡ ሌዊና ይሁዳ ። |
| ይሳኮር ፡ ወዛብሎን ፡ ወዳን ። | ፫ | ይሳኮር ፡ ዛብሎንና ዳን ። |
| ንፍታሌም ወጋድ ወአሴር ወብንያም ። | ፬ | ንፍታሌም ፡ ጋድ ፡ አሴርና ብንያም ናቸው ። |
| ወዮሴፍሰ ሀሎ ብሔረ ግብጽ ወኮነት ኵላ ነፍስ እንተ እምያዕቆብ ሰብዓ ። | ፭ | ዮሴፍ ግን (ከወንድሞቹ ተለይቶ) በግብጽ አገር ይኖር ነበር ፡ ከያዕቆብ ጋራ ወደ ግብጽ የወረደች ሰውነት ሁሉ ሰባ ናት ። ዘፍ፡ ፵፮ ፳፯ ። ዘዳ፡ ፲ ፳፪ ። |
| ወሞተ ዮሴፍ ወኵሉ አኀዊሁ ወኵሉ ውእቱ ትውልድ። | ፮ | ዮሴፍ ሞተ ፡ ወንድሞቹም ሁሉ ሞቱ ፡ ይህም ትውልድ ሁሉ ወገን ሞቱ ። ዘፍ፡ ፶ ፳፮ ። |
| ወበዝኁ ደቂቀ እስራኤል ወመልኡ ወኮኑ ሕቁራነ ወጸንዑ ጥቀ ዕዙዘ ወመልአት ምድር እምኔሆሙ ። | ፯ | የእስራኤል ልጆች በዝተው (አገሩን ሁሉ) መሉት ፡ በግብጻውያንም ዘንድ የተጠሉ ሆኑ ፡ እጅግም በረቱ ፡ ከብዛታቸውም የተነሣ ምድር መላች ። ዘፍ፡ ፩ ፩ ፳፩ ። |
| ወተንሥአ ካልእ ንጉሥ ዲበ ግብጽ ዘኢየአምሮ ለዮሴፍ ። | ፰ | በግብጽም ዮሴፍን የማያውቀው ሌላ ንጉሥ ተነሣ ። ዘፀ፡ ፪ ፳፫ ። ግብ፡ ሐዋ፡ ፯ ፲፰ ። |
| ወይቤሎሙ ለሕዝቡ ናሁ ሕዝበ ደቂቀ እስራኤል ዐቢይ ወብዙኅ ወይጸንዑነ ። | ፱ | ሕዝቡንም እንዲህ አላቸው፤ የእስራኤል ልጆች ወገኖች እነሆ ፈጽመው በዙ በኛም ይጸኑብናል ። |
| ንዑ ንጠበቦሙ እስመ እምከመ በዝኁ ወእምከመ በጽሐነ ፀብእ ይትዌሰኩ እሉኒ ዲበ ፀርነ ወይፀብኡነ እምድኅሬነ ወያወጽኡነ እምድርነ ። | ፲ | ከበዙም ሰልፍ በደረሰብን ጊዜ እሊህ ከጠላቶቻችን ጋር ተጨምረው በኋላችን ተከትለው ይወጉናል ፡ ከአገራችንም ያወጡናልና ኑ እንጠበብባቸው አላቸው ። |
| ወሤሙ ዲቤሆሙ ሊቃነ ግብር ከመ ይሣቅይዎሙ በግብር ፡ ወነደቁ አህጉረ ጽኑዓተ ለፈርዖን ፊቶም ወራምሴ ወኦን እንተ ይእቲ ሀገረ ፀሐይ ። | ፲፩ | በሥራም መከራ ያጸኑባቸው ዘንድ በላያቸው የሠራተኞች አለቆችን ሾሙ ፡ ለፈርዖንም የጸኑ አምባዎችን ሠሩ (እሊህም) ፊቶም ራምሴና ዖን ናቸው ፡ ይህችም አን ፀሐይ የፀናበት አገር ናት ። ዘፍ፡ ፲፭ ፲፫ ። ዘፀ፡ ፫ ፯ ። |
| ወበአምጣነ ይሣቅይዎሙ ከማሁ ይበዝኁ ወይጸንዑ። | ፲፪ | ነገር ግን መከራ በሚያጸኑባቸው መጠን ይበዙም ይጸኑም ነበር ። ዘፍ፡ ፳፰ ፲፬ ። ፳፪ ፫ ። |
| ወያስቆርርዎሙ ግብጽ ለደቂቀ እስራኤል ወይቀንይዎሙ በሥቃይ ። | ፲፫ | የግብጽም ሰዎች የእስራኤልን ልጆች ይጸየፉዋቸው ነበር ፡ በመከራም ይገዙዋቸው ነበር ። |
| ወያጼዕሩ ሕይወተ ነፍሶሙ በግብር ዕፁብ ወበግንፋል ወበዕቡር ወበኵሉ ግብረ ሐቅል ወበኵሉ ግብር ዘይቀንይዎሙ በሥቃይ ። | ፲፬ | ሰውነታቸውንም በጭንቅ ሥራ ጡብ በማስጣል ፡ ጭቃን በማስላቆጥ ፡ ኖራን በማስወገጥ በእርሻም ሥራ ሁሉ ያስጨንቁዋት ነበር ፡ የሚገዙዋቸውም በሥራ ሁሉ የሚያስጨንቅ ነበር ። |
| ወይቤሎን ንጉሠ ግብጽ ለመወልዳተ ዕብራውያት ስማ ለአሐቲ ሲፓራ ወስመ ካልእታ ፎሓ ። | ፲፭ | የግብጽም ንጉሥ አንዲቱ ስሟ ሲፓራ የሁለተኛይቱም ስም ፎሓ የሚባል የዕብራውያት አዋላጆችን ። |
| ሶበ ታወልዳሆን ለዕብራውያት እምከመ በጽሐት ለወሊድ እመ ተባዕት ውእቱ ቅትላሁ ወእመሰ ወለት ይእቲ አሕይዋሃ ። | ፲፮ | ዕብራውያትን በምታዋልዱዋቸው ጊዜ ወንድ ልጅ ቢሆን ግደሉት ፡ ሴት ልጅ ብትሆን ግን አድኗት አላቸው ። |
| ወፈርሃሁ ለእግዚአብሔር እልኩ መወልዳት ወኢገ | ፲፯ | እሊያ አዋላጆች ግን እግዚአብሔርን ፈርተውት |

ብሩ በከመ አዘዞን ንጉሠ ግብጽ ወአሕየዋ ተባዕተ ።

፲፰ ወጸውዖን ንጉሠ ግብጽ ለመወልዳት ወይቤሎን እፎኑ
ተገብሩ ከመዝ ወታሐይዋ ተባዕተ ፡፡
፲፱ ወይቤላሁ መወልዳት ለፈርዖን አኮ ከመ አንስተ ግብ
ጽ ዕብራውያት አላ እንበለ ትምጻእ መወልዲት ይወልዳ።

፳ ወአሠነየ እግዚአብሔር ለመወልዳት ፡፡
፳፩ ወመድኀ ሕዝብ ወጸንዑ ጥቀ እስመ ፈርሃሁ ለእግዚ
አብሔር መወልዳት ወገብረ ሎን ዐቢያተ ።
፳፪ ወአዘዘሙ ፈርዖን ለኵሉ ሕዝቡ ወይቤሎሙ ለኵሉ
ተባዕት ዘይትወለድ ለዕብራውያን ገርም ውስተ ተከዚ
ወኵሎ አንስተ አሕይዉ ፡፡

ምዕራፍ ፪ ፡፡

፩ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ እምነገደ ሌዊ ዘስሙ እንበረም
ዘነሥአ ሎቱ እምአዋልደ ሌዊ ብእሲተ ፡፡
፪ ወፀንሰት ወወለደት ተባዕተ ወሶበ ርእይዎ ከመ ሠናይ
ውእቱ እንበርዎ ሠለስተ አውራኀ ፡፡
፫ ወሶበ ስእኑ እንከ ኀቢአቶ ነሥአት እሙ ነፍቀ ወቀ
ብዐታ አስፈሊጣ ወፒሳ ወወደየቶ ለውእቱ ሕፃን ውስ
ቴታ ወሤመቶ ውስተ ማዕዶት ኀበ ተከዚ ።

፬ ወትሔውጽ እኅቱ እምርኁቅ ከመ ታእምር ምንት
ይበጽሖ ፡፡
፭ ወወረደት ወለተ ፈርዖን ትትሐፀብ በውስተ ተከዚ ፡
ወአንሶሰዋ አዋልዲሃ ኀበ ተከዚ ፡ ወሶበ ርእየታ ለይእቲ
ነፍቅ ውስተ ማዕዶት ፈነወት ወለታ ወአምጽአታ ፡፡

፮ ወከሠተታ ወርእየት ሕፃነ ይበኪ ውስተ ይእቲ ነፍቅ
ወምሀከቶ ወለተ ፈርዖን ወትቤ እምደቂቀ ዕብራውያን
ውእቱ ዝ ሕፃን ፡፡
፯ ወትቤላ እኅቱ ለውእቱ ሕፃን ለወለተ ፈርዖን ትፈቅ
ዲኑ እጸውዕ ለኪ ብእሲተ ሐፃኒተ ዕብራዊተ ወትሕፅኖ
ለዝ ሕፃን ።
፰ ወትቤላ ወለተ ፈርዖን ሑሪ ፀውዒ ወሖረት እንታክቲ
ወለት ወጸውዐታ ለእሙ ለውእቱ ሕፃን ወትቤ ነያ ሐፃኒት።

፱ ወትቤላ ወለተ ፈርዖን ዕቀቢ ሊተ ዘ ሕፃነ ወሐፅኒዮ ፡
ወአነ እሁበኪ ዐስበኪ ፡ ወነሥአቶ ይእቲ ብእሲት ለው
እቱ ሕፃን ወሐፀነቶ ፡፡
፲ ወሶበ ጸንዐ ውእቱ ሕፃን ወሰደቶ ኀበ ወለተ ፈርዖን
ወኮና ወልደ ወሰመየቶ ስሞ ሙሴ ፡ ወትቤ እስመ እማይ
አውፃእክዎ ።
፲፩ ወኮነ እምድኅረ ብዙኅ መዋዕል ልህቀ ሙሴ ወወፅአ
ኀበ አኀዊሁ ወርእየ ሕማሞሙ ወረከበ ብእሴ ግብጻዌ
እንዘ ይዘብጦ ለአሐዱ ዕብራዊ እምአኀዊሁ ደቂቀ እስራኤል።

፲፪ ወነጸረ ለፌ ወለፌ ወአልቦ ዘርእየ ፡ ወቀተሎ ለዝኩ

የግብጽ ንጉሥ እንዳዘዛቸው አላደረጉም ፡ ወንድ ወንዱን
አዳኑ ። ዘፍ፡ ፴፪ ፲፰ ፡ ምሳ፡ ፲፬ ፴፩ ።
የግብጽም ንጉሥ አዋላጆቹን ጠርቶ ለምን እንዲህ
ታደርጋላችሁ ወንድ ወንዱን ታድናላችሁ አላቸው ።
አዋላጆቹም ፈርዖንን እንዲህ አሉት ፤ የዕብራውያን ሴ
ቶች እንደ ግብጽ ሴቶች አይደሉም ፡ አዋላጂቱ ሳትመጣ
ይወልዳሉ እንጂ ።
እግዚአብሔርም ለአዋላጆቹ በጎ ነገር አደረገላቸው ።
ሕዝቡም በዙ እጅግም ጸኑ (በረቱ) አዋላጆቹም እግ
ዚአብሔርን ስለ ፈሩት ታላላቅ ነገር አደረገላቸው ።
ፈርዖንም ወገኖቹን ሁሉ ለዕብራውያን የሚወለደው
ወንድ ወንዱን ሁሉ ወደ ወንዝ ጣሉት ፡ ሴት ሴቱን በሕ
ይወት ተዉ ፡ (አድኑ) ብሎ አዘዛቸው ።

ምዕራፍ ፪ ።

ከነገደ ሌዊ የተወለደ ከሌዊ ልጆች ሚስት ያገባ ስሙ
እንበረም የሚባል አንድ ሰው ነበረ ፡ ዘኍ፡ ፳፮ ፶፱ ።
(እሷም) ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች ያማረ (የተወደደ)
ሁኖ በዩት ጊዜ ሦስት ወር ሸሽገው አኖሩት ።
ከዚህ በኋላ ሠውሮ ማኖር በተሳናቸው ጊዜ እናቱ ሣ
ጥን አምጥታ የባሕር አረፋ አዶሮ ማር ፡ ሙጫ አስሲብጣ
ያንን ሕፃን በሣሡኑ ውስጥ አድርጋ በወንዙ ዳር አኖረ
ችው ። ኢሳ፡ ፲፰ ፪፡ ዘፀ፡ ፪ ፭ ።
እኅቱም ምን እንደ እንደሚደርስበት ታውቅ ዘንድ
ሩቅ ሁና ትመለከት ነበር ። ዘኍ፡ ፳፮ ፶፱ ።
የፈርዖን ልጅ (ተርሙት) ልትታጠብ ወደ ወንዝ ወረ
ደች ፡ ደንገጥሮቿም በወንዙ ዳር ይመላለሱ ነበር ፡ ያች
ንም ሣጥን አሽግሩ በየቻት ጊዜ ብላቴናዋን ልከ አስመ
ጣቻት ። ግብ፡ ሐዋ፡ ፯ ፳፩ ።
ሣጥኒቱንም ከፍታ ሕፃኑ በሣጥኒቱ ውስጥ ሲያለቅስ
አይታ ፡ ይህ ልጅ ከዕብራውያን ልጆች ይሆናል ብላ
ራራችለት ። ዘፀ፡ ፪ ፭ ።
የዚያም ልጅ እኅት (ማርያም) የፈርዖንን ልጅ ያንን
ልጅ እንድታሳድጊልሽ ዕብራዊት የምትሆን አሳዳጊ ሴት
እጠራለሽ ዘንድ ትወጂለሽን፤ አለቻት ።
የፈርዖንም ልጅ ሂደሽ ጥሪልኝ አለቻት ፡ ያችም ብላቴ
ሂዳ የዚያን ልጅ እናት ጠራቻት እነሆም የምታሳድግ ሴት
ይህች ናት አለቻት ።
የፈርዖንም ልጅ ይህን ሕፃን ተከባክበሽ አሳድጊልኝ
እኔም ደመወዝሽን እሰጥሻለሁ አለቻት ፡ ያችም ሴት ያንን
ሕፃን ተቀብላ አሳደገችው ።
ያም ልጅ በደገ ጊዜ ወደ ፈርዖን ልጅ ወሰደችው ፡
ልጅም ሆናት ከውኃ አወጣሁት ስትል ስሙንም ሙሴ
አለችው ። ግብ፡ ሐ፡ ፯ ፳፩ ፡ ዕብ፡ ፲፩ ፳፬ ።
ከብዙ ዘመንም በኋላ እንዲህ ሆነ፤ ሙሴ አድጎ ወደ
ወንድሞቹ ሄደ ፡ መከራቸውንም አየ ፡ ከወንድሞቹም ከእ
ስራኤል ልጆች አንዱን ዕብራዊ አንድ ግብጻዊ ሲመታው
አገኘ ። ግብ፡ ሐ፡ ፯ ፳፫ - ፳፬ ።
ወድያና ወዲህም ተመለከተና ያየው ሰው አልነበረም

ግብጻዊ ወደፈኖ ውስተ ኆፃ ።
ወወፅአ በሳኒታ ዕለት ወረከበ ክልኤተ እደወ ዕብራ ፲፫
ውያነ እንዘ ይትበአሱ ወይቤሎ ሙሴ ለዘይገፍዖ ለምንት
ትዘብጦ ለካልእከ ።
ወይቤሎ ዝኩ ዘይዔምፆ ለካልኡ መኑ ሤመከ መል ፲፬
እከ ወመኰንነ ላዕሌነ፣ አው ትቅትለኒኑ ትፈቅድ በከመ
ቀተልኮ ትማልም ለግብጻዊ፣ ወፈርሀ ሙሴ ወይቤ ከመ
ዝኑ ክሡተ ኮነ ዝ ነገር ።
ወሰምዐ ፈርዖን ዘንተ ነገረ ወፈቀደ ይቅትሎ ለሙሴ ፲፭
ወተግኅሠ ሙሴ እምገጸ ፈርዖን ወኀደረ ውስተ ምድረ
ምድያም ወሰበ በጽሐ አሐተ ምድረ ምድያም ነበረ ዲበ
ዐዘቅት ።
ወቦ ለማርያ ምድያም ሰብዑ አዋልድ ወይርዕያ አባ ፲፮
ግዐ አቡሆን መጽአ ወሄባ ሎን እስከ መልአ ገብላተ ከመ
ያስትያ አባግዐ አቡሆን ።
ወሰበ መጽኡ ኖሎት አሰሰልዎን ወተንሥአ ሙሴ ፲፯
ወአድኀኖን ወአስተየ አባግዐ ።
ወሖራ ኀበ ራጉኤል አቡሆን ወይቤሎን እፎኑ አፍ ፲፰
ጠንክን መጺአ ዮም ስ ።
ወይቤላሁ ብእሲ ግብጻዊ አድኀነነ እምኖሎት ወሄበ ፲፱
ለነ ወአስተየ አባግዒነ ።
ወይቤሎን ለአዋልዲሁ አይቴ ውእቱ ብእሲሁ ወለም ፳
ንት ኀደጋሁ ለብእሲ ጸውዓሁ ከመ ይብላዕ እክለ ።

ወኀደረ ሙሴ ኀበ ውእቱ ብእሲ ወወሀበ ወለቶ ሲፓ ፳፩
ራሃ ትኩኖ ብእሲተ ።
ወፀንሰት ይእቲ ብእሲት ወወለደት ወልደ ወሰመዮ ፳፪
ስሞ ሙሴ ጌርሳም፣ ወይቤ እስመ ነግድ አነ በምድረ
ነኪር ።
ወፀንሰት ዳግመ ወወለደት ወልደ ወሰመዮ ኤልዛር፣ ፳፫
ወይቤ ፈጣሬ ዘአቡየ ረዳእየ ።

ወእምድኅረ ብዙኅ መዋዕል ሞተ ንጉሠ ግብጽ ወግ ፳፬
ዕሩ ደቂቀ እስራኤል እምግብሮሙ ወአውየዉ ወዐርገ
አውያቶሙ ኀበ እግዚአብሔር እምግብሮሙ ።
ወሰምዐ እግዚአብሔር ገዓሮሙ ወተዘከረ መሐላሁ ፳፭
ዘመሐለ ለአብርሃም ወይስሐቅ ወያዕቆብ ወሐወጾሙ ለደ
ቂቀ እስራኤል ወተአምረ ሎሙ ።

## ምዕራፍ ፫ ።

ወሀሎ ሙሴ ይርዒ አባግዐ ዮቶር ሐሙሁ ማርያ ምድ ፩
ያም፣ ወወሰደ አባግዒሁ ሐቅለ ወበጽሐ ውስተ ኮሬብ
ደብረ እግዚአብሔር ።
ወአስተርአዮ ለሙሴ መልአከ እግዚአብሔር በነደ ፪
እሳት እምዕፀት፣ ወርእየ ሙሴ ከመ እምዕፀት ይነድድ
እሳት ወዕፀታ ኢትውዒ ።
ወይቤ ሙሴ እብጻሕ ወእርአይ ዘ ራእየ ዐቢየ እፎ ፫
ኢትውዒ ዛ ዕፀት ።

ያንን ግብጻዊ ሰው ገድሎ በአሸዋ ውስጥ ቀበረው ።
በበነጋውም ዕለት ወጥቶ ሁለት የዕብራውያን ሰዎች
ሲጣሉ አግኝቶ ሙሴ የሚበድለውን አይቶ ለምን ወንድ
ምህን ትመታዋለህ፤ አለው ። ግብ፡ ሐዋ፡ ፯ ፳፯ ።
ያም ወንድሙን የሚበድለው ሰው በኛ ላይ አለቃ
ዳኛ፣ አድርጎ የሾመህ ማን ነው፤ ወይስ የግብጽን ሰው
ትላንትና እንደ ገደልከው ልትገድለኝ ትሻለህን፤ አለው፣
ሙሴም ይህ ነገር እንዲህ የተገለጠ ሆኗልን ብሎ ፈራ ።
ፈርዖንም ይህንን ነገር ሰምቶ ሙሴን ሊገድለው ፈለገ
ሙሴም ከፈርዖን ፊት ሸሽቶ በምድያም አገር ተቀመጠ፣
ከምድያም ወደ አንዲቱ አገር በደረሰም ጊዜ በውኃ ጉድ
ጓድ አጠገብ ተቀመጠ ። ግብ፡ ሐ፡ ፯ ፳፱፣ ዕብ፡ ፲፩ ፳፯።
ለምድያም ካህን ሰባት ሴቶች ልጆች ነበሩት፣ ያባታ
ቸውን በጎች ይጠብቁ ነበር፣ መጥተውም ያባታቸውን በጎች
ያጠጡ ዘንድ ገንዳው እስኪመላ ድረስ ቀዱላቸው ።
እረኞችም መጥተው በከለከሉዋቸው ጊዜ፣ ሙሴ
ተነሥቶ አዳናቸው፣ በጎችንም አጠጣ ። ዘፍ፡ ፳፱ ፲ ።
ወዳባታቸው ወደ ራጉኤልም ሄዱ፣ ዛሬስ እንዴት
ፈጥናችሁ መጣችሁ፤ አላቸው ። ዘሌ፡ ፲ ፳፱ ።
(እነሱም) አንድ የግብጽ ሰው ከእረኞች አዳነን ውኃ
ውንም ቀድቶ በጎቻችንን አጠጣልን አሉት ።
ልጆቹን ሰውየው የት ነው፤ (ወዴት አለ) ለምንስ ትታ
ችሁት መጣችሁ፤ (አሁንም) እንጀራ ይበላ ዘንድ ሰውዬ
ውን ጥሩት አላቸው ። ዘፍ፡ ፴፩ ፶፬ ።
ሙሴም በዚያ ሰው ዘንድ አደረ፣ ሚስትም ትሆነው
ዘንድ ሲፓራ የተባለች ልጁን ሰጠው ።
ያችም ሴት ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች ሙሴም ስሙን
ጌርሳም ብሎ ጠራው፣ እኔ በባዕድ አገር መጻተኛ ነኝ ሲል ።

ዳግመኛም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች ያባቴ ፈጣሪ
ረዳኝ ሲል ኤልዛር አለው፣ (ኤልዛር ማለት የእግዚአብ
ሔር ረድኤት ማለት ነው) ።
ከብዙ ዘመንም በኋላ የግብጽ ንጉሥ ሞተ፣ የእስራኤል
ልጆች ከሥራቸው ብርታት የተነሣ አለቀሱ፣ ጮኹም፣
ጩኸታቸውም ወደ እግዚአብሔር ደረሰ ።
እግዚአብሔርም ጩኸታቸውን ሰምቶ ለአብርሃም ለይ
ስሐቅና ለያዕቆብ የማለውን መሐላ አሰበ፣ (አስበም) የእስ
ራኤልን ልጆች (በረድኤት) ጐበኛቸው (በረዳትነቱም)
ታወቃላቸው ። ፩ ሳሙ፡ ፩ ፲፩፣ ዘዳ፡ ፴፫ ፱ ።

## ምዕራፍ ፫ ።

ሙሴ የአማቱ የምድያም ካህን የዮቶርን በጎች ሲጠ
ብቅ ኖረ፣ በጎቹንም ወደ በረኻ ወስዶ ወደ እግዚአብሔር
ተራራ ወደ ኮሬብ ደረሰ ። መዝ፡ ፻፴፱ ፪ ።
የእግዚአብሔርም መልአክ ከዕንጨት በወጣው እሳት
ለሙሴ ታየው፣ ሙሴም ዕንጨትነቷ ሳትቃጠል ከዕንጨ
ትነቷ ወጥቶ እሳት ሲነድ አየ ። ዘዳ፡ ፴፫ ፲፯ ።
ሙሴም ይህች ዕንጨት እንዴት አትቃጠልም ይህን
ደግ ራእይ ከዚያ ደርሼ ልይ አለ ።

፬ ወሶበ ርእየ እግዚአብሔር ከመ መጽአ ይርአይ ጸውዖ እምዕፀት ወይቤሎ ፤ "ሙሴ ሙሴ„ ወይቤ ምንት ውእቱ እግዚኦ ።

እግዚአብሔርም ያይ ዘንድ እንደ መጣ በየው ጊዜ ከዕንጨቱ ወጥቶ "ሙሴ ሙሴ„ ብሎ ጠራው ፤ (ሙሴም) አቤቱ ! ምንድር ነው አለ ።

፭ ወይቤሎ ኢትቅረብ ዝየ ፍታሕ አሣእኒከ እምእገሪከ እስመ መካን እንተ አንተ ትቀውም ባቲ ምድር ቅድስት ይእቲ ።

አንተ የቆምክበት ቦታ ክብርት ናትና ወደዚህ አትቅ ረብ ፤ ጫማህንም ከእግርህ አውልቅ አለው ።

፮ ወይቤሎ እግዚአብሔር አነ ውእቱ አምላከ አበዊከ አምላከ አብርሃም ፤ ወአምላከ ይስሐቅ ፤ ወአምላከ ያዕቆብ ፤ ወሜጠ ገጾ ሙሴ እስመ ፈርሀ ነጽሮ ቅድመ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ያባቶችህ የአብርሃም የይስሐቅና የያዕ ቆብ ፈጣሪ እኔ ነኝ አለው ፤ ሙሴም የእግዚአብሔርን ፊት ማየት ፈርቷልና ፊቱን መለሰ (አዞረ) ። ዘፍ፡ ፳፰ ፲፫ ።

፯ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ርእየ ርኢኩ ሥቃዮሙ ለሕዝብየ እለ ውስተ ግብጽ ወአውያቶሙ ሰማዕኩ እምነዳእተ ገባር ።

እግዚአብሔርም ሙሴን በግብጽ ያሉ የወገኖቼን መ ከራ ማየትን አየሁ ፤ ከአስገባሪዎቻቸውም የተነሣ ጩኸታ ቸውን ሰማሁ አለው ። ዘፀ፡ ፪ ፳፫ ፤ ነህ፡ ፱ ፱ ።

፰ ወአእመርኩ ጻዕሮሙ ወወረድኩ ከመ አድኅኖሙ እምእደ ግብጽ ወእሰዶሙ ውስተ ምድር ሠናይት ወርኅ ብት ወአወፅኦሙ እምይእቲ ወአወስዶሙ ውስተ ምድር እንተ ታውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ ውስተ ምድሮሙ ለከናኔ ዎን ወለኬጤዎን ወለአሞሬዎን ወለፌርዜዎን ወለጌርጌ ሴዎን ወለኤዌዎን ወለኢያቡሴዎን ።

ጭንቀታቸውንም አውቄ ከግብጻውያን እጅ አድናቸው ዘንድ ወደ አማረችና ሰፊም ወደ ሆነች ምድር እወስዳቸው ዘንድ ወረድሁ ፤ ከዚያችም ምድር አውጥቼ ማርና ወተትን ወደምታፈሰው (ተድላ ደስታ ወደምታስገኝ) ወደ ከናኔ ዎንና ኬጤዎን ፤ ወደ ኤዌዎንና ወደ ፌርዜዎን ወደ ጌርጌሴ ዎን ወደ አሞሬዎንና ወደ ኢያቡሴዎን አገር አገባቸዋለሁ ።

፱ ወይእዜኒ ናሁ ገዓሮሙ ለደቂቀ እስራኤል በጽሐ ኀቤ የ ፤ ወርኢኩ አነ ሥቃዮሙ ዘይሣቅይዎሙ ግብጽ ።

አሁንም እነሆ የእስራኤል ልጆች ጩኸት ወደኔ ደረ ሰ እኔም የግብጽ ሰዎች የሚያጸኑባቸውን መከራቸውን ተመለከትሁ ። ዘፀ፡ ፪ ፳፫ ።

፲ ወይእዜኒ ነዓ እፈኑከ ኀበ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ወታ ወጽኦሙ ለሕዝብየ ደቂቀ እስራኤል እምድረ ግብጽ ።

አሁንም ወደ ግብጽ ንጉሥ ወደ ፈርዖን እልክህ ዘን ድ ና ፤ የእስራኤል ልጆች ወገኖቼን ከምድረ ግብጽ ታወ ጣቸዋለህ አለው ።

፲፩ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር መኑ አነ ከመ አሐውር ኀበ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ወከመ አውጽኦሙ ለደቂቀ እስ ራኤል እምድረ ግብጽ ።

ሙሴም እግዚአብሔርን ወደ ግብጽ ንጉሥ ወደ ፈር ዖን ሄጄ የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ አገር አወጣቸው ዘንድ እኔ ማን ነኝ (ምንድር ነኝ) አለው ።

፲፪ ወይቤሎ እግዚአብሔር እስመ አነ ሀለውኩ ምስሌከ ወዝንቱ ተአምር ለከ ፤ ከመ አነ እፌንወከ ሶበ አውጻእከ ሙ ለሕዝብየ እምብሔረ ግብጽ ወትፀመድዎ ለእግዚ አብሔር በዝ ደብር ።

እግዚአብሔርም እኔ (በረድኤት) ከንተ ጋራ አለሁና ፤ እኔም እንደላክሁህ ምልክትህ ይህ ነውና ወገኖቼን ከግ ብጽ አገር በወጣኻቸው ጊዜ በዚህ ተራራ ለእግዚአብሔር ትገዛላችሁ አለው ። ዘፀ፡ ፲፱ ፫ ።

፲፫ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር ናሁ አነ አሐውር ኀበ ደቂቀ እስራኤል ወእብሎሙ አምላከ አበዊክሙ ፈነወኒ ኀቤክሙ ወሶበ ይሴእሉኒ ስሙ ምንተ እብሎሙ ።

ሙሴም እግዚአብሔርን እንዲህ አለው ፤ እነሆ ወደ እስራኤል ልጆች ሂጄ የአባቶቻችሁ ፈጣሪ ወደናንተ ላከኝ እላቸዋለሁ ነገር ግን ስምህን በጠየቁኝ ጊዜ ምን እላቸዋለሁ ፤ ዘፍ፡ ፴፪ ፳፱ ።

፲፬ ወይቤሎ እግዚአብሔር አነ ውእቱ ዘሀሎ ወይሄሉ ወከመዝ ትብሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ዘሀሎ ወይሄሉ ፈነ ወኒ ኀቤክሙ ።

እግዚአብሔርም ያለና የሚኖር እኔ የእስራኤል ልጆ ች ቅድመ ዓለም የነበረና ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ወደና ንተ ላከኝ ትላቸዋለህ አለው ። ዕብ፡ ፲፫ ፰ ።

፲፭ ወዓዲ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ከመዝ ትብሎሙ ለደቂቀ እስራኤል እግዚአብሔር አምላከ አበዊክሙ ፈነ ወኒ ኀቤክሙ ፤ ዝ ውእቱ ስምየ ዘለዓለም ወዝክርየ ለት ውልደ ትውልድ ።

ዳግመኛም እግዚአብሔር ሙሴን የ፳ልን ልጆች እን ዲህ ትላቸዋለህ የአባቶቻችሁ ፈጣሪ እግዚአብሔር ወደና ንተ ልኮኛል ፤ ለዘለዓለም ፀንቶ የሚኖር ስሜ ይህ ነው ፤ ስም አጠራሬም ለልጅ ልጅ ነው አለ በላቸው አለው ።

፲፮ ሑር አስተጋብኦሙ ለአእሩገ እስራኤል ፤ ወበሎሙ እግዚአብሔር አምላከ አበዊክሙ አምላከ አብርሃም ወአ ምላከ ይስሐቅ ፤ ወአምላከ ያዕቆብ ፤ አስተርአየኒ ወፈነወኒ እንዘ ይብል ሐውጾ ሐወጽኩክሙ በእንተ ኵሉ እንተ በጽሐተክሙ በብሔረ ግብጽ ።

ሂድና የእስራኤልን ሽማግሌዎች ሰብስበህ ያባቶቻ ችሁ የአብርሃም የይስሐቅና የያዕቆብ ፈጣሪ እግዚአብሔር ተገልጾ በግብጽ አገር ስለ ደረሰባችሁ መከራ ሁሉ (በረድ ኤት) ጐበኘኋችሁ ብሎ ወደናንተ ላከኝ በላቸው ።

፲፯ ወእቤ አነ እንሥእክሙ እምሥቃየ ግብጽ ወአዐርገ ክሙ ውስተ ምድረ ከናኔዎን ወኬጤዎን ወኤዌዎን ወአ

እኔም ተድላ ደስታ ወደምታስገኝ ወደ ከናኔዎን ወደ ኬጤዎን ፤ ወደ ኤዌዎንና ወደ አሞሬዎን ፤ ወደ ፌርዜዎን

| | | |
|---|---|---|
| ሞሬዎን ወፌርዜዎን ወጌርጌሴዎን ወኢያቡሴዎን ውስተ ምድር እንተ ታውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ ። | | ወደ ጌርጌሴዎን ወደ ኢያቡሴዎን አገር አወጣችኋለሁ አለ በላቸው ። ዘፍ፣ ፱ ፳፱፣ ዘፀ፣ ፬ ፴፩ ። |
| ወይሰምዑ ቃለከ ወትበውእ አንተ ወአእሩገ እስራኤል ኀበ ንጉሠ ግብጽ ወትብሎ እግዚአብሔር አምላከ ዕብራውያን ጸውዐነ ንሑር ምሕዋረ ሠሉስ ዕለት ውስተ ሐቅል ከመ ንሡዕ ለእግዚአብሔር አምላክነ ። | ፲፰ | ቃልህን ይሰማሉ አንተም ወደ ግብጽ ንጉሥ ትገባለህ የእስራኤልም ሽማግሌዎች ይገባሉ፣ የዕብራውያን ፈጣሪ እግዚአብሔር የሦስት ቀን ጕዳና ሂደን በምድረ በዳ ለፈጣሪያችን እግዚአብሔር መሥዋዕትን እንሠዋ ዘንድ ጠርቶናል ትሉታላችሁ ። ዘኍ፣ ፳፫ ፫-፬፣ ፲፭ ፲፪ ። |
| ወአነ አአምር ከመ ኢያበውሐክሙ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ትፃኡ ዘእንበለ በእድ ጽንዕት ። | ፲፱ | ነገር ግን በጽኑ ሥልጣን ካልሆነ የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን እንደማያሰናብታችሁ እኔ አውቃለሁ ። |
| ወእሰፍሕ እዴየ ወእቀትሎሙ ለግብጽ በኵሉ መድምምየ ዘእገብር በሙ ወእምድኅረዝ ይፌንወክሙ ። | ፳ | እጄን ዘርግቼ (ሥልጣኔን ገልጬ) የግብጽን ሰዎች በማደርግባቸው ተአምራቴ ሁሉ አጠፋቸዋለሁ፣ ከዚህ በኋላ ያሰናብታችኋል ። ዘፍ፣ ፴፩ ፪፣ ዘዳ፣ ፲፱ ፩ ። |
| ወእሁበሙ ሞገሰ ለሕዝብየ በቅድሜሆሙ ለግብጽ ። | ፳፩ | ለወገኖቼም በግብጻውያን ፊት መወደድን (መፈራትን) እሰጣቸዋለሁ ። ግብ፣ ሐዋ፣ ፯ ፴፯ ። |
| ወአመ ተሐውሩ ኢትወፅኡ ዕራቃኒክሙ፣ አላ ታስተዋሕስ ብእሲት እምጎራ ወእምኅደርታ ንዋየ ብሩር ወወርቅ ወልብስ፣ ወትወድይዎ በዲበ ደቂቅክሙ ወአዋልዲክሙ ወተሐበልይዎሙ ለግብጽ ። | ፳፪ | በሄዳችሁም ጊዜ ባዶዋችሁን አትወጡም (አትሄዱም) ሴት ከጕረቤቷ ከቤተ ሰቧም የወርቅን የብርን የልብስን (ጌጣ-ጌጥ) ትዋስ እንጂ በዶአችሁን አትወጡም በወንዶች ልጆቻችሁና በሴቶች ልጆቻችሁ ላይ ታገቡታላችሁ፣ (በዚህ) የግብጽን ሰዎች ትበዝብዙዋቸው አላችሁ አላቸው ። |
| ምዕራፍ ፬ ። | | ምዕራፍ ፬ ። |
| ወአውሥአ ሙሴ ወይቤ ለእመኬ ኢአምኑኒ ወኢሰምዑ ቃልየ ወይቤሉኒ ኢያስተርአየከ እግዚአብሔር ምንተ እብሎሙ ። | ፩ | ሙሴም ባያምኑኝና ቃሌን ባይሰሙ እግዚአብሔርም አልተነጋገረህም ቢሉኝ ምን እላቸዋለሁ፤ ብሎ መለሰ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ምንት ዝ ዘውስተ እዴከ፣ ወይቤ በትር ። | ፪ | እግዚአብሔርም ሙሴን ይህ በእጅህ የያዝከው ምንድር ነው አለው፤ በትር ነው አለው ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ግድፎ ውስተ ምድር ወገደፎ ውስተ ምድር ወኮነ አርዌ ምድር ወጕየ ሙሴ እምኔሁ ። | ፫ | እግዚአብሔር በምድር ላይ ጣለው አለው፣ በምድርም ላይ ጣለው፣ በትሩም እባብ ሆነ፣ ሙሴም ከሱ ሸሸ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ስፋሕ እዴከ ወንሥኦ በዘነቡ ወሰፍሐ እዴሁ ሙሴ ወነሥኦ በዘነቡ ወኮነ በትረ ውስተ እዴሁ ። | ፬ | እግዚአብሔር ሙሴን እጅህን ዘርግተህ ጅራቱን ያዘው አለው፣ ሙሴም እጁን ዘርግቶ ጅራቱን ይዞ አነሣው በእጁም እንዳለ በትር ሆነ ። ዘፀ፣ ፬ ፲፯ ። |
| ወይቤሎ ከመ ይእመኑከ ከመ አስተርአየከ እግዚአብሔር አምላከ አበዊሆሙ አምላከ አብርሃም፣ ወአምላከ ይስሐቅ፣ ወአምላከ ያዕቆብ ። | ፭ | እግዚአብሔር ያባቶቻቸው የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብ ፈጣሪ እንደታየህ እንዲያምኑህ ጅራቱን ያዘው (በዚህ ያምኑሃል) አለው ። ዘፀ፣ ፲፱ ፱ ። |
| ወይቤሎ ካዕበ እግዚአብሔር ለሙሴ ደይ እዴከ ውስተ ሕፅንከ፣ ወወደየ እዴሁ ሙሴ ውስተ ሕፅኑ፣ ወይቤሎ አውፅእ እዴከ እምውስተ ሕፅንከ፣ ወአውፅአ እዴሁ እምሕፅኑ፣ ወኮነት ፀዓዳ ዠለንታሃ ለምጽ ። | ፮ | ዳግመኛም እግዚአብሔር እጅህን ወደ ብብትህ አግባ አለው፣ ሙሴም እጁን ከብብቱ አገባ፣ እጅህን ከብብትህ አውጣ አለው፣ እጁን ከብብቱ አወጣ፣ ሁለንተናዋም ነጭ ለምጽ ሆነች ። ዘኍ፣ ፲፪ ፲፣ ፩ ነገ፣ ፭ ፳፯ ። |
| ወይቤሎ ካዕበ ደይ እዴከ ውስተ ሕፅንከ ወወደየ እዴሁ ውስተ ሕፅኑ ወዓዲ ይቤሎ አውፅእ እዴከ እምሕፅንከ ወአውጽአ እዴሁ እምሕፅኑ ወገብአት ከመ ኅብረ ሥጋሁ ። | ፯ | ዳግመኛም እጅህን ወደ ብብትህ አግባ አለው፣ እጁን ወደ ብብቱ አገባ፣ ዳግመኛም እጅህን ከብብትህ አውጣ አለው፣ እጁን ከብብቱ አወጣ የሰውነቱም ኅብረ መልክዕ እንደ ገላው ኅብር ሆነች ። |
| ወይቤሎ ለእመ ኢአምኑከ ወኢሰምዑ ቃለከ በተአምር ዘቀዳሚ የአምኑከ በቃለ ተአምሩ ለካልእ ። | ፰ | በፊተኛውም ተአምር ባያምኑህና ቃልህን ባይሰሙ በሁለተኛው ተአምር ቃል ያምኑሃል ። |
| ወእምከመ ኢአምኑከ በእሉ ክልኤቱ ተአምራት ወኢሰምዑ ቃለከ ትነሥእ እማየ ተከዚ ወትክዑ ውስተ የብስ ወይከውን ደመ ውስተ የብስ ዝኩ ማይ ዘንሣእከ እምተከዚ ። | ፱ | በነዚህም በሁለቱ ምልክቶች ባያምኑህና ቃልህን ባይሰሙ ከፈሳሹ ውኃ ቀድተህ በደረቁ መሬት ላይ እርጨው ይህም ከፈሳሽ ውኃ ቀድተህ የረጨኸው ውኃ ደም ይሆናል ። ዘፀ፣ ፯ ፲፱ ። |
| ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር አስተበቍዐከ እግዚእ | ፲ | ሙሴም እግዚአብሔርን አቤቱ እለምንሃለሁ፣ ጥንቱ |

ቀዳሚየ ቃል አልብየ ወትከትየ ወኢእምአመ እእኅዝ እንብብ ቍልዔከ ፀያፍ ወላእላአ ልሳን አነ ፡፡

ንም ድሮዬንም እንደበት የለኝም ፤ በለሚልህ እኔ እናገር ዘንድ ከጀመርኩ ጀምሮ ድዳ ነኝ ምላሴም ቃታታም ነው፡፡

፲፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ መኑ ወሀበ አፈ ለእጓለ እመሕያው ወመኑ ገብሮ በሃመ ወጽሙመ ወፍቱሐ ወዘ ይሬኢ ወዕዉረ አኮኑ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ፡፡

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው ፤ ለሰው ልጅ አፍን የሰጠው ማን ነው ፤ ድዳስ ደንቆሮስ ያደረገው ማን ነው ፤ አፍ የከፈተለትስ ማን ነው ፤ የሚያይስ ዕውርስ ያደ ረገው ማን ነው ፤ እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን ፡፡

፲፪ ወይእዜኒ ሑር ወአነ እፈትሕ አፉከ ወእሌብወከ ዘሀለወከ ትንብብ ፡፡

አሁንም ሂድ እንድትናገር አደርግሃለሁ ፤ ትናገርም ዘንድ ያለህንም ልብ አስደርግሃለሁ፡፡ ኢሳ፡ ፶፬ ፬ ፡፡

፲፫ ወይቤ ሙሴ አስተበቍዐከ እግዚኦ ኅሥሥ ለከ ባዕደ ዘይትለአከከ ፡፡

ሙሴም አቤቱ እማልድሃለሁ መናገር የሚችል የምት ልከው ሌላ ሰው ፈልግ አለ፡፡ ኤር፡ ፺፩ ፫ ፡፡

፲፬ ወተምዐ እግዚአብሔር መዐተ ላዕለ ሙሴ ወይቤሎ ነዋ አሮን እኁከ ሌዋዊ ወአአምር ከመ ነቢብየ ይነብብ ለከ፡ ወናሁ ውእቱ ይወፅእ ይትቀበልከ ወይሬእየከ ወይትፌሣሕ ፡፡

እግዚአብሔር በሙሴ ላይ ቁጣን ተቈጣ ፤ እነሆ የሌዊ ልጅ ወንድምህ አሮን እኔ ላንተ ንግሬህ አንተም ለሱ እን ድትነግረው አወቀ ፤ እነሆ እሱ ሊቀበልህ ይመጣል አይ ቶህም ደስ ይለዋል ፡፡ ዘፀ፡ ፯ ፪ ፤ ዘኍ፡ ፳፪ ፴፰ ፡፡

፲፭ ወትነግሮ ወትወዲ ቃልየ ውስተ አፉሁ ወአነ እፈ ትሕ አፉከ ወአፉሁ ወእሌብወክሙ ዘትገብሩ ፡፡

ነግሬህ ቃሌን በአንደበቱ ታገባለህ ፤ እኔም አፍህንና አፉን ከፍቼ የምታደርጉትን ልብ አስደርጋችኋለሁ ፡፡

፲፮ ወውእቱ ይትናገር ለከ ኀበ ሕዝብ ወውእቱ ይከው ነከ አፈ ወአንተ ትከውኖ ሎቱ ለኀበ እግዚአብሔር ፡፡

እሱ ስላንተ ከሕዝቡ ጋር ይነጋገርልሃል ፤ እሱ አንደ በት ይሆንሃል ፤ አንተም ለእግዚአብሔር ትነግርለታለህ ፡፡

፲፯ ወለዛቲኒ በትር እንተ ትገብር ባቲ ተአምረ ንሥአ ውስተ እዴከ ፡፡

ምልክት የምታደርግበት ይህችንም በትር በእጅህ ያ ዛት አለው ፡፡ ዘፀ፡ ፯ ፩ ፤ ፳፩ ፲፱ ፡፡

፲፰ ወሖረ ሙሴ ወገብአ ኀበ ዮቶር ሐሙሁ ወይቤሎ አሐ ውር ወእገብእ ኀበ አኃውየ እለ ውስተ ብሔረ ግብጽ ወእሬኢ ለእመ ሃዲሆሙ ሕያዋን ወይቤሎ ዮቶር ለሙሴ ሑር በዳኅን ፡፡

ሙሴም ተመልሶ ወደ አማቱ ወደ ዮቶር ሄደ ፤ ተመ ልሼም በግብጽ አገር ወዳሉ ወንድሞቼ እሄዳለሁ ገና በሕ ይወት እንዳሉም አያለሁ አለው ፤ ዮቶርም ሙሴን በደኅና ሂድ አለው ፡፡

፲፱ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በምድረ ምድያም ነዓ ሑር ብሔረ ግብጽ እስመ ሞቱ ኵሎሙ እለ የኀሥሥዋ ለነፍስከ ፡፡

እግዚአብሔር ሙሴን በምድያም ምድር ሰውነትህን የሚፈልጓት ሰዎች ሁሉ ሙተዋልና ወደ ግብጽ አገር ሂድ አለው ፡፡

፳ ወነሥአ ሙሴ ብእሲቶ ወደቂቆ ወጾዐኖሙ ዲበ አእ ዱግ ወገብአ ብሔረ ግብጽ ፤ ወነሥአ ሙሴ ለእንታክቲ በትር እንተ እምኀበ እግዚአብሔር ውስተ እዴሁ ፡፡

ሙሴም ሚስቱንና ልጆቹን ይዞ በአህዮች አስቀምጦ ወደ ግብጽ አገር ተመለሰ ፤ ከእግዚአብሔር ያገኛትንም ያችን በትር በእጁ ይዟት ሄደ ፡፡ ዘኍ፡ ፳፫ ፱ ፡፡

፳፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ እንዘ ተሐውር ወትገ ብእ ውስተ ብሔረ ግብጽ አእምር ኵሉ መድምምየ ዘወ ሀብኩከ ውስተ እዴከ ከመ ትግበሮ በቅድሜሁ ለፈርዖን ወአነ አጸንዕ ልቦ ወኢይፌንዎሙ ለሕዝብ ፡፡

እግዚአብሔርም ሙሴን ወደ ግብጽ አገር ተመልሰህ ስትሄድ በእጅህ ያደረግሁልህን ተአምራት ሁሉ በፈርዖን ፊት ታደርገው ዘንድ እንዳለህ ዕወቅ ፤ እኔም የፈርዖንን ልብ አጸናዋለሁ ፤ ወገኖቼንም አያሰናብታቸውም ፡፡

፳፪ ወአንተሰ ትብሎ ለፈርዖን ከመዝ ይቤ እግዚእ እግዚ አብሔር ወልድየ ዘበኵርየ ውእቱ እስራኤል ፡፡

አንተ ግን ፈርዖንን እንዲህ ትለዋለህ ፤ ጌታ (ፈጣሪ) እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤ እስራኤል የበኵር ልጄ ነው ፡፡

፳፫ ወእብለከ ፈንዎ ሕዝብየ ከመ ይፀመዱኒ ወአንተሰ እመ ኢፈቀድከ ትፈንዎ አእምርኬ እንከ ከመ እቀትሎ አነ ለወልድከ ዘበኵርከ ፡፡

መሥዋዕት ሠውተው ያገለግሉኝ ዘንድ ወገኖቼን አሰ ናብት (ልቀቅ) አንተ ግን ታሰናብታቸው ዘንድ ባትወድ እኔም እንግዲህ የበኵር ልጅህን እንደምገድለው ዕወቅ አለ በለው ፡፡ ዘፀ፡ ፲፩ ፭ ፤ ፲፪ ፳፱ ፡፡

፳፬ ወከነ በፍኖት በውኅተ ማኅደር ተራከቦ መልአከ እግ ዚአብሔር ወፈቀደ ይቅትሎ ፡፡

በደረበት ጕዳና እንዲህ ሆነ ፤ እግዚአብሔር የላከው መልአክ ተገናኘው ሊገድለውም ወደደ ፡፡

፳፭ ወነሥአት ሲፓራ መላጼ ወገዘረት ከተማ ነፍስቱ ለወ ልዳ ወወድቀት ኀበ እገሪሁ ወትቤ ለይኩን ህየንቴሁ ዝ ደመ ግዝሮሁ ለወልድየ ፡፡

ሲፓራ (ሚስቱ) ምላጭ ይዛ የልጅዋን ሸንኮፍ ገዘረ ችው ይህም የልጄ የግርዘቱ ደም ስለሱ ፈንታ ይሁን ብላ ከእግሩ በታች ወደቀች ፡፡ ኢያሱ ፭ ፪ - ፫ ፡፡

፳፮ ወሖረ እምኔሁ እስመ ትቤ ለይኩን ህየንቴሁ ዝ ደመ ግዝሮሁ ለወልድየ ፡፡

ይህ የልጄ የግርዘቱ ደም ስለሱ ፈንታ ይሁን ብላለ ችና ከሱ ተመልሶ ሄደ ፡፡ መሳ፡ ፲፩ ፴፯ ፤ ፲፱ ፱ ፡፡

፳፯ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአሮን ሑር ተቀበሎ ለሙሴ ውስተ ሐቅል ወሖረ ወተራከቦ በደብረ እግዚአብሔር

እግዚአብሔር አሮንን ሂደህ በምድረ በዳ ሙሴን ተቀ በለው አለው ፤ ሂዶም እግዚአብሔር በሚገለጽበት ተራራ

| | | |
|---|---|---|
| ወተአምኖ ። | | ተገናኘው ሳመውም ፥ (እጅ ነሣው) ። ፩ ነገ፥ ፲፱ ፳ ። |
| ወአይድዖ ሙሴ ለአሮን ኵሎ ቃለ እግዚአብሔር ዘለአከ ወኵሎ ተአምረ ዘአዘዞ ። | ፳፰ | ሙሴም ለአሮን የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ያዘዘውንም ምልክት ሁሉ ነገረው ። ዘፀ፥ ፲፭ ፲፯ ፥ ፬ ፫ - ፱ ። |
| ወሖሩ ሙሴ ወአሮን ወአስተጋብኡ ኵሎ አእሩጎሙ ለደቂቀ እስራኤል ። | ፳፱ | አሮንና ሙሴም ሄደው የእስራኤል ልጆች ሽማግሌዎችን ሁሉ ሰበሰቡ ። |
| ወነገሮሙ አሮን ኵሎ ቃለ ዘተናገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ ወገብረ ተአምረ በቅድሜሆሙ ። | ፴ | አሮንም እግዚአብሔር ለሙሴ የነገረውን ቃል ሁሉ ነገራቸው ፥ በፊታቸውም ተአምራት አደረገ ። |
| ወአምኑ ሕዝብ ወተፈሥሑ እስመ ሐወጾሙ እግዚአብሔር ወርእየ ሥቃዮሙ ወአትሐቱ ርእሶሙ ወሰገዱ ። | ፴፩ | ሕዝቡም ደስ ብሎአቸው አመኑ ፥ እግዚአብሔር (በረድኤት) ጐብኝቷቸዋልና መከራቸውንም አይቷልና ራሳቸውንም ዝቅ አድርገው ሰገዱ ። ፩ ነገ፥ ፩ ፲፯ ፴፩ ። |

## ምዕራፍ ፭ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወእምድኅረዝ ቦኡ ሙሴ ወአሮን ኀበ ፈርዖን ወይቤልዎ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ፈንው ሕዝብየ ከመ ይግበሩ በዓልየ በሐቅል ። | ፩ | ከዚህ በኋላ ሙሴና አሮን ወደ ፈርዖን ገብተው እንዲህ አሉት ፥ የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር በምድረ በዳ መሥዋዕት ይሠውልኝ ዘንድ ወገኖቼን አሰናብትልኝ አለ ብሎት ። ዘፀ፥ ፲፱ ፲፪ ። |
| ወይቤ ፈርዖን መኑ ውእቱ እግዚአብሔር ዘእሰምዖ ቃሎ ከመ እፈንዎሙ ለደቂቀ እስራኤል ለእግዚአብሔርሂ ኢየአምሮ ፥ ወለእስራኤልሂ ኢይፌንዎ ። | ፪ | ፈርዖንም የእስራኤልን ልጆች አሰናብታቸው ዘንድ ቃሉን የምሰማው እግዚአብሔር ማነው ፤ እግዚአብሔርን አላውቅም እስራኤልንም አለቅም አለ ። ኢዮብ ፳፩ ፲፩ ። |
| ወይቤልዎ አምላከ ዕብራውያን ጸውዐነ ንሑር እንከ ምሕዋረ ሠሉስ ዕለት ውስተ ሐቅል ከመ ንሡዕ ለእግዚአብሔር አምላክነ ከመ ኢይርከበነ ሞት ወቀትል ። | ፫ | ቸነፈር እንዳያገኘን ለፈጣሪያችን እግዚአብሔር በምድረ በዳ መሥዋዕት እንሠዋ ዘንድ የሦስት ቀን ጐዳና ልንሄድ የዕብራውያን ፈጣሪ ጠርቶናል አሉት ። |
| ወይቤሎሙ ንጉሠ ግብጽ ለምንት ለክሙ ሙሴ ወአሮን ትገፈትእዎ ለዝ ሕዝብ እምግብሩ ፥ ሑሩ ውስተ ግብርክሙ ። | ፬ | የግብጽም ንጉሥ ይህን ሕዝብ ሥራ የምታስፈቱት ለምንድነው ፤ ሙሴና አሮን ወደየ ሥራችሁ ሂዱ አላቸው ። |
| ወይቤሎሙ ፈርዖን ለሕዝቡ ናሁ ይእዜ በዝኑ ወመልኡ ሕዝብ ውስተ ምድር ወአዕረፍክምዎሙ እምግብሮሙ ። | ፭ | ፈርዖን ወገኖቹን እንዲህ አላቸው ፤ እነሆ ዛሬ ሕዝቡ በዝተው በአገሪቱ መሉ ከሥራቸው ብታሣርፍዋቸው ነዋ!! አላቸው ። ዘፀ፥ ፫ ፯ ፥ ፲፭ ፲፬ ። |
| ወአዘዞሙ ፈርዖን ለነዳእተ ገብር ዘሕዝብ ወለዘጸሐፍት ። | ፮ | ፈርዖንም ሥራ የሚያሠሩትን የሚያፋጥኑትን ሹማምንቱንም እንዲህ ሲል አዘዛቸው ። ዘፀ፥ ፲፰ ፬ ፥ ፫ ፯ ። |
| ወይቤሎሙ እምይእዜሰ ኢተሀብዎሙ ዳግመ ሐሠረ ለሕዝብ ለገቢረ ግንፋል በከመ መዋዕለ ትካት ፥ አላ ለሊሆሙ ይሑሩ ወያስተጋብኡ ሎሙ ሐሠረ ። | ፯ | እንግዲህ ወዲህ ለዚህ ሕዝብ እንደወትሮው ዳግመኛ ለጡብ ሥራ ገለባ አትስጡዋቸው እነሱ ሂደው ገለባን ይሰብስቡ እንጂ አላቸው ። ዘፍ፥ ፴፩ ፪ ፥ ፩ ሳሙ፥ ፲፱ ፯ ። |
| ወአምጣነ ጥቦቶሙ ዘይገብሩ ግንፋለ ከማሁ ይግበሩ ኵሎ ዕለተ ፥ ወአልቦ ዘታሐጽጽዎሙ ወኢምንተኒ ዓዲ እምኢወሰክዎሙ እስመ ፅሩዓን ጸርሑ ወይቤሉ ንሑር ወንሡዕ ለእግዚአብሔር አምላክነ ። | ፰ | የሚሠሩትንም ጡብ በጡባቸው መጠን ሁሉ ቀን እንደሉ ይሥሩ ፥ ምንም የምታጐላሉዋቸው የለም ፥ ለፈጣሪያችን እግዚአብሔር መሥዋዕት እንሠዋ ብለው ጮኹ ፥ ገና ሥራን ባትጨምሩላቸው በዝነዋልና ። |
| አክብዱ ግብሮሙ ለእሉ ሕዝብ ወዘንተ ይሐልዩ ወኢይሐልዩ ነገረ ዘይበቍዕ ። | ፱ | በነዚህ ወገኖች ሥራውን አጽኑባቸው ይህን ሥራቸውን ያስባሉ እንጂ የማይረባውን ነገር አያስቡም አላቸው ። |
| ወወፅኡ ነዳእተ ሕዝብ ወጸሐፍት ወይቤልዎሙ ለሕዝብ ከመዝ ይቤ ፈርዖን ኢየሀቡክሙ እንከ ሐሠረ ። | ፲ | የሕዝቡ ሹማምንትና ጸሐፍቱም ወጥተው ሕዝቡን ፈርዖን እንግዲህ ገለባ እንዳይሰጡዋችሁ አዝዋል አሉዋቸው ። |
| ለሊክሙ ሑሩ ወአስተጋብኡ ለክሙ ሐሠረ በኀበ ረከብክሙ ወአልበ ዘየሐፅፅ እምጥበትክሙ ወኢምንተኒ ። | ፲፩ | እናንተ ሂዱችሁ ካገኛችሁበት ቦታ ገለባውን ሰብስቡ ከጡባችሁም (ከምትሠሩት ጡብ) ምንም የሚጐድልባችሁ አይኑር አሉዋቸው ። |
| ወተዘርወ ሕዝብ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ከመ የአልዱ ሎሙ ብርዐ ወሐሠረ ። | ፲፪ | ሕዝቡም ጭዱንና ገለባውን ይሰበስቡ ዘንድ በግብጽ ምድር ሁሉ ተበተኑ ። |
| ወውእቶሙሰ ነዳእቶሙ ያጔጕእዎሙ ወይብልዎሙ ፈጽሙ ግብረክሙ ዘለለዕለትክሙ በከመ አመ ንሁብክሙ ሐሠረ ። | ፲፫ | አስገባሪዎቻቸውም ቀድሞ ገለባ እንሰጣችሁ እንደነበረ ጊዜ እየዕለቱ ሥራችሁን ፈጽሙ እያሉ ያጣድፏቸው ነበር ። |

፲፬ ወይቀሥፍዎሙ ጸሐፍት ወነዳእቶሙ ለደቂቀ እስራኤል እለ ተሠይሙ ዲቤሆሙ በኀበ ፈርዖን ወይቤልዎሙ ለምንት ኢትፌጽሙ ጥበተክሙ ግንፋለ በከመ ትካት ዮምኒ ።

፲፭ ወቦኡ ጸሐፍቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ወአውየዉ ኀበ ፈርዖን ወይቤሉ ለምንት ከመዝ ትገብሮሙ ለአግብርቲከ ሐሠረ ኢይሁቡነ ወይቤሉነ ግበሩ ግንፋለ ።

፲፮ ወናሁ አግብርቲከ ይትቀሠፉ ወይትገፍዑ ።

፲፯ ወይቤሎሙ ፈርዖን ዕሩፋን አንትሙ ወዕሩዓን ፤ ወበእንተ ዝንቱ ትብሉ ንሑር ወንሡዕ ለእግዚአብሔር አምላክነ ።

፲፰ ይእዜኒ ሑሩ ወግበሩ ሐሠረሰ ኢይሁቡክሙ ወጥብተሰ ግንፋለክሙ ታመጽኡ ።

፲፱ ወርእዩ ጸሐፍቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ከመ በእኪት ሀለዉ ወይቤሉ እምጥበትነሂ ዘለለዕለትነ ኢየሐፅፅ ግንፋለ ።

፳ ወተራከብዎሙ ለሙሴ ወለአሮን እንዘ ይመጽኡ በፀአቶሙ እምኀበ ፈርዖን ።

፳፩ ወይቤልዎሙ ይርአይ እግዚአብሔር ለነ ወይፍታሕ ከመ ገበርክሙ ለኔናነ ሰቆራረ በቅድመ ፈርዖን ወበቅድመ ዐበይቱ ከመ ትመጥውዎ ሰይፈ ውስተ እዴሁ በዘ ይቀትለነ ።

፳፪ ወገብአ ሙሴ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤ እግዚኦ ለምንት አኅሠምከ በዝ ሕዝብ ወለምንት ፈነውከኒ ።

፳፫ እምአመ መጻእኩ ኀበ ፈርዖን እንግሮ በቃልከ አሕሠመ ዲበ ሕዝብከ ወኢያድኀንከሁ ለዝ ሕዝብ ።

## ምዕራፍ ፮ ።

፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ናሁ ትሬኢ ዘእገብሮ ለፈርዖን እስመ በእድ ጽንዕት ይፌንዎሙ ወበመዝራዕት ልዕልት ያወጽኦሙ እምድሩ ።

፪ ወተናገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ዘአስተርአይኩ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ ።

፫ እስመ አምላኮሙ አነ ወስምየ ውእቱ አይዳእክዎሙ ፤

፬ ወአቀምኩ መሐላየ ኀቤሆሙ ከመ አሀቦሙ ምድረ ከነአን ምድር ዘኀደሩ ውስቴታ ።

፭ ወአነ ሰማዕኩ ገዓሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ዘይሣቅይዎሙ ግብጽ ወተዘከርኩ መሐላየ ።

፮ አፍጥን ወበሎሙ ለደቂቀ እስራኤል አነ ውእቱ እግዚእ እግዚአብሔር ወአወፅአክሙ እምኀይሎሙ ለግብጽ ወእምቅንየቶሙ ወአድኀነክሙ ወእቤዝወክሙ በመዝራዕትየ ልዑል ወበኰነኔየ ዐቢይ ።

፯ ወእነሥአክሙ ሊተ ወእከውነክሙ አምላከ ወተአምሩ እንከ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክክሙ ዘአውጻእኩክሙ እምድረ ግብጽ ወእምኀይሎሙ ለግብጽ ።

---

በነሱ ላይ በፈርዖን ዘንድ የተሾሙ ሹማምንቱም የእስራኤልን ልጆች የሚያፋጥኑ ሹማምንትን እንደ ቀድሞው ዛሬ ሥራችሁን የማትጨርሱ ለምንድር ነው፤ እያሉ ይገርፉዋቸው ነበር ።

የእኤል ሹማምንትም ገብተው በሮችህን ለምን እንዲህ ታደርጋቸዋለህ ጡብ ሥሩ ይሉቸዋል ፤ ገለባ ግን አይሰጡዋቸውም ፤ ብለው ወደ ፈርዖን ጮኹ ።

አገልጋዮችህ (እስራኤል) እነሆ ይገረፋሉ ይገፋሉ አሉዋቸው ።

ፈርዖንም እናንተ በዝናችኋል ስለዚህ ነገር ሂደን ለፈጣሪያችን ለእግዚአብሔር (የሦስት ቀን መንገድ ሂደን) መሥዋዕት እንሠዋለን ትላላችሁ ።

አሁንም ሂዱና ሥሩ ፤ ገለባ ግን አይሰጡዋችሁም ጡባችሁንም ተቈሳችሁ ታመጣላችሁ አላቸው ።

በእስራኤል ልጆች የተሾሙ አለቆችም በመከራ እንዳሉ አይተው ዕለት ዕለት ከምንሠራው ሥራ ጡቡ አይጐድልልንም አሉ ።

ሙሴንና አሮንንም ከፈርዖን ገብተው ሲወጡ ተገናኙዋቸው ።

ለሚገድለን (ለፈርዖን) በእጁ ሰይፍን ትሰጡት ዘንድ በፈርዖን ፊትና በመኳንንቱ ፊት እንደ በጎ ሽቱ እንወደድ የነበርነው እንዲጸየፉን ያደረጋችሁ እናንተንና እኛን እግዚአብሔር አይቶ ያፈራርደን አሉዋቸው ። ዘፀ፣ ፩ ፱ ።

ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ አቤቱ በዚህ ሕዝብ ላይ ለምን ክፉ ነገር አደረግህ ለምንስ ላከኸኝ፤ ።

ያንተን ቃል ልነግረው ወደ ፈርዖን ከመጣሁ ጀምሮ በወገኖችህ ላይ ክፉ ሥራ ሠራህበት ይህንም ሕዝብ አላዳንከውም አለ ።

## ምዕራፍ ፮ ።

እግዚአብሔር ሙሴን አሁን በፈርዖን ላይ የማደርገውን ታያለህ በጸናች እጅ (ሥልጣን) በበረታች ክንድ ከአገሩ አውጥቶ ይሰዳቸዋልና ። ዘፀ፣ ፲፩ ፩፣ ፲፪ ፴፱ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ተናገረው አለውም ፤ ለአብርሃም ፤ ለይስሐቅ ፤ ለያዕቆብ የታየሁዋቸው እኔ እግዚአብሔር ነኝ ። ዘፍ፣ ፲፯ ፩፣ ፴፭ ፲፩ ።

ፈጣሪያቸው እኔ ነኝና ይህንኑ ስሜም (አሸናፊ እንደ ሆነ) የነገርኋቸው እኔ ነኝ ። ዘፍ፣ ፴፰ ፲ ።

የሚኖሩበትንም የከነዓን አገር እሰጣቸው ዘንድ መሐላዬን አጸናሁላቸው ፤ (ያጸናሁላቸው እኔ ነኝ) ።

እኔ ግብጻውያን የሚያሠቃዩዋቸውን የእስራኤልን ልጆች ልቅሶ ሰማሁ ፤ መሐላዬንም አሰብሁ ። ዘፀ፣ ፪ ፳፬ ።

ፈጥነህ እንዲህ በላቸው ከግብጽ ሠራዊት ለይቼ ከአገዛዛቸው አወጣችኋለሁ ፤ ከፍ ባለ ሥልጣኔ በጽኑ ፍርዴም ተበገርቼ አድናችኋለሁ ። ዘፍ፣ ፴፰ ፲፣ ዘዳ፣ ፳፮ ፰ ።

እናንተ ልጆች ልትሆኑኝ እኔም አባት እሆናችሁ ዘንድ እወስዳችኋለሁ ፤ ከዚህ በኋላ ከግብጽ ምድር ከሠራዊታቸውም ለይቼ ያወጣኋችሁ (ቀድሞም) ፈጣሪያችሁ እኔ

| | | |
|---|---|---|
| | | እግዚአብሔር እንደ ሆንኩ ታውቃላችሁ ። |
| ወእወስደክሙ ውስተ ምድር ዘሰፋሕኩ እዴየ ከመ እሀባ ሎሙ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ ወእሁበክሙ ለክሙ፡ ለርስት አነ እግዚእ እግዚአብሔር ። | ፰ | ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ አወርሳቸው ዘንድ እጄን ዘርግቼ ወደ ማልኩባት ወደ ከነዓን እወስዳችኋለሁ ገዥ የምሆን እኔ እግዚአብሔር (እርሷንም) ርስት አድርጌ ለናንተ እሰጣችኋለሁ ። ዘፍ፡ ፲፭ ፲፰፡ ፳፯ ፫ ። |
| ወነገሮሙ ሙሴ ከመዝ ለደቂቀ እስራኤል ወኢሰምዕዎ ለሙሴ እምእንብዝኃ ነፍሶሙ ወእምዕፀበ ገበሮሙ ። | ፱ | ሙሴም ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብሎ ነገራቸው፤ ነገር ግን ሰውነታቸው አእምሮዋን ከማጣቷ ከመጨነቋም የተነሣ ሙሴን አልሰሙትም ። ዘፀ፡ ፭ ፳፩ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ባእ ወንግሮ ለፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ከመ ይፈንዎሙ ለደቂቀ እስራኤል እምድሩ ። | ፲ | እግዚአብሔር ሙሴን የእስራኤልን ልጆች ከአገሩ አሰናብቶ እንዲሰዳቸው ገብተህ ለግብጽ ንጉሥ ለፈርዖን ንገረው አለው ። ኤር፡ ፩ ፮፡ ግብ፡ ሐዋ፡ ፯ ፶፩ ። |
| ወተናገረ ሙሴ ወይቤ ቅድመ እግዚአብሔር ናሁ ደቂቀ እስራኤል ዘኢሰምዑኒ እፎ ፈርዖን ይሰምዐኒ ወአነ በሃም ። | ፲፩ | ሙሴም በእግዚአብሔር ፊት እንዲህ አለ፤ እነሆ የእስራኤል ልጆች ያልሰሙኝ ፈርዖንማ እንደምን ይሰማኛል፤ ወዲህም ድዳ ነኝ ። ዘሌ፡ ፳፮ ፵፩፡ ፲፱ ፳፫ ። |
| ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወአዘዞሙ ይበልዎ ለፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ያውጽኦሙ ለደቂቀ እስራኤል እምድረ ግብጽ ። | ፲፪ | እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዲህ ብሎ አዘዛቸው የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ ምድር ያወጣቸው ዘንድ ለግብጽ ንጉሥ ለፈርዖን ንገሩት ። |
| ወእሉ እሙንቱ መላእክት በበ ቤተ አበዊሆሙ ለደቂቀ እስራኤል፡ ደቂቀ ሮቤል በኵሩ ለእስራኤል ሄኖኅ ወፍሉስ ወአስሮን ወከርሚ ዝ ውእቱ ትውልዱ ለሮቤል። | ፲፫ | የእስራኤል ልጆች በየአባታቸው ወገን የተሾሙ አለቆች እሊህ ናቸው፤ የእስራኤል የበኵር ልጅ የሮቤል ልጆች ሄኖህ፡ ፍሉስ፡ አስሮንና ከርሚ ናቸው፡ የሮቤል የትውልዱ ቍጥር ይህ ነው ። ዘፍ፡ ፵፮ ፱ ። |
| ወደቂቀ ስምዖን ዩምኤል ወያሚን ወአኦድ ወያኩን ወሱሐር ወሳኡል ዘእምነ ፋኒኤስ፡ ዝ ውእቱ ትውልዱ ለስምዖን ። | ፲፬ | ከፋኒኤስ የተወለዱ የስምዖን ልጆች ዮምኤል፡ ያሚን፡ አኦድ፡ ያኩን፡ ሱሐርና ሳኡል ናቸው፡ የስምዖን ትውልድ ይህ ነው ። ዘፍ፡ ፵፮ ፲፡ ፩ ዜና ፬ ፳፬ ። |
| ወዝ ውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ ሌዊ በበዘመዶሙ ጌድሶን ወቀዓት ወሜራሪ፡ ወዓመተ ሕይወቱ ለሌዊ ምእት ወሠላሳ ወሰብዓቱ ። | ፲፭ | የሌዊም ልጆች በየወገናቸው የሚጠሩበት ስማቸው ይህ ነው፤ ጌድሶን፡ ቀዓት፡ ሜራሪ ናቸው፡ ሌዊም በሕይወት የኖረው ዘመኑ መቶ ሠላሳ ሰባት ነው ። |
| ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ጌድሶን ሎቤኒ ወሰሚዕ በቤተ አቡሆሙ ። | ፲፮ | በየአባታቸው ወገን የተሾሙ የጌድሶንም ልጆች እሊህ ናቸው፤ ሎቤኒ፡ ሰሚዕ ናቸው ። ዘኍ፡ ፫ ፲፰ ። |
| ወደቂቀ ቀዓት እንበረም ወይሳአር ወኬብሮን ወአዝያል ። | ፲፯ | የቀዓትም ልጆች እንበረም፡ ይሳዓር፡ ኬብሮንና አዝያል ናቸው ። ፩ ዜና መዋ፡ ፮ ፫ ። |
| ወዓመተ ሕይወቱ ለቀዓት ምእት ወሠላሳ ወሠለስቱ ። | ፲፰ | ቀዓትም በሕይወት የኖረው ዘመኑ መቶ ሠላሳ ሦስት ነው ። ዘኍ፡ ፫ ፲፱፡ ፳፯ ፶፯ ። |
| ወደቂቀ ሜራሬ ሙሒሊ ወሐሙሲ እሉ እሙንቱ ትውልደ ቤተ ሌዊ በበዘመዶሙ ። | ፲፱ | የሜራሪም ልጆች ሙሒሊ፡ ሐሙሲ ናቸው፡ በየወገናቸው በየዘመዳቸው የሚቈጠሩት የሌዊ ልጆች እሊህ ናቸው ። ዘኍ፡ ፫ ፳፡ ፩ ዜና ፮ ፲፱ ፳፫ ፳፩ ። |
| ወነሥአ ሎቱ እንበረም ብእሲተ እንተ ስማ ዮካብድ ወለተ እኁሁ ለአቡሁ ወወለደቶሙ ሎቱ ለአሮን ወለሙሴ ወለማርያ እኅቶሙ ። | ፳ | እንበረም የአባቱን የወንድም ልጅ ስሟ ዮካብድ የምትባል ሚስት አገባ፡ እሷም አሮንን ሙሴን እኅታቸው ማርያን ወለደችለት ። ዘፀ፡ ፪ ፩ ። |
| ወዓመተ ሕይወቱ ለእንበረም ምእት ወሠላሳ ወሰብዓቱ ። | ፳፩ | እንበረም በሕይወት የኖረው መላ ዘመኑ መቶ ሠላሳ ሰባት ዓመት ነው ። ዘፀ፡ ፪ ፩ ። |
| ወደቂቀ ይሳዓር ቆሬ ወናፌግ ወዝክር ። | ፳፪ | የይሳዓርም ልጆች ቆሬ፡ ናፌግና ዝክር ናቸው ። |
| ወደቂቀ አዝያን ሚሳኤል ወኤልሳፊን ወሰትሪ ። | ፳፫ | የአዝያንም ልጆች ኤልሳፊን ሚሳኤልና ሰትሪም ናቸው ። ዘኍ፡ ፳፯ ፶፱፡ ፲፮ ፩ ። |
| ወነሥአ ሎቱ አሮን ብእሲተ እንተ ስማ ኤልሳቤጥ ወለተ አሚናዳብ እኅቱ ለነአሶን ወወለደቶሙ ሎቱ ለናዳብ ወለአብዩድ ወለአልአዛር ወለይታምር ። | ፳፬ | አሮንም የነአሶን እኅት የአሚናዳብን ልጅ ስሟ ኤልሳቤጥ የምትባል ሚስት አገባ፡ እሷም ናዳብን አብዩድን አልአዛርንና ይታምርን ወለደችለት ። ሩት ፬ ፲፱ ። |
| ወደቂቀ ቆሬ አሴር ወሕልቃና ወአብያሴፍ፡ ዝ ውእቱ ትውልዱ ለቆሬ ። | ፳፭ | የቆሬም ልጆች አሴር፡ ሕልቃና፡ አብያሴፍ ናቸው፤ የቆሬ የትውልዱ ቍጥር ይህ ነው ። |

፳፭ ወአልአዛር ወልደ አሮን ነሥአ ሎቱ ብእሲተ እምአዋልደ ፋጢኤል ወወለደት ሎቱ ለፊንሐስ፡ ወእሉ ቀዳምያተ ትውልዶሙ ለሌዋውያን በበነገዶሙ ።

፳፮ ወእሉ እሙንቱ አሮን ወሙሴ እለ ይቤሎሙ እግዚአብሔር ያውፅእዎሙ ለደቂቀ እስራኤል እምድረ ግብጽ ምስለ ኀይሎሙ ።

፳፯ እሉ እሙንቱ እለ ተባሀልዎ ለፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ከመ ይፈንዎሙ ለደቂቀ እስራኤል እምብሔረ ግብጽ ሙሴ ወአሮን እሙንቱ፡ በዕለት ዘተናገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ በምድረ ግብጽ ።

፳፱ ወተናገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ንግሮ ለፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ኵሎ ዘአነ እቤለከ ።

፴ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር ናሁ ፀያፍ አነ እፎ ይሰምዐኒ ፈርዖን ።

## ምዕራፍ ፯ ።

፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ናሁ ረሰይኩከ አምላከ ለፈርዖን ወአሮን እኁከ ይኩንከ ነቢየ ።

፪ ወአንተሰ ንግሮ ኵሎ ዘአዘዝኩከ ወአሮን ይንግሮ ለፈርዖን ከመ ይፈንዎሙ ለደቂቀ እስራኤል እምድሩ ።

፫ ወአነ አጸንዕ ልቦ ለፈርዖን ወአበዝኅ ተአምርየ ወመድምምየ በምድረ ግብጽ ወኢይሰምዐክሙ ፈርዖን ።

፬ ወእወዲ እዴየ ዲበ ብሔረ ግብጽ ወአወፅኦሙ በኀይልየ ለሕዝብየ ለደቂቀ እስራኤል እምድረ ግብጽ በበቀል ዐቢይ ።

፭ ወየአምሩ እንከ ኵሉ ግብጽ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር፡ ወእሰፍሕ እዴየ ዲበ ብሔረ ግብጽ ወአወፅኦሙ ለደቂቀ እስራኤል እማእከሎሙ ።

፮ ወገብሩ ሙሴ ወአሮን በከመ አዘዞሙ እግዚአብሔር ።

፯ ወከኖ ለሙሴ ሰማንያ ዓም፡ ወለአሮን ሰማንያ ወሠለስቱ ዓም አመ ተናገርዎ ለፈርዖን ።

፰ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን፡ እመ ይቤለክሙ ፈርዖን ሀቡኒ ተአምረ ወመድምመ፡ በሎ ለአሮን እኁከ ንሥእ ለዛቲ በትር ወግድፋ ቅድሜሁ ለፈርዖን ወቅድመ ዐበይቱ ወትከውን አርዌ ምድር ።

፱ ወቦኡ ሙሴ ወአሮን ቅድመ ፈርዖን ወገብሩ ከማሁ በከመ አዘዞሙ እግዚአብሔር ።

፲ ወገደፈ አሮን በትሮ በቅድመ ፈርዖን ወበቅድመ ዐበይቱ ወኮነት አርዌ ምድር ።

፲፩ ወጸውዖሙ ፈርዖን ለጠቢባን ወለመሠርያን ወገብሩ ሐራስያነ ግብጽ በሥራያቲሆሙ ከማሁ ።

፲፪ ወወገሩ አብትሪሆሙ ወኮኑ አራዊተ ምድር ወውኅጠቶሙ በትረ አሮን ለአብትረ እልክቱ ።

፲፫ ወጸንዐ ልቡ ለፈርዖን ወአበየ ሰሚዐ በከመ ይቤ እግዚአብሔር ።

፲፬ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ክቡድ ልቡ ለፈርዖን

የአሮን ልጅ አልአዛርም ከፋጢኤል ልጆች ሚስት አግብቶ ፊንሐስን ወለደችለት፡ በየወገናቸው ከሚቈጠሩ ከሌዋውያን ልጆች የሚቀድሙ እሊህ ናቸው ።

የእስራኤልን ልጆች ከሠራዊታቸው ጋር ከግብጽ አገር ያወጡዋቸው ዘንድ እግዚአብሔር የነገራቸው እነዚህ ሙሴና አሮን ናቸው ። ዘፀ፡ ፲፪ ፲፯፡ ዘኍ፡ ፴፫ ፩ ።

የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ አገር ያሰናብታቸው ዘንድ የግብጹን ንጉሥ ፈርዖንን የተከራከሩት ሙሴና አሮን እነዚህ ናቸው፤ እግዚአብሔር በግብጽ አገር ሙሴን በተናገረው ቀን እንዲህ ሆነ ። ዘፀ፡ ፭ ፩-፫ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡ እኔ የምነግርህን ሁሉ ለግብጽ ንጉሥ ለፈርዖን ንገረው ብሎ ተናገረው ።

ሙሴም እግዚአብሔርን እነሆ እኔ ድዳ ነኝ ፈርዖን እንደምን ይሰማኛል፤ አለው ። ዘፀ፡ ፯ ፲፪፡ ፯ ፬ ፯ ፲፩ ።

## ምዕራፍ ፯ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እነሆ ለፈርዖን አምላኩ አድርጌሃለሁ ወንድምህ አሮንም አስተርጓሚ ይሁንህ አለው ።

አንተስ ያዘዝኩህን ሁሉ ለአሮን ንገረው፡ አሮንም የእስራኤልን ልጆች ከአገሩ አሰናብቶ እንዲሰዳቸው ለፈርዖን ይንገረው አለው ። ዘፀ፡ ፬ ፲፮፡ ፯ ፳ ።

እኔም የፈርዖንን ልብ አጸናዋለሁ፡ በግብጽም አገር ፍጹም ተአምራቴን አብዝቼ አደርጋለሁ፡ ፈርዖንም አይሰማችሁም ። ዘፀ፡ ፲፩ ፱ ።

እጄንም በግብጽ አገር ላይ አደርጋለሁ፡ ወገኖቼ የእስራኤልንም ልጆች በታላቅ ኃይሌ (ፍርዴ) ከግብጽ አገር አወጣቸዋለሁ ። ዘፀ፡ ፯ ፯፡ ፬ ፯ ።

እንግዲህ የግብጽ ሰዎች ሁሉ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ያውቃሉ እጄ መዓቴን በግብጽ አገር ላይ ዘርግቼ የእስራኤልን ልጆች ከመካከላቸው ለይቼ አወጣቸዋለሁ ።

ሙሴና አሮንም እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደረጉ ።

ፈርዖንንም በተናገሩት ጊዜ ለሙሴ ሰማንያ ዓመት፡ ለአሮንም ሰማንያ ሦስት ዓመት ሆኗቸው ነበር ።

እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን እንዲህ አላቸው፤ ፈርዖን ተአምራት አድርጋችሁ አሳዩኝ ቢላችሁ ወንድምህ አሮንን ይህችን በትር አንስተህ በፈርዖን ፊትና በሹማምንቱ ፊት ጣላት እባብ ትሆናለች በለው ።

ሙሴና አሮንም ከፈርዖን ዘንድ ገብተው እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደረጉ ። ዘፍ፡ ፩ ፳፡ ዮሐ፡ ፪ ፲፫ ።

አሮንም በሹማምንቱና በፈርዖን ፊት በትሩን ጣለና እባብ ሆነች ። ዘፀ፡ ፬ ፫፡ ኢሳ፡ ፭ ፱ ።

ፈርዖንም አዋቂዎቹንና አስማተኞቹን ጠራቸው፡ የግብጽ ሟርተኞችም በሥራያቸው እንደነሱ አደረጉ ።

(እነሱም) በትሮቻቸውን (ወደ መሬት) ጣሉ እባቦችም ሆኑ፡ የአሮንም በትር የነዚያን በትሮች ዋጠቻቸው ።

እግዚአብሔርም እንደተናገረ፡ የፈርዖን ልብ ጸና፡ አልሰማም አለ ። ዘፀ፡ ፯ ፳፬፡ ፰፡ ፲፱ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፤ ወገኖቼ እስ

ከመ ኢይፈንዎሙ ለሕዝብ ።

፲፭ ወሑር ኀበ ፈርዖን በጽባሕ ናሁ ኀበ ማየ ተከዚ ይወ
ፅእ ውእቱ ወይቀውም ወተቀበሎ ኀበ ገበዘ ተከዚ ፡ ወለ
እንታክቲ በትር እንተ ኮነት አርዌ ምድር ንሥአ በእዴከ፤

፲፮ ወበሎ እግዚአብሔር አምላከ ዕብራውያን ፈነወኒ ኀ
ቤከ እንዘ ይብል ፈኑአ ሕዝብየ ከመ ይፀመዱኒ በሐቅል
ወናሁ ኢሰማዕከ እስከ ዛቲ ዕለት ።

፲፯ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር በዝንቱ ተአምር ከመ አነ
ውእቱ እግዚአብሔር ናሁ አነ እዘብጥ በዛ በትር እንተ
ውስተ እዴየ ማየ ተከዚ ወይከውን ደመ ።

፲፰ ወይመውቱ ዓሣት ዘውስተ ተከዚ ወይጸይእ ተከዚ
ወኢይክሉ ግብጽ ሰትየ ማይ እምተከዚ ።

፲፱ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በሎ ለአሮን ንሥእ
ለበትርከ ወስፋሕ እዴከ ዲበ ማያተ ግብጽ ወዲበ አፍላ
ጋሙ ወዲበ አስራጊሆሙ ወዲበ አዕያጊሆሙ ወዲበ ኵሉ
ምቅዋመ ማዮሙ ፡ ወይከውን ደም ውስተ ኵሉ ምድረ
ግብጽ ወውስተ ዕፀው ወውስተ አእባን ።

፳ ወገብሩ ከመዝ ሙሴ ወአሮን በከመ አዘዞሙ እግዚአ
ብሔር ፡ ወአልዐለ አሮን በትሮ ወዘበጠ ማየ በውስተ ተከ
ዚ በቅድመ ፈርዖን ወበቅድመ ዐበይቱ ወኮነ ደመ ማይ
ዘውስተ ተከዚ

፳፩ ወሞቱ ዓሣት ዘውስተ ተከዚ ወጼአ ተከዚ ወስእኑ
ግብጽ ሰትየ ማይ እምተከዚ ፡ ወኮነ ደም ውስተ ኵሉ ም
ድረ ግብጽ ።

፳፪ ወገብሩ ከማሁ ሐራስያነ ግብጽ በሥራያቲሆሙ ፡ ወጸ
ንዐ ልቡ ለፈርዖን ወአበየ ሰሚዖቶሙ በከመ ይቤ እግዚ
እብሔር ።

፳፫ ወገብአ ፈርዖን ወቦአ ቤቶ ወኢተመይጠ ልቡ በዝ
ንቱ ኵሉ ።

፳፬ ወከረዩ ኵሉ ግብጽ ዐውዶ ለተከዚ ከመ ይስተዩ ማየ
ወስእኑ ሰትየ ማይ እምተከዚ ።

፳፭ ወተፈጸመ ሰቡዕ ዕለት እምድኅረ ዘበጦ እግዚአብ
ሔር ለተከዚ ።

ምዕራፍ ፰ ።

፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ባእ ኀበ ፈርዖን ወበ
ሎ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፈኑ ሕዝብየ ከመ ይፀመ
ዱኒ በሐቅል ።

፪ ወለእመ አበይከ አንተ ፈንዎቶሙ ናሁ አነ እዘብጥ
ኵሎ አድባሪከ በቈርነናዓት ።

፫ ወይቀድዕ ተከዚ ቈርነናዓተ ወየዓርግ ወይበውእ ውስ
ተ ሕብያቲከ ወውስተ ውሣጥያተ ቤትከ ወጽርሕከ ወዲበ
ዐራትከ ወውስተ አብያተ ዐበይትከ ወዲበ ሕዝብከ ወው
ስተ ሐሪጽከ ወውስተ እቶናቲከ ።

፬ ወዲቤከ ወዲበ ዐበይትከ ወዲበ ሕዝብከ የዐርግ ቈር
ነናዓት ።

ራኤልን እንዳይሰዳቸው የፈርዖን ልቡ ጸና አለው ።
ማልደህ ወደ ፈርዖን ሂድ፡ እነሆ እሱ ወደ ፈሳሹ
ውኃ ይቆማል ፡ ከፈሳሹ ውኃ ዳር ወጥተህ ተቀበለው ፡
እባብ የሆነች በትሪቱንም በእጅህ ይዘኻት ሂድ ።
የዕብራውያን ፈጣሪ እግዚአብሔር በምድረ በዳ ያገለ
ግሉኝ ዘንድ ወገኖቼን (እስራኤልን) አሰናብተህ ስደዳቸው
እነሆም እስከ ዛሬ ድረስ (ቃሌን) አልሰማህም ብሎ ወዳ
ንተ ልኮኛል በለው ። ዘፀ፡ ፫ ፲፰ ፡ ፯ ፰ ።
እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤ እኔ እግዚአብሔር እንደ
ሆንኩ በዚህ ታውቃለህ እነሆ በእጄ በተያዘችው በትር
ፈሳሹን እመታለሁ ደምም ይኾናል በለው አለ ።
በፈሳሹም ውስጥ ያሉ ዓሣዎች ይሞታሉ ፡ ፈሳሹም
ይሸታል ፡ የግብጽም ሰዎች የፈሳሹን ውኃ መጠጣት አይ
ችሉም ። ዘፀ፡ ፯ ፳፩ - ፳፬ ።
እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፤ አሮንን እባብ
የሆነችውን በትር አንሥተህ እጅህን በግብጽ ውኃዎች
በወንዞቻቸውም በምንጮቻቸውም በኩሬዎቻቸውም በው
ኃ ማከማቻቸውም እጅህን ዘርጋ በለው ፡ በግብጽም አገር
ሁሉ ዕንጨቶችም ደንጊያዎችም ሁሉ ደም ይሆናሉ ።
ሙሴና አሮንም እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደረጉ
አሮንም በትሩን አንሥቶ በፈርዖንና በመኳንንቱ ፊት በፈ
ሳሹ ወንዝ ያለውን ውኃ መታው ፡ የፈሳሹም ውኃ ደም
ሆነ ። መዝ፡ ፸፰ ፳፱ ፡ ፻፭ ፵፬።
በፈሳሹ ውስጥ ያሉ ዓሣዎችም ሞቱ፡ ፈሳሹም ሸተተ
የግብጽም ሰዎች ከፈሳሹ ወንዝ ውኃ መጠጣት ተሳና
ቸው ፡ በግብጽም አገር ሁሉ ደም ሆነ ። ዘፀ፡ ፯ ፲ ፡ ፰ ፳፫።
የግብጽ ሟርተኞችም (ኢያኔስ ኢያንበሬስ) በአስማ
ታቸው እንዲሁ አደረጉ እግዚአብሔር እንደተናገረም የፈ
ርዖን ልቡ (በክፋት) ጸና መስማታቸውን እምቢ አለ ።
ፈርዖን ተመልሶ ወደ ቤቱ ገባ ፡ ነገር ግን በዚህ ሁሉ
ነገር ልቡ አልተመለሰም ። ዘፀ፡ ፯ ፫ ፬ ።
የግብጽ ሰዎች ሁሉ ከፈሳሹ ውኃ መጠጣት ተስኗቸ
ዋልና ውኃ ሊጠጡ ከፈሳሹ ዳር ጒድጓድ ቆፈሩ ።
እግዚአብሔር ፈሳሹን ውኃ (ደም ከደረገው) ከመ
ታው በኋላ ሰባቱ ቀን ተፈጸመ ።

ምዕራፍ ፰ ።

እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ፈርዖን ገብተህ እንዲህ
በለው፤ በምድረ በዳ እንዲያገለግሉኝ ወገኖቼን አሰናብ
ተህ ስደድ ። ዘፀ፡ ፩ ፰ ፡ ፫ ፲፪ - ፲፰ ።
አልሰዳቸውም ብትል ግን እኔም ተራራዎችህን ሁሉ
በጓጉንቸሮች እመታለሁ (ተሰቦ ቀንዳማትል ጓጉንቸር
ዘጕል ልብሱ እንዲያስገኝ አደርጋለሁ) ። ዘፀ፡ ፯ ፲፬ ።
ፈሳሹም ጓጉንቸርን ያፈላል (ያስገኛል) ከፈሳሹም ወ
ጥቶ ወደ ቤቶችህ ወደ እልፍኞችህ ፡ ወደ አዳራሽህ ፡ ወደ
አልጋህ ፡ ወደ ሹማምንትህም ቤት ወደ ዱቄትህ ፡ ወደ
ምድጃችህ ይገባል ። ዘፍ፡ ፵፫ ፴ ፡ መዝ፡ ፸፰ ፴ ።
በንተም በሹማምንትህም በወገኖችህም ላይ ጓጉንቸር
(ቀንዳምትል) ይዘምታል ። ዘፀ፡ ፯ ፲፱ ።

፭ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በሎ ለአሮን እኑክ ስፋሕ በእዴከ ወበትረከ ዲበ አፍላግ ወዲበ አስራግ ወዲበ አዕያግ ወይጻእ ቈርነንዓት ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው ፤ ወንድምህ አሮንን እጅህን ዘርጋተህ በትርህን ይዞህ ወንዞቹን ምንጮቹን ኩሬዎቹን ምታ ጓጉንቸርም ይውጣ አለው ።

፮ ወሰፍሐ አሮን እዴሁ ዲበ ማያተ ግብጽ ወወፅአ ወዓርገ ቈርነንዓት ወከደኖ ለምድረ ግብጽ ።

አሮንም በግብጽ ውኃዎች ላይ እጁን ዘረጋ፤ ጓጉንቸር (ክዚያ) ወጥቶ የግብጽን አገር ሸፈነው ።

፯ ወገብሩ ከማሁ ሐራስያን ግብጽ በሥራያቲሆሙ ወአውጽኡ ቈርነንዓተ ዲበ ምድረ ግብጽ ።

የግብጽ ጠንቋዮች በሥራያቸው እንዲሁ አድርገው በግብጽ ምድር ላይ ጓጉንቸር ቀንዳማትል፤ ዘጕል ልብሱን አወጡ ። ዘፀ፥ ፯ ፲፩ ፳፪ ።

፰ ወጸውዖሙ ፈርዖን ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ፤ ጸልዩ ሊተ ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይሰስል ሊተ ቈርነንዓት እምኔየ ወእምሕዝብየ ወእፌንዎ ለሕዝብ ይሡዑ ለእግዚአብሔር ።

ፈርዖን ሙሴንና አሮንን ጠርቶ ጓጉንቸሩ (ቀንዳማትሉ) ከኔና ከሕዝቤ እንዲርቅልን ወደ እግዚአብሔር ጸልዩልኝ (እኔም) ሕዝቡን ለእግዚአብሔር ሊሠዋ እለቀዋለሁ አላቸው ። ዘፀ፥ ፱ ፳፰፤ ፲ ፲፰ ።

፱ ወይቤሎ ሙሴ ለፈርዖን ዐድመኒ ማእዜ እጼሊ ለከ ወለዐበይትከ ወለሕዝብከ ከመ ይማስን ቈርነንዓት እምኔከ ወእምሕዝብከ ወእምዐበይትከ እንበለ ውስተ ተከዚ ይተርፍ ።

ሙሴም ፈርዖንን እንዲህ አለው ፤ በፈሳሹ ውስጥ ከሚቀረው በቀር ከሹማምንትህ፤ ከወገኖችህ፤ ከንተም ጓጉንቸሩ እንዲርቅልህ ላንተ ለሹማምንትህና ለወገኖችህ መቼ እንድጸልይልህ ቀጠረኝ ። መሳ፥ ፯ ፪፤ ኢሳ፥ ፲ ፲፭ ።

፲ ወይቤሎ ፈርዖን ለጌሠም ወይቤሎ አሆ በከመ ትቤ ለከ ከመ ታእምር ከመ አልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበለ እግዚአብሔር ።

ፈርዖንም ለነገ አለው፤ (ሙሴም) ከእግዚአብሔር ሌላ ባዕድ አምላክ እንደሌለ ታውቅ ዘንድ እሺ እንዳልከኝ ይሁን አለው ። ፪ ሳሙ፥ ፯ ፳፪፤ ፩ ዜና መዋ፥ ፲፯ ፳ ።

፲፩ ወይሴስል ቈርነንዓት እምኔከ ወእምአብያቲከ ወእምዐበይትከ ወእምሕዝብከ እንበለ ውስተ ተከዚ ይተርፍ ።

ጓጉንቸሩም በፈሳሹ ከሚቀረው በቀር ከወገንህ፤ ከሹማምንትህ ከቤቶችህና ከንተም ይርቃል ።

፲፪ ወወፅኡ ሙሴ ወአሮን እምኀበ ፈርዖን ወአውየወ ኀበ እግዚአብሔር በእንተ ሙስና ቈርነንዓት በከመ አዘዘ ፈርዖን ።

ሙሴና አሮንም ከፈርዖን ዘንድ ወጥተው ፈርዖን እንዳዘዘ ጓጉንቸሩን አጥፋልን ብለው ወደ እግዚአብሔር ጮኹው ለመኑ ።

፲፫ ወገብረ እግዚአብሔር በከመ ይቤ ሙሴ ወሞተ ቈርነንዓት እምአብያት ወእምአህጉር ወእምሐቅል ።

እግዚአብሔር ሙሴ እንደለመነው አደረገ፤ ከቤቶች ከከተሞችና ከበረኻ የነበሩ ጓጉንቸሮች ሞቱ ።

፲፬ ወአስተጋብኡ ክምረ ክምረ ወጼአት ምድር ።

ሰብስበውም አልፈው አልፈው ከመሩት፤ ምድሪቱም ገማች ። ዘፀ፥ ፰ ፴፤ ፱ ፯ መክ፥ ፰ ፲፩ ።

፲፭ ወሰበ ርእየ ፈርዖን ከመ ኮነ ዕረፍት ከብደ ልቡ ወአበየ ሰሚያቶሙ በከመ ነበበ እግዚአብሔር ።

ፈርዖን ግን ዕረፍት እንደሆነ በየ ጊዜ ልቡ ጸና፤ እግዚአብሔርም እንደተናገረ መስማታቸውን እምቢ አለ ።

፲፮ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በሎ ለአሮን ሰፋሕ በእዴከ በትረከ ወዝብጥ መሬተ ምድር ወይወፅአ ፃዑት ዲበ ሰብእ ወዲበ እንስሳ ወውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው ፤ (ወንድምህ) አሮንን በእጅህ በትርህን አንሥተህ የምድሩን ትቢያ ምታ በሰውም በከብቱም በግብጽም አገር ሁሉ (ጭጫን ዘመሚት ትንኝ) ሳንጃ ይወጣል በለው ።

፲፯ ወሰፍሐ አሮን በእዴሁ በትሮ ወዘበጠ መሬተ ምድር ወወጽአ ፃዑት ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ።

አሮንም በእጁ በትሩን አንሥቶ የምድሩን ትቢያ መታ በሰውም በከብቱም በግብጽም አገር ሁሉ ትንኝ ሳንጃ ወጣ ። መዝ፥ ፻፭ ፴፩ ።

፲፰ ወገብሩ ከማሁ ሐራስያን ግብጽ በሥራያቲሆሙ ከመ ያውጽኡ ፃዑተ ወስእኑ ወወፅአ ፃዑት ዲበ ሰብእ ወዲበ እንስሳ ።

የግብጽ ጠንቋዮችም በሚርታቸው ትንኝን ሳንጃን ያወጡ ዘንድ እንዲሁ አደረጉ፤ ነገር ግን ማውጣት ተሳናቸው፤ ትንኙ ሳንጃው በሰውም በከብቱም ወጣ ።

፲፱ ወይቤልዎ ሐራስያን ለፈርዖን አጽባዕተ እግዚአብሔር ውእቱ ዝንቱ ወጸንዐ ልቡ ለፈርዖን ወአበየ ሰሚዖቶሙ በከመ ነበበ እግዚአብሔር ።

ጠንቋዮቹም (ኢያኔስ ኢያንበሬስ) ፈርዖንን ይህስ የእግዚአብሔር ጣት ነው አሉት፤ የፈርዖን ልብ ግን ጸና፤ እግዚአብሔር እንደ ተናገረ መስማታቸውን እምቢ አለ ።

፳ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ጊሥ በጽባሕ ወቁም ቅድሜሁ ለፈርዖን ናሁ ኀበ ማይ ይወጽእ ውእቱ ወበሎ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፈኑ ሕዝብየ ከመ ይፀመዱኒ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ነገ ጧት ገስግሰህ ሂደህ በፈርዖን ፊት ቁም፤ እነሆ እሱ ወደ ወንዝ ይወርዳል፤ እግዚአብሔር እንዲህ አለ ያገለግሉኝ ዘንድ ወገኖቼን አሰናብተህ ስደድ ብሎኻል በለው ። ዘፀ፥ ፱ ፲፫ ።

፳፩ ወለእመ አበይከ ፈንዎተ ሕዝብየ ናሁ አነ እፌኑ ዲቤከ፤ ወዲበ ዐበይትከ፤ ወዲበ ሕዝብከ፤ ወዲበ አብያቲከ

ወገኖቼን አልለቅም ያልክ እንደሆነ ግን እነሆ እኔም በንተ በሹማምንትህ በወገኖችህ በቤቶችህም ተርብ (የውሻ

ጽንጽያ ክልብ ወይመልእ ውስተ አብያተ ግብጽ ወውስተ
ምድርሂ እንተ ሀለውከ ውስቴታ ።
፳፪ ወእሴብሕ በይእቲ ዕለት በምድረ ጌሤም እንተ ውስ
ቴታ ሀለዉ ሕዝብየ ወኢይሄሉ ህየ ጽንጽያ ክልብ ከመ
ታእምር ከመ አነ ውእቱ እግዚእ ለኵሉ ምድር ።
፳፫ ወእፈልጥ ማእከለ ሕዝብየ ወማእከለ ሕዝብከ ወጌ
ሠመ ይከውን ዝ ነገር ።
፳፬ ወገብረ እግዚአብሔር ከማሁ ፡ ወመጽአ ጽንጽያ ክል
ብ ብዙኅ ውስተ አብያተ ፈርዖን ወውስተ አብያተ ዐበይቱ
ወውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ወማሰነት ምድር እምጽንጽያ
ክልብ ።
፳፭ ወጸውዖሙ ፈርዖን ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ
ሑሩ ወሡዑ ለአምላክክሙ በዛ ምድር ።
፳፮ ወይቤሎ ሙሴ ኢይትከሃል ከመዝ ይኩን እስመ ዘየ
ሐርሙ ግብጽ ንሠውዕ ለአምላክነ ወእመ ሦዕነ ዘየሐርሙ
በቅድሜሆሙ ይዌግሩነ ።

፳፯ ምሕዋረ ሠሉስ ዕለት ንሑር ውስተ ሐቅል ወንሡዕ
ለእግዚአብሔር አምላክነ በከመ ይቤለነ ።

፳፰ ወይቤሎ ፈርዖን አነ እፌንወክሙ ትሡዑ ለእግዚአ
ብሔር አምላክክሙ በሐቅል ወበሕቱ ኢትትአተቱ ወር
ኁቀ ኢትሑሩ ወጸልዩ ሊተ ኀበ እግዚአብሔር ።
፳፱ ወይቤሎ ሙሴ ናሁ አነ እወጽእ እምኀቤከ ወእጼሊ
ኀበ እግዚአብሔር ወይሴስል ጽንጽያ ክልብ እምኔከ ወእ
ምዐበይትከ ወእምሕዝብከ ፍጡነ ወኢትድግም እንከ
አስተዐብዶ ከመ ኢትፈኑ ሕዝበ ይሡዑ ሎቱ ።

፴ ወወፅአ ሙሴ እምኀበ ፈርዖን ወጸለየ ኀበ እግዚ
አብሔር ።
፴፩ ወገብረ እግዚአብሔር በከመ ይቤ ሙሴ ወአሰሰለ
ጽንጽያ ክልብ እምፈርዖን ወእምዐበይቱ ወእምሕዝቡ
ወኢተርፈ ወኢአሐዱሂ ።
፴፪ ወአክበደ ልበ ፈርዖን ወበዝንቱሂ ጊዜ አበየ ፈን
ዎቶሙ ለሕዝብ ።

## ምዕራፍ ፱ ።

፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በእ ኀበ ፈርዖን ወበ
ሎ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ ዕብራውያን ፈኑ
ሕዝብየ ከመ ይፀመዱኒ ።
፪ ወእመ አበይከ ፈንዎተ ሕዝብየ ወኑዲ አጽናዕከሙ
ናሁ ትከውን እዴየ ዲበ እንስሳከ በሐቅልከ ዲበ አፍራስ
ወዲበ አእዱግ ወዲበ አግማል ወዲበ አልሕምት ወዲበ
አባግዕ ሞት ዐቢይ ጥቀ ።

፫ ወእሴብሕ አነ ማእከለ እንስሳ ግብጽ ወማእከለ እንስሳ
ደቂቀ ፳ኤል ወኢይመውት እንከ እምኵሉ ዘደቂቀ እስ
ራኤል ወኢምንትኒ ።

ዝንብ) እሰዳለሁ ፡ ይኸውም በግብጽ ቤቶችና አንተ በም
ትኖርበት ምድርም ሁሉ ይመላል አለ በለው ።
ወገኖቼ በሉበት በጌሤም ምድር በዚያች ቀን እመሰገ
ናለሁ ፡ ለዓለም ሁሉ ገዥ እኔ እንደ ሆንኩም ታውቅ
ዘንድ ተርቡ በዚያ (በጌሤም ምድር) አይኖርም ።
በወገኖችህና በወገኖቼ መካከል (ድንበር) እለያለሁ ፡
ይህም ነገር (ተአምራት) ነገ ይደረጋል አለ በለው ።
እግዚአብሔርም እንዲሁ አደረገ ፡ ብዙም ተቆናጣጭ
ዝንብ በፈርዖን ቤት በመኳንንቱም ቤቶች ውስጥ በግብ
ጽም አገር ሁሉ መጣ ፡ ከተቆናጣጭ ዝንብ የተነሣም
ምድሪቱ ጠፋች ። መዝ፡ ፸፰ ፵፰ ፡ ፻፭ ፴፪ ።
ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን ጠርቶ ፡ ሂዱናችሁ በዚ ያች
ምድር ለፈጣሪያችሁ ሠዉ አላቸው ።
ሙሴም (ፈርዖንን) ግብጻውያን የሚጸየፉትን (ላሙን)
ለፈጣሪያችን እንሠዋለንና የሚጸየፉትን (ላሙን) በፊታ
ቸው ብንሠዋ በደንጊያ ወግረው ይገድሉናልና እንዲህ
ይሆን ዘንድ አይቻልም አለው ። ዘፍ፡ ፵፫ ፴፪ ።
እኛስ (ሠውልኝ ብሎ) እንዳዘዘን የሦስት ቀን መንገድ
ሂደን በምድረ በዳው ለፈጣሪያችን ለእግዚአብሔር እን
ሠዋ አለው ። ዘፀ፡ ፫ ፲፰ ።
ፈርዖንም ሙሴን እንዲህ አለው ፤ ለፈጣሪያችሁ ለእ
ግዚአብሔር በምድረ በዳው ልትሠዉ እሰዳችኋለሁ ፡ ነገር
ግን ርቃችሁ አትሂዱ ለኔም ወደ እግዚአብሔር ለምኑልኝ ።
ሙሴም ፈርዖንን እንዲህ አለው ፤ አሁን ከንተ ዘንድ
ወጥቼ ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ ፡ የውሻ ዝንብም
(ተርቡ) ከንተ ከሹማምንትህና ከወገኖችህ ፈጥኖ ይርቃል
ነገር ግን ይሠውለት ዘንድ ወገኖቼን (እስራኤል) እንዳት
ለቅ ሁነህ እግዚአብሔርን ዳግመኛ አላዋቂ አታድርገው ።
ሙሴም ከፈርዖን ዘንድ ወጥቶ ወደ እግዚአብሔር
ጸለየ ። ዘፍ፡ ፴፩ ፯ ፡ መሳ፡ ፲፮ ፲ ።
እግዚአብሔርም ሙሴ እንዳለው አደረገ ፡ የውሻ ዝን
ቡን ከፈርዖን ከመኳንንቱ ከሕዝቡም አራቀ (አጠፋ) አን
ድ ስንኳ አልቀረም ። ያዕ፡ ፭ ፲፮ ።
ፈርዖን ግን ልቡናውን አጸና ፡ በዚህም ጊዜ ወገኖቹን
አሰናብቶ መስደዱን እምቢ አለ ።

## ምዕራፍ ፱ ።

እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ፈርዖን ገብተህ የዕብራው
ያን አምላክ እግዚአብሔር ያገለግሉኝ ዘንድ ሕዝቤን አሰ
ናብት ብሎኻል ብለህ ንገረው አለው ። ዘፀ፡ ፩ ፪ ፡ ፯ ፲፮ ።
ወገኖቼን አሰናብተህ በትሰዳቸው ዳግመኛም ልቡና
ህን ብታጸናባቸው ግን እነሆ እደ መዓቱ በምድረ በዳ በሉ
በከብቶችህ በፈረሶችህ በአህዮችህ በግመሎችህ በላሞች
ህና በበጎችህም ላይ ትሆናለች ይኸውም እጅግ ጽኑ
ሞት ነው ። ዘፀ፡ ፰ ፪ ፡ ሮሜ ፪ ፭ ።
እኔም በእስራኤል ልጆች ከብቶችና በግብጽ ከብቶች
መካከል (ተአምራት አድርጌ) እመሰገናለሁ እንግዲህ ከእ
ስራኤል ልጆች ከብቶች ከሆነው ወገን ምንም አይሞትም
አለ ብለህ ንገረው አለው ። ፪ ሳሙ፡ ፭ ፯ ።

፮ ወወሀበ እግዚአብሔር ዕድሜ ወይቤ ጌሠመ እገብር ዘ ነገረ በዲበ ምድር ።

እግዚአብሔርም (ለፈርዖን) ይህንን ነገር ነገ በግብጽ ምድር ላይ አደርገዋለሁ ብሎ ቀጠሮ ሰጠው ።

፯ ወገብረ እግዚአብሔር ዘ ነገረ በሣኒታሁ ወሞተ ኵሉ እንስሳ ግብጽ ወእምእንስሳ ደቂቀ እስራኤልሰ ኢሞተ ወኢአሐዱ ።

እግዚአብሔር ይህንን ነገር በነጋታው አደረገው የግብጽ ሰዎች ከብት ሁሉ ሞተ፤ ከእስራኤል ልጆች ከብት ወገን ግን አንድ ስንኳ አልሞተም ። መዝ፡ ፸፰ ፶ ።

፰ ወሰበ ርእየ ፈርዖን ከመ ኢሞተ እምእንስሳ ደቂቀ እስራኤል ወኢአሐዱ ከብደ ልቡ ወኢፈነዎ ለሕዝብ ።

ፈርዖን ከእስራኤል ልጆች ከብት ወገን አንድ ስንኳ እንዳልሞተ ባየ ጊዜ ልቡ (በክፋት) ጸና፤ ሕዝቡንም አል ለቀውም ። ዘፀ፡ ፰ ፲፭ ።

፱ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ንሥኡ ለክሙ ምልአ እደዊክሙ ሐመደ እምእቶን ወይዝርዎ ሙሴ ውስተ ሰማይ በቅድመ ፈርዖን ወበቅድመ ወበይቱ።

እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን የምድጃውን አመድ በእጃችሁ ሙሉ ዘግናችሁ ወስዳችሁ ሙሴ በሹማምንቱና በፈርዖን ፊት ወደ ሰማይ ይበትነው አላቸው ።

፲ ወይከውን ቆብር ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ወይከውን ጸልአ ዘይፈልሕ ዲበ ሰብእ ወዲበ እንስሳ ወዲበ ዘአርበዕቱ እግሩ በኵሉ ምድረ ግብጽ ።

በግብጽ አገር ሁሉ ትቢያ ይሆናል፤ በሰውም በከብትም ላይ በግብጽ አገር አራት እግር ባለው ሁሉ ላይ ቍስል (ጉርምጥ ቸፌ) ይወጣል (ይፈላል) አላቸው ።

፲፩ ወነሥአ ሙሴ ሐመደ እቶን በቅድመ ፈርዖን ወዘረዎ ውስተ ሰማይ ወኮነ ጸልአ ዘይፈልሕ ዲበ ሰብእ ወዲበ እንስሳ ።

ሙሴም የምድጃውን አመድ በእጁ ዘግኖ በፈርዖን ፊት ወደ ሰማይ በተነው፤ በሰውም በከብቱም ላይ የሚወጣ ቍስል (ጉርምጥ ዋጣ ቸፌ) ሆነ ። ራእ፡ ፲፮ ፪ ።

፲፪ ወስእኑ ሰብአ ሥራይ ቀዊመ ቅድመ ሙሴ በእንተ ጸልአ እስመ አኀዞሙ ጸልአ ለመሠርያን ወለኵሉ ሰብአ ግብጽ ።

ጠንቋዮቹም (ኢያኔስ ኢያንበሬስ) ቍስል ይዟቸዋልና በቍስሉ ምክንያት በሙሴ ፊት መቆም ተሳናቸው፤ የግብጽንም ሰዎች ሁሉ ይዟቸዋልና ። ዘፀ፡ ፯ ፲፩፤ ፰ ፲፰።

፲፫ ወአጽንዐ እግዚአብሔር ልበ ለፈርዖን በከመ ነገሮሙ ወኢሰምዖሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ።

እግዚአብሔርም የፈርዖንን ልብ (በክፋት) አጸናው፤ እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን እንደ ነገራቸው አልሰማቸውም ። ዘፀ፡ ፬ ፳፩ ።

፲፬ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ጊሥ በጽባሕ ወቁም ቅድሜሁ ለፈርዖን ወበሎ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላክ ዕብራውያን ፈኑ ሕዝብየ ከመ ይፀመዱኒ ።

እግዚአብሔር ሙሴን ነገ ጧት ገስግሰህ ሂደህ በፈርዖን ፊት ቁም፤ እንዲህም በለው፤ የዕብራውያን አምላክ እግዚአብሔር (መሥዋዕት ሠውተው) ያገለግሉኝ ዘንድ ወገኖቼን አሰናብተህ ስደድ ብሎ ኀል ብለህ ንገረው አለው።

፲፭ እስመ ይእዜ በዝ ጊዜ አነ እፌኑ ኵሎ መዐትየ ውስቴትከ ወበዐበይትከ ወበሕዝብከ ከመ ታእምር ከመ አልቦ ከማየ ውስተ ኵሉ ምድር ።

በዓለሙ ሁሉ ላይ እንደኔ ያለ ሌላ እንደሌለ ታውቅ ዘንድ በአንተም በወገኖችህም በመኳንንቶችህም ላይ ቍጣዬን ሁሉ በዚህች ቀን እሰድብኻለሁ እከን ብለህ ንገረው አለው ። ዘፀ፡ ፰ ፲ ። ፩ ዜና መዋ፡ ፲፯ ፳ ።

፲፮ ወይእዜኒ እፌኑ እዴየ ወእዘብጠከ ወለሕዝብከኒ ወእቀትለክሙ ወትትቀጠቀጥ ምድርክሙ ።

አሁንም እደ መናቴን አምጥቼ አንተንም ወገኖችህንም እመታችኋለሁ እገድላችሁም አለሁ፤ ምድራችሁም ትጠፋለች አለ በለው ። ኢሳ፡ ፵፯ ፱ ።

፲፯ ወበእንተዝ ዐቀብኩከ ከመ አርኢ ብከ ጽንዕየ ወከመ ይትየዳዕ ስምየ ውስተ ኵሉ ምድር ።

እኔስ ስለዚህ ነገር ኃይሌን ከሃሊነቴን አገልጥብህ ዘንድ ስሜም በዓለሙ ሁሉ ይነገር ዘንድ (እስከ ዛሬ ድረስ) ጠብቄህ ነበር ። ሮሜ ፱ ፲፯፤ ምሳ፡ ፲፯ ፬ ።

፲፰ ወዓዲ አንተሰ ታጸንዕ ሕዝብየ ወኢትፌንዎ ።

አንተ ግን በወገኖቼ ላይ ዳግመኛ ልቡናህን (በክፋት) ታጸናባቸዋለህ፤ አታሰናብታቸውም ።

፲፱ ናሁ አነ እዘንም ጌሠመ ዘ ጊዜ በረደ ብዙኀ ጥቀ ዘኢኮነ ከማሁ እምአመ ተፈጥረ ብሔረ ግብጽ እስከ ዛቲ ዕለት ።

እኔም የግብጽ አገር ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እንደሱ ያለ ተደርጎ የማያውቅ እጅግ ብዙ የሆነ በረድን ይህን ጊዜ አዘንማለሁ ።

፳ ወይእዜኒ አፍጥን አስተጋብእ እንስሳከ ወኵሎ ዘብከ ውስተ ሐቅል እስመ ኵሉ ሰብእ ወእንስሳ ዘተረክበ ውስተ ሐቅል ወኢቦአ ቤተ ይወድቅ ዲቤሁ በረድ ወይመውት።

አሁንም በምድረ በዳ የተገኘ ከብትና ሰው ሁሉ ወደ ቤትም ያልገባ ሁሉ በርሱ ላይ በረድ ይወድቅበታልና እሱም ይሞታልና፤ በበረኸ ያለህን (ገንዘብ) ሁሉና ከብትህን ፈጥነህ ሰብስብ አለው ።

፳፩ ወዘፈርሀ ቃለ እግዚአብሔር እምዐበይተ ፈርዖን ያስተጋብእ እንስሳሁ ውስተ አብያት ።

ከፈርዖን ሹማምንትም የእግዚአብሔርን ቃል የፈራ ከብቱን ወደ ቤት ይሰበስባል (ይሰብስብ)። ዘፀ፡ ፺ ሸ፫ ።

፳፪ ወዘኢሐለየ በልቡ ቃለ እግዚአብሔር ይኅድግ እን

የእግዚአብሔርን ቃል በልቡናው ያላሰበ ግን ከብቱን

ሰሳሁ ውስተ ገዳም ።

፳፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ስፋሕ እዴከ ውስተ ሰማይ ወይኩን በረድ ዲበ ኩሉ ምድረ ግብጽ ዲበ ሰብእ ወዲበ እንስሳ ወዲበ ኩሉ ሣዕር ዘውስተ ኩሉ ምድር ።

፳፪ ወሰፍሐ ሙሴ እዴሁ ውስተ ሰማይ ፡ ወወሀበ እግዚአብሔር ቃለ ወበረደ ወርአ እሳት ዲበ ምድር ወአዝነመ እግዚአብሔር በረደ ዲበ ኩሉ ምድረ ግብጽ ።

፳፫ ወእሳቱ ይነድድ ውስተ በረዱ ፡ ወበረደሰ ብዙኀ ጥቀ ወዕዙዝ ዘኢኮነ ከማሁ እምአመ ተፈጥሩ አሕዛብ ውስተ ገጸ ምድር በግብጽ እስከ ዛቲ ዕለት ።

፳፬ ወቀተለ በረድ ኩሉ ምድረ ግብጽ እምሰብእ እስከ እንስሳ ወኩሉ ሣዕረ ዘውስተ ገዳም አማሰነ ፡ ወኩሉ ዕፀወ ዘውስተ ሐቅል ቀጥቀጠ ።

፳፭ ዘእንበለ ምድረ ጌሤም ኀበ ሀለዉ ደቂቀ እስራኤል ኢወረደ በረድ ።

፳፮ ወለአከ ፈርዖን ወጸውዖሙ ለሙሴ ወለአሮን ፡ ወይቤሎሙ አበስኩ ይእዜኒ እግዚአብሔር ጻድቅ ወአንሰ ወሕዝብየ ረሲዓን ።

፳፯ ጸልዩ እንከሰ ኀበ እግዚአብሔር ወይሁዳእ እንከ ወኢይኩን ቃለ እግዚአብሔር በረድኒ ወእሳትኒ እፌንወክሙ ወኢያነብረክሙ ዳግመ ።

፳፰ ወይቤሎ ሙሴ ለፈርዖን ሶበ ወፃእኩ እምሀገር እሴ ፍሕ እዴየ ኀበ እግዚአብሔር ወየሀድእ ቃል ወበረድኒ ወእሳት ወዝናምኒ አልቦ እንከ ከመ ታእምር ከመ ለእግዚአብሔር ይእቲ ምድር ።

፳፱ ወአንተሰ ወዐበይትከ አእምር ከመ እምአመ ኮንክሙ ኢፈራህክምዎ ለእግዚአብሔር ።

፴ ተላቤ ወሰገም ማሰነ ወሰገምሰ ዘእንበለ ይሰብል ተዘብጠ ወተላቤ በዘአውጽአ ዘርአ ።

፴፩ ወሥርናይ ወዐተር ኢተዘብጠ እስመ ብሱል ውእቱ ።

፴፪ ወወፅአ ሙሴ እምኀበ ፈርዖን አፍአ እምሀገር ወአልዐለ እዴሁ ኀበ እግዚአብሔር ወሀድአ ቃል ወበረድ ወዝናምኒ ኢነፍነፈ እንከ ዲበ ምድር ።

፴፫ ወሶበ ርእየ ፈርዖን ከመ ሀድአ ዝናም ወበረድ ወቃል ወሰከ አብሶ ወአክበደ ልበ ውእቱ ወዐበይቱኒ ።

፴፬ ወኢፈነዎሙ ለደቂቀ እስራኤል በከመ ነገረ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

ምዕራፍ ፲ ።

፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ፡ ባእ ኀበ ፈርዖን እስመ አነ አክበድኩ ልበ ለፈርዖን ወለዐበይቱኒ ከመ ዕሩየ ይምጻእ ተአምርየ ላዕሌሆሙ ።

፪ ወከመ ትንግሩ ለደቂቅክሙ ወለደቂቀ ደቂቅክሙ ኩሎ ዘተሣለቁ ላዕለ ግብጽ ወተአምርየ ዘገበርኩ በሙ-

በበረኻ ይተዋል (ይተው) ። ራእ፡ ፲፯ ፳፩ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን እጅህን ወደ ሰማይ ዘርጋ፡ በግብጽም አገር በሰውም በከብትም ሁሉ በምድርም ላይ ባለው ሣሩ (በእኽሉ) በረድ ይዝነምበት አለው ።

ሙሴም እጁን ወደ ሰማይ ዘረጋ፡ እግዚአብሔርም ቃል ሰጠ ነጕድጓድንና በረድን አዘነበ ፡ እሳትም በበረዱ መከከል ይብለጨለጭ ነበር ፡ እግዚአብሔር በግብጽ አገር ሁሉ በረድን አዘነመ ። ኢያሱ ፲ ፲፩ ፡ ራእ፡ ፰ ፯ ።

እሳቱም በበረዱ መከከል ብልጭ ይል ነበር ፡ በረዱ ግን ሕዝቦች በዓለም ላይ ከተፈጠሩ ጀምሮ በግብጽ አገር እስከዚያች ቀን ድረስ ተደርጎ የማያውቅ እጅግ ብዙ ነበር።

በረዱም ከሰው ጀምሮ እስከ ከብቱ ድረስ የግብጽን አገር ሁሉ አጠፋ፡ (ደበደበ) በበረኻም ያለ ሣሩን (እኽሉን) ሁሉ በምድረ በዳም ያለውን ዕንጨት ሁሉ አጠፋ።

ነገር ግን፡ የእስራኤል ልጆች ባሉበት በጌሤም ምድር ብቻ በረድ አልወረደም ። ዘፀ፡ ፲ ፳፪ ፡ ፪ ፬ - ፯ ።

ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን ልኮ አስጠራቸው፡ ዛሬም በደልኩ እግዚአብሔር እውነተኛ ነው ፡ እኔና ወገኖቼ ግን በደለኞች ነን ። ፪ ዜና መዋ፡ ፲፪ ፯ ፡ ሰቈ፡ ፩ ፲፰ ።

እንግዲህ ወዲያ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ፡ እንግዲህ (መቅሠፍቱ) ጸጥ ይበል ፡ የእግዚአብሔርም ቃል አይሰማ በረዱም እሳቱም አይውረድ ፡ እለቃችኋለሁ ዳግመኛም አላኖራችሁም ። መዝ፡ ፻፳፱ ፬ ፡ ዳን፡ ፱ ፲፬ ።

ሙሴም ፈርዖንን ከከተማ በወጣሁ ጊዜ እጄን ወደ እግዚአብሔር እዘረጋለሁ፡ መብረቅ ነጕድጓድ እሳቱና በረዱም ጸጥ ይላል ፡ ይህችም ምድር የእግዚአብሔር (ገንዘብ) እንደሆነች ታውቅ ዘንድ ዝናሙ አይዘንምም ።

አንተና ሹማምንትህ ግን ከተፈጠራችሁ ጀምሮ እግዚአብሔርን እንዳልፈራችሁት (እንዳላመለካችሁት) አውቃለሁ ። ፩ ነገ፡ ፳፪ ፴፫ ፡ መዝ፡ ፻፵ ፫ ።

ተልባውም ገብሱም ጠፋ፡ ገብሱ ሳይዘረዝር ፡ ተልባውም ሲዘረዝር ተመታ ። ፩ ነገ፡ ፰ ፳፪ ፡ ኢሳ፡ ፩ ፲፭ ።

ሥንዴውና አተሩ ግን ደርቆ (ተወቅቶ) ነበርና አል ተመታም ። ዘፀ፡ ፲ ፳፪ ።

ሙሴም ከፈርዖን ዘንድ ወደ ውጭ ወጥቶ እጁን አን ሥቶ ወደ እግዚአብሔር ለመነ፡ መብረቅ ነጕድጓድ ጸጥ አለ፡ ከዚያ በኋላ ዝናም ስንኳ በምድር ላይ አላካፋም ።

ፈርዖንም መብረቅ ነጕድጓድ፡ በረዱና ዝናሙ ጸጥ እንዳለ በየ ጊዜ በደልን ጨመረ፡ ልቡንም (በክፋት) አደነደነ፡ እሱም ሹማምንቱም ። ፩ ሳሙ፡ ፮ ፮ ።

እግዚአብሔር ለሙሴ እንደነገረው የእስራኤልን ልጆች አሰናብቶ አልሰደዳቸውም ። ዘፀ፡ ፯ ፲፫ ፡ ፬ ፲፫ ።

ምዕራፍ ፲ ።

እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ፈርዖን ግባ፡ ተአምራቱ ተከክሉ ይመጣባቸው ዘንድ እኔ የፈርዖንና የሹማምንቱን ልብ (በክፋት) አጽንቼዋለሁና አለው ። ዘፀ፡ ፬ ፳፩ ።

በግብጽ ሰዎች የዘበትኩባቸውን ያደረግሁባቸውን ተአምራቱን ሁሉ ለልጆቻችሁም ለልጅ ልጆቻችሁም ትነ

ወተአምሩ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ።

ግሩ ዘንድ (ይህንም ሁሉ ያደረግሁ) እኔ የዕብራውያን ፈጣሪ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ታውቃላችሁ ። ዘዳ፥ ፬ ፱ ።

፫ ወቦኡ ሙሴ ወአሮን ኀበ ፈርዖን ወይቤልዎ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ ዕብራውያን፡ እስከ ምንትኑ ተአቢ ኀፊርትየ፡ ወኢትፌኑ ሕዝብየ ከመ ይፀመዱኒ ።

ሙሴና አሮንም ወደ ፈርዖን ገብተው የዕብራውያን ፈጣሪ እግዚአብሔር እኔን የማታፍረኝ እስከ መቼ ድረስ ነው፤ (መሥዋዕት) ሠውተው እንዲያገለግሉኝ ወገኖቼን የማትለቃቸውስ እስከ መቼ ድረስ ነው፤ (እግዚአብሔር በሉት) አለ ። ፪ ዜና፥ ፴፬ ፳፯፤ ፩ ጴጥ፥ ፭ ፮ ።

፬ ወእመሰ አበይከ ፈንዎቶ ሕዝብየ ናሁ አነ አመጽእ ጌሠመ ዘ ጊዜ አንበጣ ብዙኀ ዲበ ኵሉ አድባሪከ ።

ወገኖቼን መልቀቅ እምቢ ካልክ ግን እነሆ እኔ ነገ ይህን ጊዜ በተራራዎችህ ሁሉ ላይ ብዙ አንበጣን አመጣለሁ ። ዘሌ፥ ፳፮ ፳፪፤ ምሳ፥ ፴ ፳፯ ።

፭ ወይከድን ገጸ ለምድር ወኢትክል ርእዮታ ወይበልዕ ኵሎ ተረፈ ዘተርፈ ውስተ ምድር ዘአትረፈ በረድ ወይበልዕ ኵሎ ዕፀ ዘይበቊል ለክሙ ውስተ ምድር ።

የምድሪቱንም ፊት ይሸፍናል፤ (አንተም) ምድርን ማየት አትችልም አንበጣውም በምድር ላይ በረድ ያስቀረውን ትርፍ በግብጽ የተከላችሁትን ዛፍ ሁሉ ይበላል ።

፮ ወይመልእ አብያቲከ ወዘአበይትከ ወኵሎ አብያተ ዘውስተ ምድረ ግብጽ፡ ዘእምአመ ኮኑ ኢርእዩ አበዊክሙ ወኢእምቅድሜክሙ ወኢእማሑቶሙ እምአመ ተፈጥሩ አሕዛብ ውስተ ምድር እስከ ዛ ዕለት፡ ወተግኅሠ ወወፅአ እምኀበ ፈርዖን ።

ሕዝቦች በዚህ ዓለም ከተፈጠሩ ጀምሮ እስከዚች ቀን ድረስ አባቶቻችሁ አያቶቻችሁ ቅድም - አያቶቻችሁ ከተፈጠሩ ጀምሮ አይተውት የማያውቁ አንበጣ በቤቶችህና በሹማምንትህ ቤቶች በግብጽ አገር ባለው ሰው ሁሉ ቤትም ይመላል፤ አለ እግዚአብሔር በሉት፤ ይህንም ነገር ተናግረው ከፈርዖን ዘንድ ወጥተው ሄዱ። ዘፀ፥ ፰ ፴፩።

፯ ወይቤልዎ ዐበይቱ ለፈርዖን፡ እስከ ማእዜኑ ትከውን ለዕሌነ ዛቲ እኪት ዕቅብት፡ ፈኑ ሰብአ ከመ ይፀመድዎ ለእግዚአብሔር አምላኮሙ፡ አው እንዘ ተአምርኑ ትፈቅድ ከመ ትትኀጐል ምድረ ግብጽ ።

የፈርዖን ሹማምንትም ይህች ጭንቅ መከራ የምትደረግብን እስከ መቼ ድረስ ነው፤ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርን ያገለግሉ ዘንድ ሰዎቹን አሰናብተህ ስደድ፤ ወይስ እያወቅህ የግብጽ አገር ልትጠፋ ትወዳለህን፤ አሉት ።

፰ ወጸውዕዎሙ ለሙሴ ወለአሮን ኀበ ፈርዖን ወይቤሎሙ ፈርዖን ሑሩ ወተፀመድዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ፤ ወባሕቱ መኑ ወመኑ እንትሙ እለ ተሐውሩ ።

ሙሴንና አሮንን ጠርተው ወደ ፈርዖን አመጡዋቸው ፈርዖንም ሂዱ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን አገልግሉት፤ ነገር ግን የምትሄዱት ማንና ማን ናችሁ፤ አላቸው ።

፱ ወይቤሎ ሙሴ ምስለ ወራዙቲነ ወአእሩጊነ ወምስለ ደቂቅነ ነሐውር ወአዋልዲነ ወአባግዒነ ወአልህምቲነ ንወስድ፡ እስመ በዓለ እግዚአብሔር አምላክነ ውእቱ ።

ሙሴም የፈጣሪያችን እግዚአብሔር በዓል ነውና ከጐልማሶቻችን ከሽማግሌዎቻችን ከሴቶች ልጆቻችንና ከወንዶች ልጆቻችን ጋራ እንሄዳለን፤ ላሞቻችንንና በጎቻችንንም እንወስዳለን አለው ። ዘፀ፥ ፭ ፩ ።

፲ ወይቤሎሙ ፈርዖን ይኩን ከመዝ እግዚአብሔር ምስሌክሙ ናሁ ኢያክሙሰ እፌኑ ወደቂቅክሙ አእምሩኬ ከመ እኪተ ትሔልዩ ።

ፈርዖንም እንዲህ ይሁን እግዚአብሔር ከናንተ ጋራ ይሁን እነሆ እናንተን ግን አሰናብቼ እሰዳችኋለሁ፤ ልጆቻችሁንና ገንዘባችሁንም ውሰዱ፤ ነገር ግን ክፉ እንደምታስቡ አወቁ አለው ። ዘፀ፥ ፭ ፩ ።

፲፩ ከመዝኑ የሐውሩ ሰብእ ዘይፀመዱ ለእግዚአብሔር፤ ምንተ እንከ ተኀሥሡ፤ ወአውፅእዎሙ እፍአ እምገጸ ፈርዖን ለሙሴ ወለአሮን ።

እግዚአብሔርን የሚያገለግል ሰው እንዲህ ሆኖ ይሄዳልን፤ እንግዲህ ምን ትፈልጋላችሁ፤ ያን ጊዜ ሙሴንና አሮንን ከፈርዖን ፊት ወደ ውጭ አወጡዋቸው ።

፲፪ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ስፋሕ እዴከ ዲበ ምድረ ግብጽ ወይዕርግ አንበጣ ዲበ ምድር ወይብላዕ ኵሎ ሣዕረ ምድር ወኵሎ ፍሬ ዕፅ ዘአትረፈ በረድ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን በግብጽ አገር ላይ እጅህን ዘርጋ በምድርም ላይ አንበጣ ይውጣ፤ የምድሩን ሣርና (አኽሉን) በረድ ያስቀረውንም የዛፍ ፍሬ ሁሉ ይብላ አለው ። ዘፀ፥ ፲ ፳፩፤ ፯ ፲፱፤ ፱ ፳፪ ።

፲፫ ወአልዐለ ሙሴ በትሮ ውስተ ሰማይ ወአምጽአ እግዚአብሔር ነፋስ አዜብ ውስተ ምድር ኵላ ይእተ ዕለተ ወኵሎ ሌሊተ እስከ ጸብሐ ወዝኩ ነፋስ አዜብ ነሥአ ለአንበጣ ወአምጽአ ኀበ ምድረ ግብጽ ።

ሙሴም በእጁ በትሩን ወደ ሰማይ ከፍ አድርጎ (ጸለየ) እግዚአብሔርም በግብጽ ላይ እስኪነጋ ድረስ ሙሉ ቀንና ሙሉ ሌሊት የአዜብን ነፋስ አመጣ፤ ያም የአዜብ ነፋስ አንበጣውን ወደ ግብጽ አገር አነሣው ።

፲፬ ወነበረ ዲበ ኵሉ ምድረ ግብጽ ብዙኀ ጥቀ ወዕዙዝ፤ ዘእምቅድሜሁ ኢኮነ ከማሁ አንበጣ ወእምድኅሬሁ ኢይከውን ከማሁ ።

በግብጽም አገር ሁሉ ሰፍሮ ኖረ፤ አንበጣውም ከዚህ በፊት እንደዚህ ያለ ተደርጎ የማያውቅ እንግዲህም ወዲህ እንደዚህ ያለ ይደረጋል የማይባል እጅግ ብዙ ብርቱም ነበር ። መዝ፥ ፸፰ ፵፮፤ ፻፭ ፴፬ ።

፲፭ ወከደነ ገጻ ለምድር ወማሰነት ምድር ወበልዐ ኵሎ ማዕረ ምድር ወኵሎ ፍሬ ዕፀ ዘተርፈ እምበረድ ወኢተ ርፈ ሐመልማል ውስተ ዕፀው ወኢአሐዱ ወኢውስተ ኵሉ ማዕረ ሐቅል በኵሉ ምድረ ግብጽ ።

፲፮ ወአፍጠነ ፈርዖን ጸውዖቶሙ ለሙሴ ወለአሮን ወይ ቤሎሙ አበስኩ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወዲ ቤክሙ ።

፲፯ ሥረዩ እንከ ይእዜኒ ኃጢአትየ ወጸልዩ ኀበ እግዚ ብሔር አምላክክሙ ይሰስል እምኔየ ዝ ሞት ።

፲፰ ወወፅአ ሙሴ እምኀበ ፈርዖን ወጸለየ ኀበ እግዚአብ ሔር ።

፲፱ ወሚጠ እግዚአብሔር ነፋሰ እምባሕር ዐቢይ ወነሥአ ለአንበጣ ወወሰዶ ውስተ ባሕረ ኤርትራ ወኢተርፈ ወኢ አሐዱ አንበጣ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ።

፳ ወአጽንዐ እግዚአብሔር ልበ ለፈርዖን ወኢፈነዎሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

፳፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ስፋሕ እዴከ ውስተ ሰማይ ወይኩን ጽልመት ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ጽል መት ዘይትገሠሥ ።

፳፪ ወሰፍሐ እዴሁ ሙሴ ውስተ ሰማይ ወኮነ ጽልመት ወቆባር ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ሠሉሰ ዕለተ ።

፳፫ ወኢርእየ አሐዱ ካልአ ወአልቦ ዘተንሥአ እምስካቡ ሠሉሰ ዕለተ ወለኵሉ ደቂቀ እስራኤልሰ ብርሃ በኵሉ ኀበ ሀለዉ ።

፳፬ ወጸውዖሙ ፈርዖን ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ ሑሩ ወተፀመድዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ እንበለ አባግዒክሙ ወአልሕምቲክሙ ዘተኀድጉ ወደቂቅክሙሰ ንሥኡ ምስሌክሙ ።

፳፭ ወይቤሎ ሙሴ ለፈርዖን አልቦ፣ አንተኑ ዓዲ ትሁበነ ለመሥዋዕት ዘንገብር ለእግዚአብሔር አምላክነ፣ እብነኑ ንገብር ።

፳፮ ወእንስሳነሂ የሐውር ምስሌነ፣ ወኢንኀድግ ወኢምን ተኒ እስመ እምኔሁ ንነሥእ ለመሥዋዕተ እግዚአብሔር አምላክነ፣ ወንሕነሰ ኢንአምር ምንተ ውእቱ ተፀምዶ ለእ ግዚአብሔር አምላክነ፣ እስከ ንበጽሕ ህየ ።

፳፯ ወአጽንዐ እግዚአብሔር ልበ ለፈርዖን ወአበየ ፈንዎ ቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

፳፰ ወይቤሎ ፈርዖን ለሙሴ ሑር እምኀቤየ ወዑቅ ርእ ሰከ ዳግመ እንከ እመ ርኢከ ገጽየ ወእምከመ ርኢኩከ ዳግመ ትመውት ።

፳፱ ወይቤሎ ሙሴ አሆ ኢይሬኢ እንከ ገጸከ ።

ምዕራፍ ፲፩ ።

፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ዓዲ አሐተ መቅሠ

የምድሪቱን ፊት ሸፈነው፣ ምድሪቱም (እልም ድር ግም ብላ) ጠፋች፣ የምድሩን ሣር (እኽሉን) ከበረድ የቀ ረውንም የዛፉን ፍሬ ሁሉ በላው፣ በዛፎቹም ልምላሜ አንድም አልቀረም፣ በግብጽ አገር ሁሉ በለው የበረኻ ሣር ሁሉ ልምላሜ አልቀረም ። ዘፀ፣ ፱ ፲፭፣ ፱ ፴፪ ።

ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን ፈጥኖ አስጠርቶ ፈጣሪያ ችሁ እግዚአብሔርንና እናንተን በደልሁ ። ዘፀ፣ ፱ ፳፯ ።

እንግዲህ አሁን ዛሬ የበደልሁትን በደል ይቅር በሉኝ ይህ ሞት ከኔ ይርቅልኝ ዘንድ ወደ ፈጣሪያችሁ ወደ እግ ዚአብሔር ለምኑልኝ አላቸው ። ዘፀ፣ ፱ ፳፰ ።

ሙሴም ከፈርዖን ዘንድ ወጥቶ ወደ እግዚአብሔር ለመነ ። ፩ ነገ፣ ፲፫ ፮፣ ኢዩ፣ ፴፬ ፴፩ ።

እግዚአብሔርም ነፋሱን ከታላቁ ባሕር መለሰው፣ ነፋሱም አንበጣውን (ከግብጽ አገር) አንሥቶ ወደ ኤርትራ ባሕር ወሰደው፣ በግብጽ አገር ሁሉ አንድ አንበጣ ስንኳ አልቀረም ። መሰ፣ ፬ ፳፩፣ ፲፯ ፲፬፣ ኢዮብ ፪ ፳ ።

እግዚአብሔርም የፈርዖንን ልብ አጸና፣ የእስራኤል ንም ልጆች አሰናብቶ አልሰደዳቸውም ። ዘፀ፣ ፲ ፳፯ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እጅህን ወደ ሰማይ ዘርጋ፣ በግ ብጽ አገር ሁሉ ላይ ጨለማ ይሁን፣ ጨለማውም በእጅ የሚዳሰስ (ግዙፍ ጨለማ) ነው ። ዘፀ፣ ፱ ፳፪ ።

ሙሴም እጁን ወደ ሰማይ ዘረጋ፣ በግብጽ አገር ሁሉ ላይ ሦስት ቀን ጭጋግና ጨለማ ሆነ ። መዝ፣ ፻፭ ፳፰ ።

አንዱም አንዱን አያየውም ነበር፣ ሦስቱንም ቀን ከም ኝታው የተነሣ ሰው አልነበረም፣ ለእስራኤል ልጆች ሁሉ ግን በሉበት ቦታ ሁሉ ብርሃን ሆኖላቸው ነበር ።

ፈርዖን ሙሴንና አሮንን ጠርቶ ትታችሁት የምትሄ ዱት ላሞቻችሁንና በጎቻችሁን ነው እንጂ ፈጣሪያችሁ እግ ዚአብሔርን ሂዱችሁ አገልግሉት፣ ልጆቻችሁን ግን ከና ንተ ጋራ ውሰዷቸው አላቸው ። ዘፀ፣ ፲፰ ፲፫ ።

ሙሴም ፈርዖንን አይደለም!!፣ ለፈጣሪያችን እግዚአ ብሔር የምናቀርበው መሥዋዕት ገና አንተ ትሰጠናለህን፣ ወይስ ደንጊያውን መሥዋዕት እናቀርበዋለን፣ አለው ።

ለፈጣሪያችን ለእግዚአብሔር ከሱ እናቀርባለንና እኛ ም ከዚያው እስክንደርስ ድረስ ለፈጣሪያችን እግዚአብ ሔር ማገልገልም ምን እንደሆነ እናውቅምና ላሞቻችን በጎ ችን አብሮን ከኛ ጋር ይሄዳል እኛም ላሞቻችንን በጎችንን አንተውም አለው ።

እግዚአብሔርም የፈርዖንን ልብ (በክፋት) አጸና፣ የእ ስራኤልን ልጆች አሰናብቶ መስደድን እምቢ አለ ።

ፈርዖን ሙሴን ከኔ ዘንድ ሂድ እንግዲህ ዳግመኛ ፊቴ ን ያየህ እንደሆነ፣ እኔም ዳግመኛ ያየሁህ እንደሁ ለራስህ ዕወቅ፣ ትሞታለህ አለው ። ዘፀ፣ ፲ ፳ ።

ሙሴም እሺ በጎ እንግዲህ ወድያ ፊትህን አላይም አለው ። ዕብ፣ ፲፩ ፳፯

ምዕራፍ ፲፩ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንግዲህ አለው፣ በፈርዖንና

| | | |
|---|---|---|
| ፍተ አመጽእ ዲበ ፈርዖን ወዲበ ግብጽ፥ ወእምድኅረዝ ይፌንወክሙ እምዝየ ወአመ ይፌንወክሙ ምስለ ኵሉ ንዋየ ፀአት ያወፅአክሙ ። | | በግብጽ ላይ ገና አንዲት መቅሠፍት አመጣለሁ፥ ከዚያ በኋላ ግን ከዚህ (ከግብጽ) አሰናብቶ ይሰዳችኋል፥ አሰና ብቶ ሲሰዳችሁም የምትወጡበትን ገንዘብ ሁሉ ሰጥቶ ያወጣችኋል ። ዘፀ፥ ፪ ፳፫፥ ፲፪ ፴፩፥ ፴፫ ፵፱ ። |
| ወንግሮሙ ጽሚተ በዕዝኖሙ ለሕዝብ ወይትወሐስ ኢሐዱ እምካልኡ ወብእሲትኒ እምካልእታ ንዋየ ብሩር ወወርቅ ወልብስ ። | ፪ | ይህንንም ለሕዝቡ ቀስ ብለህ በጆሮአቸው ንገራቸው አንዱ ከንዱ (ጎረቤቱ) ሴቲቱም ከጐረቤቷ የብርንና የወር ቅን የልብስንም ዕቃ ይዋስ ። ዘፀ፥ ፫ ፳፪፥ ፲፪ ፴፭ ። |
| ወወሀቦሙ እግዚአብሔር ለሕዝብ ሞገሰ በቅድመ ግብጽ ወአውሐስዎሙ፥ ወዝ ብእሲ ሙሴ ዐቢየ ኮነ ጥቀ ቅድመ ግብጽ ወቅድመ ፈርዖን ወቅድመ ዐበይቱ ። | ፫ | እግዚአብሔርም ለወገኖቹ (ለእሥራኤል) በግብጻውያን ፊት በሰሟልነትን ሰጠኋቸው (ያሉትን ዕቃ ሁሉ) አዋሰዋቸው ይህም ሙሴ በግብጽ ሰዎች በፈርዖንና በሹማምንቱ ፊት እጅግ ታላቅ ሰው ሆነ (ከበረ)። ዘፀ፥ ፲፪ ፴፯ ። |
| ወይቤ ሙሴ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር መንፈቀ ሌሊት እበውእ እነ ማእከለ ግብጽ ። | ፬ | ሙሴ እንዲህ አለ እግዚአብሔር እኔ በመንፈቀ ሌሊት ወደ ግብጽ ሰዎች መከከል እገባለሁ አለ ። |
| ወይመውት ኵሉ በኵር በምድረ ግብጽ እምበኵረ ፈርዖን ዘይነብር ዲበ መንበረ መንግሥት እስከ በኵረ አመት እንተ ትነብር ዲበ ማኅረፅ ወእስከ ኵሉ በኵረ እንስሳ ። | ፭ | በመንግሥት ዙፋን ከሚቀመጠው ከፈርዖን በኵር ጀ ምሮ፥ በወፍጮ እስከለችው ባርያ በኵር ድረስ እስከ ከብ ቱም ሁሉ በኵር ድረስ የግብጽ አገር በኵር በኵሩ ሁሉ ይሞታል ። ምሳ፥ ፲፯ ፳፩፥ ማቴ፥ ፳፬ ፴፩ ። |
| ወይከውን ጽራኅ ዐቢይ በኵሉ ምድረ ግብጽ ዘከማሁ ኢኮነ ወኢይከውንኒ እንከ ዘከማሁ ። | ፮ | ከዚህ በፊት እንደዚህ ያለ ተደርጎ የማያውቅ እንግ ዲህም ወዲህ እንደዚህ ያለ የማይደረግ በግብጽ አገር ሁሉ ታላቅ ጩኸት ይሆናል ። ዘፀ፥ ፲፪ ፴ ። |
| ወለኵሉ ደቂቀ እስራኤል ከልብ ኢይልሕሶሙ በልሳኑ እምሰብእ እስከ እንስሳ ከመ ታእምር መጠነ ይሴብሕ እግዚአብሔር ማእከለ ግብጽ ወማእከለ እስራኤል ። | ፯ | እግዚአብሔር በግብጻውያንና በእስራኤል መከከል ተአምራት አድርጎ ምን ያኽል እንዲመሰገን ልታውቅ ከ ሰው ጀምሮ እስከ ከብቱ ድረስ የእስራኤልን ልጆች ሁሉ ግን ውሻ ስንኳ በምላሱ አይልሳቸውም ። ዘፀ፥ ፰ ፳፪ ። |
| ወይወርዱ እሉ ኵሎሙ ደቂቅ ኀቤየ ወይሰግዱ ሊተ ወይብሉኒ ፃእ አንተ ወሕዝብከ ይእዜ እምዛ ምድር ወእም ድኅረዝ አውፅእ ወወፅአ ሙሴ እምኀበ ፈርዖን በመዐት ። | ፰ | እነዚህ ልጆች ሁሉ ወደኔ መጥተው ለኔ ይሰግዳሉ፥ ሻሬ ከዚህች ምድር አንተና ወገኖችህ ውጣ ይሉኛል፥ ከዚያ በኋላ አወጣዋለሁ ሙሴም ከፈርዖን ዘንድ በቍጣ ወጣ ። ዘፀ፥ ፲፪ ፴፫፥ መሳ፥ ፬ ፲፥ ፰ ፭ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ኢይሰምዐክሙ ፈርዖን ከመ እብዝኅ ተአምርየ ወመድምምየ በምድረ ግብጽ ። | ፱ | እግዚአብሔርም ሙሴን በግብጽ አገር ላይ ፍጹም ተአ ምራቴን አብዝቼ አደርገው ዘንድ ፈርዖን አይሰማችሁም አለው ። ዘፀ፥ ፫ ፲፱፥ ፯ ፬ ። |
| ወሙሴ ወአሮን ገብሩ ኵሎ መድምመ በቅድመ ፈርዖን፥ ወአጽንዐ እግዚአብሔር ልበ ለፈርዖን ወአበየ ፈን ዎቶሙ ለደቂቀ እስራኤል እምድረ ግብጽ ። | ፲ | ሙሴንና አሮንም በፈርዖን ፊት ተአምራቱን ሁሉ አደረጉ፥ እግዚአብሔርም የፈርዖንን ልብ አጸናው፥ የእስ ራኤልን ልጆች ከግብጽ ምድር አሰናብቶ መስደዱን እምቢ አለ ። ዘፀ፥ ፲ ፳ ። |

ምዕራፍ ፲፪ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን በምድረ ግብጽ፥ ዝ ወርኅ ቀዳማየ አውራኅ ይኩንክሙ ወአቅ ድምዎ እምአውራኀ ዓመት ። | ፩ | እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን በግብጽ አገር እንዲህ አላቸው፥ ይህ ወር (ሚያዝያ) የወሮች መጀመሪያ ይሁና ችሁ፥ ከዓመትም ወሮች አስቀድሙት ። ዘፀ፥ ፲፫ ፬ ። |
| ወንግር ለኵሉ ማኅበረ ደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ በዐሡሩ ለዝ ወርኅ ይንሣእ ሎቱ ብእሲ ብእሲ በበ ቤቱ ወበበ ዘመዱ ወለለ ማኅደሩ በግዐ ። | ፪ | በዚህ ወር በአሥረኛው ቀን አንዱም አንዱም ሰው በየቤቱና በየዘመዱ በየአንድነቱም በጉን ይያዝ ብለህ ለእ ስራኤል ልጆች ጉባኤ ሁሉ ንገር አለው ። ዘፀ፥ ፳፪ ፩ ፱። |
| ወለእመ ውኁዳን እሙንቱ እለ ውስተ ቤት ወኢይ ፄድኡ አሐደ በግዐ ይንሣእ ምስሌሁ ካልአ ዘኀሩ በኍ ልቍ ዘነፍስ ለለ አሐዱ አሐዱ ዘየአክሎ ከመ ይፄድኡ በግዐ፥ ወበግዕ ፍጹም ተባዕት ዘዓመት ይኩንክሙ እም ራዕይ ትነሥኡ መሐስአ ። | ፫ | በቤት ውስጥ ያሉት ሰዎች አንሰው አንዱን በግ የማ ይጨርሱ ቢሆኑ አንዱን በግ ለመጨረስ የሚበቃውን ያኽ ል እንዲጨርስ አንዱንም አንዱን በሰው ቍጥር የጐረቤቱ ሌላውን ሰው ከርሱ ጋራ ሊበላ ጠርቶ ያምጣው፥ በጉም ዓመት የሆነው ጠቦት ይሁን ጠቦቱንም ከመንጋው ለይታ ችሁ ታመጣላችሁ ። ዘሌ፥ ፳፪ ፲፱፥ ሚል፥ ፩ ፰ ። |

፮ ወዕቀበ ይኩንክሙ እስከ ዓሥሩ ወረቡዑ ለዝ ወርኅ፤ ወይሕርድዎ ኵሉ ማኅበሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ፍና ሠርክ ።

፯ ወይንሥኡ እምደሙ ወይደዩ ውስተ ራግዛት ክልኤቱ ወውስተ መርፈቁ ለውእቱ ቤት ኀበ ይበልዕዎ ።

፰ ወይበልዑ ሥጋሁ በዛ ሌሊት ጥብሶ በእሳት ወናእተ ምስለ ሐምለ ብሒእ ትበልዑ ።

፱ ወኢትብልዑ እምኔሁ ጥሬየ ወኢብሱለ በማይ ዘእንበለ ጥብሶ በእሳት ርእሶ ምስለ እገሪሁ ትዌድእዎ ።

፲ ወኢታትርፉ እምኔሁ ለነግህ፡ ወዐፅሞ ኢትስብሩ እምኔሁ፤ ወእመበ ዘተርፈ እምኔሁ ለነግህ አውዕይዎ በእሳት ።

፲፩ ወከመዝ ብልዕዎ እንዘ ቅኑት ሐቌክሙ ወአሣእኒክሙ በእገሪክሙ ወቀስታማቲክሙ ውስተ እደዊክሙ ወትበልዕዎ እንዘ ትጔጕኡ እስመ ፋሲካሁ ለእግዚአብሔር ውእቱ ።

፲፪ ወእመጽእ ውስተ ምድረ ግብጽ በዛ ሌሊት፤ ወእቀትል ኵሎ በኵረ በምድረ ግብጽ እምሰብእ እስከ እንስሳ ወእገብር በቀለ እምኵሉ አማልክተ ግብጽ አነ እግዚአብሔር ።

፲፫ ወይከውን ዝ ደም ተአምረ ለክሙ ውስተ አብያት ኀበ ሀለውክሙ ህየ ወእሬእዮ ለውእቱ ደም ወእከድነክሙ ወኢይከውን ዲቤክሙ መቅሠፍት ዘቅጥቃጤ ሶበ አምጻእክዎ በምድረ ግብጽ ።

፲፬ ወትኩንክሙ ዛ ዕለት ተዝካረ ወትገብሩ በዓለ እግዚአብሔር ባቲ በመዋዕሊክሙ ሕገ ዘለዓለም በዓልክሙ ይእቲ ።

፲፭ ሰቡዐ ዕለተ ናእተ ትበልዑ ወእመ ቀዳሚት ዕለት ታማስኑ ብሑእ እምአብያቲክሙ ወኵሉ ዘበልዐ ብሑአ ለትሠሮ ነፍሱ እምእስራኤል እምዕለት ቀዳሚት እስከ ዕለት ሳብዕት ።

፲፮ ወዕለት ቀዳሚት ትሰመይ ቅድስት፤ ወዕለት ሳብዕት ትኩንክሙ ዕረፍተ፤ ወኵሎ ግብረ ማሕረስ ኢትግበሩ ባቲ ዘእንበለ ኵሉ ዘይትገበር ለነፍስ ባሕቲቱ ይትገበር ለክሙ ።

፲፯ ወዕቀብዋ ለዛቲ ትእዛዝ እስመ በዛቲ ዕለት አወፅእ ለኀይልክሙ እምድረ ግብጽ፤ ወትገብርዋ ለዛቲ ዕለት በዓለ ሕገ ዘለዓለም ።

፲፰ ወትቀድሙ ትእኀዙ እምዕለት ዐሡሩ ወረቡዑ ለዝ ወርኅ ዘትቀድሙ እምሠርኩ ትበልዑ ናእተ እስከ ዕሥራ ወአሚሩ ለዝ ወርኅ እስከ ሠርኩ ።

፲፱ ሰቡዐ ዕለተ ብሑእ ኢይትረከብ ውስተ አብያቲክሙ፤ ወኵሉ ዘበልዐ ብኍአ ለይሠሮ ውእቱ ብእሲ እማኅበረ እስራኤል እምግዩር እስከ ዘፍጥረቱ ውስተ ምድርክሙ ።

፳ ወኵሉ ብኍአ ኢትብልዑ በኵሉ ማኅደርክሙ ናእተ ብልዑ ።

ይኸውም በዚህ ወር እስከ አሥራ አራተኛው ቀን ድረስ የተጠበቀ ይሁናችሁ በጉንም የእስራኤል ልጆች ጉባኤ ሁሉ ሲመሽ ይረዱት ። ዘሌ፡ ፳፫ ፭፡ ዘኍ፡ ፱ ፫ ።

ከደሙም ወስደው በሁለቱ መቃኖች በጉን በሚበሉበትም ቤት መድረክ ይቅቡት ።

ሥጋውን በእሳት የተጠበሰ ጥብሱን ከእርሾ ጋራም ቂጣውን በዚያች ሌሊት ይብሉት ። ዘፀ፡ ፲፪ ፲፪ ፲፯ ።

ከዚያውም (ከበጉ ሥጋ) በእሳት የተጠበሰውን እንጂ ብርንዶውንና በውኃ የበሰለ ቅቅሉን (ዝግኑን) አትብሉ፤ ራሱንም ከእግሩ ጋራ ጨርሱት (ጋጡት)። ዘዳ፡ ፲፯ ፯ ።

ከሱም ለነገ ብላችሁ አታስቀሩ (አታሳድሩ) ከበጉም አጥንቱን አትስበሩ በልታችሁ ከሱ የተረፈ ቢኖርም በእሳት አቃጥሉት። ዘፀ፡ ፳፫ ፲፰፤ ዘኍ፡ ፯ ፲፱ ።

(ስትበሉትም) እንዲህ አድርጋችሁ እየቸኰላችሁ ወገባችሁን ታጥቃችሁ ጫማችሁን በእግራችሁ ተጫምታችሁ በእጃችሁም መንደርቆ (ጠርሙዝ በትር) ይዛችሁ ብሉት፤ የእግዚአብሔር ፋሲካ ነውና ። ዘዳ፡ ፲፮ ፩ ።

በዚህችም ሌሊት ወደ ግብጽ አገር እመጣለሁ፤ መጥቼም ከሰው ጀምሮ እስከ ከብት ድረስ በግብጽ አገር ያለውን በኵር በኵሩን ሁሉ እገድላለሁ፤ በግብጽ ጣኦታትም ሁሉ ላይ እኔ እግዚአብሔር በቀልን አደርጋለሁ ።

ይህም (የበጉ) ደም ባላችሁበት ቤት የደኅንነታችሁ ምልክት ይሆንላችኋል እኔም ያነን ደም አይቼ (ከጥፋት) እሠውራችኋለሁ፤ መቅሠፍቱንም በግብጽ አገር ባመጣሁት ጊዜ ጥፋት የታዘዘበት መቅሠፍት በናንተ አይደረግባችሁም ። ዘፀ፡ ፲፩ ፬-፯፤ ፱ ሳሙ፡ ፳፬ ፲፯ ።

ይህችም ቀን መታሰቢያ ትሁናችሁ፤ እናንተም ባለዘመናችሁ የእግዚአብሔርን በዓል አድርጉባት፤ ይህችውም የዘለዓለም ሕጉን የምትጠብቁባት በዓላችሁ ናት ።

ሰባት ቀን ቂጣውን ብሉ፤ በመጀመሪያይቱም ቀን ከቤቶቻችሁ መጻጻውን አጥፉ፤ ከመጀመሪያይቱም ቀን ጀምሮ እስከ ሰባተኛይቱ ቀን ድረስ መጻጻን የበላ ሰው ሰውነቱ ከእስራኤል ተለይታ ትጥፋ ። ዘፀ፡ ፲፫ ፯፡ ፳፰ ፲፱ ።

መጀመሪያይቱም ቀን የከበረች ትሁን፤ ሰባተኛይቱ ቀን ግን ዕረፍት ትሁንላችሁ፤ (ዕረፉባት) ለሥጋችሁ ከተሠራላችሁ ሥራ ብቻ በቀር አትረሱባት አትቆፍሩባት ። ዘሌዋ፡ ፳፫ ፯፡ ዘኍ፡ ፳፰ ፲፩ ።

በዚህች ቀን ሠራዊታችሁን ከግብጽ አገር አወጣዋለሁና ይህችን ትእዛዝ ጠብቋት፤ ይህችንም ቀን የዘለዓለም ሕጉ የሚጠበቅበትን በዓል አድርጓት ። ዘፀ፡ ፲ ፫ ።

በዚሁ ወር (ሚያዝያ) ከአሥራ አራተኛው ቀን ከሠርኩ ከማታው ጀምራችሁ እስከ ፳፩ኛው ቀን እስከ ሠርኩ ድረስ ቂጣውን ትበላላችሁ ።

ሰባቱን ቀን በቤቶቻችሁ መጻጻ አይገኝ (በሰባቱ ቀናት) መጻጻውን የበላ ሰው ሁሉ ከእስራኤል ማኅበር ከመጻተኛውም በአገራችሁ ከተወለደውም ሰው ሁሉ ተለይቶ (በዲንጋይ ተወግሮ በእሳት ተቃጥሎ) ይጥፋ (ይሙት)።

በየቤታችሁ ቂጣውን ብሉ እንጂ (የበከ) መጻጻውን አትብሉ ። ዘፀ፡ ፳፫ ፲፭፤ ዘኍ፡ ፱ ፲፫ ።

፲፱ ወጸውዖሙ ሙሴ ለኵሎሙ አእሩገ እስራኤል ወይቤሎሙ ሑሩ ንሥኡ ለክሙ በግዐ በበዘመድክሙ ወሕርዱ ለፋሲክ ።

ሙሴም የእስራኤል ሽማግሌዎችን ሁሉ ጠርቶ በየወገናችሁ ሂዱ ችሁ በጉን ይዛችሁ ለፋሲክ እረዱት ።

፳ ወንሥኡ አስረተ አዛብ ወጥምዕዎ እምዝኩ ደም ዘኀበ ንዋይ ወሚጥዎ ዲበ መርረቅ ወዲበ ክልኤሆሙ ራግዛት እምውእቱ ደም ወአንትሙሰ ኢትፃኡ እምውእቱ ቤት እስከ ይጸብሕ ።

አውቡን (ስሚዛ እንዶድ) በሐር ገመድ አሥራችሁ በዕቃው ካለው ደም ንከሩት ፤ በዕቃው ካለውም ደም ወስዳችሁ በሁለቱ መቃኖችና በመድረኩ ቀቡት (እርጩት) እናንተ ግን እስኪነጋ ድረስ ከዚያ (ካላችሁበት) ቤት አትውጡ ። ዘሌ ፲፬ ፮ ፤ ዕብ ፲፩ ፳፰ ።

፳፩ ወይመጽእ እግዚአብሔር ከመ ይቅትሎሙ ለግብጽ ፤ ወይሬእዮ ለውእቱ ደም ዲበ መርረቀ ወዲበ ክልኤሆሙ ራግዛት ወይትዐደዎ እግዚአብሔር ለይእቲ ኆኅት ፤ ወኢየኅድግ ለቀታሊ ይባእ ውስተ አብያቲክሙ ከመ ይቅትል ።

እግዚአብሔር ግብጻውያንን ሊገድላቸው ይመጣል ፤ (መጥቶም) በሁለቱ መቃኖችና በመድረኩ ላይ ያለውን ደም አይቶ ደጃፏቱን አልፎ ይሄዳል ፤ አጥፊውን (ቸነፈሩን) እናንተን ይገድል ዘንድ ወደ ቤታችሁ እንዲገባ አይተውም ። ዘፀ ፲፪ ፯ ።

፳፪ ወዕቀቡ ዘንተ ሕገ ይኩንክሙ ወለውሉድክሙ ዘለዓለም ።

ለናንተም ለልጆቻችሁም ለዘለዓለሙ ሥርዓት ይሆናችሁ ዘንድ ይህንን ሕግ ጠብቁ ። ሕዝ ፱ ፮ ።

፳፫ ወእመ በእክሙ ውስተ ምድር ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር ዘከመ ነበበ ዕቀብዋ ለዛቲ ሥርዐት ።

እግዚአብሔር ለናንተ (አወርሳችኋለሁ) ብሎ እንደ ተናገረ ወደሚያወርሳችሁ ምድር ብትገቡም ይህችን ሥርዓት ጠብቋት ። ዘፀ ፫ ፰ ፤ ፲፯ ።

፳፬ ወእመ ይቤሉክሙ ውሉድክሙ ምንትኑ ዛቲ ሥርዓት ትብልዎሙ መሥዋዕተ ፋሲካሁ ዝንቱ ለእግዚአብሔር ዘከደነ አብያቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል በምድረ ግብጽ አመ ቀተሎሙ ለግብጽ ወአድኀነ አብያቲነ ፤ ወደነነ ሕዝብ ወሰገዱ ።

ኋላ ልጆቻችሁ ይህች ሥርዓት ምንድር ናት ፤ ብለው ቢጠይቋችሁ ይህ ግብጻውያንን በጠፋ ጊዜ በግብጽ አገር የእስራኤልን ልጆች ቤት (ከጥፋት) የሠወረ ቤቶቻችንም (ወገኖቻችን) ያዳነ የእግዚአብሔር የፋሲካው መሥዋዕት ነው ትሉዋቸዋላችሁ ፤ ሕዝቡም ተጐንበሱ ሰገዱም ።

፳፭ ወሖሩ ወገብሩ ከማሁ ደቂቀ እስራኤል በከመ አዘዞሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ።

የእስራኤል ልጆች ሂደው እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዳዘዛቸው እንዲሁ አደረጉ ። ዘፀ ፲፪ ፳ ።

፳፮ ወሶበ ኮነ መንፈቀ ሌሊት ቀተለ እግዚአብሔር ኵሎ በኵረ በምድረ ግብጽ እምበኵረ ፈርዖን ዘይነብር ዲበ መንበረ መንግሥት እስከ በኵረ ፄዋዊት ቀዳሒት ወኵሎ በኵረ እንስሳ ።

መንፈቀ ሌሊትም በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር በግብጽ አገር በመንግሥት ዙፋን ከሚቀመጠው ከፈርዖን በኵር ጀምሮ በግዞት እስከሉቸው ውኃ ቀጅ በኵር ድረስ በኵሩን አጠፋ ፤ የከብቱንም በኵር ሁሉ አጠፋ ።

፳፯ ወተንሥአ ፈርዖን በሌሊት ወኵሉ ዐበይቱ ወኵሉ ግብጽ ።

ፈርዖን በሌሊት ተነሣ ፤ ሹማምንቱም ሁሉ ግብጻውያንም ሁሉ ተነሡ ።

፳፰ ወኮነ አውያት ዐቢይ በኵሉ ምድረ ግብጽ እስመ አልቦ ቤት ዘአልቦ ውስቴቱ ምውት ።

በግብጽ አገር ሁሉ ታላቅ ልቅሶ ሆነ ፤ የሞተ ሰው የሌለበት ቤት የለም ነበርና ። ዘፀ ፲፩ ፮።

፳፱ ወጸውዖሙ ፈርዖን ለሙሴ ወለአሮን በሌሊት ወይቤሎሙ ተንሥኡ ወፃኡ እምሕዝብየ አንትሙሂ ወደቂቀ እስራኤል ወሑሩ ወተፀመድዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ በከመ ትቤሉ ።

ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን በሌሊት አስጠርቶ እናንተም የእስራኤል ልጆች ተነሥታችሁ ከወገኖቼ ተለይታችሁ ሂዱ ፤ ለፈጣሪያችን እግዚአብሔር እናገለግለዋለን እንዳላችሁ ለፈጣሪያችሁ ለእግዚአብሔር አገልግሉት አላቸው ።

፴ ወአባግዒክሙሂ ወአልህምቲክሙሂ ንሥኡ ወሑሩ ወባርኩኒ ኪያየ ።

በጎቻችሁንና ላሞቻችሁንም ይዛችሁ ሂዱ ፤ እኔንም ባርኩኝ (መርቁኝ) አላቸው ። ዘፀ ፫ ፳፱ ፤ ፳፭ ፳፮ ።

፴፩ ወአጽሐብዎሙ ግብጽ ለሕዝበ እስራኤል ከመ ፍጡነ ያውፅእዎሙ እምድረ ግብጽ እስመ ይቤሉ ኵልነ ንመውት ።

ሁላችንም እንሞታለን ብለዋልና የግብጽ ሰዎች የእስራኤልን ልጆች ፈጥነው ያወጡዋቸው ዘንድ አስቸኰሉዋቸው (ውጡልን ውጡልን ብለው አጣደፉዋቸው) ።

፴፪ ወነሥኡ ሕዝብ ሐሪጾሙ ዘእንበለ ይትበኀእ ዕቍረ በአልባሲሆሙ ዲበ መትከፍቶሙ ።

ሕዝቡም ሳይቦካ ዱቄታቸውን በልብሳቸው ቋጥረው በትከሻቸው ተሸከሙ ። ዘፀ ፫ ፫ ።

፴፫ ወገብሩ ደቂቀ እስራኤል በከመ አዘዞሙ ሙሴ ወተወሐሱ እምግብጽ ንዋየ ብሩር ወወርቅ ወልብስ ።

የእስራኤል ልጆችም ሙሴ እንዳዘዛቸው አደረጉ ፤ ከግብጽ ሰዎች የብርን የወርቅን ዕቃ ልብስንም ተዋሱ ።

፴፬ ወወሀበሙ እግዚአብሔር ሞገሰ ለሕዝበ እስራኤል በቅድሜሆሙ ለግብጽ ወአውሐስዎሙ ወሐብለይዎሙ ለግብጽ ።

እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች በግብጻውያን ፊት በለሟልነትን ሰጣቸው ፤ (ግብጻውያን) አዋሱዋቸው (እስራኤልም) የግብጽን ሰዎች በዝብዘዋቸው ወጡ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወግዕዙ ደቂቀ እስራኤል እምራምሴ ውስተ ሰኩት ስሳ እልፍ አጋር እደው ዘእንበለ ዘምስለ ንዋይ ። | ፴፭ | የእስራኤልም ልጆች ከራምሴ ተነሥተው ወደ ሱኩት ተጓዙ ፤ እነዚህም ከጓዝ ጋር ካሉት በቀር ስሳ እልፍ (እጋር) እግረኞች ናቸው ። ዘኍ፡ ፴ ፫ ፤ ዘዳ፡ ፵፯ ፲፭ ። |
| ወዘተደመረ ዘዐርገ ምስሌሆሙ ብዙኅ ወአባግዕ ወእልሕምት ወእንስሳ ብዙኅ ጥቀ ። | ፴፮ | ከነሱም ጋር ተደባልቆ የወጣ ብዙ ነው ፤ በጎች ፤ ላሞችና ከብቱም እጅግ ብዙ ነበሩ ። |
| ወኀበዙ ሐሪጾሙ ዘአውፅኡ እምግብጽ ወገብርዎ ዳፍንተ ናእተ እስመ ዘእንበለ ያብኅኡ አውጽእዎሙ ግብጽ ወኢክህሉ ነቢረ ወኢገብሩ ሎሙ ስንቀ ለፍኖት ። | ፴፯ | ከግብጽም ያወጡት ዱቄታቸውን (ቂጣ እንጎቻ) ድፎ (እምበሻ ዳቦ) እያደረጉ ጋገሩት ፤ ዱቄቱን ሳያቦኩ (ሳይጋግሩ) ግብጻውያን አስወጥተዋቸዋልና ፤ (በግብጽም) መኖር አልቻሉምና (ከዚያም አስቀድሞ) ለጕዳና ስንቅን አላዘጋጁም ነበሩና ፣ ዘፀ፡ ፯ ፩፡ ፲፩ ፩ ። |
| ወኀድረቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ዘነበሩ ምድረ ግብጽ ወምድረ ከነአን እሙንቱሂ ወአበዊሆሙሂ አርባዕቱ ምእት ወሠላሳ ዓመት ። | ፴፰ | የእስራኤል ልጆች እነሱም አባቶቻቸውም በግብጽና በከነዓን የኖሩበት ዘመን አራት መቶ ሠላሳ ዓመት ነው ። |
| ወኮነ እምድኅረ አርባዕቱ ምእት ወሠላሳ ዓመት ወፅአ ኵሉ ኀይለ እግዚአብሔር እምድረ ግብጽ ሌሊተ ። | ፴፱ | ከአራት መቶ ሠላሳም ዓመት በኋላ እንዲህ ሆነ ፤ የእግዚአብሔር ሠራዊት ሁሉ ከግብጽ አገር በሌሊት ወጣ ። |
| እምቅድመ ዕቅበቱ ውእቱ ለእግዚአብሔር ከመ ያውጽኦሙ እምድረ ግብጽ ወኪያሃ ዛቲ ሌሊት ይእቲ እምቅድመ ዕቅበቱ ለእግዚአብሔር ለኵሉ ደቂቀ እስራኤል በበትውልዶሙ ። | ፵ | ይህችም ሌሊት ከግብጽ አገር ያወጣቸው ዘንድ ለእግዚአብሔር የተጠበቀች ናት ፡ ይህም መጠበቁ እስራኤል ሁሉ በየወገናቸው በንተው ይኖሩ ዘንድ ይህች የወጡባት ሌሊት እስከ ልጅ ልጆቻቸው ድረስ የተጠበቀች ናት ። |
| ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ዝ ውእቱ ሕጉ ለፋሲካ ኵሉ ዘእምባዕድ ዘመድ ኢይብላዕ እምኔሁ ። | ፵፩ | እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዲህ አላቸው ፤ የበዓለ ፋሲካው ሥርዓት ይህ ነው ፤ ከርሱም የሌላ ዘመድ ሁሉ (ከአሕዛብ የተወለደ) አይብላ ። |
| ወኵሉ ገብር ዘከነ ወዘበሤጥ ትገዝርዎ ወይእተ ጊዜ ይበልዕ እምኔሁ ። | ፵፪ | ውላጅና በወርቅ ተገዝቶ የመጣውንም ባርያ ትገዝሩት አላችሁ ያን ጊዜ ከርሱ ይበላል (ይብላል) ። ዘፍ፡ ፲፯ ፲፪ ። |
| ኀዳሪ ወገባኢ ኢይብላዕ እምኔሁ ። | ፵፫ | ሎሌና የዕለት ሞያተኛም (ሳይገዘር) ከርሱ አይብላ ። |
| ወበአሐዱ ቤት ይትበላዕ ወኢታውፅኡ አፍአ እምቤት እምውእቱ ሥጋ ወዐፅሞሂ ኢትስብሩ ። | ፵፬ | በአንድ ቤትም ይበላ ፡ ከዚያም የበግ ሥጋ ከቤት ወደ ውጭ አታውጡ ፤ አጥንቱንም አትስበሩ ። |
| ወኵሉ ማኅበረ እስራኤል ለይግበሮ ። | ፵፭ | ይህንንም የእስራኤል ጉባኤ ሁሉ ያድርገው ። |
| ወእመቦ ዘመጽአ ኀቤክሙ ግዩር ይግበር ፋሲካሁ ለእግዚአብሔር ትገዝር ኵሉ ተባዕቶ ፤ ወይእተ ጊዜ ይበውእ ይግበር ወይከውንክሙ ከመ ትውልደ ብሔር ወኵሉ ቈላፍ ኢይብላዕ እምኔሁ ። | ፵፮ | የእግዚአብሔር ፋሲካን ሊያደርግ ወደናንተ የመጣ መጻተኛ ቢኖር ወንዱ ወንዱን ሁሉ ግዘሩት ፡ ያን ጊዜ በዓሉን ሊያደርግ ይግባ ፡ በአገራችሁም እንደ ተወለደ ይሆናችኋል ያልተገዘረው ወሸላው ሁሉ ግን ከበጉ ሥጋ አይብላ ። ዘፀ፡ ፲፪ ፲፱ ፤ ዘኍ፡ ፱ ፲፪ ። |
| አሐደ ሕገ ይኩን ለትውልድክሙ ለሐቃል ወለግዩር ዘይመጽእ ኀቤክሙ ። | ፵፯ | በዓሉን ሊያደርግ ወደናንተ ለመጣ መጻተኛና (ለትውልዳችሁ) ለናንተ አንድ ሕግ ይሁን ። |
| ወገብሩ ከማሁ ደቂቀ እስራኤል በከመ አዘዞሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ። | ፵፰ | የእስራኤልም ልጆች እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዳዘዛቸው አደረጉ ። |
| ወኮነ በይእቲ ዕለት አውፅኦሙ እግዚአብሔር ለደቂቀ እስራኤል እምድረ ግብጽ ምስለ ኀይሎሙ ። | ፵፱ | በዚያም ቀን እንዲህ ሆነ ፤ እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ አገር ከሠራዊቶቻቸው ጋር አወጣቸው ። ዘፀ፡ ፲፪ ፵፩ ። |

ምዕራፍ ፲፫ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ቀድስ ሊተ ኵሎ በኵረ ቀዳሚ ውሉድ ፡ ኵሉ ዘይፈትሕ ማኅፀነ እምደቂቀ እስራኤል እምሰብእ እስከ እንስሳ ሊተ ውእቱ ። | ፩ | እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው ፡ ከእስራኤል ልጆች መጀመሪያ የተወለደውን ከሰው ጀምሮ እስከ ከብቱ ድረስ ለኔ ነውና በኵር በኵሩን ለይልኝ ። |
| ወይቤሎሙ ሙሴ ለሕዝብ ተዘከርዋ ለዛቲ ዕለት እንተ ባቲ ወፃእክሙ እምብሔረ ግብጽ እምቤተ ቅንየት እስመ በእድ ጽንዕት አውፅአክሙ እግዚአብሔር እምዝየ ወኢትብልዑ ብኁአ ። | ፪ | ሙሴም ሕዝቡን እግዚአብሔር በጽኑ ሥልጣኑ ከግብጽ አገር ከጽኑ አገዛዝ (ከባርነት ቤት) አውጥቷችኋልና ከግብጽ አገር የወጣችሁባት ይህችን ቀን አስቧት ፤ ስለ ዚህም መጻጻውን አትብሉ አላቸው ። ዘዳ፡ ፲፮ ፩ ። |

፫ እስመ በዛቲ ዕለት ትወጽኡ አንትሙ በወርኀ ሃሌ
ሉያ ኔሳን ።
፬ ወእመ ወሰደከሙ እግዚአብሔር ውስተ ምድረ ከና
ኔዎን ወኬጤዎን ወአሞሬዎን ወኤዌዎን ወኢያቡሴዎን
ወጌርጌሴዎን ወፌርዜዎን ዘመሐለ ከመ የሀበሙ ለአበዊ
ከሙ ምድረ እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ ተዘከርዋ
ለዛቲ ሥርዐት በዝ ወርኅ ።
፭ ሰዱሰ ዕለተ ትበልዑ ናእተ ወሳብዕት ዕለት በዓሉ ለእ
ግዚአብሔር እግዚእ ።
፮ ናእተ ትበልዑ ሰቡዐ ዕለተ ወኢያስተርኢ ብከሙ ብ
ኁእ ወኢየሀልዉ ብኁእት ውስተ ኵሉ አድባሪክሙ ።
፯ ወትዜንዎ ለወልድከ በይእቲ ዕለት ወትብሎ በእን
ተዝ ገብሮ እግዚአብሔር ሊተ አመ ወፃእኩ እምብሔረ
ግብጽ ።
፰ ከመ ይኩን ለከ ተአምረ ውስተ እዴከ ወተዝካረ ቅ
ድመ አዕይንቲከ ወከመ ይኩን ሕጉ ለእግዚአብሔር ውስ
ተ እዴከ ወውስተ አፉከ እስመ በእድ ጽንዕት አውፅአከ
እግዚአብሔር እምግብጽ ።
፱ ወዕቀብዎ ለዝንቱ ሕግ በበጊዜሁ እምዕለት ለዕለት ።
፲ ወሶበ ወሰደከ እግዚአብሔር ውስተ ምድረ ከናኔዎን
ዘመሐለ ለአበዊከ ወወሀበከሃ ፍልጥ ኵሉ ዘይፈትሕ ማኅ
ፀነ እመራዕይከ ወእምእንስሳከ ዘይትወለድ ተባዕተ ለእ
ግዚአብሔር ።
፲፩ ወለኵሉ ዘይፈትሕ ማኅፀነ አድግት ትዌልጦ በበግዕ
ወእመ ኢወለጥከሁ ትቤዝዎ ፡ ወለኵሉ በኵር ተባዕት
እምውሉድከ ትቤዝዎ ።
፲፪ ወእመ ተስእለከ ወልድከ እምድኅረዝ ወይቤለከ ምን
ትኑ ውእቱ ዝ፡ ትብሎ እስመ በእድ ጽንዕት አውፅአነ
እግዚአብሔር እምድረ ግብጽ እምቤተ ቅንየት ።
፲፫ ወከነ አመ አበየ ፈርዖን ፈንዎተነ ቀተለ እግዚአብ
ሔር ኵሎ በኵረ በምድረ ግብጽ እምበኵረ ሰብእ እስከ
እንስሳ ።
፲፬ ወበእንተዝ አነ እሠውዕ ለእግዚአብሔር ኵሎ ተባዕተ
ዘይፈትሕ ማኅፀነ ወኵሎ በኵረ ውሉድየ እቤዙ ።
፲፭ ወይኩን ተአምረ ውስተ እዴከ ወዘኢይሴስል እምቅ
ድመ አዕይንቲከ እስመ በእድ ጽንዕት አውፅአከ እግዚ
አብሔር ።
፲፮ ወሶበ ፈነዎሙ ፈርዖን ለሕዝብ ኢመርሖሙ እግዚአ
ብሔር ፍኖተ ፍልስጥኤም እስመ ቅርብት ይእቲ፣ እስመ
ይቤ እግዚአብሔር ዮጊ ይኔስሕ እምከመ ርእየ ቀትለ ወይ
ገብእ ውስተ ግብጽ ።
፲፯ ወአዖዶሙ እግዚአብሔር ለሕዝብ ላዕለ ፍኖተ ሐቅለ
ባሕረ ኤርትራ፣ ወበኃምስ ትውልድ ዐርጉ ደቂቀ እስራ
ኤል እምድረ ግብጽ ።
፲፰ ወነሥአ ሙሴ አዕፅምቲሁ ለዮሴፍ ምስሌሁ፣ እስመ
መሐላ አምሐሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ወይቤሎሙ አመ

የተድላ ደስታ ምስጋና በሚደረግበት በሚያዝያ ወር
በለች በዚህች ቀን ትወጣላችሁና ።
እግዚአብሔር ወተትና ማር የምታፈስውን ምድርን
ለአባቶቻችሁ ሊያወርሳቸው ወደ ማለበት ወደ ከናኔዎን
ወደ ኬጤዎንና ወደ አሞሬዎን ወደ ኤዌዎን ወደ ኢያ
ቡሴዎን ወደ ጌርጌሴዎን ወደ ፌርዜዎን አገር በወሰዳችሁ
ጊዜ ይህችን ሥርዓት አስቧት አላቸው ። ዘዳ፡ ፮ ፲ ።
በዚህ (በሚያዝያ ወር) ስድስት ቀን ቂጣ ትበላላችሁ
ሰባተኛይቱ ቀን ግን የእግዚአብሔር ጌታ በዓል ናት ።
ሰባት ቀን ቂጣ ብሉ፣ መጻጸም አይታይባችሁ፣ በተ
ራራዎቻችሁ ሁሉ መጻጸዎች አይኑሩ አላቸው።
በዚህም ቀን ከግብጽ አገር በወጣሁ ጊዜ፣ ጌታዬ
(ፈጣሪዬ) እግዚአብሔር ስለዚህ ይህን ሥርዓት አደረገልኝ
ብለህ ለልጅህ ትነግረዋለህ (ንገረው) ።
እግዚአብሔር ከግብጽ አውጥቶኻልና፣ የእግዚአብ
ሔር ሕግ ለእጅህ ምልክት ሊሆንህ በዓይኖችህም ፊት
መታሰቢያ ይሁንልህ፣ ለእጅህም እንደቀለበት በዓይኖች
ህም ፊት እንደመስተዋት ይሁንልህ ። ዘዳ፡ ፮ ፰ ።
ይህንንም ሕግ ከዛሬ ነገ እያላችሁ በየጊዜው ጠብቁት።
እግዚአብሔር ለአባቶችህ አወርሳችኋለሁ ብሎ ወደ
ማለበት ወደ ከናኔዎን ምድር በወሰደህ ጊዜ እሷንም በወ
ረሰህ ጊዜ ከመንጋህም ከከብትህም መጀመሪያ የተወለደ
ውን ወንዱ ወንዱን ሁሉ ለእግዚአብሔር ለይተህ ስጥ ።
ከአህያይቱም መጀመሪያ የተወለደውን በኵሩን በበግ
ለውጠው፣ በትለውጠውም አንገቱን ራስህ ዋጀው፣ ከል
ጆችህም መጀመሪያ የተወለደውን በኵሩን ተቤዠው፣
(ወርቁን ብሩን ሰጥተህ ልጅህን አስቀር) ። ዘፀ፡ ፴፬ ፳ ።
ከዚህ በኋላ ልጅህ (አባቴ) ይህ ምንድር ነው፡ ብሎ
በጠየቀህ ጊዜ እግዚአብሔር በጽኑ ሥልጣኑ ከግብጽ አገ
ር ከጽኑ አገዛዝ አውጥቶናልና ስለዚህ ነው ትለዋለህ ።
ፈርዖን (እኛን) ከግብጽ አገር አላሰናብትም ባለ ጊዜ
እግዚአብሔር ከሰው በኵር ጀምሮ እስከ ከብት በኵር ድረ
ስ ከግብጽ አገር ያለው በኵር በኵሩን ሁሉ ገድሏልና።
ስለዚህ እኔም በኵር ሆኖ የተወለደውን ሁሉ ለእግ
ዚአብሔር እሠዋለሁ፣ ከልጆቼም መጀመሪያ ሆኖ የተወ
ለደውን ሁሉ እበዥዋለሁ ትለዋለህ።
እግዚአብሔር በጽኑ ሥልጣኑ (ከግብጽ) አውጥቶኻ
ልና፣ ይህ የሠራልህ ሕግ ለጣትህ እንደቀለበት ለፊትህ
እንደ መስተዋት ይሁንልህ ። ዘፀ፡ ፲፫ ፱ ።
ፈርዖን እስራኤልን ከግብጽ አሰናብቶ በሰደዳቸው
ጊዜ እግዚአብሔር እስራኤል በልፉን ከየ ያዝናል፣ አዝ
ኖም ወደ ግብጽ አገር ይመለሳል ብሏልና፣ (ፍልስጥኤም)
የግብጽ አቅራቢያ ስለሆነች እግዚአብሔር ወደ ፍልስጥ
ኤም ጐዳና አልመራቸውም ። ዘፀ፡ ፲፬ ፲፭ ።
እግዚአብሔር ሕዝቡን በኤርትራ ባሕር ዳር ባለው
ጐዳና አዞራቸው፣ የእስራኤልም ልጆች ከግብጽ አገር
በአምስተኛው ትውልድ ወጡ ። ዘፀ፡ ፲፬ ፱ ።
ዮሴፍም እስራኤልን እግዚአብሔር (በረድኤት) መጐ
ብኘትን በጐበኛችሁ ጊዜ አፅንቴን ከናንተ ጋር ይዛችሁ

ሐውጾ ይሔውጸክሙ እግዚአብሔር ንሥኡ አዕፅምትየ
ወአውጽኡ ምስሌክሙ እምዝየ ።
፲፱ ወግዕዙ ደቂቀ እስራኤል እምሰኩት ወኀደሩ ውስተ
ኦቶም ዘመንገለ በድው ።
፳ ወእግዚአብሔር ይመርሖሙ መዓልተ በደመና ወሌ
ሊተ በብርሃነ እሳት ።
፳፩ ወኢሰሰለ ዐምደ ደመና መዓልተ ወኢዐምደ እሳት
ሌሊተ እምቅድመ ኵሉ ሕዝብ ።

## ምዕራፍ ፲፬ ።

፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ፡ በሎሙ ለደቂቀ እስ
ራኤል ይግብኡ ወይኅድሩ አንጻረ ኤጳውሎስ ማእከለ
መግደሎ ወማእከለ ባሕር መንገለ ብኤልሴፎን በቅድሜሁ
ይኅድሩ ኀበ ባሕር ።
፪ ወይብል ፈርዖን በእንተ ደቂቀ እስራኤል ሳኩዩ እሙ
ንቱ ውስተ ምድር ወአርከበቶሙ ሐቅል ።
፫ ወአነ አጸንዕ ልቦ ለፈርዖን ወይዴግኖሙ እምድኅሬ
ሆሙ ፡ ወእሴባሕ አነ በፈርዖን ወበኵሉ ሐራሁ ወየአምሩ
ኵሉ ግብጽ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ፡ ወገብሩ ከማሁ።
፬ ወዜነውዎ ለንጉሠ ግብጽ ከመ ነፍጸ ሕዝብ ፡ ወተ
መይጠ ልቡ ለፈርዖን ወዘሀበይቶሂ ኀበ ሕዝብ ወይቤሉ
ምንትኑ ዝ ዘገበርነ ዘፈነውናሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ከመ
ኢይትቀነዩ ለነ ።
፭ ወአንሥአ ፈርዖን ኵሉ ሠረገላቲሁ ወኵሉ ሕዝበ
አስተጋብአ ምስሌሁ ።
፮ ወነሥአ ስድስተ ምእተ ሠረገላተ ኅሩያነ ወኵሉ አፍ
ራሲሆሙ ለግብጽ ወሠለሰሙ ለኵሎሙ ።
፯ ወአጽንዐ እግዚአብሔር ልበ ለፈርዖን ንጉሠ ግብጽ
ወዴገነ ድኅሬሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ወደቂቀ እስራኤ
ልሰ ፡ የሐውሩ በእንድ ጽንዕት ወልዕልት ።
፰ ወዴገንዎሙ ግብጽ እምድኅሬሆሙ ወረከብዎሙ በኀበ
ተአየኑ መንገለ ባሕር ፡ ወኵሉ አፍራስ ወኵሉ ሠረገላ
ፈርዖን ወኵሉ ሐራሁ አንጻረ ኤጳውሎስ መንገለ ብኤል
ሴፎን ።
፱ ወነጸሩ ደቂቀ እስራኤል ወርእይዎሙ ይግዕዙ ግብጽ
እምድኅሬሆሙ ወፈርሁ ጥቀ ወአውየዉ ኀበ እግዚአብ
ሔር ።
፲ ወይቤልዎ ለሙሴ ዝክርነሂ ከመ ኢየሀሉ ውስተ ብ
ሔረ ግብጽ አውጻእከነ ከመ ትቅትለነ ውስተ በድው ።
፲፩ ወምንትኑ ዝ ዘገበርከ ላዕሌነ ዘአውፃእከነ እምብሔረ
ግብጽ ።
፲፪ አኮሁ ዝ ውእቱ ቃልነ ዘንቤለከ በብሔረ ግብጽ ኅድ
ገነ ንትቀነይ ለግብጽ እስመ ይኄይሰነ ተቀንዮ ለግብጽ
እመዊት በበድው ።

ውጡ ብሎ አምሎአቸው ነበርና ፡ ሙሴ የዮሴፍን አጥንት
ከሱ ጋር ይዞት ወጣ ። ዘፍ ፡ ፶ ፳፭ ፡ ኢያ ፡ ፳፬ ፴፪ ።
የእስራኤልም ልጆች ከሰኩት ተነሥተው በምድረ
በዳው አጠገብ ባለው በኦቶም ሠፍረው አደሩ ።
እግዚአብሔርም ቀን በዓምደ ደመና ሌሊት በዓምደ
እሳት ይመራቸው ነበር ። ዘኁ ፡ ፲፬ ፲፬ ፡ ፱ ፴፰ ።
ዓምደ ደመናው በቀን ፡ ዓምደ እሳቱም በሌሊት ከሕ
ዝቡ ሁሉ ፊት አልራቀም ነበር ። ዘፍ ፡ ፳ ፳፫ ።

## ምዕራፍ ፲፬ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው ፤ የእስራኤል ል
ጆች በፊታቸው ባለ በኤልሴፎን ባሕርና በመግደሎ መካ
ከል ባለው በኤጳውሎስ አንጻር ተመልሰው ያድሩ ዘንድ
ተመልሳችሁ በኤጳውሎስ አንጻር እደሩ በላቸው ።
ፈርዖንም ስለ እስራኤል ልጆች እንዲህ አለ ፤ እሊህ
(እስራኤል) በምድር (በግብጽ) ተቅበዘበዙ ፡ ምድረ በዳ
ውም ዘጋቸው ፡ (ጐዳናውን አያውቁትም) ።
እኔም የፈርዖንን ልብ አጸናለሁ ፡ እርሱም በኋላቸው
ተከትሎ (ይሄዳል) እኔም ፈርዖንንና ሠራዊቱን አጥፍቼ
እመሰገናለሁ ፡ ግብጻውያንም ሁሉ እኔ እግዚአብሔር እን
ደሆንኩ ያውቃሉ ፡ እነሱም እንዳላቸው አደረጉ ።
ለግብጽም ንጉሥ (ለፈርዖን) ሕዝቡ እንደኰበለለ ነገ
ሩት ፡ የፈርዖንና የሹማምንቱም ልብ እስራኤል እንከተ
ላቸው ወደማለት ተለወጠ ፡ እንዳይገዙልን የእስራኤልን
ልጆች አሰናብተን የሰደድናቸው ይህ ነገር ምንድር
ነው ፤ አሉ ። መዝ ፡ ፻፭ ፳፭ ።
ፈርዖንም ሠረገላዎቹን አስጫነ ፡ ወገኖቹንም ሁሉ
ከሱ ጋር ሰበሰበ ። ዘፀ ፡ ፲፭ ፱ ፡ ኢሳ ፡ ፴ ፳፩ ።
ስድስት መቶ የተመረጡ ሠረገላዎችንና የግብጽ ፈረ
ሶችን ሁሉ ይዞ ተነሣ ፡ ሁሉንም ከሦስት ከፈላቸው ።
እግዚአብሔርም የግብጽን የንጉሥ የፈርዖንን ልብ
(በክፋት) አጸና ፡ ተከትሎም የእስራኤልን ልጆች አሳ
ደደ ፡ የእስራኤል ልጆች ግን በጽኑ ሥልጣን ተጠብቀው
ይጓዙ ነበር ። ሮሜ ፱ ፲፯ ።
የግብጽም ሰዎች ተከትለዋቸው ሄዱ ፡ ፈረሶቹም የፈ
ርዖን ሠረገላም ሠራዊቱም ሁሉ ተሰብስበው ሂደው በብ
ኤልሴፎን አጠገብ ባለ በኤጳውሎስ አንጻር በባሕሩ ዳር
ሰፍረው አገኙዋቸው ። ዘፀ ፡ ፲፭ ፱ ።
የእስራኤልም ልጆች ግብጻውያን እነሱን ተከትለው
ሲጓዙ አይተው ፈጽመው ፈሩ ፡ ወደ እግዚአብሔርም
ጮኹ ፡ (ለመኑ) ። ኢያሱ ፳፬ ፯ ፡ ነህ ፡ ፱ ፱ ።
(እስራኤል) ሙሴን ስም አጠራራችን እንኳ በግብጽ
አገር እንዳይኖር (እንዳይጠራ) በምድረ በዳው ልታጠፋን
አወጣኸን አሉት ።
ከግብጽ አገር ያወጣኸን ይህ በኛ ላይ ያደረግኸው
ነገር ምንድር ነው ፤ ። መዝ ፡ ፻፯ ፯ ።
በምድረ በዳ ከመሞት ለግብጽ ሰዎች መገዛት ይሻለ
ናልና ለግብጽ ሰዎች እንገዛ ዘንድ ተወን ብለን በግብጽ
አገር ሳለን የነገርንህ ቃል ይህ አይደለምን ፤ አሉት ።

፲፫ ወይቤሎሙ ሙሴ ለሕዝብ ተአመኑ ወቊሙ ወትሬእዩ መድኃኒተ እንተ እምኀበ እግዚአብሔር ዘይገብር ለነ ዮም ፤ እስመ በከመ ትሬእይዎሙ ዮም ለግብጽ ዳግመ ኢትሬእይዎሙ እንከ ኍንዱየ ለዓለም ።

ሙሴም ሕዝቡን ግብጻውያንን ዛሬ እንደምታዩዋቸው እንግዲህ ዳግመኛ ለዘለዓለም አታዩዋቸውምና እግዚአብሔር ዛሬ የሚያደርግልንን ከእግዚአብሔር ዘንድ የምናገኛት ደኅንነታችንን ልታዩ እምናችሁ ቁሙ አላቸው ።

፲፬ ወእግዚአብሔር ይጸብእ ለክሙ ወአንትሙሰ አርምሙ ።

(ጠላታችሁን) የሚያጠፋላችሁ እግዚአብሔር ነው እናንተ ግን ዝም በሉ አላቸው ። ዘዳ፡ ፩ ፴ ፡ ፫ ፳፪ ።

፲፭ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ለምንት ትጸርሕ ኀቤየ በሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ይንድኡ እንስሳሆሙ ።

እግዚአብሔር ሙሴን ለምን ወደኔ ትጮኻለህ ፤ (አሁንም) የእስራኤልን ልጆች ከብቶቻቸውን እንዲነዱ ንገራቸው ፤ (ከብታችሁን ንዱ) በላቸው ። ኢያሱ ፲ ፲፬ ፤

፲፮ ወአንተሰ ንሣእ በትረከ ወስፋሕ እዴከ ዲበ ባሕር ወዝብጣ ፤ ወይባኡ ደቂቀ እስራኤል ውስተ ማእከለ ባሕር በየብስ ።

አንተ ግን በትርህን አንሣ ፤ እጅህንም በባሕር ላይ ዘርግተህ ባሕሩቱን ምታት ፤ የእስራኤልም ልጆች (ባሕሩ ተከፍሎላቸው) የብስ ወደ ሆነው ባሕር ይግቡ ።

፲፯ ወናሁ አነ አጸንዕ ልበ ለፈርዖን ወለኵሉ ግብጽ ወይበውኡ ድኅሬሆሙ ፤ ወእሴባሕ አነ በፈርዖን ወበኵሉ ሐራሁ ፤ ወበሠረገላቲሁ ወበኵሉ አፍራሲሁ ።

እነሆ እኔ የፈርዖንንና የግብጻውያንን ልብ አጸናለሁ ፤ ተከትለዋችሁ ወደ ባሕሩ ይገባሉ ፤ እኔም ፈርዖንን ሠራዊቱንም ሁሉ ሠረገላዎቹንና ፈረሶቹን ሁሉ አስጥሜ አመሰግናለሁ ። ዘፀ፡ ፲፬ ፬ - ፰ ።

፲፰ ወያእምሩ ኵሉ ግብጽ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አመ ተሰባሕኩ በፈርዖን ወበሠረገላቲሁ ወበኵሉ አፍራሲሁ ።

የግብጽ ሰዎችም ሁሉ ፈረሶቹን ሠራዊቱንና ሠረገሎቹን ሁሉ አጥፍቼ በተመሰገንሁ ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ያን ጊዜ ያውቃሉ ። ዘፀ፡ ፲፬ ፰ ።

፲፱ ወሰሰለ መልአከ እግዚአብሔር ዘየሐውር ቅድመ ትእይንቶሙ፣ለደቂቀ እስራኤል ወቆመ እምድኅሬሆሙ ወሰሰለ ዐምደ ደመናሂ እምቅድሜሆሙ ወቆመ እምድኅሬሆሙ ።

በእስራኤል ልጆች ሠራዊት ፊት ፊት ይሄድ የነበረው የእግዚአብሔር መልአክም (ቅዱስ ሚካኤል) ተመልሶ በስተኋላቸው ቆመ ፤ ፊት ፊት ይመራቸው የነበረ ዓምደ ደመናም ተመልሶ በስተኋላቸው ተጋረደ ።

፳ ወቦአ ማእከለ ትእይንቶሙ ለግብጽ ወማእከለ ትእይንቶሙ ለእስራኤል ወኮነ ቆብር ወጽልመት ወኢተደመሩ በበይናቲሆሙ ኵላ ይእተ ሌሊተ ።

(ደመናው) በእስራኤል ሰፈርና በግብጻውያን ሰፈር መከከል ገብቶ ተጋረደ ፤ ጭጋግና ጨለማም ሆነ ፡ በዚያች ሌሊት (ስንኳን ሲላው) እርስ በርሳቸው እንኳ (እስራኤልና እስራኤል) አልተገናኙም ። ዘኍ፡ ፳ ፲፮ ፤ ሚል ፡ ፫ ፩ ።

፳፩ ወሰፍሐ ሙሴ እዴሁ ዲበ ባሕር ወአምጽአ እግዚአብሔር ላዕለ ባሕር ነፋሰ አዜብ ጽኑዐ ኵላ ሌሊተ ወገብሮ ለባሕር የብሰ ወሠጠጦ ለማይ ።

ሙሴም እጁን ዘርግቶ ባሕሩን መታው ፤ እግዚአብሔርም በዚያች ሌሊት ጽኑ (ብርቱ) የአዜብን ነፋስ ወደ ባሕሩ አምጥቶ ባሕሩን የብስ አደረገው ውኃውንም ከፈለው ። ዘፀ፡ ፲፬ ፳፯ ፤ መዝ፡ ፸፬ ፲፫ ፤ ፻፯ ፱ ።

፳፪ ወቦኡ ደቂቀ እስራኤል ማእከለ ባሕር ላዕለ የብስ ፤ ወማይሰ ኮነ አረፍተ በየማኖሙ ወአረፍተ በፀጋሞሙ ።

የእስራኤልም ልጆች በየብስ ወደ ባሕር ማኽል ገቡ ፤ ውኃውም በቀኛቸውና በግራቸው እንደ ግድግዳ ሆናቸው ። ዘፀ፡ ፲፭ ፲፱ ፤ መዝ፡ ፸፯ ፯ ።

፳፫ ወዴገንዎሙ ግብጽ ወቦኡ ድኅሬሆሙ ወኵሉ አፍራሰ ፈርዖን ወሠረገላቲሁ ወኵሉ ወመስተጽዕናን በእማእከለ ባሕር ።

የግብጽም ሰዎች በኋላቸው ተከትለዋቸው (ወደ ባሕሩ) ገቡ ፡ የፈርዖን ፈረሶቹ ሠረገሎቹም ፈረሰኞቹም ሁሉ ወደ ባሕሩ ማኽል ገቡ ። ዘፀ፡ ፲፭ ፲፱ ፤ ፩ ቆሮ፡ ፲፩ ፳፬ ።

፳፬ ወሰበ ኮነ ዕቅበተ ሌሊት እንተ አፈ ጽባሕ ነጸረ እግዚአብሔር ውስተ ትእይንቶሙ ለግብጽ በዓምደ እሳት ወደመና ወአዘዘ ላዕለ ትእይንተ ግብጽ ።

ንጋት የተከተለው ሦስተኛው ሰዓት በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር በዓምደ እሳትና በዓምደ ደመና ሁኖ የግብጽን ሠራዊት ተመለከተ ፤ በግብጻውያንም ከተማ ላይ መዓትን አዘዘ ። መሳ፡ ፯ ፲፱ ፤ ፩ ሳሙ፡ ፲፩ ፲፩ ።

፳፭ ወአሰረ መአስርተ ሠረገላቲሆሙ ወወሰዶሙ በሥቃይ ወይቤሉ ግብጽ ንንፍጽ እምገጸሙ ለእስራኤል እስመ እግዚአብሔር ይፀብእ ሎሙ ።

የሠረገሎቹንም መንኰራኵር አስተሳስሮ በነፋሱ እያዳፋ ወሰዳቸው ግብጻውያንም እግዚአብሔር ይዋጋላቸዋልና ከእስራኤል ፊት እንሽሽ አሉ ። ዘፀ፡ ፲፬ ፲፭ ፲፯።

፳፮ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ስፋሕ እዴከ ዲበ ባሕር ወይትጋባእ ማይ ዲበ ግብጽ ወዲበ ሠረገላቲሆሙ ወመስተጽዕናኒሆሙ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው ፤ እጅህን በባሕር ላይ ዘርጋ ፤ ውኃውም በግብጻውያን በሠረገላዎቻቸውና በፈረሰኞቻቸው ላይ ይመለስባቸው ።

፳፯ ወሰፍሐ ሙሴ እዴሁ ዲበ ባሕር ወከደኖሙ ባሕር በጊዜሁ ወበገቶሙ እምድኅር ፤ ወጎየ ግብጽ ውስተ ባሕር

ሙሴም እጁን በባሕሩ ላይ ዘረጋ ፤ ባሕሩም ያን ጊዜ ተመለሰ (ደፈናቸው) ከወደኋላም ከበባቸው ፤ ግብጻው

ወወገሮሙ እግዚአብሔር ለግብጽ ማእከለ ባሕር።

፳፰ ወተመይጠ ባሕር ወተሰጥሙ ምስለ ሠረገላቲሆሙ ወመስተጽዕናኒሆሙ ወኵሉ ኀይሉ ለፈርዖን በከመ መጽኡ ውስተ ባሕር፣ ወኢተርፈ እምኔሆሙ እስከ አሐዱ። ወኢአሐዱ እምኔሆሙ ።

፳፱ ወደቂቀ እስራኤልሰ ሖሩ ውስተ ይብስት ባሕር፣ ወባሕርኒ፣ አረፍተ ከናሙ እምይምን ወእምጽግም ።

፴ ወአድኀኖሙ እግዚአብሔር ለእስራኤል በይእቲ ዕለት እምእዴሆሙ ለግብጽ፡ ወርእዩ እስራኤል ከመ ሞቱ ግብጽ በውስተ ድንጋጉ ለባሕር ፡ ወእደ ዐቢየ ዘገብረ እግዚአብሔር በግብጽ፡ ወፈርሁ ሕዝብ ።

፴፩ ወአምኑ በእግዚአብሔር ወሙሴሃኒ ላእኮ አዕበዩ ።

## ምዕራፍ ፲፭ ።

፩ ወባረኩ ዘ ቡራኬ ሙሴ ወደቂቀ እስራኤል ለእግዚአብሔር በፍትሐተ ቃል እንዘ ይብሉ ንባርክ ለእግዚአብሔር እስመ ክቡር ውእቱ ወሎቱ ይደሉ ስብሐ፣ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ ፈረሰ ወዘይጼዕኖ ወረወ ውስተ ባሕር ።

፪ ረዳኤ ወመሠውረ ኮነኒ ለአድኅኖትየ፣ ውእቱ አምላኪየ እሴብሖ፣ አምላከ አቡየ ወእሌዕሎ ።

፫ እግዚአብሔር ይቀጠቅጥ ፀብአ ፡ ወእግዚአብሔር ስሙ ።

፬ ሠረገላቲሁ ለፈርዖን ወሠራዊቶ ወረወ ውስተ ባሕር፣ ኀሩያነ ወመስተጽዕናነ በመሥልስት፣ ወተሰጥሙ ውስተ ባሕረ ኤርትራ ።

፭ ወደፈኖሙ ማዕበል ወተሰጥሙ ውስተ ቀላይ ከመ እብን ።

፮ የማንከ እግዚእ ተሰብሐ በኀይል፡ የማነ እዴከ እግዚእ ሠረቶሙ ለፀር ።

፯ ወበብዝኀ ስብሐቲከ ቀጥቀጥኮሙ ለጸላእትከ፣ ፈነውከ መዐተከ ወበልዖሙ ከመ ብርዕ ።

፰ ወበመንፈሰ መዐትከ ቆመ ማይ ወጠግአ ከመ አረፍት ማይ፣ ወረግአ ማዕበል በማእከለ ባሕር ።

፱ ወይቤ ጸላኢ ዴገንየ እእኅዞሙ እትከፈል ምህርካ ወአጸግብ ለነፍስየ፣ እቀትል በመጥባሕትየ ወእኴንን በእዴየ ።

፲ ፈነውከ መንፈሰከ ወደፈኖሙ ባሕር፣ ወተሰጥሙ ከመ ዐረር ውስተ ማይ ብዙኅ ።

፲፩ መኑ ይመስለከ እምነ አማልክት እግዚእ፣ ወመኑ ከማ

ያንም ተመልሰው ወደ ባሕሩ ማኸል ገቡ፣ እግዚአብሔርም በባሕሩ መካከል ጣላቸው (አሰጠማቸው)።

ባሕሩም ተመልሶ እንደቀድሞው ሆነ፣ የግብጽም ሰዎች ከሠረገላዎቻቸውና ከአርበኞቻቸው ጋር የፈርዖንም ሠራዊት ሁሉ ወደ ባሕሩ እንደ መጡ ሰጠሙ፣ (እስራኤልን ተከትለው) ከመጡት ሁሉ ከነርሱ አንድ ስንኳ የቀረ የለም ። ዕንባ፣ ፫ ፰ ፲፫፣ መዝ፣ ፻፮ ፲፩ ።

የእስራኤል ልጆች ግን ባሕሩ በግራ በቀኝ እንደ ግድግዳ ሆኖላቸው በደረቀው ባሕር ሄዱ ። ዘፀ፣ ፲፬ ፳፪ ።

እግዚአብሔር በዚያች ቀን እስራኤልን ከግብጻውያን እጅ አዳናቸው፣ እስራኤልም ግብጻውያን እንደ ሞቱ በባሕር ዳር ሁነው ተመለከቱ፣ ሕዝቡም በግብጻውያን ላይ ያደረገባቸው ታላቋን እጅግ (ተአምራቱን) አይተው ፈሩ።

በእግዚአብሔርም አመኑ፣ አገልጋዩ ሙሴንም አከበሩ።

## ምዕራፍ ፲፭ ።

ያን ጊዜም ሙሴና የእስራኤል ልጆች እንደበታቸው ተፈቶላቸው ለእግዚአብሔር ይህን ምስጋና አቀረቡ፣ እሱ ክቡር ምስጉን ነውና ለርሱም ምስጋና ይገባልና እግዚአብሔርን እናመስግነው እያሉ፣ ፈረሱንና በፈረሱ ላይ የተቀመጠውን አርበኛ (በኤርትራ) ባሕር አስጥሟልና የተመሰገነ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን ። ዘፀ፣ ፲፬ ፳፩ ።

እኔንም ለማዳን ረዳት (ከመከራው) ሠዋሪም ሆነኝ፣ እሱ ፈጣሪዬ ነው አመሰግነዋለሁ፣ የአባቴም ፈጣሪ ነው፣ አከብረዋለሁ (አገናዋለሁ)። መዝ፣ ፶፱ ፲፯፣ ፲፰ ፪ ።

እግዚአብሔር ጠላትን ያጠፋል፡ ስሙም እግዚአብሔር ነው ። መዝ፣ ፳፱ ፰፡ ራእ፣ ፲፱ ፲፫ ።

የፈርዖንን ሠረገሎቹንና ሠራዊቱን በባሕር ጣለ (አሰጠመ) በሦስት ወገን የተመረጡ እነዚህ በኤርትራ ባሕር ሰጠሙ ። ዘፀ፣ ፲፬ ፳፰፣ ፲፱ ፯ ።

ማዕበሉም ደፈናቸው እንደ ደንጊያ ወደ ጥልቅ ባሕር ሰጠሙ ። ነህ፣ ፱ ፲፩ ።

አቤቱ ቀኝህ (ሥልጣንህ) በደረገው ኃይል ተመሰገነ፣ አቤቱ የሥልጣንህም ኃይል ጠላቶችን አጠፋቻቸው ።

አቤቱ በተአምራትህ ብዛት ጠላቶችህን አጠፋኻቸው ቁጣህንም ሰደድክ እንደ ቋያም በላቸው (አጠፋቸው)።

ቁጣህን በምትፈጽምበት (ረቂቅ ሥልጣንህ) ውኃው ተከፍሎ ጸና፣ ውኃውም ግራና ቀኝ እንደ ግድግዳ ጸና፣ ሞገዱም በባሕሩ መከከል ረጋ ። መዝ፣ ፸፰ ፲፫ ።

ጠላትም አሳድጄ እይዛቸዋለሁ፣ ምርኮንም እከፈላለሁ ልቡናዬንም ደስ አሰኛታለሁ፣ በሾቶሌም አገድላለሁ፣ በሥልጣኔም እገዛለሁ ብሎ ነበር ። ዘፀ፣ ፲፬ ፱ ።

ነፋስህን አነፈስክ፣ ረቂቅ ሥልጣንህን ሰደድህ ባሕሩም ቀበራቸው ደፈናቸው ርሳስ በጥልቅ ውኃ ውስጥ እንዲሰጥም እንደዚያ ሰጠሙ ። ዘፀ፣ ፲፭ ፭ ።

አቤቱ በስም አማልክት ተብለው ከሚጠሩ የሚመስ

ከ ስቡሕ በውስተ ቅዱሳን፡ መንክር ስብሐቲከ ዘትገብር መድምመ።

፲፪ ሰፋሕከ የማነከ ወውኅጠቶሙ ምድር።
፲፫ ወመራሕኮሙ ለሕዝብከ እለ ቤዘውከ፡ ወአስተፍሥሕከ በኀይልከ ተረፈ መቅደስከ።

፲፬ ሰምዑ አሕዛብ ወተምዑ ወአኀዞሙ ማሕምም ለእለ ይነብሩ ፍልስጥኤም።
፲፭ ወውእተ አሚረ መምዑ መሳፍንተ ኤዶም፡ ወአኀዞሙ ረዓድ ለመላእክተ ሞአብ ወተመሥዉ ኵሎሙ እለ ይነብሩ ከነዓን።
፲፮ ወአኀዞሙ ፍርሀት ወረዓድ፡ ኀይለ መዝራዕትከ ጸንዐ እምኰኵሕ፡ እስከ የኀልፉ ሕዝብከ ዝንቱ ዘቤዘውከ።

፲፯ ወሰድኮሙ ወተከልኮሙ ውስተ ደብረ መቅደስከ ውስተ ድልው ማኅደርከ እግዚኦ ዘገበርከ፡ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘአስተዳለዋ እደዊከ።

፲፰ ይነግሥ እግዚአብሔር ለዓለመ ዓለም ወዓዲ።

፲፱ እስመ ቦአ ወረገላቲሁ ለፈርዖን ምስለ አፍራሲሁ ወመስተፅዕናን ውስተ ባሕር ወአስተጋብአ እግዚአብሔር ላዕሌሆሙ ማየ ባሕር፡ ወደቂቀ እስራኤልሰ ኀለፉ እንተ የብስ ማእከለ ባሕር፡ ማይሰ ሎሙ አረፍተ በይምን፡ ወአረፍት በጽግም።
፳ ወነሥአት ማርያም ነቢዪት እኅቱ ለአሮን ከበሮ በእዴሃ ወወፅአ ኵሎን አንስት ድኅሬሃ በከበሮ ወበቡራኬ።

፳፩ ወቀደመት ማርያም ወትቤ ንበርከ ለእግዚአብሔር ይትኄከር ውእቱ ይትነከር፡ ፈረሰ ወዘይጼዐን ላዕሌሁ ወረወ ውስተ ባሕር።
፳፪ ወአውፅኦሙ ሙሴ ለውሉደ እስራኤል እምባሕር ዕሙቅ፡ ወወሰዶሙ ውስተ ገዳመ ዘሡር ወግዕዙ ሠሉሰ ዕለተ ወኢረከቡ ማየ ከመ ይስተዩ።

፳፫ ወበጽሑ ሰትየ ማይ እመራ እስመ መሪር ማዩ፡ ወበእንተዝ ተሰምየ ውእቱ ፍና መሪር።

፳፬ ወአንጐርጐሩ ሕዝብ ላዕለ ሙሴ ወይቤሉ ምንተ ንሰቲ።

፳፭ ወአውየወ ሙሴ ኀበ ፈጣሪ፡ ወአርአዮ ዕፀ ወወደዮ ውስተ ማይ ወጥዕመ ማዩ፡ ወበህየ አርአዮ ጽድቀ ወፍትሐ ወአመከሮ።

፳፮ ወይቤ ለእመ ትሰምዕ ወታጸምእ ቃለ እግዚአብሔር ፈጣሪከ ወጽድቀ ትገብር በቅድሜሁ ወታጸምዕ ትእዛዛቲሁ ዘአዘዘከ ኵሉ ደዌ ዘአምጻእኩ ላዕለ ግብጽ ኢይፈኑ ላዕሌከ፡ እነ እግዚአብሔር ፈዋሲከ (መሀኪከ)።

ልህ ማን ነው፤ በነቢያት በካህናት ሸንጎም እንዳንተ የተመሰገነ ማን ነው፤ ድንቅ ተአምራትን የምታደርግ አንተ ጌትነትህ ድንቅ ነው። ፪ ሳሙ፡ ፯ ፳፪፡ ፩ ነገ፡ ፰ ፳፫።

ቀኝህን ዘረጋህ ምድርም ዋጠቻቸው።

(በቸርነትህ) የተቤዠኻቸው ወገኖችህን (ወደ ከነዓን) መራኻቸው፤ የመቅደስህ ትራፊ የሚሆኑ (ማለት የአብርሃም ልጆች እስራኤልን) በተአምራትህ ደስ አሰኘህ።

አሕዛብ ይህን ሰምተው ተበሳጩ በፍልስጥኤም የሚኖሩትን ሰዎች ምጥ (መከራ) ያዛቸው።

ያን ጊዜም የኤዶምያስ መሳፍንት ተሸበሩ፤ የሞዓብንም አለቆች ረዓድ (እንቅጥቅጥ) ያዛቸው በከነዓን የሚኖሩትም ሁሉ (እንደ ሰም) ቀለጡ። ዘኁ፡ ፴፪ ፲፭።

ፍርሃት ረዓድም ያዛቸው አቤቱ የተቤዠኻቸው ወገኖችህ (እስራኤል) አልፈው እስኪሄዱ ድረስ የሥልጣንህ ኃይል ከዲንጋይ ይልቅ ጸና። ዘዳ፡ ፪ ፳፭፡ ኢያሱ ፪ ፱።

ከዚያም ወስደህ በመቅደስህ ተራራ ተከልኻቸው (አጽንተህ አኖርኻቸው) አቤቱ በዘጋጀኸው ማደሪያህም አኖርኻቸው፤ ንጹሕ ክቡር እግዚአብሔር፤ ይህችም እጆችህ (ሥልጣኖችህ) ያዘጋጁዋት ናት። መዝ፡ ፵፬ ፪፡ ፸፰ ፶፬።

እግዚአብሔር ለዘለዓለም እስከ ፍጻሜ ንግሥ ይኖራል፤ (ወዓዲ) እንግዲህም ወድያ ነግሦ ይኖራል።

የፈርዖን ሠረገሎች ከፈረሰኞቹ ጋር በፈረስ በሠረገላም ላይ የተቀመጡ ሁሉ ወደ ባሕር ሰጥመዋልና፤ እግዚአብሔርም የባሕሩን ውኃ መለሰባቸው፤ የእስራኤል ልጆች ግን በባሕር መካከል በየብስ አልፈው ሄዱ፤ ውኃውም በቀኝ በግራ እንደ ግድግዳ ተከፍሎ ጸናላቸው።

የአሮን እኅት ነቢይቱ ማርያም ከበሮውን በእጅዋ ያዘች ሴቶቹም ሁሉ በከበሮና በምስጋና (ዘፈን) እሷን ተከትለው ወጡ። መሳ፡ ፬ ፬፡ ፩ ሳሙ፡ ፲፰ ፯።

ማርያም አስቀድማ እግዚአብሔርን እናመስግነው አለች፤ ፈረሱንና በፈረሱ ላይ የተቀመጠውን በባሕር ውስጥ አስጥሟልና እሱ ይደነቃል፤ (እሱ ይደነቅ ይደነቅ) አለች።

ሙሴም የእስራኤልን ልጆች ከጥልቅ ባሕር አውጥቶ በሱር አጠገብ ወዳለው ምድረ በዳ ወሰዳቸው፤ በምድረ በዳም ሦስት ቀን ተጓዙ፤ ሊጠጡም (የሚጠጡት) ውኃ አላገኙም። ዘፍ፡ ፲፯ ፯፡ ፳፭ ፲፰፡ ፩ ሳሙ፡ ፲፭ ፯።

ውኃው መራራ (ጕምራራ) ነውና ከመምረሩ (ከመጐምረሩ) የተነሣ ውኃን መጠጣት ተሳናቸው፤ ስለዚህም ነገር ያ በታ መራራ ጕዳና ተባለ። ሩት ፩፡ ፳።

ሕዝቡም ምን እንጠጣለን ብለው በሙሴ ላይ አንጐራጐሩ። ዘፀ፡ ፲፯ ፪።

ሙሴም ወደ ፈጣሪ ጮኸ (ለመነ) እግዚአብሔርም (ዘጲ. የሚባል) ዕንጨትን አሳየው፤ በውኃውም ላይ ጣለው፤ ውኃውም ጣፈጠ፤ በዚያም እውነትን ፍትሕን ገለጠለት ፈተነውም። ዘዐ፡ ፲፬ ፲፡ ፲፯ ፬፡ ፪ ነገ፡ ፪ ፳፩።

የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል አድምጠህ ብትሰማ በፊቱም በጎ ሥራ ብትሠራ፤ ያዘዘህንም ትእዛዝ ብታደምጥ በግብጽ ላይ ያመጣሁትን መከራ ሁሉ በንተ ላይ አላመጣብህም፤ እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝና፤ አለ።

፴፮ ወበጽሑ ኀበ ኤሉም ወሀለዉ ሀየ ዐሠርቱ ወክልኤቱ አንቅዕተ ማያት ወሰብዓ ጸበርተ ተመርት ጥቃ ማያት ብቅለቶን፣ ወተዐየኑ ህየ በኀበ ማይ ።

(እስራኤልም) ኤሉም ከምትባል አገር ደረሱ፣ በዚያም በታ አሥራ ሁለት ምንጮችና አበቃቀላቸው በውኃ ዳር የሚሆን ሰባ ዘንባባዎች አሉበት፣ በውኃውም አጠገብ ሰፈሩ ። ዘኍ፡ ፴፫ ፱ ።

ምዕራፍ ፲፮ ።

ምዕራፍ ፲፮ ።

፩ ወግዕዙ እምኤሉም ወበጽሑ ውስተ ገዳም ዘሲን ወውእቱ ማእከለ ኤሉም ወሲና አመ ዐሡሩ ወኀሙሱ ለካልእ ወርኅ እምዘወፅኡ እምድረ ግብጽ ።

ከኤሉምም ተጕዘው ሄደው በሲን አጠገብ ወዳለው ምድረ በዳ ደረሱ፣ እሱም በሲናና በኤሉም መካከል ነው። ይኸውም ከግብጽ አገር ከወጡ በኋላ በሁለተኛው ወር (በግንቦት) በሥራ አምስተኛው ቀን ነው ። ዘኍ፡ ፴፫ ፲፩።

፪ ወአንጐርጐሩ ኵሉ ውሉደ እስራኤል በላዕለ ሙሴ ወአሮን ።

የእስራኤልም ልጆች ሁሉ በሙሴና በአሮን ላይ አን ጐራጐሩ ። ዘፀ፡ ፲፭ ፳፬፡ ፩ ቆሮ፡ ፲ ፲ ።

፫ ወይቤልዎሙ እምኀየሰነ ሰበ ሞትነ በመቅሠፍተ እግዚአብሔር በምድረ ግብጽ አመ ንነብር ጥቃ ጽሕርት ዘሥጋ ወንበልዕ ሥጋ ወኅብስተ እስከ ንጸግብ፣ እምጻእክነ አንተ ውስተ ዝ ገዳም ከመ ትቅትለነ ለኵልነ በኀበ ተጋባእነ ።

አንተ በተሰበሰብንበት በታ ሁላችንን ልታጠፋን ወደ ዚህ ወደ ምድረ በዳ አመጣኸን፣ እኛ ግን እስክንጠግብ ድረስ ዳቦውን ሥጋውን በምንበላበት ሥጋው በሚቀቀል በት በድስቱም አጠገብ በምንቀመጥበት ጊዜ በግብጽ አገ ር ሳለን እግዚአብሔር በመጣው መቅሠፍት በሞትን በተ ሻለን ነበር፣ አሉዋቸው ። ዘኍ፡ ፲፩ ፬ ።

፬ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ናሁ አነ አወርድ ለክሙ ኅብስተ እም ሰማይ ፤ ወይፃእ ሕዝብ ወያስተጋብእ ለለዕለቱ ከመ አመክሮሙ ለእመ የሐውሩ በትእዛዝየ ወ እመ አልቦ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን እነሆ ፲ኔ ከሰማይ እንጀራ (መና) አወርድላችኋለሁ ሕዝቡም በትእዛዜ ፀንተው ይኖ ሩ እንደሁ (አይኖሩም እንደሁ) እንድፈትናቸው የዕለት የዕለት ምግባቸውን ወጥተው ይሰብስቡ አለው ።

፭ ወአመ ዕለተ ዐርብ ያስተዳልዉ ዘአብኡ ይኩኖሙ ካዕበተ ለለዕለት ወዘያስተጋብኡ ዘልፈ ለለዕለቱ ።

ዓርብ ቀን የሰበሰቡትም መናው ለሁለት ቀን ይሆና ቸው ዘንድ ለዓርብና ለቅዳሚት የሚሆናቸውን ዓርብ ቀን ያዘጋጁ ። ዘፀ፡ ፲፯ ፳፪፡ ዘሌ፡ ፳፭ ፳፩ ።

፮ ወይቤልዎሙ ሙሴ ወአሮን ለኵሉ ሕዝበ እስራኤል በሠርክ ተአምሩ ከመ እግዚአብሔር አውፅአክሙ እም ድረ ግብጽ ።

ሙሴና አሮንም ለእስራኤል ወገኖች ሁሉ እግዚአብ ሔር ከግብጽ ምድር ማታ እንዳወጣችሁ ታውቃላችሁ ።

፯ ወበነግህ ትሬእዩ ኀይለ እግዚአብሔር በሰሠርክ ይሁብ ክሙ ሥጋ ትብልዑ፣ ወበነግህ ኅብስተ እስከ ትጸግቡ እስ መ ሰምዐ እግዚአብሔር ነጐርጓሬ ዘታንጐረጕሩ አንትሙ በላዕሌነ ።

ሲነጋም የእግዚአብሔርን ኃይል (ተአምራት) ታያላ ችሁ፣ እናንተ በኛ ላይ የምታንጐራጕሩትን ማንጐርጐር እግዚአብሔር ሰምቷልና የምትበሉትን ሥጋ በሠርክ (ማታ) ይሰጣችኋል አሉዋቸው ። ዘፀ፡ ፲፯ ፳ ፲ ።

፰ ወንሕነ ምንት ንሕነ ወዝ ነጐርጓርክሙ አኮ በላዕሌነ ዘታንጐረጕሩ አላ በላዕለ ፈጣሪ ።

በኛ ላይ የምታንጐራጕሩብን እኛ ምንድር ነን፤ ይህ በኛ ላይ የምታንጐራጕሩት እንጐርጐሮስ በፈጣሪ እንጂ በኛ ላይ አይደለም ። ፩ ሳሙ፡ ፳ ፯ ።

፱ ወይቤሎ ሙሴ ለአሮን፣ በል ለኵሉ ኀበ ተጋብኡ ውሉደ እስራኤል ቅረቡ ቅድመ ፈጣሪ፣ እስመ ሰምዐ ነጐር ጓሬክሙ ።

ሙሴ አሮንን የእስራኤል ልጆት ሁሉ ከተሰበሰቡበት በታ ሂደህ ማንጐራጐራችሁን ሰምቷልና ወደ ፈጣሪያችሁ ፊት ቅረቡ በላቸው አለው ። ዘፀ፡ ፱ ፲፱፡ ፲፫ ፲፮ ።

፲ ወሰበ ተናገሮሙ አሮን ለኵሉ ውሉደ እስራኤል ኀበ ተጋብኡ ተመይጡ ውስተ ገዳም ወሡራኄ እግዚአብሔር ተርእየ በደመና ።

አሮንም የእስራኤል ልጆች በተሰበሰቡበት በታ ለሁሉ በነገራቸው ጊዜ ፊታቸውንም ወደ ምድረ በዳ በመለሱ ጊዜ የእግዚአብሔር ብርሃን በደመና ላይ ታየ ።

፲፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ አነ ሰማዕኩ ነጐርጓ ሮሙ ለውሉደ እስራኤል ።

እግዚአብሔር ሙሴን እኔ የእስራኤል ልጆች ነጐርጓ ራቸውን ሰማሁ አለው ። ዘኍ፡ ፲፯ ፡ ፲፱ ።

፲፪ ወበሎሙ በሠርክ ትበልዑ ሥጋ ወበጽባሕ ትጸግቡ ኅብስተ ወተአምሩ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ፈጣ ሬ ዚአክሙ ።

በሠርክ ሥጋን ትበላላችሁ፣ ሲነጋም መናውን ትጠግ ባላችሁ እኔም ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ታውቃላችሁ በላቸው አለው ። ዘፀ፡ ፲፯ ፮-፳ ።

፲፫ ወመስየ ወመጽአ ፍርፍርት ወከደነ ኵሉ ትዕይን ቶሙ፣ ወበነግህ እንዘ የኀድግ ህዐ በዐርጓኔ ትዕይንቶሙ ።

በመሸም ጊዜ (ድርጭት የባሕር ዶሮ) ከተማቸውን ሁሉ ከደነ በዝቶም ወረደ ።

| | | |
|---|---|---|
| እምፍጽመ ገጸም ድቁቅ ከመ ተቀጻ ወፀዐዳ ከመ አስሐትያ ዲበ ምድር። | ፲፬ | ሲነጋም ውርጭ ሲጥል በከተማቸው ዙርያ እንደ ድንብላል የደቀቀ እንደ ውርጭ የነጣ መና በመሬት ላይ ወረደላቸው ። ዘኍ፣ ፲፩ ፯፣ ነህ፣ ፱ ፲፭፣ መዝ፣ ፸፰ ፳፬ ። |
| ወርእዩ ደቂቀ እስራኤል ወይቤ ብእሲ ለካልኡ ምንትውእቱ ዝ፣ እስመ ኢየአምሩ፣ ወይቤሎሙ ሙሴ ዝ ውእቱ ኅብስት ዘወሀበክሙ እግዚአብሔር ከመ ትብልዑ ። | ፲፭ | የእስራኤልም ልጆች ይህን አይተው አንዱን አንዱ ይህ ምንድር ነው፤ አለው፣ ከዚያ በፊት አያውቁትም ነበርና፣ ሙሴም ልትበሉት እግዚአብሔር የሰጣችሁ መና ነው፤ አላቸው ። ዘዐ፣ ፲፮ ፬ ፴፭ ። |
| ዝ ውእቱ ቃል ዘይቤ እግዚአብሔር ከመ ትግበሩ አስተጋብኡ አምኔሁ በበንዋይክሙ ለለብእሲ በበጎሞር ለለርእሱ በንዋዩ ለያስተጋብእ ። | ፲፮ | ልታደርጉት እግዚአብሔር አድርጉት ብሎ የተናገረው ቃል ይህ ነው፣ ከሱም በየዕቃችሁ ሰብስቡ እያንዳንዱ በቤተ ሰቡ ቍጥር ለየራሱ በዕቃው ይሰብስብ። ፪ ቆሮ፣ ፰ ፲፭ ። |
| ወገብሩ ከማሁ ውሉደ እስራኤል ወአስተጋብኡ ዘብዙኀ ወዘኅዳጥ ። | ፲፯ | የእስራኤልም ልጆች እንዲሁ አደረጉ፣ አብዝተውም አሳንሰውም ሰበሰቡ ። |
| ወሠፈሩ በጎሞር ወኢፈድፈደ ለዘብዙኀ አስተጋብአ፣ ወኢሐፀ ለዘኅዳጠ አስተጋብአ፣ ብእሲ ብእሲ ለለማኅደሩ አስተጋብአ ። | ፲፰ | በጎሞርም ሰፈሩ፣ ብዙ ለሰበሰበው አልበዛለትም (አልተረፈውም) ጥቂት ለሰበሰበውም አላነሰበትም አንዱም አንዱም ሰው ለየቤቱ ሰበሰበ ። ፪ ቆሮ፣ ፰ ፲፭ ። |
| ወይቤሎሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል ኢታትርፉ ለጌሠም ። | ፲፱ | ሙሴም የእስራኤልን ልጆች ለነገ ይሆነናል ብላችሁ አትርፋችሁ አታሳድሩ አላቸው ። |
| ወአበዩ ወኢሰምዕዎ ለሙሴ ወአቤቱ ለነግሁ ወዐፀየ ወጼአ ወተምዐ ሙሴ በላዕሌሆሙ ። | ፳ | ነገር ግን እምቢ ብለው ሙሴን አልሰሙትም፣ ለነገ ይሆነናል ብለውም አትርፈው አሳደሩ፣ መናውም ተላ ሸተተም፣ ሙሴም ተቈጣባቸው ። |
| ወአስተጋብኡ በበነግህ ለውሉዶሙ ወለርእሶሙ ወእምከመ ሞቀ ፀሐይ ይመሁ ። | ፳፩ | ማለዳ ማለዳ ወጥተው ለራሳቸውና ለልጆቻቸው መናውን ይሰበስቡ ነበር፣ ፀሐይም የሞቀ እንደሆነ ይቀልጥ ነበር ። |
| ወበዕለተ ዐርብ ያስተጋብኡ ክዕበተ ጎሞር ለለአሐዱ ወበኡ ኵሉ መኳንንተ ማኅበር ወይቤልዎ ለሙሴ ምንተ ንግበር ። | ፳፪ | ዓርብ ቀን ለያንዳንዱ ሰው ሁለት ሁለት ጎሞር ይሰበስቡ ነበር፣ የማኅበሩም አለቆች ሁሉ ሙሴ ካለበት ገብተው ሙሴን ምን እናድርግ፤ አሉት ። |
| ወይቤሎሙ ሙሴ ዝ ውእቱ ዘእቤሎሙ ሰንበት ዕረፍት ወቡርክት ለእግዚአብሔር ጌሠመ ዘትገብሩ ሀለወክሙ ዮም ግበሩ፣ ወዘታበስሉ ሀለወክሙ አብስሉ፣ ወዘተርፈ አትርፉ ለነግህ ። | ፳፫ | ሙሴም ቅዳሚ ቀን ለእግዚአብሔር የከበረች ዕረፍቱ ናት፣ ብዬ የነገርኋችሁ ቃል ይህ ነው፣ ነገ የምታደርጉትን ዛሬ አድርጉት፣ ነገ የምታበስሉትንም ዛሬ አብስሉት፣ የተረፈውንም ለነገ አታሳድሩት አላቸው ። |
| ወአትረፉ ለነግህ በከመ አዘዞሙ ሙሴ ወኢጼአ፣ ወዕፄ ኢተረክበ ወኢተፈጥረ በላዕሌሁ ። | ፳፬ | ሙሴ እንዳላቸውም ለነጋው አሳደሩ፣ አልሸተተም ትልም አልተገኘበትም በርሱም ላይ አልተፈጠረም ። |
| ወይቤሎሙ ሙሴ ብልዑ ዮም፣ እስመ ዮም ሰንበት ዘእግዚአብሔር ወኢትትረከቡ በገዳም ። | ፳፭ | ሙሴም ዛሬ የእግዚአብሔር በዓል ናትና አሁን ብሉ፣ ቅዳሚ ቀን (መናውን ለመሰብሰብ) በምድረ በዳ አትገኙ አላቸው ። |
| ሰዱስ ዕለተ ታስተጋብኡ፣ ወአመ ሳብዕት ዕለት ሰንበት ኢትትረከቡ በገዳም ። | ፳፮ | ስድስቱ ቀን ምግባችሁን ሰብስቡ፣ በሰባተኛይቱ ቀን ግን የከበረች በዓል ናትና መናውን ለመሰብሰብ በምድረ በዳ አትገኙ ። |
| ወአመ ሳብዕት ዕለት ፀ ዘወፅአ እምሕዝብ ከመ ያስተጋብእ ወኢረከበ ። | ፳፯ | በሰባተኛይቱ ቀን ቅዳሚ መናውን ለመልቀም ከሕዝቡ የወጣ ነበረ፣ ነገር ግን አላገኘም ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ እስከ ማእዜኑ ተአብዩ ሰሚዐ ትእዛዝየ ወሕግየ ። | ፳፰ | እግዚአብሔር ሙሴን ሕጌንና ሥርዓቴን መስማት እምቢ የምትሉ እስከ መቼ ድረስ ነው፤ አለው ። |
| ወርእዩ ከመ እግዚአብሔር ወሀበክሙ ዛ ዕለተ ሰንበት፣ በእንተዝ ወሀበክሙ በዕለተ ዐርብ ምሳሐ ለክልኤቱ ዕለት ። | ፳፱ | እግዚአብሔር ይህችን የዕረፍት ቀን እንደ ሰጣችሁ ተመልከቱ፣ ስለዚህ ቅዳሚና ዓርብ ለሁለት ቀን የምትመገቡትን መና ሰጣችሁ ። |
| ወይንበር ብእሲ ብእሲ ለለማኅደሩ፣ ወኢይፃእ እምንባሪሁ አመ ዕለተ ሰንበት፣ ወአሰንበተ ሕዝብ በዕለተ ሰንበት ። | ፴ | አሁንም አንዱም አንዱም ሰው ከየማደሪያው (ከየድንኳኑ) አይውጣ፣ በየድንኳኑ ይቀመጥ፣ ሕዝቡም በሰባተኛይቱ ቀን ቅዳሚ አረፈ አከበረ ። |

፴፩ ወሰመይዎ ውሉደ እስራኤል መና ፡ ወውእቱ ድቁቅ ከመ ፍሬ ተቅዳ ወፀዐዳ ከመ አስሐትያ ወጣዕሙ ከመ አያያተ መዓር ።

የእስራኤል ልጆች መናውን መና ብለው ጠሩት ፡ እርሱም እንደ ድንብላል ፍሬ ደቃቅ መልኩ እንደ ውርጭ ነጭ ፡ ጣዕሙ እንደ ማር ወለላ ነበር ። ዘፀ ፲፮ ፲፭ ።

፴፪ ወይቤ ሙሴ ዝ ውእቱ ቃል ዘአዘዘ እግዚአብሔር ከመ ትምልኡ ጎሞረ መና ውስተ መዛግብቲክሙ ከመ ይትዓቀብ ለትውልድክሙ ከመ ይርአዩ ኅብስተ ዘአብላዕ ኩክሙ በገዳም አመ አውጻእኩክሙ እምድረ ግብጽ ።

ሙሴም እንዲህ አለ ፤ ከግብጽ አገር በወጣችሁ ጊዜ ያበላኋችሁን መና እንዲያዩ ለልጆቻችሁ ይጠበቅላቸው ዘንድ በየዕቃችሁ ጎሞር ሙሉ መና ትሞሉ ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዘው ቃል ይህ ነው ።

፴፫ ወይቤሎ ሙሴ ለአሮን ንሣእ ቈጽለ ወርቅ አሐተ ረቃቀ ፡ ወግሎ በቲ መሶበ ወአንብር ፡ ውስቴታ መና ምሉአ ጎሞር ቅድመ እግዚአብሔር ለደኃሪ መዋዕል ለደቂቅክሙ ።

ሙሴም አሮንን አንዲት የወርቅ ቅጠል አሳስተህ መሶቡን ውስጡን አፍአውን በወርቅ ለብጠው በውስጧም (ዘመን ሳትወስን) ጎሞር ሙሉ መና አግብተህ ለኋላ ዘመን ለልጅ ልጆቻችሁ ይጠበቅ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት አኑር አለው ። ዕብ ፱ ፬ ።

፴፬ ከመ ይርአዩ ኅብስተ ዘበላዕክሙ አንትሙ በገዳም እስመ ከመዝ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ እንበለ ዓለም ፡ ወአንበሮ አሮን በቅድመ መርጡል ከመ ይትዐቀብ ።

አሮንም ሙሴን ዘመን ሳትወስን ጎሞር ሙሉ መና አኑር ብሎ እግዚአብሔር አዝዞታልና በምድረ በዳ ሳላችሁ የበላችሁትን መና የኋላ ልጆች እንዲያዩት ለልጆቻችሁ ለኋላ ዘመን ተጠብቆ እንዲቈያቸው ጎሞር ሙሉ መና ያለበትን መሶብ በደብተራ ኦሪት ፊት አኖረው ።

፴፭ ወደቂቀ እስራኤል በልዑ መና አርብዐ ክረምተ እስከ ይበጽሑ ምድረ ኅበ ያነብሮሙ እግዚአብሔር ልዑል እስከ ደወለ ፊንቆን ።

የእሥራኤል ልጆች ልዑል እግዚአብሔር በከነዓን ውስጥ ባለች በፊንቆን አውራጃ እስኪያኖራቸው ድረስ ዓርባ ዘመን ሙሉ መናውን በሉ (ተመገቡ) ።

፴፮ ወጎሞር ዐሥርቱ እድ ዘሠለስቱ መስፈርተ ኢፍ ይእቲ ።

ጎሞርም የኢፍ መሥፈሪያ ሦስት እጅ አሥረኛ ክፍል ናት ።

## ምዕራፍ ፲፯ ።

፩ ወአንሥኡ ትዕይንቶሙ ኵሉ ውሉደ እስራኤል እምገዳም ዘሲን በበትዕይንቶሙ በቃለ እግዚአብሔር ወበጽሑ ኀበ ራፊድ ወአልበ ዘየ ማይ ዘይሰትዩ።

የእስራኤል ልጆች ሁሉ ከሲን ምድረ በዳ ሠራዊቶቻቸውን አንሥተው በእግዚአብሔር ትእዛዝ ተጕዘው ራፊድ ከሚባል አገር ደረሱ ፤ በዚያም የሚጠጡት ውኃ አልነበረም ። ዘፀ ፲፯ ፩ ፤ ዘኍ ፴፫ ፲፬ ።

፪ ወግዕዘም ሕዝብ ለሙሴ ወይቤልዎ ሀበነ ማየ ዘንሰቲ ወይቤሎሙ ሙሴ ምንተ ትገአዙ ኪያየ ወታሜክርዎ ለእግዚአብሔር ።

ሕዝቡም ሙሴን ነቀፉት ፡ የምንጠጣውንም ውኃ ስጠን አሉት ፤ ሙሴም እኔን ለምን ትነቅፉኛ አላቸሁ ፤ እግዚአብሔርስ ለምን ትፈታተኑታላችሁ ፤ አላቸው ።

፫ ወጸምአ በህየ ሕዝብ ማየ ወአንጐርጐሩ ዲበ ሙሴ ወይቤልዎ ለምንት አውጻእከነ እምግብጽ ከመ ትቅትለነ ምስለ ውሉድነ ወምስለ እንስሳነ በጽምእ ።

ሕዝቡም በዚያ በታ ውኃ ተጠምተው ከልጆቻችን ከከብቶቻችን ጋራ በውኃ ጥም ትገድለን ዘንድ ከግብጽ አገር ለምን አወጣኸን ፤ ብለው በሙሴ አንጐራጐሩበት ።

፬ ወጸርሐ ሙሴ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤ ፡ ሚ እግበሮ ለዝ ሕዝብ ንስቲተ ክመ ተርፎሙ ወይዌግሩኒ በእብን ።

ሙሴም በደንጊያ ወግረው ሊገድሉኝ ጥቂት ብቻ ቀርታቸዋል ፡ ይህን ሕዝብ ምን ላድርገው ፤ ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ (ለመነ) ። ፩ ሳሙ ፴ ፮ ።

፭ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ሑር ቅድሜሆሙ ለሕዝብ ወንሣእ ምስሌከ መላሕቅተ ሕዝብ ወበትረከ ዘበቱ ዘበጥከ ፈለገ ግብጽ በእደከ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን በሕዝቡ ላይ የተሾሙ አለቆችን አስከትለህ የግብጽ ወንዝ የመታህባት በትርህን በእጅህ ይዘህ በሕዝቡ ፊት እለፍ አለው ።

፮ ወትመጽእ ለፌ ኀበ አነ እቀውም መንገለ ኰኵሕ ዘኮሬብ ፡ ወትዘብጦ ለኰኵሕ ወይወጽእ እምውስቴቱ ማይ ወይሰትዩ ሕዝብ ፡ ወገብረ ሙሴ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር በቅድሜሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

እኔ ወደ ምቆምበት ወደ ኮሬብ አለት መጥተህ አለቱን ትመታዋለህ ፡ ከአለቱ ውስጥ ውኃ ይፈልቃል ፡ ሕዝቡም ውኃውን ይጠጡ ፡ ሙሴም በእስራኤል ልጆች ፊት እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ ። መዝ ፸፰ ፲፭ ።

፯ ወሰመዮ ለውእቱ መካን ፍና መንሱት ወጋእዝ በእንተ ግእዘት ዘግእዝዎ ውሉደ እስራኤል ወአመከሩ ፈጣሬ ኵሉ ወይቤሉ ለእመ ሀሎ እግዚአብሔር ምስሌነ ወለእመ ኢሀሎ ።

ሙሴም የእስራኤል ልጆች ነቀፋን ስለ ነቀፉት የሁሉ ፈጣሪንም ከኛ ጋር አለን ፤ ወይስ የለም ፤ ብለው ስለ ተፈታተኑት ፡ ያንን በታ የጥልና የክርክር መንገድ አለው ።

፰ ወመጽአ አማሌቅ ከመ ይትቃተሎ ምስለ እስራ-

አማሌቃውያንም በዚያ ወራት በራፊድ ከእስራኤል

ኤል በራፊድ ።

፱ ወይቤሎ ሙሴ ለኢያሱ ኅረይ ለከ እደወ ወፃእ ወተ አንበሮሙ ለአማሌቅ ጌሠመ ወናሁ አነ እቀውም ዲበ ርእሰ ወግር ወበትር ዘእግዚአብሔር ውስተ እዴየ ።

፲ ወገብረ ኢያሱ በከመ አዘዞ ሙሴ ወተራከቦሙ ለአማሌቅ ፣ ወሙሴ ወአሮን ወሆር ዐርጉ ውስተ ርእሰ ወግር ።

፲፩ ወሶበ ያነሥእ ሙሴ እደዊሁ ይትዌጽዑ አማሌቅ ፣ ወሶበ የዐጽብ ሙሴ ያወርድ እደዊሁ ወይትዌጽዑ እስራኤል ፣ ወአንበሩ ሎቱ እብነ ወነበረ ላዕሌሁ ።

፲፪ ወእደዊሁ ለሙሴ ክቡዳት ወአሮን ወሆር ይፀውሩ እደዊሁ ለሙሴ አሐዱ በለፌ ወአሐዱ በለፌ ወቆማ እደዊሁ ለሙሴ ርቡብቲሆን እስከ ዕርበተ ፀሐይ ።

፲፫ ወሜጦሙ ኢያሱ ለአማሌቅ ምስለ ሕዝቡ ወቀተሎሙ በሐፂን ።

፲፬ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ጸሐፎ ለዝ ተዝካር ፣ ወአይድዖ ለኢያሱ ድምሳሴ እደመስሶሙ ለአማሌቅ እምታሕተ ሰማይ ።

፲፭ ወአሕነጸ ሙሴ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር ወሰመዮ ስሞ ምምኅፃን ።

፲፮ ወይቤ እስመ በእድ ኅቡአት ይፀብኦሙ እግዚአብሔር ለአማሌቅ ለዘመደ ዘመድ ።

## ምዕራፍ ፲፰ ።

፩ ወሰምዐ ዮቶር ካህነ ምድያም ሐሙሁ ለሙሴ ኵሎ ዘገብረ ሎቱ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለእስራኤል ሕዝቡ ወዘከመ አውፅኦሙ እምግብጽ ።

፪ ወነሥኣ ዮቶር ሲፓራሃ ብእሲቶ ለሙሴ እምዘ ኀደጋ ወክልኤቲ ደቂቃ ።

፫ ስሙ ለወልደ ሙሴ አሐዱ ጌርሳም ወይቤ እስመ ፈላሲ አነ በምድረ ባዕድ ።

፬ ወስሙ ለካልኡ ወልዱ ኤልዓዛር ፣ ወይቤ ፈጣሬ ዘአቡየ ረዳእየ ወአድኀነኒ እምእዴሁ ለፈርዖን ።

፭ ወመጽአ ዮቶር ሐሙሁ ለሙሴ ወብእሲቱ ወደቂቁ ኀበ ሙሴ ውስተ ገዳም ኀበ ኀደሩ ገንጸ ደብር ዘእግዚአብሔር ።

፮ ወይቤልዎ ለሙሴ ናሁ ዮቶር ሐሙከ ወክልኤሆሙ ደቂቅከ ።

፯ ወወፅአ ሙሴ ወተቀበሎ ለሐሙሁ ወአምኆ ወሰዐሞ ወተአምኁ በበይናቲሆሙ ወቦኡ ውስተ ትአይንት ።

፰ ወዜነዎ ሙሴ ለሐሙሁ ኵሎ ዘገብረ እግዚአብሔር በፈርዖን ወበግብጽ በእንተ እስራኤል ወኵሎ ሕማመ ዘኮነ

ጋር ሊዋጉ መጡ ። ዘዳ፡ ፳፭ ፲፯ ፤ ፩ ሳሙ፡ ፲፭ ፪ ።

ሙሴም ኢያሱን አርበኞችን መርጠህ ወጥተህ ነገ አማሌቃውያንን ተያያዛቸው (ተዋጋቸው) እኔም እግዚአብሔር በእጄ ተአምራት ያደረገበትን በትር ይዤ በኮረብታው ራስ ላይ እቆማለሁ አለው ። ግ፡ ሐ፡ ፯ ፵፭ ።

ኢያሱም ሙሴ እንዳዘዘው አደረገ ፣ አማሌቃውያንንም ተዋጋቸው ፣ ሙሴና አሮን ሆርም ሁነው ወደ ኮረብታው ራስ ላይ ወጡ ።

ሙሴ እጆቹን በዘረጋ ጊዜ አማሌቃውያን ይሸነፉ (ይደክሙ ድል ይነሡ) ነበር ፤ ሙሴ እጆቹ ከብደውት ባጠፋቸው ጊዜ እስራኤል ይሸነፉ (ድል ይነሱ ይሸሹ) ነበር ፣ ያን ጊዜ በኮረብታው ድንጊያ ተከሉለት በዚያም ላይ ተቀመጠ ።

የሙሴ እጆች የከበዱ ነበርና አሮንና ሆር አንዱ በቀኝ አንዱ በግራ ሆነው የሙሴን እጆች ተሸክመው ይውሉ ነበር ፣ የሙሴም እጆች ፀሐይ እስኪገባ ድረስ ተዘርግተው ይውሉ ነበር ።

ኢያሱም ከወገኖቹ ጋር ሁኖ አማሌቃውያንን ተዋግቶ መለሳቸው በጦርም አጠፋቸው ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ይህንን ለመታሰቢያ ጻፈው ፣ ከሰማይ በታች ያሉ አማሌቃውያንን ፈጽሜ እደመስሳቸዋለሁ ብሏል ብለህ ለኢያሱ ንገረው አለው ።

ሙሴም ለእግዚአብሔር መሠውያን ሠርቶ ስሙንም መማፀኛ ብሎ ጠራው ። መሳ፡ ፮ ፳፬ ።

ለእስራኤል የዘመድ ዘመድ የሚሆኑ አማሌቃውያንንም እግዚአብሔር በተሠወረች እጅ (በረቂቅ ሥልጣኑ) ያጠፋቸዋል አለ ።

## ምዕራፍ ፲፰ ።

የምድያም ካህን የሙሴ አማት ዮቶር ፣ እግዚአብሔር ለሙሴ ያደረገለትን ሁሉ ሰማ ፣ ለወገኖቹ እስራኤልም ከግብጽ አውጥቶ ያደረገላቸውን ሁሉ ሰማ ። ዘፀ፡ ፲፪ ፲፰ ።

ዮቶርም (ይህን ሰምቶ) የሙሴን ሚስት ሲፓራን ከተዋት በኋላ ሁለቱንም ልጆቹ ይዞ ሄደ ። ዘፀ፡ ፬ ፳፮ ።

የአንዱ የሙሴ ልጅ ስሙ ጌርሳም ይባላል ፣ እኔ በባዕድ አገር ስደተኛ መጻተኛ ነኝ ብሏልና ።

የሁለተኛ ልጁም ስሙ ኤልዛር ይባላል ፤ የአባቴ ፈጣሪ ረዳቴ መድኃኒቴ ነው ፤ ከፈርዖን እጅ ረዳኝ አዳነኝ ብሏልና ። ፩ ሳሙ፡ ፱ ፲፱ ። ዘፀ፡ ፪ ፲፭ ፤ ዘፍ፡ ፬ ፳፭ ።

የሙሴ አማት ዮቶር ሚስቱን ልጆቹን ይዞ ሙሴ ወዳለበት ወደ ምድረ በዳ መጣ ፣ ይኸውም (ምድረ በዳ) በእግዚአብሔር ተራራ አጠገብ ያለ ያደሩበት በረኻ ነው ።

ሙሴን እነሆ አማትህ ዮቶር ወዳንተ መጣ ፤ ሚስትህም ሁለቱ ልጆችህም መጡ ብለው ነገሩት ።

ሙሴም አማቱን ዮቶር ወጥቶ ተቀበለው እጅ ነሥቶም ሳመው ፣ እርስ በርሳቸውም እጅ ተነሣስተውና ተሳስመው ወደ ሰፈር (ከተማ) ገቡ ። ዘፍ፡ ፲፬ ፲፯ ፤ ፲፰ ፪ ።

ሙሴም ለአማቱ ለዮቶር እግዚአብሔር ስለ እስራኤል በፈርዖንና በግብጻውያን ላይ ያደረገውን ሁሉ በጉዳና

ሐሙ በፍኖት ወዘከመ አድኅኖሙ እግዚአብሔር ።

፱ ወደንገፀ ዮቶር በኵሉ ሰሚዖ ኵሉ ዘገብረ ሎሙ እግ
ዚአብሔር ወዘከመ አድኅኖሙ እምእደ ግብጽ ወእምእደ
ፈርዖን ።
፲ ወይቤ ዮቶር ቡሩክ እግዚአብሔር ዘአድኀነ ሕዝቦ
እምእደ ግብጽ ወእምእደ ፈርዖን ።
፲፩ ይእዜ አእመርኩ ከመ ዐቢይ እግዚአብሔር እምኵሉ
አማልክት ወበበይነ ዝ ተኰነኑ ሎቱ ።

፲፪ ወነሥአ ዮቶር ሐሙሁ ለሙሴ ወገብረ መሥዋዕተ በጽ
ድቅ ለእግዚአብሔር፥ ወመጽኡ አሮን ወሊቃናተ እስራ
ኤል ከመ ይብልዑ ኅብስተ ምስለ ሐሙሁ ለሙሴ በቅ
ድመ እግዚአብሔር ።
፲፫ ወእመ ሣኒታ ነበረ ሙሴ ይኰንን ሕዝበ ወይጸንሕ
ሕዝብ ሙሴሃ እምነግሀ እስከ ሠርክ ።

፲፬ ወርእየ ዮቶር ኵሎ ዘይገብር በላዕለ ሕዝብ ወይ
ቤሎ ዮቶር ለሙሴ ምንትኑ ዝ ዘትገብር በሕዝብ በሕ
ቲትከ ትነብር ወኵሉ ሕዝብ ይቀውሙ እምነግሀ እ
ስከ ሠርክ ።

፲፭ ወይቤሎ ሙሴ ለሐሙሁ እስመ ይመጽኡ ኀቤየ
ሕዝብ ወይሴአሉኒ ፍትሐ በኀበ እግዚአብሔር ፤ ወእ
ምከመ ተጋአዙኒ ይመጽኡ ኀቤየ እፍትሖሙ አስተና
ጺሕየ ለለአሐዱ አሐዱ በኵነኔ እግዚአብሔር ወሕጉ ።

፲፮ ወይቤሎ ሐሙሁ ለሙሴ አኮ ርቱዕ ዝ ነገር ዘአንተ
ትገብር ።
፲፯ ዓቢየ ሕማመ ተሐምም አንተ ወኵሉ ሕዝብ ዘሀሎ
ምስሌከ፥ ይከብደከ ዝ ቃል ወኢትክል በሕቲትከ ገቢሮቶ ።

፲፰ ወይእዜኒ ስምዐኒ ወአነ አምክርከ ወእግዚአብሔር
የሀሉ ምስሌከ ፤ ወኩኖሙ አንተ ለሕዝብ ለኀበ እግዚአብ
ሔር ወትበትክ ቃሎሙ በኀበ እግዚአብሔር ።

፲፱ ወአስምዖሙ ትእዛዘ ለእግዚአብሔር ወሕጎ ወትዜን
ዎሙ ፍኖቶ በእለ የሐውሩ ውስቴቶን ወግብረ ዘይገብሩ ።

፳ ወአንተኒ ለሊከ ምክር ወኅሥሥ እምኵሉ ሕዝብ
ኀያላነ እደወ ወጻድቃነ ወሰብአ እለ ይጸልኡ ትዕቢተ ወ
ሢም ሎሙ መኰንነ ለዐሠርቱ ምእት፥ ወለምእት፥ ወለኀ
ምሳ፥ ወለዐሠርቱ ።

፳፩ ወይኰንኑ ሕዝበ ኵሎ ሰዓተ ወቃለ ዘየዐጽበሙ ያም
ጽኡ ኀቤከ ወቀሊለ ኵነኔ እሙንቱ ይኰንኑ ወይቀልለከ
ወይረድኡከ ።

፳፪ ወዘንተ ቃልየ ለእመ ገበርከ ያኀይለከ እግዚአብ

ውም ያገኛቸውን መከራ ሁሉ እግዚአብሔር ከመከራው
ያዳናቸውንም ማዳን ሁሉ ነገረው ። ዘፍ፡ ፵፬ ፴፬ ።
ዮቶርም እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ከግብጻውያን
እጅና ከፈርዖን እጅ እንዳዳናቸው ሁሉ ሰምቶ በዚህ
ሁሉ ደነገጠ ። ኢዮ፡ ፫ ፳።
ዮቶርም ወገኖቹን ከፈርዖን እጅና ከግብጻውያን እጅ
ያዳነ እግዚአብሔር ክቡር ምስጉን ነው አለ ።
(በስም) አማልክት ተብለው ከሚጠሩም ጣኦታት ይ
ልቅ እግዚአብሔር ዓቢይ ገናና እንደሆነ ዛሬ ዓወቅሁ፥
ስለዚህም ተገዙለት አለ ። ፱ ዜና መዋ፡ ፱ ፰ ።
የሙሴ አማት ዮቶርም የሚሠዋውን ወስዶ ለእግዚአ
ብሔር እውነተኛ መሥዋዕትን አቀረበ፥ የእስራኤል ሽማ
ግሌዎችና አሮንም ከሙሴ አማት ከዮቶር ጋር በእግዚአ
ብሔር ፊት መሥዋዕቱን ሊበሉ መጡ ።
በነጋውም ሙሴ ወገኖቹን ሊሠራ ሊቀጣ በአደባባይ
ተቀመጠ፤ ሕዝቡም ከጧት እስከ ማታ ድረስ ሙሴን ደጅ
ይጠና ነበር ። ዘዳ፡ ፲፪ ፯፥ ፩ ዜና መዋ፡ ፳፱ ፳፩ ።
ዮቶርም ሙሴ በሕዝቡ ላይ የሚያደርገውን ሁሉ አይ
ቶ ሙሴን ይህ በወገኖችህ የምታደርገው ምንድር ነው፤
አንተ ብቻህን በአደባባይ ትቀመጣለህ፥ ሕዝቡም ሁሉ
ተራውን ሲጠብቅ ከጧት እስከ ማታ ቆሞ ይውላል
አለው ። ዘሌ፡ ፳፬ ፲፪፥ ዘኁ፡ ፲፭ ፴፬ ።
ሙሴም አማቱ ዮቶርን እንዲህ አለው፤ ሕዝቡ ወደኔ
መጥተው ከእግዚአብሔር የሚገኝ ፍርድን ይጠይቁኛል
ከተጣሉም በኋላ በእግዚአብሔር ሕግና ሥርዓት እያንዳ
ንዱ አውጥቼ አውርጄ መርምሬ እፈርድላቸው ዘንድ ሕዝ
ቡ ተሰብስበው ወደኔ ይመጣሉና ስለዚህ ነው አለው ።
የሙሴ አማቱም (ዮቶር) ይህ አንተ በሕዝቡ የምታደ
ርገው ነገር የቀና አይደለም አለው ።
ይህ ነገር ይከብድኻልና አንተ ትደክማለህ ካንተም
ጋር ያለው ሕዝቡ ሁሉ ይህንንም ነገር አንተ ብቻ ማድ
ረግ አትችልም ። ዘኁ፡ ፲፩ ፲፬፥ ዘዳ፡ ፲፱ ።
አሁንም እኔ እመክርኻለሁ ስማኝ፤ እግዚአብሔርም
ካንተ ጋር ይሁን አንተ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጠይቀህ
ለሕዝቡ ንገራቸው ፍርዱንም ከእግዚአብሔር ዘንድ አስ
ቈርጥላቸው አለው ። ዘፀ፡ ፫ ፲፪፥ ፬ ፲፯ ።
የእግዚአብሔርንም ትእዛዙንና ሕጉን አሰማቸው (ንገ
ራቸው) ጸንተው የሚኖሩበትን ሥርዓት የሚሠሩትንም
ሥራ አስተምራቸው ። መዝ፡ ፲፱ ፲፩፥ ፻፵፫ ፰ ።
አንተም ለራስህ ምከር፥ ከሕዝቡ ሁሉ አዋቂዎችን
ደጋጎችን ትዕቢት የሚጠሉን ሰዎች መርጠህ ፈልገህ
ለሺሁ አለቃ፤ ለመቶው አዝማች፤ ላምሳው ደምሳሽ ለአ
ሥሩ መጨኔ ሹም፥ (የሺ አለቃ፥ የመቶ የአምሳ የአሥር
አለቃ ሹም)። ዘዳ፡ ፬ ፩፥ መዝ፡ ፻፵፫ ፰ ።
የተሾሙትም በየሰዓቱ ለሕዝቡ ይፍረዱለት ይፍረዱ
በት፥ የጸኑባቸውን ፍርድ ወዳንተ ያምጡ፥ ቀላሉን ፍር
ድ ግን እነሱ ይፍረዱ፥ ይህን ብታደርግ ላንተ ነገሩ ይቀ
ልልኻል፥ (እነሱም በፍርዱ ይረዱኻል) አለው ።
ይህንን ምክሬን ብታደርገው እግዚአብሔር በዕው

ሔር ወትክል ኰንኖ ሕዝብ ይገብእ ውስተ ምንባሪሁ በፍሥሓ ።

፳፬ ወሰምዐ ሙሴ ቃለ ሐሙሁ ወገብረ በከመ ይቤሎ ።

፳፭ ወኀረየ ሙሴ እደወ ዘይክሉ እምኵሉ እስራኤል ወሤሞሙ በላዕሌሆሙ መኰንነ ለአሠርቱ ምእት ፡ ወለምእት ፡ ወለኀምሳ ፡ ወለአሠርቱ ።

፳፮ ወይኰንኑ ኵሎ ሕዝበ ኵሎ ሰዓተ ወዘየዐጽቦሙ ነገረ ያዕርጉ ኀበ ሙሴ ወቀሊለ ነገረ እሙንቱ ይፍትሑ ።

፳፯ ወፈነዎ ሙሴ ለሐሙሁ ውስተ ምድሩ ወኀለፈ ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

፩ ወበሣልስ ወርኅ እምዘወፅኡ ውሉደ እስራኤል እምድረ ግብጽ በዛቲ ዕለት ወፅኡ ወሖሩ እምራፊድ ወበጽሑ ውስተ ገዳም ዘሲና ወኀደሩ ህየ መንጸረ ደብሩ ።

፪ ወሙሴ ዐርገ ውስተ ደብረ እግዚአብሔር ወጸውዖ እግዚአብሔር ለሙሴ እምደብረ ደብር ወይቤሎ በሎሙ ለቤተ ያዕቆብ ወዜንዎሙ ለውሉደ እስራኤል ።

፫ ወአንትሙ ርኢክሙ መጠነ ገበርክዎሙ ለግብጽ ወነሣእኩክሙ ከመ ክንፈ ንስር ወአቅረብኩክሙ ኀቤየ ።

፬ ወይእዜኒ ለእመ ሰማዕክሙኒ ቃልየ ወዐቀብክሙ ትእዛዝየ ትከውኑኒ ሕዝበ ዘጽድቅ እምኵሉ አሕዛብ እስመ ዚአየ ይእቲ ኵለንታሃ ምድር ።

፭ ወአንትሙ ትከውኑኒ እለ መንግሥት ፡ ወእለ ትሠውዑ ሊተ ወሕዝበ ዘጽድቅ ፡ ዘ ቃለ አይድዖሙ ለውሉደ እስራኤል ።

፮ ወመጽአ ሙሴ ወጸውዐ ሊቃናተ ሕዝብ ወአይድዖሙ ኵሎ ቃለ ዘአዘዘ እግዚአብሔር ።

፯ ወአውሥኡ ኵሉ ሕዝብ በአሐዱ ቃል ወይቤሉ ኵሎ ዘአዘዘነ እግዚአብሔር ንገብር ወንሰምዕ ።

፰ ወአዕረገ ሙሴ ቃለ ሕዝብ ኀበ እግዚአብሔር ።

፱ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ እመጽእ አነ ኀቤከ በዐምደ ደመና ከመ ይስምዑ ሕዝብ እንዘ እትናገር ምስሌከ ወይእመኑ ብከ ለዓለመ ዓለም ።

፲ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ወሪደከ ኰንን ሕዝበ ያንጽሑ ርእሶሙ ዮም ፡ ወጌሠመ ወይሕጽቡ አልባሲሆሙ ።

፲፩ ወይጽንሑ ድልዋኒሆሙ ለእመ ሣልስት ዕለት እስመ

ቀት ያጸናኝል ያበረታኝል መፍረድንም ትችላለህ ሕዝቡም ተፈርዶለት ተፈርዶበት ደስ እያለው ወደ ሥፍራው ይመለሳል ። ዘፀ፡ ፲፰ ፲፰፡ ዘዳ፡ ፲፰ ፴፫ ።

ሙሴም የአማቱ የዮቶርን ቃል ሰምቶ እንዳለው አደረገ ።

ሙሴም ከእስራኤል ሁሉ (ለውጥተው አውርዶው) መርምረው መፍረድ የሚቻላቸው ደጋግ ሰዎች መርጦ የሺህ አለቆች ፡ የመቶ ፡ የአምሳ ፡ የአሥር አለቆች አድርጎ ሾመላቸው ። ዘዳ፡ ፩ ፲፭ ፡ ፪ ሳሙ፡ ፲፱ ፴፱ ።

አለቆቹም በየጊዜው እንዲፈርዱላቸው እንዲፈርዱባቸው የጠነናቸውንም ፍርድ ወደ ሙሴ ሊያደርሱ የቀለሰውን ግን እነሱ ይፈርዱ ዘንድ ሾመላቸው ።

ሙሴም አማቱ ዮቶርን ወደ አገሩ ሸኝቶ ተመለሰ ፡ (ዮቶርን ወደ አገሩ ሸኘው) ፡ እሱም ወደ አገሩ ሄደ ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

የእስራኤል ልጆች ከግብጽ አገር ከወጡ በኋላ በሦስተኛው ወር (ሰኔ) በዚያች ቀን ከራፊድ ወጥተው በሲና አጠገብ ወዳለ ምድረ በዳ ደረሱ ፡ በሲናም ተራራ ፊት ለፊት ሰፍረው አደሩ ። ዘፀ፡ ፲፯ ፲፰፡ ፫ ፲፪ ።

ሙሴም ወደ እግዚአብሔር (መዲና) ደብረ ሲና ወጣ እግዚአብሔርም ከደብረ ሲና ሆኖ ሙሴን ጠርቶ እንዲህ አለው ፤ ለእስራኤል ልጆች ለያዕቆብ ወገኖች እንዲህ አለ ብለህ ንገራቸው ። ዘፀ፡ ፫ ፳፩፡ ግብ፡ ሐዋ፡ ፯ ፴፰ ።

እናንተ በግብጻውያን ያደረግሁባቸውን መከራ አይታችኋል እናንተን ግን እንደ ጭላት (ፈጥኜ) አውጥቼ ወደኔ አቀረብኋችሁ ።

አሁንም ቃሌን ብትሰሙኝ ትእዛዜንም ብትጠብቁ መላዋ ምድር የኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ ተለይታችሁ እውነተኛ ወገኖቼ ትሆናላችሁ አለ ብለህ ንገራቸው ።

እናንተም የነገሥታት ወገን ትሆኑኛላችሁ (ነገሥታት ከናንተ ይወለዱልኛል) መሥዋዕትንም ትሠውልኛላችሁ እውነተኛ ወገኖችንም ትሆኑኛላችሁ ፡ ለእስራኤል ልጆች ይህን ሁሉ ቃል ንገራቸው ።

ሙሴም መጥቶ የሕዝቡን አለቆች ጠርቶ እግዚአብሔር ሊጠብቁት (ሊሠሩት) ያዘዘውን ቃል ሁሉ ነገራቸው ።

ሕዝቡም ሁሉ አንድ ቃል ሁነው እግዚአብሔር ያዘዘንን ቃል ሁሉ ሰምተን እናደርጋለን አሉ ።

ሙሴም የሕዝቡን ቃል ወደ እግዚአብሔር አደረሰ ። ዘፀ፡ ፳፬ ፫ ፯ ፡ ዘዳግ፡ ፭ ፲፯ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው ፤ እኔ ካንተ ጋር ስነጋገር ሕዝቡ እንዲሰሙ እኔ የላክሁህ እውነተኛ ነቢይ እንደ ሆንክም ለዘለዓለም እንዲያምኑብህ በዓምደ ደመና ወዳንተ እመጣለሁ አለው ።

እግዚአብሔር ሙሴን ዛሬም ነገም ራሳቸውን እንዲያነጹ ልብሶቻቸውን (አጥበው) ሊያደርቁ ሕዝቡን ሥራቀጣ አለው ።

በሦስተኛው ቀን ሕዝቡ እያዩኝ በዓምደ ደመና ሁኜ

| | | |
|---|---|---|
| እመ ሣልስት ዕለት እወርድ ውስተ ደብር ዘሲና በቅድሜሆሙ ለሕዝብ ። | | ወደ ደብረ ሲና እወርዳለሁና ለምወርድበት ለሦስተኛው ቀን ዝግጁዎች ሁነው ይጠብቁ አለው ። |
| ወትከፍል ሕዝበ ይዑድዋ ለደብር ወለይትዐቀቡ ኢይዕርጉ ውስተ ደብር ዜኑ በቅድሜሆሙ ለሕዝብ ወኵሉ ዘለከፈ ለደብር ሞተ ለይሙት ። | ፲፪ | ሕዝቡን ከሦስት ከፍለህ ደብሪቱን ይከበቡዋት ወደ ተራራውም እንዳይወጡ ይጠንቀቁ፣ ይህንንም እግዚአብሔር ብሏል ብለህ በሕዝቡ ፊት ተናገር፣ ተራራውንም የነካው ሰው ሁሉ ፈጽሞ ይሙት ። |
| ወበእዴዊሆሙ ኢያርእዩ ወኵሉ ዘይወግር እብነ አው ዘይወጽፍ ሞፀፈ ኢይሕየው፣ እመኒ ሰብእ ወእመኒ እንስሳ ዘቀርበ ኢይሕየው ወእምከመ ቃለ መጥቅዕ ወደመና ኅለፈ እምደብር ይዕርጉ ኀበ ደብር ። | ፲፫ | ተራራውንም በእጃቸው ጠቅሰው እያሳዩ ደንጊያንም የወረወረ ሁሉ ወይም የወነጨፈ ሰው ሁሉ አይዳን፣ ሰውም ሆነ ከብትም ሆነ ወደ ተራራው ከቀረበ አይዳን፤ የመለከትም ድምፅ ከተሰማ ደመናውም በተራራው ሰፍሮ ከታየ ከንዱ ተራራ ወዳንዱ ተራራ ከወጡ አይዳኑ ይሙቱ አለው ። |
| ወወረደ ሙሴ እምዲበ ደብር ኀበ ሕዝብ ወቀደሶሙ ወሐፀቡ አልባሲሆሙ ። | ፲፬ | ሙሴም ከደብረ ሲና ሕዝቡ ወዳሉበት እግረ ደብር ወርዶ ቀደሳቸው (ከሴት ለያቸው) እነሱም ልብሶቻቸውን አጥበው በፀሐይ አደረቁ ። |
| ወይቤሎሙ ለሕዝብ ተደለዉ ለሠሉስ ዕለት ወኢትቅረቡ ኀበ አንስት ። | ፲፭ | ሙሴም እስከ ሦስት ቀን ድረስ ተዘጋጁ ከሴቶች አትቅረቡ ንጽሕናችሁን ጠብቁ አላቸው ። |
| ወእመ ሣልስት ዕለት ገይሠክሙ በጽባሕ ናሁ ትሰምዑ ቃለ መብረቅ ወደመና ወጊሜ በደብሩ ለሲና ወቃለ መጥቅዕ በቢይ ይደምፅ ወይደነግፁ ኵሉ ሕዝብ በውስተ ትእይንት ። | ፲፮ | በሦስተኛውም ቀን ማለዳ ገስግሳችሁ ሂዳችሁ እነሆ የመብረቅንና የነጐድጓድን ድምፅ ትሰማላችሁ፤ በደብረ ሲናም ጉም ሰፍሮበት ታያላችሁ፤ የነጋሪትም ድምፅ ገንትቶ በርትቶ ይሰማል፣ በከተማም ያሉ ሕዝብ ሁሉ ይደነግጣሉ ። |
| ወአውፅአ ሙሴ ሕዝበ እማእከለ ትእይንት ይትራከቡ ምስለ ፈጣሪ ወበጽሑ ኀበ ደብር ። | ፲፯ | ሙሴም ከፈጣሪ ጋር ሊገናኙ ሕዝቡን ከከተማ አወጣቸው ወደ ተራራውም ደረሱ ። |
| ወደብረ ሲና ይጠይስ ኵለንታሁ ከመ ጢስ ዘእቶን እምቅድመ ይረድ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ወእድለቅለቀት ደብር ጥቀ እስመ ወረደ እግዚአብሔር ውስቴታ በእሳት ወይወፅእ እምውስቴታ ከመ ጢስ ዘእምእቶን ወደንገፁ ኵሉ ሕዝብ ጥቀ ። | ፲፰ | እግዚአብሔር ወደ ደብረ ሲና ከመውረዱ አስቀድሞ ደብረ ሲና እንደ ምድጃ ጢስ በዝቶ ሁለመናው ይጤያጤያስ ነበር፣ ደብረ ሲናም በእሳት ተከበ ሳለች እግዚአብሔር ወደርሷ ወርዷልና ፈጽማ ተናወጠች ሕዝቡም ሁሉ ያን አይተው ፈጽመው ደነገጡ ። |
| ወይደምፅ ድምፀ መጥቅዕ እንዘ ይበልኀ ወይኀይል ጥቀ፤ ወሙሴ ይትናገር ወእግዚአብሔር ያወሥእ በቃሉ ። | ፲፱ | የነጋሪትም ድምፅ ፈጽሞ ገንትቶ (በርትቶ) ፈጥኖ ይሰማ ነበር፣ ሙሴም ይናገራል (ይጠይቃል) እግዚአብሔርም ለጠየቀው ይመልስለት ነበር ። |
| ወወረደ እግዚአብሔር ውስተ ደብረ ሲና ዲበ ከተማሁ ለደብር ወዐርገ ሙሴ ። | ፳ | እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ወደ ተራራው ራስ ወረደ፤ ሙሴም (ወደ ደብረ ሲና) ወጣ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ሑር ረድ ወአይድዖሙ ለሕዝብ ይቅረቡ ኀበ ደብር ለጠይቆ ኢይደቅ እምኔሆሙ ብዙኅ ። | ፳፩ | እግዚአብሔር ሙሴን ከዚህ ከተራራው ወርደህ ሕዝቡ ወዳሉበት ወደ ደብረ ሲና ሂድ፣ ይህንን ነገር ለመረዳት ወደ ተራራው እንዳይቀርቡ በዚህም ምክንያት ከነሱ ወገን ብዙ ሰው እንዳይጠፉ አትቅረቡ በላቸው አለው ። |
| ወሠዋዕት እለ ይቀርቡ ኀቤየ ይትቀደሱ ኢያኅልቅ እምኔሆሙ ። | ፳፪ | ወደኔ የሚቀርቡ ካህናት (ሌዋውያን) ተቈጥቼ ከነሱ ወገን እንዳላጠፋ (እስከ ሦስት ቀን ድረስ) እንዲነጹ ማለት ከሴት እንዲለዩ ንገራቸው ። |
| ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር ኢይክሉ ሕዝብ ዐሪገ ውስተ ደብረ ሲና እስመ አስማዕከነ ወትቤለነ ኢትልከፉ ደብረ ወባርክዎ ። | ፳፫ | ሙሴም እግዚአብሔርን ሕዝቡ ወደ ደብረ ሲና እንዳይወጡ አዳኝተህብናልና አክብሩት እንጂ ደብሩን አትንኩት ብለኸናልና ሕዝቡ ወደ ደብረ ሲና መውጣት አይችሉም አለው ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ሑር ወረድ ወዕርግ አንተ ወአሮን ምስሌከ ወሠዋዕትሰ ወሕዝብ ኢይትኀየሉ ዐሪገ ኀበ ደብር ከመ ኢያኅጕል እምኔሆሙ ። | ፳፬ | እግዚአብሔር ደግሞ ሙሴን አንተ ከአሮን ጋር ሁነህ ነገ እኔ ወዳለሁበት ተራራ ራስ ውጣ ሌዋውያንና (ካህናት) ሕዝቡ ግን ተቈጥቼ እንዳላጠፋቸው ደፍረው በርትተው እንዳይወጡ አንተ ከዚህ ወርደህ ሂደህ ንገራቸው አለው። |

፳፭ ወወረደ ሙሴ ኀበ ሕዝብ ወይቤሎሙ ከመዝ ።
ሙሴም ሕዝቡ ወዳሉበት ወርዶ እግዚአብሔር እንዳ ዘዘው ነገራቸው ።

## ምዕራፍ ፳ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ኵሉ ዘ ቃለ ወይቤ ።
እግዚአብሔር ለሙሴ ይህን ሁሉ ቃል ነገረው ።

፪ አነ ውእቱ እግዚእ እግዚአብሔር ዘአውፃእኩከ እም ድረ ግብጽ እምቤተ ቅኔት ።
ከግብጽ አገር ከጽኑ አገዛዝ (ከባርነት ቤት) ያወጣሁህ እኔ ገዢ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ ነገረው ።

፫ "ኢታምልክ አማልክተ ወኢምንተኒ ዘእንበሌየ„ ።
"ያለኔ (ከኔ በቀር) ምንም ምን ሌሎች አማልክትን አታ ምልክ„ ።

፬ ወኢትግበር ለከ አምላከ ዘበውስተ ሰማይ በላዕሉ ወዘበውስተ ምድር በታሕቱ ወዘበውስተ ማያት ዘበታ ሕቴሃ ለምድር ።
ከምድር በላይ ባለ በሰማይ ፡ ከሰማይም በታች ባለ በምድር ፡ ከምድርም በታች ባለ በውኃው ሥነ ፍጥረት ሁሉ አምላክ አታድርግ ።

፭ ኢትስግድ ሎሙ ወኢታምልኮሙ እስመ አነ እግዚእ እግዚአብሔር አምላክከ አምላክ ቀናኢ ዘእፈዲ ኃጢአተ አብ ላዕለ ውሉድ እስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ ለእለ ይጸልኡኒ ።
አትስገድላቸው አታምልካቸውም ፡ በሚጠሉኝ እስከ ሦስትና አራት ትውልድ የአባትን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ለአምላክነቱ የምቀና ፈጣሪህ ገዥህ እግዚአብ ሔር እኔ ነኝና ።

፮ ወእገብር ምሕረተ ለዐሠርቱ ምእት ትውልድ ለእለ ያፈቅሩኒ ፡ ወለእለ የዐቅቡ ትእዛዝየ ወሕግየ ።
እኔን ለሚወዱኝ ሥርዓቴንና ሕጌን ለሚጠብቁ ግን እስከ ሺሕ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግ ዚአብሔር ነኝ ።

፯ "ኢትምሐል ስመ እግዚአብሔር ፈጣሪከ በሐሰት„ እስመ ኢያነጽሖ እግዚአብሔር ለዘያነሥእ ስሞ በሐሰት ፤
ስሙን በሐሰት ጠርቶ የሚምለውን ሰው እግዚአብ ሔር ከፍዳ አያነጻውምና "የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ስም በሐሰት ጠርተህ አትማል„ ።

፰ " ተዘከር ዕለተ ሰንበት ከመ ትቀድሳ„ ።
"የሰንበትን (ቅዳሜ) ቀን እንድታከብራት አስብ„ ።

፱ ሰዱሰ ዕለተ ትገብር ኵሎ ግብረከ ወኵሎ ትካዘከ ።
ስድስት ቀን ሥራህን ሁሉ ሥራ ፡ ግዳጅህንም ሁሉ ።

፲ ወሳብዕት ዕለት ሰንበቱ ለእግዚአብሔር አምላክከ ኢትግበር ባቲ ወኢምንተኒ ግብረ ፡ ኢአንተ ወኢወለ ትከ ፡ ኢገብርከ ፡ ወኢአመትከ ፡ ወኢአድግከ ወኢኵሉ እንስሳከ ወኢፈላሲ ዘይነብር ኀቤከ ።
ሰባተኛይቱ ቀን (ቅዳሜ) የፈጣሪህ የእግዚአብሔር በ ዓል ናትና ምንም ምን (ሥራ) አትሥራበት ፡ አንተ ወንድ ልጅህም ሴት ልጅህም ወንድ ባርያህም ሴት ባርያህም ምንም ምን ሥራ አትሥሩበት ፡ አህያህም ከብትህም ሁሉ አይሥሩ (ማለት አታውሉ)፡ ካንተ ዘንድ የሚኖር መጻተ ኛም አይሥራበት ።

፲፩ እስመ በሰዱስ ዕለት ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወም ድረ ወበሕረ ወኵሎ ዘውስቴቶሙ ወአዕረፈ አመ ሳብዕት ዕለት ፡ በበይነ ዝ ባረከ እግዚአብሔር ለሳብዕት ዕለት ወቀደሳ ።
እግዚአብሔር በስድስቱ ቀን ሰማይና ምድርን ባሕሩ ንና በውስጣቸው ያለ ሥነ ፍጥረትንም ሁሉ ፈጠረ በሰባ ተኛይቱ ቀን (ቅዳሜ) ግን ዓረፈ ፡ (ሥራውን ተወ)፡ ስለዚህም እግዚአብሔር ሰባተኛይቱን ቀን ከስድስቱ ቀን ለይቶ ፈጽሞ አከበራት ።

፲፪ "አክብር አባከ ወእመከ„ ከመ ይኩንከ ጽድቀ ወይ ኑኅ መዋዕሊከ በውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ።
ቸርነቱ (ረድኤቱ) ይደረግልህ ዘንድ እግዚአብሔርም በዚህ ዓለም የሰጠህ ዕድሜህ ይረዝምልህ ዘንድ "እናት አባትህን አክብር„ (ርዳ) ።

፲፫ " ኢትቅትል„ ።
"ነፍስ አትግደል„ ።

፲፬ " ወኢትዘሙ„ ።
"አትሰስን„ (አታመንዝር) ።

፲፭ " ወኢትሰርቅ„ ።
"አትስረቅ„ (የሰው ገንዘብ) ።

፲፮ " ወኢትኩን ሰምዐ በሐሰት ላዕለ ቢጽከ„ ።
"በባልንጀራህም ላይ በሐሰት አትመስክር„ ።

፲፯ ወኢትፍቱ ብእሲተ ካልእከ ፡ ወኢትፍቱ ቤቶ ለካል እከ ፡ ወኢገራህቶ ፡ ወኢገብሮ ፡ ወኢአመቶ ፡ ወኢላሕሞ ፡ ወኢብዕራይሁ ፡ ወኢኵሎ እንስሳሁ ፡ ዘአጥረየ አጥረዮ ቢጽከ ።
"የባልንጀራህንም ሚስት አትመኝ ፡ የባልንጀራህንም ቤቱን ፡ እርሻውን ፡ ወንድ ባርያውን ፡ ሴት ባርያውን ላሙ ንና በሬውን ባልጀራህ የገዛው ከብቱንም ሁሉ አትመኝ በት„ ፡ (አትውሰድበት) ።

፲፰ ወኵሉ ሕዝብ ይሬኢ ቃለ ወብርሃነ ዘለንጻስ ወቃለ መጥቅዕ ወደብሩ ይጠይስ ወፈርሀ ኵሉ ሕዝብ ቆመ እ ምርኁቅ ።
ሕዝቡም ሁሉ ቃሉን ይሰማ ፡ ነበልባል ያለበት ብርሃ ኑን ያይ ነበር ፡ የነጋሪቱንም ድምፅ ይሰማ ነበር ፡ ተራራ ውም ይጤስ ነበር ፡ ሕዝቡም ሁሉ ፈርቶ ርቆ ቆሞ ነበር ።

፲፱ ወይቤልዎ ለሙሴ አንተ ተናገር ምስሌነ ወኢይትናገር እግዚአብሔር ምስሌነ ከመ ኢንሙት ።

ሙሴንም አንተ ከኛ ጋር ተናገር፤ እግዚአብሔር ግን ከንተ ጋር ይናገር እንዳንሞት አሉት ።

፳ ወይቤሎሙ ሙሴ በእንተዝ ከመ ያመክርክሙ መጽአ እግዚአብሔር ኀቤክሙ፤ ወከመ ይኅድር ፍርሀተ እግዚአብሔር ላዕሌክሙ ከመ ኢተአብሱ ።

ሙሴም እንዳትበድሉ እግዚአብሔርን መፍራት (ማምለክ) በናንተ አድሮ ይኖር ዘንድ ስለዚህ ነገር እግዚአብሔር ሊፈታተናችሁ መጣ አላቸው ።

፳፩ ወቆሙ ሕዝብ ርኁቀ ወሙሴ ቦአ ውስተ ብርሃን ኀበ ሀሎ እግዚአብሔር ።

ሕዝቡም ርቀው ቆሙ ሙሴም እግዚአብሔር ወዳለበት ብርሃን (መጋረጃ) ገባ ።

፳፪ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በሎሙ ለቤተ ያዕቆብ አንትሙ ርኢክሙ ከመ እምሰማይ ተናገርኩክሙ ።

እግዚአብሔር ሙሴን ለያዕቆብ ወገኖች እናንተ ከሰማይ ወርጄ እንደተነጋገርኋችሁ አይታችኋል፤ አለ ብለህ ንገራቸው ።

፳፫ ኢታምልኩ አምላከ ዘብሩር ወኢታምልኩ አምላከ ዘወርቅ፤ ወኢታምልኩ አምላከ ዘዕፅ ወዘእብን፤ ወኢትግበሩ ለክሙ ዘከመዝ አምላከ ።

የወርቅና የብርን አምላክ አታምልኩ፤ የድንጋይንና የዕንጨቱን አምላክ አታምልኩ፤ እንደዚህ ያለውን አምላክ አትሥሩ ።

፳፬ ወምሥዋዐ በዲበ ምድር ግበሩ ሊተ ወሡዑ በላዕሌሁ መባአክሙ ወቤዛክሙ በግዐ ወላሕመ በኵሉ መከን በኀበ ሰመይኩ ስምየ በህየ ወእመጽእ ኀቤከ ወእባርከከ ።

ምሥዋዑንም በምድር ላይ ጸፍጽፋችሁ ሥሩልኝ፤ (ለኔ ብላችሁ ያቀረባችሁትን) መባውንም በላዩ ላይ ሠዉልኝ፤ ስሜንም በስጠራሁበት በታ ሁሉ ላሙንና በጉን ሠዉበት፤ (ይህን ያደረግህ እንደሁ) እኔም ወዳንተ መጥቼ አከብርኻለሁ አለ በላቸው ።

፳፭ ወለእመ ምሥዋዐ ዘእብን ገበርከ ሊተ ኢትንድቆ ፈጺሒከ እስመ መጥባሕተከ አንበርከ ላዕሌሁ ወአርኰስኮ ።

የደንጊያውን መሠውያ ብታደርግልኝ (ብትጸፈጽፍልኝ) ፈልጠህ ቈርጠህ ብልት አታውጣለት፤ አንተ ቈርጬ ልቀረጸው (ብልት ላውጣለት) ብለህ አርክሰኸዋልና ።

፳፮ ወርኩሰ ኢታዕርግ ዲበ ምሥዋዕየ ወኢትክሥት ኀፍረተከ በህየ ።

ርኩሱን መሥዋዕት በመሠውያዬ ላይ አትሠዋ፤ በዚያም ኃፍረተ ሥጋህን (አትጣል) አትግለጥ፤ (ኃጢአትህን በሰው ፊት ገልጠህ አትሥራ ሲል ነው) ።

## ምዕራፍ ፳፩ ።

፩ ወዝ ውእቱ ኵነኔ ዘታነብር በቅድሜሆሙ ።

በፊታቸው የምታኖረው ፍርድ ሥርዓት ይህ ነው ።

፪ ለእመ አጥረይከ ገብረ አይሁዳዌ ቅንዮ ስድስተ ክረምተ፤ ወበሳብዕ ክረምት አግዕዞ በከንቱ ።

ዕብራዊ ባርያ ብትገዛ ስድስት ዓመት ግዛው፤ በሰባተኛው ዓመት ግን መበገር ሳትሰጥ ነፃ አውጣው ።

፫ ለእመ በሕቲቶ አጥረይከ ይፃእ ባሕቲቱ፤ ወለእመ ምስለ ብእሲቱ አጥረይከ ይፃእ ምስለ ብእሲቱ ።

ብቻውን ብትገዛው እርሱ ብቻ ይውጣ፤ ከሚስቱ ጋር ብትገዛው ግን ከሚስቱ ጋር ነፃ ይውጣ ።

፬ ወለእመ ወሀበ እግዚኡ ብእሲተ ወወለደት ሎቱ ርሰ፤ ወአዋልደ፤ ብእሲቱ ወደቂቁ ይትቀነዩ ለእግዚኡ፤ ወውእቱ ባሕቲቱ ይግዓዝ ።

ጌታው ሚስት ቢያጋባው ወንድ ልጅ ሴት ልጅ ብትወልድለት ሚስቱና ልጆቹ ለጌታው ይገዙ፤ እርሱ ብቻ ግን ነፃ ይውጣ ። ዘዳግ፡ ፲፭ ፲፯ ።

፭ ወለእመ ይቤ ገብር አፍቀርኩ እግዚእየ ወእግዝእትየ ወብእሲትየ ወደቂቅየ ወኢይፈቅድ ግዕዛነ ።

ባርያው ጌታዬን እመቤቴን ሚስቴንና ልጆቼን እወዳለሁ፤ ለብቻዬ ነፃ አልወጣም ቢል ግን ።

፮ ይስዶ እግዚኡ ኀበ ቤተ ፈጣሪ ወያቅርቦ ኀበ ኆኅት ዘኀበ መድረክ ወይስቍሮ እንዘ በመስፌ ወይትቀነይ ሎቱ ዘልፈ ።

ጌታው ወደ ቤተ እግዚአብሔር ወስዶ መድረኩ ወዳለበት ደጃፍ አቅርቦ አፍንጫውን (ጆሮውን) በመስፌ ይብሳው ለዘለዓለሙ ይገዛለት ።

፯ ወለእመበ ዘአስተዋሰበ ወለቶ ኢትጸጐጐ በከመ ይጸጐጓ አእማት ።

ጌትዮው ሴት ልጁን ቢድራት፤ ሴቶች ባሮች ትሎት እንዲሄዱ የዕብራዊ ባርያ ሴት ልጅ ትሎት አትሂድበት ።

፰ ወለእመ ኢያሥመረት ለእግዚኣ ለሊሃ ዘአምነት ያድኅና፤ ወለእመ ለሕዝብ ካልእ፤ እግዚኣ ኀበ ፈቀደ ይሢጣ እስመ ለሊሃ ፈቀደት ።

ጌታዋን ደስ አሰኝታ በታገለግል ግን፤ ከእስራኤል ወገን እገሌ ይግዛኝ ላለችው ተሸጣ ይግዛት፤ እሷ መሸጥ መለወጧን ወድዳለችና ።

፱ ወለእመ ፈቀደ ለወልዱ የሀባ ከመ እንተ አዋልዱ ይረስያ ።

ለወንድ ልጁ ሊያጋባትም ቢወድ እንደ ሴቶች ልጆቹ ያድርግላት፤ (ጌጥ ልብስ ገንዘብ ሰጥቶ ይዳራት) ።

፲ ወለእመ ካልእተ ነሥአ ሎቱ ዘባ ወአልባሲሃ የሀባ ወስምዐ ያስምዕ ላቲ ከመ ኢየዐምፃ ።

ሌላ ሚስት ቢያጭለት ግን ያላት ገንዘቧን ልብሷን ጌጽዋን ይስጣት፤ ይህንንም እንዳይከዳት ምስክር ያዳኝላት ።

| | | |
|---|---|---|
| ወዘንተ ሠለስተ ለእመ ኢገብረ ላቲ ትፃእ እምኀቤሁ ዘእንበለ ቤዛ ። | ፲፩ | ይህንን ሦስቱን ባያደርግላት ግን መበዣ ሳትሰጥ ከሱ ወጥታ ትሂድ ። |
| ለእመቦ ዘአቍሰለ ከልአ ከልአ ወሞተ፡ መቍሰሊሁ ለይሙት ። | ፲፪ | አንዱ አንዱን አቍስሎት ቢሞት ያቈሰለው ሰው ይሙት ። ዘፍ፡ ፱ ፮፡ ዘሌዋ፡ ፳፬ ፲፯ ። |
| ወለእመሰ አቍሰለ እንዘ ኢይፈቅድ ወመጠዎ እግዚአብሔር በየማነ መቍስሊ እስፍርከ መካነ ኀበ ይትመኀፀን ቀታሊ ። | ፲፫ | ነገር ግን ሊገድለው ፈልጎ ሳይሆን (ለወፍ ለዛፍ ብሎ ወርውሮት) እግዚአብሔር በዚያ በወረወረው እጅ ለሞት አሳልፎ ሰጥቶት ቢሞት ያ የገደለው ሰው ሃገረ ምስክይ ገብቶ እንዲማፀን ዕወቅ ። |
| ወለእመቦ ዘቈጸረ ከመ ይቅትል ጸላኢሁ ወተማኅፀነ ይንሥእዎ እምህየ ወይቅትልዎ ። | ፲፬ | ጠላቱን ሊገድለው አስቦ እርሱን ገድሎ ሀገረ ምስክይ ቢማፀን ግን ከዚያ (ከሀገረ ምስክይ) አውጥተው ይግደሉት ። ዘኍ፡ ፲፭ ፴፡ ዘዳግ፡ ፲፱ ፲፩ ። |
| ዘይዘብጥ አባሁ ወእሞ ይሙት መዊተ፡ ወዘይረግም አባሁ ወእሞ ይትኰነን መዊተ ። | ፲፭ | እናት አባቱን የሚመታ ይሙት፡ እናት አባቱንም የሰደበ ተፈርዶበት ይሙት ። |
| ለእመቦ ዘሰረቀ እምውሉደ እስራኤል ወረዲአክሙ አግበእክሙ በላዕሌሁ ዘረከብክሙ ይሙት መዊተ ። | ፲፮ | ከእስራኤል ልጆች አፍኖ ሽፍኖ ሠርቆ የወሰደ ሰው ቢኖር (እናንተ በአሬታ በጭኸት) ተራድታችሁ ብትመልሱለት ልጁን ያገኛችሁበት ሰው ፈጽሞ ይሙት ። |
| ዘይረግም አባሁ ወእሞ ይትኰነን መዊተ ። | ፲፯ | እናት አባቱን የሚሰድብ ፈጽሞ ይሙት (ይገደል)። |
| ወለእመ ተሰኰዩ ክልኤሆሙ እደው በበይናቲሆሙ ወአቍሰለ ክልአ ለእመ በእብን ወለእመኒ በበትር ወእስከቦ ላዕለ ምስካብ ። | ፲፰ | ሁለት ሰዎች እርስ በርሳቸው ቢጣሉ በድንጋይም ቢሆን በበትርም ቢሆን መትቶት አንዱ አንዱን ቢያቈስ ለው ያ የቈሰለው ሰው ታሞ ቢተኛ ። |
| ወያንስሱ ጽጕ ዘአቍሰሎ ይድኅን መቍስሊ ባሕቱ ዕርፍቲሁ ለየሀብ ወዐስበ ለየዐስብ ለዓቃቤ ሥራይ ። | ፲፱ | ኋላ ግን በኅ ሆኖ የቈሰለው ሰው በአጥር ቢመላለስ፡ ከዚህ በኋላ ቢሞት ያቈሰለው ሰው ከሞት ይዳን፡ (ይድናል) ነገር ግን ምንም ከሞት ቢድን ከሥራ የበዘነበትን ዋጋ ለበለመድኃኒትም የሰጠውን ዋጋ ይስጠው ። |
| ወለእመቦ ዘአቍሰለ ገብሮ ወእመኒ አመቶ በበትር ወሞተ፡ ይመውት መዊተ መቍሰሊ ። | ፳ | ወንድ ባርያውን ሴት ባርያውንም ቢሆን በበትር መትቶ ከወንድ ባርያው ከሴት ባርያው አንዱ ቢሞት ያቈሰ ለው ጌታው ይሙት ። |
| ወእመ በጽሐ አሐተ ዕለተ፡ ወለእመ ሰኒታ ይድኅን እመዊት እስመ ዘዚአሁ ብሩር ውእቱ ። | ፳፩ | አንድ ወይም ሁለት ቀን ውሎ አድሮ ቢሞት ግን ገን ዘቡ ነውና (ገንዘቡ ስለሆነ) ከሞት ይዳን (ይድናል)። |
| ወለእመ ተበአሱ ክልኤቱ እደው በበይናቲሆሙ ወአቍሰሉ ብእሲተ ፅንስተ ወአድኀፀት ምስለ ሰብእ አልበ ያኅሥርዎ፡ ወለእመሰ ዕርቀ ተኀረቀ ምስለ ምታ እንዘ ያስተበቍዕ፡ አልቦ ሞት ። | ፳፪ | ሁለት ሰዎች እርስ በርሳቸው ቢጣሉ፡ ሲታገሉ የፀነ ሰችውን ሴት ቢያቈስሏት ቢያስወርዳት፡ ተሥእሎተ መልክዕ ያልተፈጸመለትም ቢሆን እስከዚያው ድረስ አስረው አግዘው ያኑሩት፡ ማላጅ ልኮ ወድቆ ተነሥቶ ከባልዋ ጋር ቢታረቅ ግን፡ ሞት የለበትም (አይሞትም)። |
| ወለእመሰ አድኀፀት እንዘ ምሱል፡ ይፍዲ መንፈሰ ፍዳ መንፈስ ። | ፳፫ | ተሥእሎተ መልክዕ ከተፈጸመለት በኋላ ቢያስወርዳት ግን (አርባ ቀን ነው)፡ ስለ ነፍስ ነፍሱን ይክፈል (ይሙት)። |
| ዐይን ፍዳ ዓይን፡ ስን ፍዳ ስን፡ እድ ፍዳ እድ፡ እግር ፍዳ እግር ። | ፳፬ | (ሥርዓት ይሠራል) ነፍስ ቢገድል ይሙት፡ ዓይን ቢያፈስ ዓይኑ ይፍሰስ፡ ጥርስ ቢያረግፍ ጥርሱ ይርገፍ፡ እጅ እግር ቢሰብር እጁ እግሩ ይሰበር ። |
| ውዕየት ህየንተ ውዕየት፡ ወፍቅአት ህየንተ ፍቅአት፡ ቍስል ህየንተ ቍስል ። | ፳፭ | ቢያቃጥል ይቃጠል፡ ቢገምስ ይገመስ፡ ቢያቈስል ይቍሰል፡ (ቢገርፍ ይገረፍ)። |
| ወለእመቦ ዘአቍሰለ ዐይነ ገብሩ ወእመሂ ዘአመቱ ወአዖርሙ፡ ያግዕዞሙ ቤዛ ዐይኖሙ ። | ፳፮ | የወንድ ባርያውን፡ የሴት ባርያውን ዓይን መትቶ ዕዉር ቢያደርጋቸው ዓይናቸውን ስለ አጠፋ ፈንታ ነፃ ያውጣቸው ። ቈላስ፡ ፬ ፩ ። |
| ወለእመኒ ሰበረ ጥረሰ ወስነ ዘገብሩ ወዘአመቱ፡ ያግዕዞሙ ቤዛ ስኖሙ ። | ፳፯ | የወንድ ባርያውን የሴት ባርያውን (ጥረስ) መንጋጋቸውን (ስን) የወደፊት ጥርሳቸውን ቢያወልቅ፡ መንጋጋቸውንና ጥርሳቸውን ስላወለቃቸው ፈንታ ነፃ ያውጣቸው ። |
| ወለእመ ወግአ ላሕም ብእሴ ወብእሲተ ወቀተለ በእብን ይውግርዎ ለላሕሙ ወሥጋሁ ኢይብልዑ ወባዕለ ላሕ | ፳፰ | በሬው ወንድም ሴትም ወግቶ ቢገድል፡ በሬውን በድንጋይ ወግረው ይግደሉት፡ ሥጋውንም አይብሉት፡ የ |

ሙ ይድኅን እምኃጢአት ።
፳፱ ወለእመሰ ወግአ ላሕሙ ከመ ትማልም ወሣልስት ወአስምዑ በቱ ለእግዚኡ ወኢአማሰኖ ወቀተለ ብእሴ ወእመሂ ብእሲተ ላሕሞ ይውግሩ ወለእግዚኡኒ ይቀትሉ ።

፴ ወለእመ ሰአለ ቤዛ ርእሱ የሀብ ቤዛ መንፈሱ አምጣነ ተክህሎ ።

፴፩ ወለእመ ወግአ ወልደ ወአዋልደ ዘአየኑ ያስተዋህቡ ።

፴፪ ወለእመ ወግአ ገብረ አው አመተ ሠላሳ ብሩረ የሀብ ለእግዚአሙ ወላሕሙ ይትወገር ።

፴፫ ወእመ ቦ ዘከሠተ ዐዘቅተ ወለእመ አክረየ ግበ ወኢከደኖ አፉሁ ወጸድፈ ውስቴቱ ላሕም ወእመሂ አድግ እግዚአ ዐዘቅት ይፍዲ ብሩረ ወገደላሁ ውእቱ ይንሣእ ።

፴፭ ወላሕም ለእመ ወግአ ላሕመ ዘካልኡ ወሞተ ፡ ይሤጥዎ ለውእቱ ላሕም ሕያው ወይትካፈሉ ሤጠ ወገደላሁ ይትካፈሉ ።
፴፮ ወለእመ ወግአ ላሕሙ ከመ ትማልም ወሣልስት ወአስምዑ ሎቱ ፡ ይፍዲ ላሕመ ተክለ ላሕሙ ወገደላሁ ውእቱ ይንሣእ ።

ምዕራፍ ፳፪ ።

፩ ወለእመቦ ዘሰረቀ ላሕመ ወእመሂ በግዐ ወጠብሖ ይትክል ሀየንተ አሐዱ ላሕም ትኅምስተ ፡ ወሀየንተ አሐዱ በግዕ ትርብዕተ ።
፪ ወከረዮ ሰራቂ ለእመ ቈሰለ ወሞተ ኢይኩኖ ቀቲለ ለዘቀተለ ።
፫ ወለእመሰ ሠረቀ ፀሐይ ላዕሌሁ ፡ ደም ወይመውት ዘቀተሎ ።
፬ ለብእሲ ዘሰረቀ ለእመ አኃዝዎ ወለእመ አልቦ ውስተ እዴሁ ይሠየጥ ሀየንተ ዘሰረቀ ፡ ወለእመ አኃዝዎ ወረከቡ በእዴሁ ለዘሰረቀ እመሂ ላሕመ ወእመሂ በግዐ ፡ ክዕበተ ይፍዲ ።

፭ ወለእመቦ ዘአብልዐ ገራህተ ሰብእ እንስሳሁ ወዐፀደ ወይን ዘባዕድ ይርአይዎ ወአሥማር ይፍዲ ፡ ወለእመሰ አግመረ ገራህተ እንዘ ያበልዕ በሠምረ ገራህቱ ይፍዲ ፡ ወለእመኒ ዐፀደ ወይን በሠምረ ዐፀደ ወይን ይፍዲ ።

፮ ወለእመ ወፅአ እሳት ወአኀዘ ገዳመ ወአውዐየ ዐውደ ፡ ወእመሂ ክምረ ፡ ዘአውዐየ ይፍዲ ።
፯ ወለእመቦ ዘአዕቀበ ብሩረ ወእመሂ ንዋየ ወተሰርቀ

ሬው ባለቤት ግን አይሙት (ይዳን) ። ዘፍ፡ ፱ ፮ ።
በሬው ዛሬም ነገም ሣልስትም እያለ ሰው ቢወጋ በጌትየው ቢያዳኙበት (ባይሸጠው ባይለውጠው ባያርደው) ወንድም ሴትም ወግቶ ቢገድል በሬውን በደንጊያ ወግረው ይግደሉት ጌታውንም ይግደሉት ።
የነፍስ ዋጋ ልክፈል ተዉኝ አትግደሉኝ ብሎ ቢለምን ግን ይህን ያህል እሰጣለሁ ያለውን ለሰውነቱ ቤዛ (ካሣ) ይስጥ ። ዘኍ፡ ፴፭ ፴፩ ።
በሬው ወንድ ልጅ ፡ ሴት ልጅ ቢወጋ ሽማግሌዎች የገመገሙትን ፡ ያስጡ ።
ወንድ ባርያ ወይም ሴት ባርያ ቢወጋ ባለበሬው ለባሮቹ ጌታ ሠላሳ ብር ይስጥ ፡ በሬውም ተወግሮ ይሙት ።
የኖረ ጕድጓድ የከፈተ አዲስ ጕድጓድም ያስቈፈረ ቢኖር አፉን ባይገጥመው ፡ በሬውም ቢሆን አህያውም ቢሆን (ከዚያ ወድቆ) ቢሞት የጕድጓዱ ባለቤት ለባለቤታቸው (የተገመገመውን) ዋጋ ይክፈል ፡ ወደቃቱን ግን እሱ ይውሰድ ። ዘካ፡ ፲፩ ፲፪ - ፲፫ ፡ ማቴ፡ ፳፮ ፲፭ ።
የሰው በሬ የሌላውን በሬ ወግቶት ቢሞት በሬው የሞተበት ሰውና በሬ የገደለበት ሰው ደኅናውን በሬ ሸጠው ዋጋውን ይካፈሉ ፡ ወደቃቱንም ይካፈሉ ።
በሬው ዛሬም ትላንትም ነገም እያለ ያንዱን በሬ ወግቶ ቢገድል ባለ በሬው ካዳኘበት በኋላ (ሳይሸጠው ሳይለውጠው ሳያርደው) ቀርቶ ወግቶ ቢገድልበት የበሬው ባለቤት ስለሞተበት በሬ ፈንታ በተገመገመ ዋጋ ይክፈል ፡ ወደቃቱን ግን እሱ ይውሰድ ።

ምዕራፍ፡ ፳፪ ።

በሬ በግ ሰርቆ ያረደ ሰው ቢኖር ስለ አንድ በሬ ፈንታ አምስት በሬ ይክፈል ፡ ስለ አንድ በግ ፈንታ አራት በግ ይክፈል ። ፪ ሳሙ፡ ፲፪ ፮፡ ምሳ፡ ፮ ፴፩ ።
ሌባ ሌሊት ቤት ሲቈፍር ተገኝቶ ቈስሎ ቢሞት ፡ ለገደለው ሰው ዕዳ አይሆንበትም ። ዘሌ፡ ፲፱ ፲፩ ።
ፀሐይ ከወጣ በኋላ ቢገድለው ግን የደሙ ፍዳ በርሱ ላይ ነው ፡ የገደለውም ሰው ይሙት ።
ሌባውን ሰርቆ ሲሄድ አግኝተው ቢይዙት ከእጁ ገንዘብ ባይገኝበት ስለ ሰረቀው ገንዘብ ፈንታ ይሸጥ (ይገዛ) ሲሰርቅ አግኝተዉት ቢይዙት ግን በሌባውም እጅ ገንዘብ ቢያገኙበት በሬውም ቢሆን በጉም ቢሆን አህያውም ቢሆን ፡ በአንድ ሁለት ይክፈል ። ዘፀ፡ ፳፩ ፲፮ ።
ከብቱን ሰዶ የሰውን እርሻ ያስበላ ሰው ቢኖር ፡ የሌላውንም የወይን ቦታ ያስበላ ቢኖር ፡ (እርሻውን ዞረው) ይመርምሩት በበጀው እኽል በበጀው ተክል ልክ ይክፈል ፡ ከብቱ እርሻውን ጨርሶ ቢበላው የወይኑንም ቦታ ጨርሶ ቢበላው በጎረቤቱ እርሻ ልክ በጎረቤቱ የወይን ቦታ ልክ ይክፈል ።
እሳት ተነሥቶ ምድረ በዳውን ቢያቃጥል ዓውድማውንም ክምሩንም ቢያቃጥል ያ ያቃጠለው ሰው ይክፈል።
የብር አደራ ያኖረ ሰው ቢኖር ሌላውንም ገንዘብ አደ

ለዘአዕቀብዎ ወረከበ ለዘሰረቆ ፡ ይፍዲ ክዕበተ ።

፰ ወለእመ ኢተረክበ ሰራቂ ለይሑር በዓለ ቤት ቅድመ ፈጣሪ ወይምሐል በማኅፀንት ዘአማኅፀንዎ ከመ ኢተኬነወ ወከመ ኢቈጸረ ።

፱ እመኒ ላሕመ ወእመኒ አድገ ወእመኒ በግዐ በዘኑሠ በማኅፀን በዘከነ ከዊኖ በሀየ ይኅልቍዎሙ በበይናቲሆሙ ወዘገደፈ ፡ ክዕበተ ይፍዲ ለማዕቀቢሁ ።

፲ ወለእመበ ዘወሀበ ለካልኡ ብዕራይሁ አው ላሕሞ እመኒ በግዖ ዘከነ እምእንስሳሁ ወሞተ ቈሲሎ ፡ ወእመኒ ማህረኩ በቱ ወአልቦ ዘአእመረ ሎቱ ፡ መሐላ ዘእግዚአብሔር ተርፈ ማእከሎሙ ከመ ተፈቲዎ ኢተኬነወ ተማኅፃኒ ፡ ወበበይነዝ ኢይፈዲ ዘተማኅፀነ ።

፲፩ ወለእመ ሰረቅዎ ዘአዕቀብዎ ፡ ይፍዲ ለዘአዕቀቦ ።

፲፪ ወለእመኒ አርዌ አኀዘ በገዳም ይመርሕ ገደላሁ ወኢይፈዲ ።

፲፫ ወለእመ ተውሕሰ ብእሲ እምቢጹ ወተሰብረ ወሞተ ወኢሀሎ አውሐሲ ፡ እግዚኡ ንዋይ ይፍዲ ።

፲፬ ወለእመ ሀሎ እግዚኡ ኢይፈዲ ፡ ወለእመ ገብኢሁ ውእቱ ዐስበ ይፍዲ ።

፲፭ ወለእመበ ዘአስሐታ ለድንግል እንተ ኢኮነት ፍኅርተ ወሰከበ ምስሌሃ ፡ ይንሥእ ትኩኖ ብእሲተ ።

፲፮ ወለእመሰ አበየ አቡሃ ከመ ኢየሀባ ኅዲሃ የሀበ ለአቡሃ ከመ የኀፅዪዋ ለድንግል ።

፲፯ ወምስላ ዘሥራይ ኢትትዋሰቡ ።

፲፰ ወኵሎ ዘየሐውር ኀበ እንስሳ ፡ ሞተ ለይሙት ።

፲፱ ወዘይሠውዕ ለአማልክት ዘእንበለ ለእግዚአብሔር በሕቲቱ ፡ ይሠረው ።

፳ ወኢታሕስሙ ለግዩር ወኢታጥቅዎ እስመ አንትሙኒ ግዩራን ከንክሙ በምድረ ግብጽ ።

፳፩ ወለኵሉ ዕቤራት ወእጓለ ማውታ ኢታሕስሙ ።

፳፪ ወለእመ አሕሰምክሙ ወጸርሑ ወአውየዉ ኀቤየ ሰሚዐ እሰምዕ ገዓሮሙ ።

፳፫ ወእትመዓዕ በመዓትየ ወእቀትለክሙ በሐፂን ወይከውና አንስቲያክሙ መበለታተ ወውሉድክሙ እጓለ ማውታ ።

፳፬ ወለእመ ለቃሕከ ብሩረ ለነዳየ ሕዝብከ ኢታጥቆ ወኢትትረደዮ ።

፳፭ ወለእመ አኀዝከ ልብሰ ቢጽከ ዘእንበለ ይዕርብ ፀሐይ አግብእ ሎቱ ።

፳፮ እስመ ይእቲ በሕቲታ ዐራዙ ወኀፍረት ሎቱ እስመ አልቦ በዘይበይት ፡ ወለእመ ገዐረ ኀቤየ ፍጡነ እሰምዖ ፡

ሉ ያኖረ ሰው ቢኖር ያም አደራ ያኖረበት ሰው ገንዘቡ ቢሰረቅበት ሌባውን ፈልጎ ቢያገኘው፡ ሌባው በአንድ ሁለት ይክፈል ።

ሌባው ተፈልጎ ባይገኝ ግን ባለ ገንዘቡ ከፈጣሪ ፊት (ቤተ እግዚአብሔር) ቀርቦ እንዳልተተነኰለና እንዳልቋጠረ ይማል ። ዘዳግ፡ ፳፬ ፲፥

በሆነው ነገር ሁሉ በአደራ ወግ በተመራመሩት ገንዘብ በግም ቢሆን አህያም ቢሆን በሬም ቢሆን ባለ አደራውንና ባለ ገንዘቡን ያቈጣጥርዋቸውና ያ የጠፋበት ባለ አደራው በአንድ ሁለት ዕጥፍ ይክፈል ።

በሬውን በጉንም ከከብቱም የሆነውን ለሌላው ያዋሰ ቢኖር ያ የተዋሰው ከብቱ ቈስሎ ቢሞት (ወራሪዎች) ማርከው ቢወስዱበት የሚያውቅለት (ምስክር) ባይኖር ፡ ባለ አደራው ገንዘቡን ወዶ እንዳልተተነኰለው በመካከላቸው እግዚአብሔር ያዘዘው መሐላ አለ (ተሠርቷል ቃሊል) ስለዚህ ባላደራው አይከፍልም ።

ሳይጠብቀው ቀርቶ ሌቦች ሰርቀው ቢወስዱበት አደራ የተቀመጠበት ሰው ለባለ አደራው ይክፈል ።

በምድረ በዳም አውሬ ቢይዝበት (ቢገድልበት ቢበላበት) መርቶ ወስዶ ወደቃኑን ያሳይ አይክፈል አይከፍልም።

ሰው ከባለንጀራው(ፈረስ በቅሎ አህያ)ቢዋስ ተሰብሮ ቢሞትበት ያዋሰው የገንዘቡ ባለቤት ባይኖር እሱ ይክፈል ።

የገንዘቡ ባለቤት ቢኖር ግን አይክፈል (አይከፍልም) ምንደኛው ቢሆን ደመወዙን ይክፈል (ይከፍላል)።

ያልታጨች ድንግሊቱን ልጅ ቢያስታት ከርሷም ጋር ቢተኛ (ቢደርስባት) ሚስት ትሁነው (ይውሰዳት)።

አባቷ ለርሱ አልሰጠውም ቢል ግን ድንግሊቱ ልጅ የምትታጭበትን ማጫ፡ ማጫዋን ለአባቷ ይስጥ ።

ከሚርተኛው ጋር አትጋቡ ።

ከእንስሳ (ከፈረስ ከበቅሎ ከአህያ) የሚደርስ ሰው ሁሉ (በድንጋይ ተወግሮ በእሳት ተቃጥሎ) ይሙት ።

ለእግዚአብሔር ብቻ እንጂ ለጣዖታት የሚሠዋ ሰው ተነቅሎ ይጥፋ ።

እናንተም በግብጽ አገር መጻተኞች ሁናችሁ ተጠቃችሁ ነበርና፡ መጻተኛውን አታስጨንቁት በመጻተኛውም ክፉ ሥራ አትሥሩበት ። ዘኍ፡ ፳፫ ፱ ።

እናት አባት በሌላቸው ደኻ አደጎችና ባልቴቶች ሁሉ ክፉ ሥራ አትሥሩባቸው ። ዘክ፡ ፯ ፲ ።

ክፉ ሥራ ሠርታችሁባቸው ወደኔ ቢጮሁ ጩኸታቸውን ፈጽሜ እሰማለሁ ። ኢሳ፡ ፩ ፲፯ ።

እኔም ተቈጥቼ በጦር አጠፋችኋለሁ እናንተም አልቃችሁ ሚስቶቻችሁ መበለቶች ይሆናሉ (ባልአልባ) ይቀራሉ ልጆቻችሁም ደኻ አደጎች ይሆናሉ ።

ለድኻ ወገንህ ብር ብታበድረው አስጨንቀህ አራጣ አታስከፍለው (አትቀበለው) ። ኢዮብ ፴፩ ፳፫ ።

የባልንጀራህን ልብስ መያዣ አድርገህ ብትይዝበት ለብሲት የሚያድር እሷ ብቻ ናትና ፀሐይ ሳይገባ መልስለት።

ለብሲት የሚያድር ሌላ ልብስ የለውምና ዕራቁቱን ብታሳድረው ኃፍረት ነው፡ ወደኔም ቢጮኽ ጩኸቱን ፈ

እስመ መሐሪ አነ ።
፳፯ አማልክተ ኢትሕሚ ፡ ወለመኰንነ ሕዝብከ ኢትበሎ እኪተ ።

፳፰ ከተማ ዐውድከ ወዓውደ ዐውድከ ኢታአኅር ወበኵረ ውሉድከ ትሁበኒ ሊተ ።

፳፱ ከማሁ ትገብር ሊተ ላሕምከ ወበግዕከ ወአድግከ ሰቡዐ ይንበር ኅበ እሙ ፡ ወአመ ሳምንት ዕለት ትሁበኒ ሊተ ።

፴ ወትከውኑኒ እደወ ቅዱሳነ ወሥጋ ገደላ አርዌ ኢትብልዑ ለከልብ ግድፍዎ ።

ምዕራፍ ፳፫

፩ ወስምዐ ዘሐሰት ኢትሰጠው ወኢትንበር ምስለ ዘይዔምፅ ከመ ኢትኩን ስምዐ በዐመፃ ።

፪ ወኢትደመር ምስለ ብዙኃ ለዐምፃ ወኢትትወሰክ ምስለ ብዙኃ ለገሚፀ ፍትሕ ።

፫ ወለነዳይ ኢትምሐሮ በፍትሕ ።

፬ ወለእመ ረከብከ ላሕመ ጸላኢከ ወእመሂ አድገ ሚጥ ወአግብእ ሎቱ ።
፭ ወለእመ ርኢከ አድገ ጸላኢከ ዘተኀየሎ ፆሩ ኢትትአደዎ አላ ተራድኦ ምስሌሁ ።
፮ ወኢትሚጥ ፍትሐ ለነዳይ በውስተ ፍትሕ ወኢተዐምፅ ።

፯ ወእምኵሉ ፍትሕ ዘዐመፃ ተገኃሥ ፡ ዘአልበ ጌጋይ ወጻድቀ ኢትቅትል ወኃጥአ ኢታድኅን ።

፰ ወሕልያነ ኢትንሣእ እስመ ሕልያን ያዐውሮሙ አዕይንቶሙ ለጠቢባን ወይመይጥ ቃለ ጽድቅ ።

፱ ወግዩራነ ኢትግፍዑ እስመ አንትሙ ግዩራነ ኮንክሙ በምድረ ግብጽ ።
፲ ስድስተ ክረምተ ዝራእ ገራህተከ ወአስተጋብእ እክለከ ።
፲፩ ወበሳብዕት ክረምት ኅድጋ ታዕርፍ ወይብልዖ ነዳየ ሕዝብከ ወዘተርፈ ይብልዖ አርዌ ዘገዳም ፡ ከመዝ ትገብር ዐፀደ ወይንከ ወዘይተከሂ ።

፲፪ ሰዱሰ ዕለተ ትግብር ኵሎ ግብረከ ወአመ ሳብዕት ዕለት ተዓርፍ ከመ ያዕርፍ ላሕምከ ወአድግከ ወከመ ያስተንፍስ ወልደ አመትከ ወግዩር ።

ጥኜ እሰማዋለሁ ፡ እኔ መሐሪ (ይቅር ባይ) ነኝና ።
ክህናትን ሹሞኞችን አትማ አትጥላ የወገንህንም አለቃ አትርገመው (ማለት በርሱ ዘመን መከራ ቢመጣብህ የእገሌ ዘመን ፡ ዘመን አይሁን ብለህ አትንቀፈው) ።
በዓውድማህ መከከል ያለ ጭልባውን በዓውድማህ ዙርያ ያለውን አትጥረገው ፡ የልጆችህንም በኵር በኵሩን ለኔ ትሰጠኛለህ ። ዘፍ፡ ፴፩ ፴፱ ።
የልጅህን በኵር እንደ ሰጠኸኝ የላምህን የበግህንና የአህያህንም በኵር ትሰጠኛለህ ፡ (ስጠኝ ስላልኩህም ዕለቱን ተወልዶ አይደለም) ሰባት ቀን (ሲጠባ) ከናቱ ጋር ይሰንብት ፡ በስምንተኛውም ቀን ለኔ ትሰጠኛለህ ።
(ይህን ብታደርጉ) የከበራችሁ ወገኖቼ ትሆናላችሁ ፡ አውሬ የቢጨረውንም ወደቃን ሥጋ ለውሻ ጣሉት እንጂ አትብሉት ። ዘዳ፡ ፲፭ ፲፱ ።

ምዕራፍ ፳፫

በሐሰት የተመሰከረውን ምስክርነት አትቀበል ፡ ሐሰተኛ ምስክርም እንዳትሆን ከሐሰተኛ ምስክር ከሐሰተኛ ዳኛ ጋር አትቀመጥ ። ምሳ፡ ፲ ፲፰ ።
ሐሰት ለመመስከር ሐሰት ለመፍረድ ከብዙ ሰዎች ጋር አንድ አትሁን ፡ ፍርድንም ለማድላት ለማጥመም ከብዙ ሰዎች ጋራ አትጨመር ። ፩ ነገ፡ ፲፱ ፲ ።
በፍርድም ጊዜ ደኃ ነው ብለህ ለደኃው አትዘንለት (አትራራለት) ። ዘሌ፡ ፲፱ ፲፭ ።
የጠላትህን በሬውን ወይም አህያውን ጠፍቶ ብታገኘው ፈጽመህ መልስለት ። ፩ ተሰ፡ ፭ ፲፭ ።
ሸክሙ ያጋደለበት የጠላትህን አህያ ብታይ አጫጭ ነው እንጂ አልፈኸው አትሂድ ከርሱ ጋር አንሳው እንጂ ።
ደኻውን ደኃ ነው ብለህ እውነቱን በሐሰት አትለውጥበት ፡ (አትለውጥለት) በፍርድም ጊዜ ፍርድን አታጣምም ። ኢዮብ ፴፩ ፲፫ ።
ከሐሰት ፍርድ ሁሉ ራቅ ፡ በደል የሌለበትንና ጻድቁን አትግደል ፡ (ይሙት በቃውን ይድን በቃ ይድን በቃውን ይሙት በቃ ብለህ አትፍረድ) ።
መማለጃን አትቀበል ፡ መማለጃ መቀበል የብልሆችን ዓይነ ልቡናቸውን ዕዉር ያደርገዋልና እውነተኛውንም ቃል ወደ ሐሰት ይለውጠዋል ።
እናንተም በግብጽ አገር መጻተኞች ነበራችሁና መጻተኞችን አትበድሏቸው ። መዝ፡ ፻፱ ፮ ።
ስድስት ዓመት በእርሻህ ዘርህን ዝራ ፡ በስድስቱ ዓመት የዘራኸው እኽልንም ሰብስብ ። ዘሌ፡ ፳፭ ፫ ።
በሰባተኛው ዓመት ግን እርሻይቱ ከመታረስ ከመቈፈር ታርፍ ዘንድ ተዋት ፡ የወገንህ ችግረኛ ይብላው ፡ ከዚያ የቀረውንም የምድረ በዳ አውሬ ይብላው የወይኑንና የዘይቱንም በታ እንዲሁ አድርግ ።
ስድስቱን ቀን ሥራህን ሁሉ ሥራ ፡ በሰባተኛው ቀን ግን በሬህም አህያህም የሴት ባርያ ልጅህም በንተ ዘንድ ተጠግቶ የሚኖር መጻተኛውም እፎይ ብሎ ዐርፎ ይውል ዘንድ አንተ ከእርሻ ከቁፋሮ ታርፋለህ (ዕረፍ) ።

| | | |
|---|---|---|
| ወኵሎ ዘነበብኩ ዕቀቡ፡ ወስሞሙ ለአማልክተ ባዕድ ኢትዝክሩ፤ ወኢትትናገሩ በአፉክሙ ። | ፲፫ | የተናገርሁትን ሁሉ ጠብቁ የሌሎች አማልክትን ስም አትጥሩ በአንደበታችሁም አትናገሩ ማለት ምስጋና አታቅርቡ ። ሆሴ ፪ ፲፯ ። |
| ሠለስተ ጊዜያተ በዓመት ግበሩ ሊተ በዓለ ። | ፲፬ | በአንድ ዓመት ውስጥ ሦስት ጊዜ በዓል አድርጉልኝ ። |
| ወዕቀቡ በዓለ ዘናዕት፡ ሰቡዐ ዕለተ ትበልዑ ናእተ በከመ አዘዝኩክሙ በወርኃ ሐዲስ እስመ ቦቱ ወፃእክሙ እምድረ ግብጽ፡ ወኢትትረአዩ በቅድሜየ ዕራቀክ ። | ፲፭ | ቂጣ የምትበሉበትን በዓል (ፋሲካ) ጠብቁት አክብሩት ከግብጽ አገር የወጣችሁበት ወር ነውና፡ በሚያዝያ ወር ቂጣውን በልታችሁ አክብሩ ብዬ እንዳዘዝኋችሁ ቂጣውን እየበላችሁ አክብሩት፡ በፊቴም ባዶ እጅህን አትታይ፡ ራቁትህን አትጣል ። |
| ወበዓለ ዘአመ ሀሢድ ዘቀዳሚ እክልከ ግበር በምግባርከ በውስተ ዘዘራእከ ገራህትከ፡ ወበዓለ ዘአስተጋብኦ አመ ይወጽእ ዓመት በጊዜ አስተጋብእከ ኵሎ ተግባረከ እምውስተ ገራህትከ ። | ፲፮ | መጀመሪያ የደረሰው እኽልህ በሚታጨድበት ጊዜ ዓመቱ ሳያልቅ በእርሻ ከተዘራው አዝመራ እሸት ነዶውን እያቀረብክ በዓለ ሰዊትን አክብር፡ ዛሬ የዘራኸውን አዝመራ በምትሰበስብበት ጊዜ የመከር ክታች በዓል ዳስ ጥለህ በዓለ መጸለትን አክብር ። ዘሌ፡ ፳፫ ፲ ። |
| ሠለስተ ጊዜያተ ይትረአይ ኵሉ ተባዕት በቅድሜየ አነ እግዚእ እግዚአብሔር ። | ፲፯ | ከዓመት ሦስት ጊዜ ወንድ ወንዱ ሁሉ በፊቴ (በእግዚአብሔር ለገቢረ በዓል እየወጣ) ይታይ፡ ይኸንንም ያዘዝኩህ እኔ ገዢህ እግዚአብሔር ነኝ ። |
| ወኢትሡዕ መሥዋዕትየ በብኁዕ ደም ወኢይቢት ስብሐ ዘበዓልየ እስከ ሣኒታ ። | ፲፰ | መሥዋዕቴንም በቦካ (በደረ) ደም አትሠዋው ለበዓሌ ተብሎ የቀረበውንም ስብ እስከ ነገ አይደር ። |
| ቀዳሚ ፍሬ ገራውሂከ ታበውእ ሊተ እምዚአከ፡ ወኢታብስል ማዕዋ በሐሊበ እሙ ። | ፲፱ | መጀመሪያ ከእርሻህ የተገኘውን የእኽሉን ቀዳምያት ከገንዘብህ አቅርብልኝ ወይፈኑንም በእናቱ ወተት አትቀቅለው ። ነህ፡ ፲ ፴፭፡ ምሳ፡ ፫ ፱ ። |
| ወናሁ እፌኑ መልአክየ ቅድመ ገጽከ ከመ ይዕቀብከ በፍኖትከ ወከመ ያብእከ ውስተ ምድር ዘአስተዳሎኩ ለከ ። | ፳ | በምትሄድበት ጐዳና ይጠብቅህ ዘንድ ወደ አዘጋጀሁልህም ምድር መርቶ ያገባህ ዘንድ እነሆ መላክተኛዬን እሰድልሃለሁ ። ኤፌ፡ ፬ ፴ ። |
| ዕቀብ ርእሰከ ስምዖ ወኢትእበዮ እስመ ኢየኀድገከ ወይሰመይ ስምየ በላዕሌሁ ። | ፳፩ | ራስህን ጠብቅ ሕጉንም ስማው (ተማረው) እምቢ አልሰማውም (አልማረውም) አትበል ስሜም በርሱ ይጠራ ዘንድ (በረድኤት) አልለይህምና ። ኤፌ፡ ፬ ፴ ። |
| ወለእመሰ ሰማዕከ ቃልየ ወሀቀብከ ኵሎ ዘእቤለከ እጸልእ ጸላኢከ ወእፃረሮ ለዘይፃረረከ ። | ፳፪ | ቃሌን ብትሰማ ያልኹህንም ነገር ሁሉ ብትጠብቅ ጠላትህን እጠላለሁ፡ የሚጻረረህንም እጻረረዋለሁ ። |
| ወየሐውር መልአክየ እንዘ ይመርሐከ ወያበውእከ ውስተ ምድረ አሞሬዎን ወኬጤዎን ወፌርዜዎን ወከናኔዎን ወጌርጌሴዎን ወኤዌዎን ወኢያቡሴዎን ወአጠፍኦሙ ። | ፳፫ | መላክተኛዬ (ሚካኤል፡ ሙሴ፡ ኢያሱ) መርቶ ወደ አሞሬዎን ወደ ኬጤዎን ወደ ፌርዜዎን ወደ ከናኔዎን ወደ ጌርጌሴዎን ወደ ኤዌዎንና ወደ ኢያቡሴዎን አገር ያገባሃል (እኔም ጠላቶችህን) አጠፋቸዋለሁ ። ኢያሱ ፳፬ ፰ ። |
| ወኢትስግድ ለአማልክቲሆሙ ወኢታምልኮሙ፡ ወኢትግበር ከመ ምግባሪሆሙ ነሢተ ንሥቶሙ ወቀጥቅጦ ቀጥቅጥ ምሥዋዒቲሆሙ ። | ፳፬ | ለአማልክቶቻቸው አትስገድ አታምልካቸውም እንደ ሥራቸውም አትሥራ ፈጽመህ አፍርሳቸው መሠውያቻቸውንም ቀጥቅጠህ አጥፋቸው ። |
| ወአምልክ እግዚአብሔርሃ ፈጣሪከ ወእባርክ ኅብስተከ ወወይነከ ወማየከ ወእሰስል ደዌ እምላዕሌከ ። | ፳፭ | ፈጣሪህ እግዚአብሔርን አምልክ (ይህን ያደረግህ እንደሆነ) እንጀራህን ወይንህንና ውኃህን እባርካለሁ (አበዛዋለሁ) ደዌህን ከንተ አርቃለሁ ። ዘፀ፡ ፳፰ ፫ ። |
| ወአልቦ መካን ዘኢይወልድ በውስተ ምድርከ ወኍልቈ መዋዕሊከ እፌጽም ለከ ። | ፳፮ | በአገርህም የማይወልድ መኻን የለም የዘመንህም ቍጥር (በተድላ በደስታ) እፈጽምልሃለሁ ። ኢዮ፡ ፳፩ ፲ ። |
| ወፍርሀተ እፌኑ ቦቱ ለዘይጸንዐከ ወይደነግፁ ኵሎሙ አሕዛብ ዘበእከ ኀቤሆሙ ወእሬሲ ኵሎ ፀረከ ከመ ይጕየዩከ ። | ፳፯ | በሚበረታብህም ላይ መፍራትን አመጣበታለሁ፡ (እንዲፈራህ አደርገዋለሁ)፡ የገባህባቸውም አሕዛብ ሁሉ ይደነግጣሉ ጠላቶችህም ፊርተው ከንተ እንዲሸሹ አደርጋለሁ ። |
| ወእፌኑ ዘያደነግፆሙ ቅድሜከ ለአሞሬዎን ወታወጽኦሙ ለኬጤዎን ወለኤዌዎን ወለከናኔዎን ። | ፳፰ | በፊትህም የአሞሬዎንን ሰዎች የሚያስደነግጣቸው ተርብን እሰድባቸዋለሁ፡ የኬጤዎንን የኤዌዎንን የከናኔዎንንም ሰዎች ታስወጣቸዋለህ ። |

፳፱ ወኢያወፅኦሙ በአሐቲ ዓመት ከመ ኢትኩን ምድር
ዓፀ ወከመ ኢይብዝኁ ላዕሌከ አራዊተ ገዳም ።
፴ በበንስቲት አወፅኦሙ እምኔከ እስከ ትትባዛኃ ወት
ወርሳ ለምድር ።
፴፩ ወአሰፍሕ አድዋሊከ እምባሕረ ኤርትራ እስከ ፍልስ
ጥኤም ወእምገዳም እስከ ፈለግ ዐቢይ ፈለገ ኤፍራጥስ
ወእሜጡ ውስተ እዴከ እለ ይነብሩ ውስተ ምድር ወአወ
ፅኦሙ እምኔከ ።

፴፪ ወኢታኅድሮሙ ወለአማልክቲሆሙ ኢትትአዘዝ ።

፴፫ ወኢይንበሩ ውስተ ምድርከ ከመ ኢይግበሩከ ተአ
ብስ ወለእመ አምለከ አማልክቲሆሙ እሙንቱ ይከውኑከ
ዕቅፍተ ።

ምዕራፍ ፳፬ ።

፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ዕርግ አንተ ወአሮን
ወናዳብ ወአብዩድ ወመላህቅተ ሕዝብ ሰብዓ እምእስራኤል
ወይስግዱ ሊተ እምርኁቅ ።

፪ ወቅረብ አንተ በሕቲትከ ወእሙንቱሰ ኢይቅረቡ
ወሕዝብሂ ኢይዕርጉ ምስሌሆሙ ።
፫ ወቦአ ሙሴ ወአይድዖ ለሕዝብ ኵሎ ቃለ እግዚአብ
ሔር ወጽድቆ ወአውሥኡ ኵሉ ሕዝብ በአሐዱ ቃል ወይ
ቤሉ ኵሎ ቃለ ዘነበበ እግዚአብሔር ንገብር ወንሰምዕ ።

፬ ወጸሐፈ ሙሴ ኵሎ ቃለ እግዚአብሔር ወተንሥአ
በጽባሕ ወሐነጸ ምሥዋዐ ታሕተ ደብር በ፲ወ፪ አእባን
በኍልቈ ፲ወ፪ ሕዝበ እስራኤል ።

፭ ወፈነወ ወራዙቶሙ ለውሉደ እስራኤል ወአዕረጉ
መሥዋዕተ መድኃኒት ለእግዚአብሔር አልሕምተ ።

፮ ወነሥአ ሙሴ መንፈቀ ደሙ ወአንበረ ውስተ መቅ
ለድ ፡ ወመንፈቀ ደሙ ከዐወ ላዕለ መሥዋዕት ።
፯ ወነሥአ ሙሴ መጽሐፈ ሕግ ወአንበበ በዕዝነ ሕዝብ
ወይቤሉ ኵሎ ዘነበበ እግዚአብሔር ንገብር ወንሰምዕ ።

፰ ወነሥአ ሙሴ ደመ ወነዝኃ ላዕለ ሕዝብ ወይቤ ናሁ
ደመ ሕግ ዘሐገገ ለክሙ እግዚአብሔር በእንተ ኵሉ
ዝ ቃል ።
፱ ወዐርጉ ሙሴ ወአሮን ወናዳብ ወአብዩድ ወሰብዓ
ሊቃናተ እስራኤል ።
፲ ወርእዩ መካነ ኀበ ይቀውም እግዚአብሔር አምላከ
እስራኤል ወዘታሕተ እግሩ ከመ ግብረተ ግንፋል ዘሰንፔር
ወከመ ርእየተ ጽንዐ ሰማይ ሶበ ሐወጸት ።

፲፩ ወኅሩያኒሆሙ ለእስራኤል ዘአልቦ ዘይመስሎሙ አስ
ተርአዩ በመካን ዘእግዚአብሔር ፡ ወበልዑ ወሰትዩ ።

ነገር ግን ምድሪቱ ምድረ በዳ እንዳትሆን የምድረ በዳ
አራዊትም እንዳይበዙብህ በአንድ ዓመት አላወጣቸውም ።
እንተም እስክትበዛና ምድሪቱንም እስክትወርሳት
ጥቂት ጥቂት እያልኹ አስወጥቼ እሰዳቸዋለሁ ።
ድንበርህንም ከኤርትራ ባሕር እስከ ፍልስጥኤም ከም
ድረ በዳም ፡ እስከ ታላቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ድረስ
አሰፋልሀአለሁ (አቀናል'ኻለሁ) ፡ በምድር (በከነዓን) የሚ
ኖሩትንም በእጅህ እጥላለሁ (እንዲገዙልህ አደርጋለሁ)
(ላንተ የማይገዙትን ግን) ከንተ አስወጥቼ እሰዳቸዋለሁ ።
(የከነዓንን ሰዎች ካንተ ጋር) አታኑራቸው ለጣዖቶቻ
ቸውም አትታዘዝ ፡ (ለነሱ አሠዋለሁ አትበል) ።
(ፈጣሪህን) እንድትበድል እንዳያደርጉህም በአገርህ
አይኑሩ ፡ አማልክቶቻቸውን ብታመልክ ዕንቅፋት ይሆኑ
ብኻልና (ከፈጣሪህ ይለዩ'ኻል) ።

ምዕራፍ ፳፬ ።

እግዚአብሔር ሙሴን አንተና አሮን ናዳብና አብዩድ ፤
ከእስራኤል ተለይተው በሕዝቡ የተሾሙ ሰባ ሊቃውን
ትም (ወደ ደብረ ሲና) ውጡ ፡ ከሩቅ ሁነውም ይስገዱ
ልኝ አለው ። ዘፀ ፡ ፳፰ ፩ ፡ ዘሌ ፡ ፲ ፩ - ፪ ።
አንተ ብቻህን ቅረብ ፡ እነሱ ግን አይቅረቡ ፡ ሕዝቡም
ከነሱ ጋር አይውጡ ።
ሙሴም ሕዝቡ ወዳሉበት ገብቶ የእግዚአብሔርን እው
ነተኛ ቃል ለሕዝቡ ነገራቸው ፡ ሕዝቡም ሁሉ በአንድ ድ
ምፅ እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል ሁሉ ሰምተን እና
ደርጋለን አሉ ።
ሙሴም የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉ ጻፈ ፡ ማለዳም
ተነሥቶ በዓሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ወገኖች ልክ አሥ
ራ ሁለት ደንጊያዎችን አንሥቶ ከተራራው ሥር መሠው
ያን ሠራ (ጸፈጸፈ) ። ዘፀ ፡ ፴፩ ፱ ።
(ሙሴም) የእስራኤልን ጐበዞች ሰደዳቸው (እነሱም)
ከመከራ የሚድኑበት መሥዋዕት አድርገው ላሞቹን
ለእግዚአብሔር አቀረቡ ።
ሙሴም የደሙን እኩሌታ ወስዶ በብርት ውስጥ አኖ
ረው ፡ የደሙንም እኩሌታ በመሥዋዕቱ ዙርያ አፈሰሰው ።
ሙሴ ሕጉ የሚነገርበትን መጽሐፍ ወስዶ ሕዝቡ እየ
ሰሙ አነበበላቸው ፡ ሕዝቡም እግዚአብሔር የተናገረውን
ሁሉ ሰምተን እናደርጋለን አሉ ።
ሙሴ በብርት ያኖረውን ደም ወስዶ በሕዝቡ ላይ ረጨ
ው (ሰምተን እናደርጋለን ስላላችሁት ቃል) እግዚአብሔር
ሕግ አድርጎ የሠራላችሁ ደሙ ይህ ነው አለ ።
ሙሴ አሮን ናዳብ አብዩድና ሰብዓ የእስራኤል ሊቃ
ናት (ወደ ደብረ ሲና) ወጡ ።
ወጥተውም የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር በቆመበት
ከእግሩ በታች ባለው በታ ሰንፔር እንደሚባል ዕንቍ ጡብ
ያለ ሥራ የጸናችም ሰማይ በበራች ጊዜ እንደሚታይ ያለ
ብርሃን አዩ ። ዘፍ ፡ ፴፪ ፴ ፡ ኢሳ ፮ ፩ ፭ ።
የሚመስላቸው የሌለ ከእስራኤል የተመረጡ ጐበዞች
እግዚአብሔር በተገለጸበት በታ (በደብረ ሲና) ታዩ ፡ (ተገ

፲፪ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ዕርግ ኀቤየ ውስተ ደብር ወሀሉ ዝየ ወእሁበከ ሰሌዳተ ዘእብን ዘሕግ ወትእዛዝ ዘጸሐፍኩ ወትሕግግ ሎሙ።

፲፫ ወይቤሎሙ ሙሴ ለሊቃናት ሕዝብ ኢትትዋቀሱ እስከ ንሠወጥ ኀቤክሙ፤ ወናሁ አሮን ወሆር ምስሌክሙ ወለእመቦ ዘቦ ነገር ይሑር ኀቤሆሙ።

፲፬ ወተንሥኡ ሙሴ ወኢያሱ ወዓርጉ ውስተ ደብረ እግዚአብሔር ወሠወረ ደብሮ ደመና።

፲፮ ወወረደ ግርማ ለእግዚአብሔር ውስተ ደብረ ሲና ወሠወሮ ደመና ሰዱሰ ዕለተ፤ ወበሳብዕት ዕለት ጸውዖ እግዚአብሔር ለሙሴ እማእከለ ደመና።

፲፯ ወአስተርአየ ግርማ ለእግዚአብሔር ከመ ነደ እሳት ዐቢ ያንበለብል ዲበ ክተማሁ ለደብር በቅድሜሆሙ ለውሉደ እስራኤል።

፲፰ ወቦአ ሙሴ ማእከለ ደመና ወዐርገ ውስተ ደብር፤ ወነበረ አርባዐ መዓልተ ወአርባዐ ሌሊተ።

ምዕራፍ ፳፭።

፩ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ በሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ንሥኡ ሊተ እምጥሪትክሙ መባእ ዘሐሰይክሙ በልብክሙ።

፪ ወዝንቱ ውእቱ መባእ ዘትነሥኡ እምኔሆሙ ወርቀ ወብሩረ ወብርተ።

፫ ወያክንተ ወኅብረ ከብድ ወለየ ክዑበ ወቢሦሰ ክዑበ ወፀጕረ ጠሊ።

፬ ወማእሰ በግዕ ሕሡየ ወማእሰኒ ዘሥርየቱ ኅብረ ያክንት ወዕፀ ዘኢይነቅዝ።

፭ ወቅብእ ለማኅቶት፤ ወአፈዋተ ለተቀብእ፤ ወዕጣነ ለማዕጠንት።

፮ ወእእባነ መረግድ ወእእባነ ዘይትጌረው ለኤፉድ ወለሎግዮ።

፯ ወትገብር ሊተ መቅደሰ ወአኀድር በማእከሎሙ።

፰ ወትገብር ሊተ ኵሎ ዘአነ አርእየከ በውስተ ደብር አርአያ ደብተራ ወአርአያ ንዋያ ለደብተራ፤ ወኵሎ ከማሁ ትገብር።

፱ ወግበር ታቦተ ዘመርጡል እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ዘክዕበ እመት፤ ወመንፈቀ እመት ኑኁ፤ እመት ወመንፈቀ እመት ራኅቡ፤ እመት ወመንፈቀ እመት ቆሙ።

፲ ወትቀፍላ ወርቀ ንጹሐ እምውሣጤሃኒ ወእምአፍአሃኒ ትቀፍላ፤ ወግበር ላዕሌሃ ቀጸላ ወርቅ ዘየዐውዳ።

ለጹ) ተረፈ መሥዋዕቱንም በሉ ጠጡም።

እግዚአብሔር ሙሴን ወደኔ ወደ ተራራው ውጣ፤ በዚህም ሰንብት አንተ ሥርዓት አድርገህ ትሠራላቸው ዘንድ እኔ የጻፍኩት (ዘጠኙ ቃላትና ኢታምልክ) ያለበት ሁለቱን የዕንቍ ጽላቶች እሰጥሃለሁ አለው።

ሙሴም በሕዝቡ የተሾሙ አለቆችን (እኔና ኢያሱ ደብረ ሲና ደርሰን) እስክንመለስ ድረስ አትጣሉ፤ ነገር ያለው ሰው ቢኖር እነሆ አሮንና ሆር ከናንተ ጋር አሉ፤ ወደነርሱ ይሂድ (እነሱ ይፍረዱባችሁ ይፍረዱላችሁ) አላቸው። ዘፀ፡ ፴፫ ፲፩።

ሙሴና ኢያሱ ተነሥተው ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወጡ፤ ተራራውንም ደመና ሸፈነው።

የእግዚአብሔርም ብርሃኑ ወደ ደብረ ሲና ወርዶ ተራራውን ስድስት ቀን ሸፈነው፤ በሰባተኛውም ቀን እግዚአብሔር ከደመናው ማኸል ሁኖ ሙሴን ጠራው።

እሳት በነደደ ጊዜ ከሩቅ እንዲታይ በእስራኤል ልጆች ፊት በተራራው ራስ ላይ የእግዚአብሔር ብርሃኑ እንደ እሳት ሁኖ ፊት ለፊት ይታያቸው ነበር።

ሙሴም ወደ ደብረ ሲና ወጥቶ ከደመናው ውስጥ ገባ፤ ገብቶም አርባ ቀን አርባ ሌሊት ቈየ (ሰነበተ)።

ምዕራፍ ፳፭።

እግዚአብሔር ሙሴን የእስራኤልን ልጆች ከገንዘባቸሁ በልቡናቸሁ ያሰባችሁልኝ መባውን አቅርቡልኝ ብሏል ብለህ ንገራቸው ብሎ ተናገረው።

ከገንዘባችሁ ለይታችሁ የምታመጡልኝም መባው ይህ ነው፤ ወርቁን ብሩን ብርቱን (ናሱን) ነው።

(ያክንተ) ሰማያዊ ሀር፤ (ኅብረ ከብድ) ብጫ (ለየ ክዑበ) ቀይ ሐር፤ (ወቢሦሰ ክዑበ) ዕጽፍ ሁኖ የተሠራ ነጭ ሐር (ፀጕረ ጠሊ) ማእሰ መጸጺት ነው።

(ማእሰ በግዕ ሕሡየ) የለፋ የአውራ በግ ቍርበት፤ (ወማእሰኒ ዘሥርየቱ ኅብረ ያክንት) ሰማያዊ ኅብረ ቀለም የገባ የማይነቅዝ ዕንጨት (ሽምሽር ሰጢን)።

ለመብራት የሚሆን ዘይቱን ለመቀባት የሚሆኑ ሽቶዎችን፤ ለማጠን ዕጣኖችን።

መረግድ የሚባሉ አዕናቍን፤ (ለኤፉድ) ለልብሰ እንግድዓ (ለሎግዮ) ለልብሰ መትከፍ የሚሆኑ የፈርጥ አዕናቍን አምጡ በላቸው።

የምመስገንበት (ደብተራ ኦሪትን) ሥራልኝ፤ እኔም (በረድኤት) አድሬባቸው እኖራለሁ። ዘፀ፡ ፳፰ ፲፩።

በደብረ ሲና እኔ የማሳይህ የደብተራ ብርሃንን ሥራ አምሳል የደብተራ ብርሃንን የዕቃዋን ሥራ አምሳል ሁሉንም እንዲሁ እንዳሳየሁህ ሥራ አለው።

ክንድ ከስንዝር ቁመቷ፤ ክንድ ከስንዝር ወርዱ፤ ሁለት ክንድ ከስንዝር አቈልቋይዋ የሚሆን ሽምሽር ሰጢን የሚባል የማይነቅዘውን ዕንጨት ቈርጠህ (ዘመርጡል) የሕግ ታቦትን ሥራልኝ። ዘሌ፡ ፬ ፯፤ ዕብ፡ ፫ ፮።

ከውስጧ ጀምረህ እስከ ውጭዋ ድረስ በጸራ ወርቅ ለብጣት በዙርያዋም የወርቅ ክንፈር (አክሊል ሥራላት)።

| | | |
|---|---|---|
| ወትዘብጥ ዕበነ አርባዕ ዘወርቅ ወታነብር ላዕለ አርባዕቱ ምስማከቲሃ፤ ዕበነ ክልኤቱ ውስተ ምስማክ አሐዱ፤ ወዕበነ ክልኤቱ ውስተ ዳግም ምስማክ ። | ፲፩ | የወርቁን አራቱን ቀለበት መትተህ በአራት እግሮቿ አኑር፤ ከዚህም ከአራቱ ሁለቱን በአንድ ወገን ሁለቱን በአንድ ወገን አኑረው ። |
| ወግበር ላቲ መፃውሪሃ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ወትቀፍሎሙ ወርቀ ። | ፲፪ | መሎጊያዎቿን (መሸከሚያዎቿን) ሽምሸር ሰጢን ከሚባል ከማይነቅዝ ዕንጨት ሥራላት እነዚህንም በወርቅ ለብጣቸው ። |
| ወታበውእ መፃውሪሃ ውስተ ውእቶን ዕበን አርባዕ ዘዲበ ምስማክ ዘታቦት መሰከሚሃ ለታቦት በዘይሰከምዋ በሙ ። | ፲፫ | መሸከሚያዎቿንም በሚሸከሙበቸው ገንዘብ ከታቦቷቱ በላይ በአራቱ መዓዝን ወዳሉ ወደ አራቱ ቀለበቶች አግባ ። |
| ወአዕበን ዘዲበ ታቦት ለይኩኑ ድንበዘቲሃ በዘይትዋደዱ ወዘኢያንቀለቅሉ ። | ፲፬ | በታቦቷቱ ላይ በራቱ መዓዝን ባሉ ባራቱ ቀለበቶች (ሌዋውያን) በሚሸከምዋት ገንዘብ የታቦቷቱ ድንበዛት (መሸከሚያዎች) ወለቅ ወለቅ የማይሉ ከላይ እስከታች የተስማሙ ይሁኑ ። |
| ወግበር ላቲ ተድባበ ዘወርቅ ንጹሕ ዘክዕበ እመት ወመንፈቀ እመት፤ ኑኁ እመት ወመንፈቀ እመት ራኅቡ ። | ፲፭ | አቈልቋዩ ሁለት ክንድ ከስንዝር፤ ቁመቱ ክንድ ወርዱ ክንድ የሆነ የጸሩ ወርቅ መግጠሚያ ለታቦቷቱ ሥራላት፤ (እንደ አጎበር ያለ ነው) ። ፩ ነገ፡ ፰ ፰ ። |
| ወግበር ላቲ ክልኤተ ኪሩቤነ ዘወርቅ ፍሑቅ ወትገብሮሙ እምክልኤቱ ምስማከቲሁ ለተድባብ ። | ፲፮ | ሁለቱንም ኪሩቤል ከለዘበ ከጸሩ ወርቅ ሥራላት፤ ሁለቱንም በመግጠሚያው ላይ ከሁለት ወገን አድርጋቸው። |
| ወይትገበር አሐዱ ኪሩብ እምጽንፈ አሐዱ ምስማክ፤ ወአሐዱ ኪሩብ እምጽንፈ ካልእ ምስማክ ። | ፲፯ | አንዱ ኪሩብ በአንድ ወገን፤ አንዱም ኪሩብ በአንድ ወገን በመግጠሚያው ላይ ይቀረጹ ። |
| ወግበር ክልኤሆሙ ኪሩበነ ላዕለ ክልኤሆሙ ምስማካት ። | ፲፰ | ሁለቱንም ኪሩቤል በሁለቱ መግጠሚያዎች ላይ አድርጋቸው (ቅረጻቸው) ። |
| ወይኩኑ ኪሩባን እንዘ ይረብቡ ክነፊሆሙ እመልዕልተ ተድባብ ወገጾሙ ይትናጸሩ በበይናቲሆሙ ወኀበ ተድባብ ይኩን ገጾሙ ለኪሩባን ። | ፲፱ | ኪሩቤልም ከላይ ክንፎቻቸውን ዘርግተው ከታቦቷቱ በላይ ያለ መግጠሚያውን ሸፍነው የኪሩቤል ፊታቸው ወደ መግጠሚያው ዞሮ (እንደሚናከሱ ዶሮዎች) እርስ በርሳቸው ፊት ለፊት የሚተያዩ ይሁኑ ። |
| ወታነብር ተድባበ ዲበ ታቦት መልዕልቴሃ፤ ወውስተ ታቦት ትወዲ ትእዛዘ ዘአነ እሁበከ ። | ፳ | መግጠሚያውንም በታቦቷቱ ላይ አኑረው፤ ከዚህ በኋላ እኔ የሰጠሁህን ትእዛዝ ዓሠርቱ ቃላት የተጻፉባቸው ሁለቱን ጽላቶች በታቦቷቱ ውስጥ አኑር ። |
| ወእትኤመር ለከ በህየ ወእትናገረከ እምላዕለ ተድባብ ማእከለ ክልኤቱ ኪሩባን እለ ሀለዉ ዲበ ታቦት ዘመርጡል ኵሎ ትእዛዘ ዘእኤዝዘከ ኀበ ውሉደ እስራኤል ። | ፳፩ | እኔም በዚያ ሁኜ እገለጽልሃለሁ፤ ለእስራኤል ልጆች ብዬ እኔ የማዝህን ትእዛዝ ሁሉ በታቦቷቱ ላይ ባሉ በሁለቱ ኪሩቤል መካከል ባለ በመግጠሚያው ላይ ሁኜ እነጋገርሃለሁ ። ዘፀ፡ ፳፯ ፴፩፡ ፵ ፳ ። |
| ወግበር ማእደ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ኑኁ ክዕበ እመት፤ ወራኅቡ እመት፤ ወቆሙ እመት ወመንፈቀ እመት ። | ፳፪ | ከማይነቅዝ ዕንጨት ቈርጠህ ማእድን ሥራ፤ ይኸውም አቈልቋዩ ሁለት ክንድ ወርዱ ክንድ ቁመቱ ክንድ ከስንዝር ነው ። ዘሌ፡ ፲፯ ፪፡ ሕዝ፡ ፱ ፫ ። |
| ወትቀፍሎ ወርቀ ንጹሐ ወግበር ሎቱ ቀጸላ በዓውዱ ወግበር ግብረ ማዕበል ዘወርቅ ። | ፳፫ | በጸሩ ወርቅ ለብጠው በክፈፉ ዙርያም ክንፈር አውጣለት፤ የማይረጋ ወርቅም አድርግበት ። |
| ወግበር ክንፈረ መጠነ አርባዕቱ አፃብዕ በዓውዱ ። | ፳፬ | በዙርያውም አንድ ጋት የሚያህል ክፈፍ አድርግለት። |
| ወግበር አርባዕተ አውቃፋተ ዘወርቅ ወአንብር ውስተ አርባዕቱ መዓዝኒሁ ለማእድ ። | ፳፭ | አራት የወርቅ አምባር ሠርተህ በማእድ ከራት እግሩ በላይ ባለ ክንፈሩ በአራቱ መዓዝኖች አኑረው። |
| ወይኩኑ አውቃፋት መንገለ ክንፈሩ ለማእድ ። | ፳፮ | አምባሮቹ በማእዱ ክንፈር ላይ ይሁኑ ። |
| ወይኩኑ አውቃፋቲሁ አብያተ ለመፃውሪሁ ዘያነሥኡ ማእደ ። | ፳፯ | በማእዱ ክንፈሮች አምባሮችም ማእድን ለሚያነሡ መሸከሚያዎች ቤት ይሁኑ ። |
| ወግበር መፃውሪሁ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ወትቀፍሎሙ ንጹሐ ወርቀ ወበሙ ይትገኀሥ ማእዱ ። | ፳፰ | መሸከሚያውንም ሽምሽር ሰጢን ከሚባል ከማይነቅዝ ዕንጨት ሥራ መሸከሚያዎቹንም በጸሩ ወርቅ ለብጣቸው ማእዱም በነሱ ይነሣ ። |
| ወግበር አጽሕልቲሁ ወመጸብሒሁ ወመዳምሂሁ ወመዋጽሂሁ በዘበቱ ታወጽሕ እምንጹሕ ወርቅ ግበሮሙ ። | ፳፱ | (መጸብሕ) ታላቅ ሥልስ ወጭት (አጽሕልት) ታናሽ ሥልስ ወጭት (መዳምህ) ማንኪያ (መዋጽሕ) ማፍሰሻ ዘይቱን |

በምታፈስበት ገንዘብ ጽዋዎቹንም ከጸሩ ወርቅ ሥራቸው።

፴ ወአንብር ኅብስተ ዲበ ማእድ በቅድሜየ ዘልፈ ።

ኅብስቱንም ዘወትር ጧት ማታ በፊቴ አኑር (ሠዋው)።

፴፩ ወግበር ተቅዋመ ማኅቶት እምወርቅ ንጹሕ ፍሕቆ ለተቅዋመ ማኅቶት ዓምዳ ወአብራዒሃ ወመአኃዚሃ፡ ወከበበ ርእሳ ወጽጌያቲሃ እምኔሃ ይትገበሩ ።

ከጸሩ ከለዘበ ወርቅ ፋናው የሚቀመጥበት መቅረዝንም ሥራ፡ ፋናው ለሚቀመጥበትም መቅረዝ ዓምዱ፡ (አብራዕ) ግራ ቀኝ ያሉ አጽቆቿ መአኃዝ ሽቦዎቿ (ከበበ ርእስ) መግለጫቷ አበባዎችዋ ከዚ የማይለዩ ሥረ-ወጽ ሁነው ይሠሩ ። ዘሌዋ፡ ፳፬ ፩ ።

፴፪ ወስድስቱ አብራዕ እለ ይትገበራ በገቦሃ ለተቅዋመ ማኅቶት ሠለስ አብራዕ እምአሐዱ ፍናሃ፡ ወሠለስ አብራዕ እምፍናሃ ካልእ ።

ፋናው በሚያበራበት ተቅዋም በጐኗ የተሠሩ አጽቆች ስድስት ናቸው፡ (እነዚህም) ሦስቱ አጽቆች በአንድ ወገን ሦስቱ አጽቆች በአንድ ወገን ናቸው ።

፴፫ ወሠለስቱ መአኃዚሁ እለ የኀብሩ ምሳሌ በአሐዱ ከበበ ርእስ ጽጉይ ከማሁ ለሰብዓቲሆሙ አብራዕ እለ ይወፅኡ እምተቅዋመ ማኅቶት ።

ሦስቱ ሽቦዎች በሥራ የተባበሩ ናቸው፡ ለአንዱ መግለጫ አበባ እንዳለው መብራቱ ከሚበራበት ከተቅዋም ሥረ-ወጽ ሁነው ለተሠሩ ስድስቱ መግለጫች እንዲሁ አበባ አላቸው ። ዘፀ፡ ፴፯ ፲፯-፲፱፡ ዘኍ፡ ፰ ፬ ።

፴፬ ወለተቅዋመ ማኅቶት መአኃዚሃ አርባዕቱ ወጽጌያቲሃ፤

መብራቱ የሚበራበት የተቅዋም ሽቦዎቿ አራት ናቸው፡ አበባዎቿም ከዚያው ሥረ-ወጽ ናቸው ።

፴፭ ወከበብ መትሕተ ክልኤቱ አብራዕ ለሰብዓቱሂ አብራዕ እለ ይወፅኡ እምተቅዋመ ማኅቶት ።

ፋናው ከሚበራበት ከተቅዋም ሥረ-ወጽ ሁነው በተሠሩ ከሁለቱ አጽቆች በታች ሦስት መሸቢያዎች (ሽቦዎች) አሉ ።

፴፮ ከበቢቲሆሙ ወአብራዒሆሙ እምኔሃ ይኩኑ ኵሎሙ ፍሕቅ እምአሐዱ ወርቅ ንጹሕ ።

መግለጫቻቸውና አጽቆቻቸው ከዚ የማይለዩ ሥረ ወጽ ይሁኑ፡ እነዚህም ሁሉ ከንድ ከጸሩ ከለዘበ ወርቅ ይሁኑ ።

፴፯ ወትገብር መኀትዊሃ ሰብዓቱ ወያብርሀ እምአሐዱ ገጽ።

ምንባረ ፈትሏን ሰባት ሰባት አድርገው (ይኸውም) ከሥረ ወጹ ሌላ ሦስቱ በፊት፡ ሦስቱ በኋላ ሁኖ ያብራ ።

፴፰ ወዘእምድኅሬሃ ወበዘያሜንዋ ወጽዋዓቲሃ ዘወርቅ መክሊተ ወርቅ ትገብራ ።

ፈትሉን የሚስቡበት ወለባው የሚኰስትሩበት መቀሉ ዘይቱን የሚቀዱበት ጽዋው ከጸሩ ከለዘበ ወርቅ የተሠራ ይሁን ።

፴፱ ወአላንተ ኵሎን ንዋያቲሃ ግበር በአርአያ ዘከመ አርአይኩከ በደብር ።

እነዚህንም ዕቃዎቿ ሁሉ በደብረ ሲና እንዳሳየሁህ አድርገህ ሥራ ። ዘኍ፡ ፰ ፬፡ ፩ ዜና መዋ፡ ፳፰ ፲፩ ።

## ምዕራፍ ፳፮ ።

፩ ወለደብተራ ግበር ላቲ ዐሠርተ አዕፃደ እምቢሶስ ፅፁፍ፡ ወእምኅብረ ያክንት ወእምኅብረ ክብድ፡ ወለይ ከዐብ ወኪሩቤነ ግበሩ፡ ወበግብረ ምእናም ትገብርዎ ።

ለደብተራ ኦሪት ዕጽፍ ሁኖ ከተሠራ ከነጭ ሐርና ከሰማያዊ ሐር ከብጫና ዕፅፍ ሁኖ ከተሠራ ከቀይ ሐር አሥር ፈርጅ ሥራላት (ከሊህም ከአራቱ ኅብር) ኪሩቤልን ሥራቸው፡ (ስትሠሩትም) በግብረ መርፌ ሥራ ሥሩት ።

፪ ወኑኁ ለአሐዱ ዓፀድ ዕሥራ ወሰመንቱ በእመት፡ ወራኅቡ አርባዕቱ በእመት፡ ለአሐዱ ዐፀድ በመስፈርቱ ከማሁ ለይኩኑ ።

የአንዱ ፈርጅ አቁልቋዩ ሃያ ስምንት ክንድ ነው፡ ወርዱም አራት ክንድ ነው፡ የመጋረጃዎቹም (ፈርጆች) ሁሉ መጠን ልክ እንደዚሁ ይሁን ።

፫ ወኀምስቱ አዕፃድ ይሳመኩ በበናቲሆሙ ።

አምስቱም ፈርጆች አንድ ወገን ሁነው አንዱ ከንዱ ጋር እርስ በርሳቸው ይገናኙ (ይጋጠሙ)።

፬ ወግበር ኵሎ ኀምሳ መግስጠ ዘኅብረ ያክንት ላዕለ ከንፈረ አሐዱ ዓፀድ እምአፍአሃ ።

እርስ በርሳቸው ከንፈር ለከንፈር ይገናኙ ዘንድ በአንድ ፈርጅ ከንፈር በጫፉ ከሰማያዊ ሐር የተሠራ አምሳ ተበት ቀለፍ (ቀለበት) አድርግ ። ኤፌ፡ ፬ ፲፫ ።

፭ ወኀምሳ መግስጠ ግበር በጽንፈ ካልእ ዐፀድ፡ እምገጸ አፍአ ገጾሙ እንዘ ይሳመኩ በበይናቲሆሙ ።

በሁለተኛው ፈርጅ ከንፈር በጫፉ ከሰማያዊ ሐር የተሠራ ፊታቸው እርስ በርሳቸው እንዲገናኙ ሆነው አምሳ ተበት ቀለፍ ሥራ ።

፮ ወግበር ኃምሳ ኖኅዳተ ዘወርቅ ወደምር አዕኑዳተ አሐዱ ምስለ ካልኡ በኖኅዳት ወይኩኑ አሐደ ደብተራ ።

አምሳ የወርቅ ቀለበቶችን ሥራ፡ ፈርጆቹንም አንዱ ከንዱ ጋር በቀለበቶቹ አገናኝ ድንኳኑም (በቀለበት) አንድ ይሁን ። ዘፀ፡ ፴፮ ፲፬ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወግበር ዐሠርተ ወአሐደ አዕፃደ ዘሠቅ ዘይከድኖ እምላዕሉ ለደብተራ ። | ፯ | ድንኳኑን ከላይ እስከ ታች የሚሸፍነው የብስጥ አሥራ አንድ ፈርጅ ሥራ ። |
| ወለለአሐዱ አሐዱ ሠቅ ኑኑ ሠላሳ በእመት ወራኅቡ ርብዕ በእመት ፡ ከመዝ አምጣኒሆሙ ለዐሠርቱ ወአሐዱ ። | ፰ | እያንዳንዱም የብስጥ ፈርጅ አቈልቋዩ ሠላሳ ክንድ የወርዱም ስፋት አራት ክንድ የአሥራ አንዱም ፈርጆች መጠናቸው (ልካቸው) እንደዚሁ ነው ። |
| ወደምር ኃምስተ ሠቃተ በበይናቲሆሙ ወሰብዓተ ሠቃተ ደምር በበይናቲሆሙ ፡ ወተዓፅፍ ሰብዓተ ሠቃተ መንገለ ገጸ ደብተራ ዐሡርተ ። | ፱ | አምስቱን ፈርጅ ብስጥ እርስ በርሳቸው (በቀለበት) አንድ አድርጋቸው ሰባቱ ፈርጅ ብስጥም እርስ በርሳቸው እንዲገናኙ አድርግ ፡ ሰባተኛውም ፈርጅ መጋረጃ በድንኳኑ ፊት ይደረብ ። |
| ወግበር ኃምሰ መማስጠ ላዕለ ከንፈረ አሐዱ ሠቅ ፡ ወኃምሰ መማስጠ ግበር ውስተ ከንፈረ ሠቅ ካልእ በዘተደምር ቀዳማዊ ። | ፲ | አሥሩን ፈርጅ አንድ እንዳደረግኸው በአንድ ብስጥ ፈርጅ ከንፈር ላይ አምሳ ተባት ቍልፍ በሁለተኛውም ብስጥ ፈርጅ ከንፈር ላይ አምሳ ተባት ቍልፍ ሥራ ። |
| ወግበር ኃምሳ ኆፃዳተ ዘብርት ፡ ወትዴምር መማስጠ በኆፃዳት ፡ ወታኀብር ሠቃተ ወይከውኑ አሐደ ። | ፲፩ | ከዚህም አምሳ የብርት (የናስ) እንስት ቍልፍ ሥራ ፡ ተባት ቍልፉንም በእንስት ቍልፍ አገጣጥመው አምስቱንም ብስጥ ፈርጅና ስድስቱን ፈርጅ ብስጥም በተባት ቍልፍና በእንስት ቍልፍ አንድ አድርገው ሁሉም በቀለበት አንድ ይሁኑ ። |
| ወታነብር ዘይፈደፍድ እምሠቅ ዲበ ደብተራ ዘተርፈ ወትከድን ከዋላ ደብተራ ። | ፲፪ | ከብስጥ የተረፈውን ከአራት ኅብር የበለጠውን በአራት ኅብር ላይ አልብሰው ስታለብስም በፊት በኋላ አልብሰው ። |
| እመተ ዘይተርፍ ሠቃተ ደብተራ እምገዳሚሃ ለደብተራ እምለፌ ወእምለፌ ይከድኖ ። | ፲፫ | የምታለብሰው ከክበር ቤት እስከ ደጃፉ ከግራ እስከ ቀኝ ያለውን ዓምድ ከድንኳኑ ብስጥ የተረፈው ክንድ ሙሉ ይሸፍነው ። ዘፀ ፡ ፴፮ ፲፱ ፡ ዘኍ ፡ ፳፬ ፭ ። |
| ወአግብር ማእሰ በግዕ ሕሡየ ዘሥርየቱ ኅብረ ያክንት ዘይከድኖ ለሠቅ ። | ፲፬ | ብስጡንም ከላይ ጀምሮ እስከ ታች ድረስ የሚሸፍነው ተለፍቶ ቀለም የገባ የበግ ማእሰ መጸጺትን ሥራ ። |
| ወአግብር አዕማደ ለደብተራ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ፡ ዘዐሥራ በእመት ቆሙ ለአሐዱ ዓምድ ፡ ወራኅቡ እመት ወመንፈቀ እመት ። | ፲፭ | ሸምሸር ሰጢን ከሚባል ከማይነቅዝ ዕንጨት ለድንኳኑ ዓምዶችን ሥራለት ፡ ይኸውም የአንዱ ዓምድ ቍመቱ ሃያ ክንድ ፡ ወርዱ ክንድ ከስንዝር ይሁን ። |
| ወመሰምክተ ሥረዊሁ ክልኤቱ ለአሐዱ ዓምድ እንዘ ይሰመክ ዓምድ ለዓምድ ፡ ከማሁ ግበር ለኵሉ ዓምደ ደብተራ ። | ፲፮ | (ከመ ይሰመክ) ዓምድ ከዓምድ ጋር ተጠጋግቶ ይቆም ዘንድ አንድ ዓምድ የሚቆምበት ምዕማዱ ሁለት ይሁኑ ፡ ለያንዳንዱም የድንኳን ዓምድ እንዲህ አድርገህ ሥራለት ። |
| ወአግብር ዕሥራ አዕማደ መንገለ አዜብ ። | ፲፯ | ሃያውን አዕማድ በአዜብ በኩል እንዲቆሙ አድርገህ ሥራቸው ። |
| ወግበር ሎሙ ምዕማደ ዘብሩር አርበዐ ለዕሥራ አዕማድ ክልኤቱ ምዕማዱ ፡ ለአሐዱ ዓምድ ለክልኤሆሙ ገጸቲሁ ። | ፲፰ | ለሃያው ዓምዶች አርባ የብር ምዕማድ ሥራላቸው ፡ ለአንዱ ዓምድ በሁለት ጥፍሮቹ የሚቆምባቸው ሁለት ምዕማድ ይሁኑ ። ዘፀ ፡ ፴፰ ፳፯ ። |
| ወካልእ እምገጸ ሰሜን ዕሥራ አዕማደ ። | ፲፱ | ሁለተኛ በሰሜን በኩል ሃያ አዕማድ ይቁሙ ። |
| ወምዕማዶሙ ዘይበውኡ አዕማደ አርበዐ ዘብሩር ለለ አሐዱ ዓምድ ክልኤቱ ምእማዱ እምክልኤሆሙ ገጸቲሁ ፡ | ፳ | አዕማዱን የሚሸከሙ አርባ የብር አዕማድ ይሁኑ ፡ እያንዳንዱም ዓምድ የሚቆምባቸው ምዕማዶች ሁለት ሁለት ናቸው ። |
| ወእምድኅር እምገጸ ደብተራ መንገለ ባሕር ግበር ሰብዓተ አዕማደ ። | ፳፩ | ለድንኳኑ በስተፊት በምዕራብ በኩል የሚቆሙ ስድስት ዓምዶችን ሥራ ። |
| ወክልኤተ አዕማደ ግበር ዓዲ ለመዓዝነ ደብተራ እምድኅር ። | ፳፪ | ዳግመኛ በስተኋላ ለድንኳኑ መዓዝን ማቅኛ የሚሆኑ ሁለት ዓምዶችን ሥራ ። |
| ዕሩያነ ይኩኑ ወይድረጉ ፍጹመ እምታሕቱ እስከ ላዕሉ ፡ ወከማሁ ግበር ለክልኤሆሙ መዓዝን ። | ፳፫ | ዓምዶቹም ትክክል ይሁኑ ፡ እነዚህም ከላይ ጀምሮ እስከ ታች ድረስ አንድ ይሁኑ ፡ እንዲሁም ለሁለቱ መዓዝኖች ማቅኛ መሰብሰቢያ ሁለት ሁለት ምዕማድ ሥራላቸው ። |
| ወይኩኑ አዕማድ ሰመንተ ፡ ወምዕማዲሆሙ ዘብሩር ዐሠርቱ ወሰብዐቱ ። | ፳፬ | ስምንት አዕማድ ይሁኑ ፡ ከብር የተሠሩ ምዕማዶቻቸውም አሥራ ሰባት ይሁኑ ። |

፳፬ ወለለአሐዱ ዓምድ ክልኤቱ ክልኤቱ ምዕማዱ እምክልኤሆሙ ገጸቲሁ።

የያንዳንዱም ዓምድ ምዕማድ በሁለት ጥፍሩ የሚቆምበቸው ሁለት ሁለት ይሁን።

፳፭ ወግበር መናሥግተ ለአዕማደ ደብተራ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ።

ለደብተራ አሪት ሸምሸር ሰጢን ከሚባል ከማይነቅዝ ዕንጨት ማገሮችን ሥራላቸው። ዘፀ፥ ፴፮ ፴፩።

፳፮ ሐምስቱ መናሥግት እምአሐዱ ገጽ፤ ወሐምስቱ መናሥግት ዘመንገለ ባሕር።

አምስቱንም ማገሮች በአንድ ወገን በሰሜን አድርግ አምስቱንም ማገሮች በአንድ ወገን ማለት በምዕራብ በኩል አድርግ።

፳፯ ወግበር ለመንሥግ ዘማእከል ይዕዱ በማእከለ አዕማድ እምጽንፍ ኀበ ጽንፍ።

ሰማገሩም ከዳር እስከ ዳር ድረስ በዓምዶቹ መከከል ውስጥ ለውስጥ እንዲያልፍ አድርግለት፤ (እንደ ሸማኔ መወርወሪያ)።

፳፰ ወለለአዕማድኒ ወለመናሥግት ቅፍሎሙ ወርቀ ወግበር አውቃፋተ ዘወርቅ ዘይከውኑ አብያተ ለመናሥግት።

ዓምዶቹንም ማገሮቹንም ወርቅ ለብጣቸው፤ ለማገር ቤቶች የሚሆኑ የወርቅ አፃ ባሮችንም ሥራ።

፳፱ ወግበር ለደብተራ በአርአያ ዘአርአይኩከ በደብር።

ደብተራይቱንም በደብረ ሲና እንዳሳየሁህ አምሳል አድርገህ ሥራ።

፴ ወግበር ላቲ መንጦላዕተ ዘኅብረ ያክንት ወኅብረ ከብድ ወለይ ክዑብ ወቢሦስ ፍትል ወግበር በግብረ ምእናም ኪሩቤን።

መጋረጃውንም ከሰማያዊ፤ ከሐምራዊ ዕጽፍ ሁኖ ከተሠራ ቀይ ሐርና ከተፈተለ ከጥሩ በፍታ አድርግ፤ ኪሩቤልንም በግብረ መርፌ ጠልፈህ ሥራ፤ (ኪሩቤልን አስመስለህ ሥራ)። ዘፀ፥ ፳፰ ፱፤ ግብ፥ ሐዋ፥ ፯ ፵፬።

፴፩ ወግበር አርባዕተ አዕማደ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ወቅፍሎሙ ወርቀ ወአርእስቲሆሙ ወርቅ ወግበር ሎሙ አርባዕተ ምዕማደ ዘብሩር።

ሸምሸር ሰጢን ከሚባል ከማይነቅዝ ዕንጨት ቈርጠህ አራቱን አዕማድ ሥራ፤ ወርቅንም ለብጣቸው ክባሶቻቸውም ወርቅ ይሁን፤ አራት የብር አዕማድንም ሥራላቸው።

፴፪ ወአንብር መንጦላዕተ ዲበ አዕማድ ወአብእ ውስተ ውሣጢሁ ለመንጦላዕት ታቦተ ዘመርጡል፤ ወይፍልጥ መንጦላዕት ውሣጢተ ወቀሰፋዩ ቤተ መቅደስ።

መጋረጃውን በአዕማድ ላይ አድርገው፤ ሕጉ ሥርዓቱ የሚጸናበት ታቦቲቱንም ከመጋረጃው ውስጥ አግበት መጋረጃውም የቤተ መቅደስ አፍአውንና ውስጡን የሚለይ ይሁን። ዘኁ፥ ፫ ፴፩፤ ኢያ፥ ፬ ፲፩።

፴፫ ወይሜውር መንጦላዕት ታቦተ ዘመርጡል በቅድስተ ቅዱሳን።

መጋረጃውም በቅድስተ ቅዱሳን ሁኖ ሕጉ ሥርዓቱ የሚጸናበት ታቦቲቱን ይጋርዳት።

፴፬ ወአንብር ለማእድ እምአፍአሁ ለመንጦላዕት መንገለ መስዕ ወለተቅዋም አንብራ አንጻረ ማእድ በገጸ ደብተራ መንገለ አዜብ።

ገበታውን ማእዱን ከመጋረጃው ውጭ በመስዕ በኩል አኑረው መቅረዙንም በገበታው ፊት ለፊት በአዜብ በኩል አኑራት። ዘፀ፥ ፵ ፳፪፤ ዕብ፥ ፱ ፪።

፴፭ ወግበር ብዕ መንጦላዕተ ዘይከድና ለኆኅተ ደብተራ እምያክንት ወኅብረ ከብድ ወለይ ክዑብ፤ ወቢሦስ ክዑብ በብዑድ ግብረት።

ከሰማያዊና ከሐምራዊ ሐር፤ ከቀይና ከብጫ ሐር፤ በጥልፍ አሠራር የተሠራ የደብተራ ኦሪትን ደጃፍ የሚጋርዳት መጋረጃ ሥራላት። ዘፀ፥ ፴፮ ፴፯።

፴፮ ወግበር ለመንጦላዕት ሐምስተ አዕማደ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ወቅፍሎሙ ወርቀ፤ ወአርእስቲሆሙኒ ወርቅ፤ ወግበር ሎሙ ሐምስተ አዕማደ ዘብርት።

ለመጋረጃውም ከማይነቅዝ ዕንጨት ቈርጠህ አምስት ምሰሶዎች አድርገህ ወርቅ ለብጣቸው፤ ኵላቦቻቸውም (ክባሶቻቸውም) ወርቅ ይሁን አምስት የብርት ምዕማድንም ሥራላቸው።

## ምዕራፍ ፳፯።

፩ ወእግብር ምሥዋዐ ዘመሥዋዕት እምዕፅ ዘኢይነቅዝ፤ ዘሐምስቱ በእመት ኑኁ፤ ወሐምስቱ በእመት ራኅቡ፤ ርቡዐ ለይኩን፤ ወሥልሰ በእመት ይኩን ቆሙ።

ርዝመቱ አምስት ክንድ፤ ወርዱ አምስት ክንድ የሚሆን ከማይነቅዝ ዕንጨት መሥዋዕት የሚሠዋበትን መሠውያ ሥራ ይኸውም አራት ገጽ ሁኖ ምዕዙን ይሁን ቁመቱም ሦስት ክንድ ይሁን። ሕዝ፥ ፵፫ ፲፫።

፪ ወግበር ሎቱ አቅርንተ ዲበ አርባዕቱ መዓዝኒሁ፤ ወእምኔሁ ይፃኡ አቅርንቲሁ ወቅፍሎ ብርተ።

በአራት መዓዝኑም ላይ ቀንዶችን አውጣለት ቀንዶቹም ከሱ የማይለዩ ሥረወዕ ይሁኑ ከብርትም ለብጠው።

፫ ወግበር ሎቱ ቀጸላ፤ ወግበር ንዋያተ ለምሥዋዕ፤ ምግኅሣተ ወጸሐራተ ወፍያላተ ወመኖስሰ ሥጋ፤ ወመሳውደ እሳት፤ ወኵሎ ግበር እምብርት።

በዙርያውም ክንፈር አውጣለት ለመሠውያውም ዕቃዎችን ሥራለት፤ አመዱን የሚያፍሱበት የብርት እንቅብ ደም የሚቀበሉበት የብርት እንሥራ፤ ጣሳዎች ሦስት ጨሳን ያለው የሥጋ መውጊያ፤ እሳቱን የሚጭሩበት

፬ ወእግብር መጥበስቶ ለምሥዋዕ ስቅሱቀ ከመ መሥገርተ ዓሣ ዘብርት ፡ ወእግብር ሎቱ ለመጥበስት አርባዕተ ኅልቀታተ ዘብርት ፡ ውስተ አርባዕቱ መዓዝኒሁ ።

፭ ወአንብሮ ለመጥበስት በቤተ መሥዋዕት ታሕተ ፡ ወይኩን በመንፈቀ ቤተ መሥዋዕት ።

፮ ወግበር አርባዕተ አውቃፋተ ዘብርት በአርባዕቱ መዓዝኒሁ ፡ ከመ ይኩኑ አብያተ ለመግውሪሁ ።

፯ ወግበር መግውርተ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ለቤተ ምሥዋዕ ፡ ወቅፍሎሙ ብርተ ።

፰ ወአብእ መግውሪሁ ውስተ አውቃፋት ዘላዕለ ገበዋተ ምሥዋዕ ከመ ያንሥኡ በሙ ።

፱ ወፍሉገ ይኩን ሰሌዳሁ በከመ አርአይኩከ በደብር ከማሁ ግበር ።

፲ ወግበር ላቲ ዓፀደ ለደብተራ መንገለ አዜብ እንተ የማን ወመንጦላዕቱ ለዓፀድ እምቢሶስ ዕፁፍ ወኑኁ ምእት በእመት እምአሐዱ ምስማክ ።

፲፩ ወአዕማዲሁ ዕሥራ ፡ ወምዕማዲሆሙ ዕሥራ ዘበርት ወሞዓዳቲሆሙ ወጥንፈሆሙ ለአዕማድ ዘብሩር ።

፲፪ ከመዝ ግበር ለምስማክ ዘመንገለ ሰሜን ወመንጦላዕቱ ምእት በእመት ኑኁ ፡ ወአዕማዲሁ ዕሥራ ዘብሩር ፡ ወምዕማዲሆሙ ዕሥራ ዘብርት ፡ ወሞዓዳቲሆሙ ፡ ወጥንፈሆሙ ለአዕማድ ዘብሩር ።

፲፫ ወለራኅበ ዓፀድ ዘገጸ ባሕር መንጦላዕቱ ሐምሳ በእመት ፡ ወአዕማዲሁ ዐሠርቱ ወምዕማዲሆሙ ዓሠርቱ ።

፲፬ ወዐሠርቱ ወሐምስቱ በእመት ኑኁ ለመንጦላዕት እምገጹ አሐዱ ምስማክ ፡ ወአዕማዲሁ ሠለስቱ ፡ ወምዕማዲሆሙ ሠለስቱ ።

፲፭ ወእምክልኡ ምስማክ ዐሠርቱ ወሐምስቱ በእመት ኑኁ ለመንጦላዕት ፡ አዕማዲሁ ሠለስቱ ፡ ወምዕማዲሆሙ ሠለስቱ ።

፲፮ ወለአንቀጸ ዐፀድ መንጦላዕት ዕሥራ በእመት ኑኁ ዘያክንት ወኅብረ ክብድ ወለይ ክዑብ ወቢሶስ ክዑብ ፡ ወብዑደ ይኩን በግብረ መርፍእ ፡ አዕማዲሁ አርባዕቱ ፡ ወምዕማዲሆሙ አርባዕቱ ።

፲፯ ወኵሉ አዕማድ ዓፀድ ዘዓውዱ ይትቀፈሉ ብሩረ ፡ ወአርእስቲሆሙኒ ብሩር ፡ ወምዕማዲሆሙኒ ብርት ።

፲፰ ወኑኁ ለዓፀድ ምእት በእመት ፡ ወራኅቡ ሐምሳ በእመት ፡ ወቆሙ ሐምሳ በእመት ፡ እምቢሶስ ክዑብ ፡ ወምዕማዲሆሙ ብርት ።

፲፱ ወኵሉ ንዋየ ደብተራ በኵሉ ግብሩ ፡ ወመታግሪሁ ወመታክሊሁ ፡ ወመታክለ ዓፀዱ ብርት ።

፳ ወአንተ አዝዞሙ ለደቂቀ እስራኤል ይንሥኡ ቅብዐ

መጫሪያዎችን ይህን ሁሉ ዕቃ ከብርት (ከናስ) ሥራው ።

የብርት የሚሆን የመሠውያውንም መጥበሻ እንደ ዓሣ መረብ የተበሳሳ አድርገህ ሥራው ፡ ለመጥበሻውም በአራት መዓዝኑ ከብርት የተሠራ አራት ቀለበት ሥራለት።

መጥበሻውንም ከመሠውያው ውስጥ በታች አድርገው እሱም በመሠውያው ቤት ውስጥ እኩሌታ ይንጠልጠል።

ለመሸከሚያዎቹ ማንሻ ቤት እንዲሆኑ በአራቱ መዓዝን ከብርት የሚሠሩ አራት አምባሮችን ሥራ ።

ለምሥዋዑ መሸከሚያዎች ከማይነቅዝ ዕንጨት ቈርጠህ መሸከሚያዎችን መሎጊያዎችን ሠርተህ ብርት ለብጠጣቸው ። ዘኁ ፩ ፲፩ ፡ ኢሳ ፶፪ ፲፩ ።

ምሥዋዑን ያነሡባቸው ዘንድ ከምሥዋዑ ጐኖች በላይ ባሉ ቀለበቶች መሎጊያዎቹን አግባ ።

በጐኑም ፈለግ (ፈሳሽ) አውጣለት ፡ በደብረ ሲና እንዳሳየሁህ እንዲሁ አድርግ ።

ምሥራቅ ቀኝዋ በሚሆን በአዜብ በኩል ለደብተራ ኦሪት የሸማ አጥር መጋረጃ ሥራላት ፡ የሸማውም አጥር ዕጽፍ ሁኖ ከተሠራ ከነጭና ከብጫ ሐር የተሠራ የተፈተለ ይሁን ፡ አቈልቋዩም በአንድ ወገን መቶ ክንድ ይሁን።

የብርት የሚሆኑ ምዕማዶች ሃያ ፡ አዕማዶቹም ሃያ ናቸው ፡ የምሰሶዎቹም ቀለበቶችና ዘንጎች የብር ናቸው ።

በአዜብ በኩል እንደ ሠራኸው ፡ በሰሜንም በኩል እንደዚያው የሸማ አጥር መጋረጃ ሥራለት ፡ የሸማውም አጥር አቈልቋዩ መቶ ክንድ ይሁን ፡ የብር የሆኑ ዓምዶቹም ሃያ ናቸው ።

በስተምዕራብ ያለ የሸማው አጥር ስፋት አምሳ ክንድ ነው ፡ አዕማዱም አሥር ናቸው ፡ ምዕማዶቻቸውም እግሮቻቸውም ዓሥር ናቸው ። ዘዐ ፴፱ ፯ ፡ ዘኁ ፯ ፲፫ ።

በአንድ ወገን ያለው የመጋረጃው አቈልቋዩ አሥራ አምስት ክንድ ነው ፡ አዕማዱም ሦስት ናቸው ፡ ምዕማዶቻቸውም ሦስት ናቸው ።

በሁለተኛው ወገን ያለው የመጋረጃው አቈልቋዩ አሥራ አምስት ክንድ ነው ፡ አዕማዱና ምዕማዶቻቸውም ሦስት ሦስት ናቸው ።

በስተ መግቢያው ያለው ከሰማያዊ ሐር ዕጽፍ ሁኖ የተሠራ የመጋረጃው አቈልቋዩ ሃያ ክንድ ሁኖ በልዩ ግብረ መርፌ የተሠራ ይሁን አዕማዱና ምዕማዶቻቸውም አራት አራት ናቸው ፡ ዘሌዋ ፳ ፳ ።

በዙርያው ያሉ የሸማው አጥር ምሰሶዎች ሁሉ ብር ይለበጡ ፡ ክበሶቻቸውም የብር ናቸው ፡ ምዕማዳቸውም ብርት ይሁን ።

ዕጽፍ ሁኖ ከተፈተለ ከነጭና ከብጫ ሐር የተሠራው የሸማው አጥር (መጋረጃው) ወደላይ ቍመቱ አምስ ክንድ ነው ፡ የአዕማዱም ምዕማድ የብርት ነው ።

የደብተራ ኦሪት ዕቃ ሁሉ በሚሠራበት ሥራ ሁሉ (መታግሪሁ) ቍልፉ (መታክል) ካስማው ብርት ይሁን ፡ የአደባባዩ ካስማውም የናስ ይሁን ።

አንተም መብራቱን ያበሩ ዘንድ ለመብራት መጀመ

ዘይት ዘቀዳሚ ቅስመታ ንጹሐ ወውጉአ፡ ለብርሃን ከመ ያኅትዉ ማኅቶተ በውስተ ደብተራ እፍአ እመንጦላዕት ዘቅድመ ትእዛዝ ።

፳፩ ወያኅትዉ አሮን ወደቂቁ እምሠርክ እስከ ነግህ፡ ቅድመ እግዚአብሔር ሕግ ለዝሉፉ ለትውልዶሙ፡ እምደቂቀ እስራኤል ።

ምዕራፍ ፳፰ ።

፩ ወአቅርብ ኀቤከ ለአሮን እኁከ ወለደቂቁ ምስሌሁ እም ደቂቀ እስራኤል ከመ ይሡዑ ሊተ አሮን ወናዳብ ወአብዩድ ወአልአዛር ወይታምር ።

፪ ወግበር አራዘ ቅዱሰ ለአሮን ለክብር ወለሡራኄ ።

፫ ወአንተ አይድዖ ለኵሉ ጠቢበ ልብ ዘመላእኩ ላዕሌሆሙ መንፈሰ ጥበብ ወእሙንቱ ይግበሩ አራዘ ቅዱሰ ለቤተ መቅደስ፡ በዘቦቱ ይቄድሱ ኪያየ ።

፬ ወእሉ አልባስ ዘይገብሩ ኤፉድ ወሎግዮ፡ ወጵዴሬ ወቢሶስ ዘቍጽሮ ወአክሊል ወድርማንቅ ዘሐጺ ወቅናታት፤

፭ ወእሙንቱ ይንሥኡ ወርቀ ወያክንተ ወኅብረ ከብድ፡ ወለየ ክዑበ ወቢሶሰ ።

፮ ወይግበሩ ኤፉደ እምወርቅ፡ ወያክንት ወኅብረ ከብድ ወለይ ወቢሶስ ፍቱል በግብረ መርፍእ፡ ወግብሩ ግብረ ምእናም ብዑድ ።

፯ ወክልኤተ ይኩና መታክፊሁ እለ ይትላጸቃ በበይናን አሐቲ ዲበ አሐቲ እምክልኤሆን ገጸ ግብረቶን ።

፰ ወእንመተ ትብልያሁ ዘላዕሌሁ እምግብረቶን ድሙራተ ይኩና ዘወርቅ ወያክንት፡ ወኅብረ ከብድ ወለይ ክዑብ፡ ወቢሶስ ክዑብ ።

፱ ወንሣእ ክልኤተ አእባነ መረግድ ወግልፍ ላዕሌሆሙ አስማተ ደቂቀ እስራኤል ።

፲ ስድስተ አስማተ ላዕለ አሐዱ እብን፡ ወስድስተ አስማተ ላዕለ አሐዱ እብን በበአዝማዲሆሙ ።

፲፩ ወግበር ግብረ ዘኪን ኅርወተ ዓይነ ማኅተም፡ ወበክልኤቱ አእባን ዘላዕሌሆሙ አስማተ ደቂቀ እስራኤል ።

፲፪ ሙእኃዘ ወርቅ ትንበር በዓውዶሙ ወታነብሮሙ ለክልኤቱ አእባን ላዕለ መትከፈ ኤፉድ፡ ተዝካረ በእንቲአሆሙ ።

፲፫ ወይንሥእ አሮን አስማቲሆሙ በቅድመ እግዚአብሔር ላዕለ ክልኤቱ መታክፍቲሁ ለአዘክሮቶሙ፡ ወግበር አራዊተ ምድር እምወርቅ ንጹሕ ።

ረያ የተቀዳውንና መላልሶ የተጠራውን ዘይቱን ያመጡ ዘንድ የእሥራኤልን ልጆች እዘዛቸው፡ ይህም ትእዛዝ በሚጠበቅበት በአሥሪቱ ክንድ እንጻር ከመጋረጃው ውጭ ይሁን ።

፳፩ ይኸውንም ልጆቹና አሮን ከማታ ጀምሮ እስከ ጧት ድረስ በእግዚአብሔር ፊት ሲያበሩ ይኑሩ፡ ይኸውም ከእስራኤል ለሚወለዱ ሰዎች ለዘለዓለሙ ሥርዓት ይሁን ። ዘሌዋ፡ ፳፬ ፪ ።

ምዕራፍ ፳፰ ።

፩ ከእስራኤል ልጆች ለይተህ ወንድምህ አሮንን ከልጆቹ ጋር ወደ አንተ አቅርበው አሮንና ልጆቹ አብዩድ ናዳብ አልአዛርና ይታምር ይሠውልኝ ዘንድ ።

፪ ለክብር ለጌጽ እንዲሆን ለወንድምህ ለአሮን የከበረ ልብስ ቀሚስ አሠራለት ። ዘኍ፡ ፰ ፳፮

፫ የጥበብን ሀብት ላሳደርኩባቸው ዕውቀት ላላቸው ሁሉ አንተ ንገር፡ እነሱም (ካህናቱ) ለቤተ መቅደስ መገልገያ ሊሆን እኔን የሚያመሰግኑበትን የተለየ ልብስ ይሥሩ።

፬ የሚሠሩባቸውም ልብሶች እሊህ ናቸው፤ (ኤፉድ) ልብሰ መትከፍ (ሎግዮ) የደረት ልብስ (ጵዴሬ) እጅ ሰፊ ቀሚስ፡ (ወቢሶስ ዘቍጽሮ) ከነጭ ሐር የተሠራ እጀጠባብ አክሊል ኩፌት ወገባቸውን የሚታጠቁበት ልባልብ ዝናር።

፭ እነሱም ወርቁን ሰማያዊውን ሐር ዕጽፍ ሁኖ የተሠራ የተፈተለ ቀይ ሐር ብጫ ሐር (ከእስራኤል ይውሰዱ) ።

፮ ከወርቅ ከሰማያዊ ሐር፡ ከብጫ ሐር፡ ከሐምራዊ ሐር ዕጽፍ ሁኖ ከተሠራ ቀይ ሐር ከተፈተለ ከነጭ ሐር ከዚህ ከራቱ ኅብር ግምጃ ጋር ወርቁን በጥልፍ እያስማሙ የጫንቃውን ልብስ በግብረ መርፌ ሥራ ይሥሩ፡ የዚህም ሁሉ ሥራው በተለየ በግብረ መርፌ ሥራ ይሁን ።

፯ በጫንቃው የሚለብሳቸው የኤፉድ ፊርጆች አሠራራቸው ሁለት ወገን ሁኖ አንዲቱ ከአንዲቱ ጋር እርስ በርሳቸው የተጋጠሙ ሁለት ይሁኑ ። ዘፀ፡ ፴፱ ፬ ።

፰ ሥራቸውም ከወርቅ ከሰማያዊ ሐር ከሐምራዊ ሐር፡ ዕጽፍ ሁኖ ከተሠራ ብጫ ሐር፡ ዕጽፍ ሁኖ ከተፈተለ ቀይ ሐር የሚሆን (በአሮን) ጫንቃ ላይ ያሉ የኤፉድ ሥራዎች በጫንቃው ላይ የተገናኙ ይሁኑ ።

፱ የመረግድ ዕንቍ አምጥተህ የአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ስም በላያቸው ላይ ቅረጽበት ።

፲ ስድስቱን ስሞች በአንድ ዕንቍ፡ ስድስቱን ስሞች በአንድ ዕንቍ፡ በየወገናቸው ቅረጽ ።

፲፩ የእስራኤልን ልጆች አስማት በተጻፈባቸው በሁለቱ እዕናቍ ዙርያ ዕንቍን የሚይዝ የወርቅ ቀለበት አበጅለት በዕንቍ ላይ የሚጻፈውም የስማቸውን አቀራረጽ እንደ ማኅተም አቀራረጽ አድርገህ በጥበብ ሥራ ።

፲፪ ሁለቱንም ዕንቆች ለእስራኤል መታሰቢያ ሊሆኑ በልብሰ መትከፍ በኤፉድ ላይ በሐር ጠልፈህ አያይዛቸው ።

፲፫ አሮንም የአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ስም የተጻፈባቸው እዕናቍ ያሉበትን ኤፉድን እስራኤልን በእግዚአብሔር ፊት ለማሳሰብ በሁለት ጫንቃዎቹ ላይ ለብሶ ይግባ ።

፲፬ ወአግብር ክልኤተ ሰናስለ እምወርቅ ንጹሕ ድሙረ ፡ ግብረ ጽፉረ ወአንብር ሰናስለ ዲበ አራዊተ ምድር ።

ለሁለቱም እበቦች እንደ ቋድ ሥራ የተታታ አድርገህ ከጸሩ ወርቅ ሁለት የወርቅ ሰንሰሎቶች አሠራ ፡ ሁለቱንም የወርቅ ሰንሰለቶች በሁለቱ የወርቅ እበቦች ላይ አኑር ።

፲፭ ወግበር ሎግዮ ዘፍትሕ በግብረ ምእናም ፡ በሐሳበ ኤፉድ ግበር በወርቅ ወበያክንት ወበኅብረ ከበድ ወለይ ከዐብ ወቢሶስ ከዐብ ።

ከዚህም በኋላ ኢታምልክ የሚጠበቅበት በግብረ መርፌ ሥራ የተሠራ ልብሰ እንግድዓ ሥራ ፡ ወርዱንም ቁመቱንም በኤፉድ ልክ አድርገህ ከአራቱ ኅብር አምስተኛ ወርቅ ሥራው ። ዘሌዋ፡ ፰ ፰ ፡ ኢሳ፡ ፶፱ ፲፯ ።

፲፮ ወትገብሮ ርቡዐ ወውጡሐ ወይኩን ዓጽፍ ዘእመት ኑኁ ፡ ወእመት ራኅቡ ።

ይህንም በአራት ወገን ምዕዙን አድርገህ የተነፋ አድርገው ልብሰነቱም አቄልቋዩ ክንድ ወርዱም ክንድ ይሁን።

፲፯ ወአንብር ላዕሌሁ አእባነ በአርባዕቱ ፆታ ፡ አሐዱ ፆታ ዘእብን ይትገበር ዘሰርድዮን ወዘጳዝዮን ወዘመረግድ ።

እነዚህንም ዕንቆች በሎግዮ ላይ በአራት ወገን አኑራቸው ፡ ከዕንቊ የተሠራ አንድ ወገን ሰርድዮን ፡ ጳዝዮን መረግድ ከሚባል ዕንቊ ነው ።

፲፰ ወክልእ ፆታ ዘእብን ከመ ፍሕም ወሰንፔር ወኢያሰጲድ ።

የሁለተኛውም ወገን የዕንቊ ስም ፍሕም ፡ ሰንፔር ፡ ኢያሰጲድ የሚባል ሦስት ዕንቊ ነው ።

፲፱ ወሣልስ ፆታ ዘለግርዮን ወአከጥስ ፡ ወአሜቴስጢኖስ ።

ሦስተኛውም ወገን ለግርዮን አካጥስ አሜቴስጢኖስ የሚባል ሦስት ዕንቊ ነው ።

፳ ወራብዕ ፆታ በእብን ዘኅብረ ወርቅ ወቢረሌ ፡ ወሦም ወይኩን ልቡጠ በወርቅ ፡ ወእሱረ በወርቅ በበፆታሁ ።

በዕንቊ የተሠራ አራተኛውም ወገን ኅብረ ወርቅ ቢረሌ ሦም የሚባል ሦስት ዕንቊ ነው ፡ ይኸውም በየወገን በየወገኑ በወርቅ የተለበጠ በወርቅ የታሰረ ይሁን ።

፳፩ ወእእባኒሁ ይትገበሩ በአስማቲሆሙ ለዐሥርቱ ወክልኤቱ ሕዝበ እስራኤል ፡ ወይትገለፉ ከመ ግልፈተ ዓይነ ማኅተም ለለስሞሙ ለዐሥርቱ ወክልኤቱ ሕዝበ እስራኤል ፤

ዕንቆቹም በአሥራ ሁለት የእስራኤል ልጆች ስሞች ይሠሩ እንደ ማኅተም መልክ አቀራረጽ ሁነው ለአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል በየስማቸው ይቀረጹ ።

፳፪ ወግበር ሰናስለ ለሎግዮ ዘጽፍሮ ወጽፍርሁኒ ከመ ዘርዚቅ ዘወርቅ ንጹሕ ።

ለተጐነጐነው ሎግዮም የወርቅ ሰንሰለት ሥራለት ፡ ከጸሩ ወርቅ የተሠራው ሰንሰለትም (ከመ ዘርዚቅ) እንደ ዓሣ መረብ የተበሰሰ ይሁን ።

፳፫ ወግበር ክልኤተ ኅልቀታተ ወርቅ ፡ ወታነብሮሙ ለክልኤቱ ኅልቀታት ላዕለ ክልኤቱ ጽነፊሁ ለሎግዮ ።

ሁለት የወርቅ ቀለበቶችን ሠርተህ ሁለቱንም ቀለበቶች በሁለቱ የሎግዮ ዘርፍ ላይ አኑራቸው ።

፳፬ ወታነብሮሙ ለክልኤቱ ጽፍሮ ወርቅ ላዕለ ክልኤቱ ኅልቀታት ዘጽንፈ ሎግዮ ።

እንደ ዓሣ መረብ የተበሰሱ ሁለቱን የወርቅ ሰንሰለቶችንም በሎግዮ ዳርቻ ላይ ባሉ በሁለቱ የወርቅ ቀለበቶች ላይ በሁለት ወገን አኑራቸው ።

፳፭ ወለክልኤቱ ጽነፊሁ ታነብር ክልኤተ ጽፍሮ ላዕለ ክልኤቱ ክበበ ጥውዮ ፡ ወታነብሮ ላዕለ መትከፈ ኤፉድ መንገለ ገጹ በማኅበርቱ ።

ሁለቱን የወርቅ ሰንሰለቶች በኤፉዱ ጫንቃ ላይ በስተፊቱ በሁለት ወገን አገናኛቸው ።

፳፮ ወግበር ክልኤተ ሕልቀታተ ወርቅ ፡ ወታነብሮሙ ላዕለ ክልኤቱ ጽነፊሁ ለሎግዮ ኀበ ክንፈሩ ፡ ኀበ ዘየኃልፍ ኤፉድ እንተ ውስጥ ።

ለእነዚህ ሁለት የወርቅ ቀለበቶች ሥራላቸው ፡ እነዚህም ሁለት የወርቅ ቀለበቶች ኤፉድ በውስጡ በሚያልፍበት በከንፈረ ሎግዮ ላይ በሁለት ወገን አኑራቸው ።

፳፯ ወግበር ክልኤተ ኅልቀታተ ወርቅ ወታነብሮሙ ላዕለ ክልኤቱ መታክፈ ኤፉድ ኀበ ይትረአይ መንገለ ገጹ በማኅበርቱ ፡ መልዕልቴሁ ለእንመተ ኤፉድ ።

ዳግመኛ ለኤፉድና ለሎግዮ ሁለት የወርቅ ቀለበቶች ሥራላቸው እነዚህንም ሁለት የወርቅ ቀለበቶች በኤፉድ ሥራ ላይ ኤፉድና ሎግዮ በሚገናኙበት ፊቱም በሚተያይበት በሁለቱ የኤፉድ ጫንቃዎች ላይ አኑራቸው ።

፳፰ ወያስተእኅዝዎ ለሎግዮ እምኅልቀታቲሁ ኀበ ኅልቀታተ ኤፉድ በፈትለ ያክንት ፡ ከመ ይኩን ላዕለ እንመተ ኤፉድ ወኢያንጠልል ሎግዮ እምኤፉድ ።

ሎግዮ በኤፉድ ሥራ ላይ ይሆን ዘንድ ሎግዮም ከኤፉድ ተለይቶ እንዳይነጣጠል ፡ ሎግዮን ከቀለበቶቹ ወደ ኤፉድ ቀለበቶች በሰማያዊ ሐር ፈትል ያያይዙት ።

፳፱ ወይንሣእ አሮን አስማተ ደቂቀ እስራኤል መልዕልተ እንግድዓሁ ለሎግዮ ዘፍትሕ ፡ በበዊአቱ ውስተ መቅደስ ከመ ያዘክሮሙ ቅድመ እግዚአብሔር ዘልፈ ።

እስራኤልን ዘወትር በእግዚአብሔር ፊት በበጎ ነገር ሊያሳስባቸው አሮን ወደ ቤተ መቅደስ በሚገባበት ጊዜ (የቸርነቱ ፍርድ በሚፈረድበት) በሎግዮ በደረቱ ላይ አድርጎ የእስራኤልን ልጆች ስም ይዞ ይሂድ ።

፴ ወታነብር ኀበ ሎግዮ ዘፍትሕ ፡ መብርሂያተ ወማኅተ ማተ ወይኩኑ ላዕለ ልበ አሮን ሶበ ይበውእ ቤተ መቅደስ

የቸርነቱ ፍርድ በሚፈረድበት ፡ በሎግዮ በሐርና በወርቅ ግርጻ የተቈለፉ ንሥራ ሁለቱን አዕናቍ በሎግዮ ላይ

ቅድመ እግዚአብሔር ያብእ ፍትሖሙ ለውሉደ እስራኤል ዲበ እንግድዓሁ ዘልፈ ።

አኑራቸው፡ እንዚህም አሮን ስለ እስራኤል ልጆች ሊያስ ፈርድላቸው ልመናቸውን ይዞ ወደ ቤተ መቅደስ በሚገባበት ጊዜ በደረቱ ላይ እንደ ወርቅ ማርዳ ይሁኑ ።

፴፩ ወግበር ጽዱሬ ዘኵለንታሁ በያክንት ።

ለንዚህም ከእግር እስከ ራሱ ከሰማያዊ ሐር የተሠራ እጀ ሰፊ ቀሚስ ሥራለት ። ዕገ፡ ፪ ፳፫ ።

፴፪ ወእፈ መልበስቱ እምኔሁ ይኩን ማእከለ በዓውዱ በግብረ ምእናም፡ ወድማሬሁ እንም እምኔሁ ከመ ኢይትበተክ ።

አንገትጌውም በግብረ መርፌ የተጠለፈ ሁኖ በዙርያው መካከል ሥረ-ወዕ ይሁን፡ እንዳይቀደድም እንደ ጥሩር የተሠራ ጥልፍ በአንገትጌው ዙርያ ይሁንበት ።

፴፫ ወግበር እመልዕልቴሁ በዓውዱ መትሕተ መልበስቱ ከመ ፍሬያተ ሮማን ዘያክንት ወኅብረ ከብድ ወለይ ክዑብ ወቢሶስ ክዑብ ።

በታችኛውም ዘርፍ ዙርያ ከሰማያዊ ከሐምራዊ ከቀይም ግምጃ እንደ ሮማን ፍሬ ያለ ሥራለት፡ የወርቅ ጸናጽሎችንም ሥራለት ።

፴፬ ወጸናጽላተ ወርቅ በማእከለ ሮማን፡ ወሮማን ማእከለ ጸናጽለ ወርቅ መልዕልተ ጽዱሬ እንተ ዓውድ፡ ወይኩን ላዕለ አሮን ለተልእኮ ።

በሞሉጣ ግምጃ ላይ በዙርያው ጸናጽል መካከል የወርቅ ሮማንን በወርቅ ሮማን መካከል የወርቅ ጸናጽልን አድርግበት፡ ይህም ሁሉ በአሮን ላይ ሁኖ ለመገልገያ ይሁን።

፴፭ ወይግበር አሮን ሶበ ይሠውዕ በቃል ዘይሰማዕ እንዘ ይበውእ ቤተ መቅደሰ ቅድመ እግዚአብሔር፡ ወእንዘሂ ይወጽእ ከማሁ ከመ ኢይሙት ።

አሮንም ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ በእግዚአብሔር ፊት በሚሠዋበት ጊዜ በሚሰማ ቃል ያድርግ፡ ሲወጣም (እንዳይቀሠፍ) እንዲሁ ያድርግ ።

፴፮ ወግበር ቈጽለ ወርቅ ረቀቀ እምወርቅ ንጹሕ ወትገብር ላዕሌሃ አርአያ ማኅተም ቅዱስ ለእግዚአብሔር ።

ወርቁን ከጸሩ ወርቅ ለይተህ እንደ ቅጠል አሳስተህ ሥራ፡ በላይዋም ላይ እንደ ማኅተም ቅርጽ (ራስ ወርቅ) ቅረጽበት፡ በራስ ወርቁም ላይ (አህያ ሽራህያ አልሻዳይ) የሚባሉ ቃላት ቅረጽበት ።

፴፯ ወታነብራ ዲበ ዘኅብረ ያክንት ፍትሎ ወታነብራ ዲበ አክሊል መንገለ ፍጽሙ፡ ወትኩን ውስተ ፍጽሙ ለአሮን።

ይህችንም እንደ ራስ ወርቅ ያለችውን ከሰማያዊ ኅብር በተፈተለ ክር በአሮን አክሊል ላይ በስተፊቱ አንጠልጥላት ። ፩ ዜና መዋ፡ ፲፯ ፳፱፡ ዘኩ፡ ፲፬ ፳ ።

፴፰ ወይንሣእ አሮን ኃጢአተ ቅድሳት ዘቀደሱ ውሉደ እስራኤል እምኵሉ ሀብተ ቅድሳቶሙ፡ ወይኩን ውስተ ፍጽሙ ለአሮን ከመ ይኩን ሎሙ ሥጥወ ለእግዚአብሔር ።

በአሮንም ግምባር ላይ ትሁን፡ እስራኤል ስለ ኃጢአታቸው ከከብታቸው ለይተው ካቀረቡት ሁሉ ጋር ለኃጢአታችን ማስተሥረያ ይሆነናል፡ እግዚአብሔር ይቀበለናል ብለው አክብረው ያቀረቡት ይህን ራስ ወርቅ አሮን በራሱ ላይ ደፍቶ ወደ ቤተ መቅደስ ይግባ ።

፴፱ ወትገብር አራዘ እምቢሶስ፡ ወአክሊለ ዘቢሶስ፡ ወቅናተ ዘኅብረ ግብረቱ ።

ከነጭ ሐር፡ እጀ ጠባብ ቀሚስ ከነጭ ሐርም ኵፌት ከአራቱ ኅብር የተጠለፈ ዝናርንም ሥራ ።

፵ ወለደቂቀ አሮን ትገብር ሎሙ አልባሰ ዘቢሶስ፡ ወቅናታተ ወቆብዓተ ወይኩን ለክብር ወለአንክሮ ።

ለአሮንም ልጆች ሊከበሩበት ሊደነቁበት ከነጭ ሐር ቀሚስ ዝናር ኵፌት ሥራላቸው ።

፵፩ ወእግብር ሎሙ ድርማንቀ ዘአኄ ከመ ይሠውሮሙ ኀፍረቶሙ ፡ ወንበ ይከድና እምሐቋ እስከ መናቅዕ ለይኩና ።

ኃፍረታቸውን እንዲሠውርላቸው ከወገባቸው እስከ ቁርጭምጭሚታቸው የሚያለብሳቸው የነጭ ሐር ልብልብ አሠራላቸው ። ዘፀ፡ ፴፱ ፳፯፡ ሕዝ፡ ፵፬ ፲፯ ።

፵፪ ወታለብሶ ለአሮን እኁከ ወለደቂቂሁ ምስሌሁ፡ ወቀብአሙ ወአጽሕዶሙ እደዊሆሙ ወእገሪሆሙ፡ ወቀድሶሙ ከመ ይሡኡ ሊተ ።

(ይህንም) ልብስ (አስቀድመህ) ለወንድምህ ለአሮን አልብሰው፡ ከሱም ጋራ ለልጆቹ አልብሳቸው (ሃብተ ክህነት የሚቀበሉበት) አራት ሽቱ አምስተኛ ዘይትንም ቀብቸው፡ በሽቱና በዘይትም እግሮቻቸውንና እጆቻቸውን አለዝበህ ለኔ መሥዋዕት እንዲያቀርቡልኝ አክብረህ ሹማቸው ። ዘፀ፡ ፳ ፯፡ ሌዋ፡ ፲ ፯ ።

፵፫ ወከማሁ ለይልበሱ አሮን ወደቂቁ ሶበ ይበውኡ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ሶበ ይቀርቡ ይሡዑ ኀበ ምሥዋዐ ቤተ መቅደስ ።

አሮንና ልጆቹ ወደ ደብተራ ኦሪት በገቡ ጊዜ በምስጋና ማደሪያው በቤተ መቅደስ አጠገብ ወዳለ መሠውያም ሊሠዉ በቀረቡ ጊዜ እንዳዘዝኩት ያለ ልብስ ይልበሱ ።

፵፬ ወኢያምጽኡ ላዕሌሆሙ ኃጢአተ ወኢይሙቱ፡ ሕግ ዘለዓለም ውእቱ ሎቱ ወለዘርኡ እምድኅሬሁ ።

በራሳቸውም ዕዳ በደል እንዳያመጡና እንዳይቀሠፉ ለሱና ለልጆቹ፡ ከሱም በኋላ ለልጅ ልጆቹ ለዘለዓለሙ ሥርዓት ነው፡ (ይሁን) ። ዘሌዋ፡ ፳ ፲፱ ።

ምዕራፍ ፳፱ ።

፩ ወዝ ውእቱ ዘትገብር ሎሙ አመ ትቄድሶሙ ከመ
ይትለአኩኒ ንሣእ አሐደ ላሕመ እምአልሕምት ወአባግዐ
ንጹሓነ ክልኤተ ።
፪ ወኅብስተ ናእት ልዉስ በቅብዕ ወጸራይቀ ናእት ዘበ
ቅብዕ ዘሥንዳሴ እምሥርናይ ትገብሮን ።
፫ ወታነብሮን ዲበ መሶብ ወታቄርቦን በመሶብ ወለላ
ሕም ወለክልኤቱ አባግዕ ።
፬ ወለአሮን ወለደቂቁ ታቀርቦሙ ኀበ ኆኅተ ደብተራ
ዘመርጡል ፡ ወታሐጽቦሙ በማይ ።
፭ ወነሢአከ አልባሲሁ አልብሶ ለአሮን እኁከ ፡ ልብሰ
ቢሶስ ወጶዴሬ ወኤፉደ ወሎግዮ ፡ ወታጸንዖ በሰናሲሁ ።
፮ ወታነብር አክሊለ ዲበ ርእሱ ፡ ወታነብር ቀጸላ ዘወ
ርቅ ዲበ አክሊሉ ።
፯ ወትነሥእ እምቅብዕ ዘበረከ ወትክዑ ዲበ ርእሱ ወት
ቀብዖ ።
፰ ወለደቂቁኒ ታቀርቦሙ ወታለብሶሙ አልባሲሆሙ ፡
ወታቀንቶሙ ቅናታቲሆሙ ።
፱ ወትወዲ ዲቤሆሙ ቅብዐ ወይከውኑኒ ሠዋዕተ ሊተ
ለዓለም ወትፌጽም እዴሁ ለአሮን ወእደወ ደቂቁ ።
፲ ወታቀርብ ላሕመ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወያ
ነብሩ አሮን ወደቂቁ እደዊሆሙ ዲበ ርእሰ ላሕም ለቅ
ድመ እግዚአብሔር ፡ በኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ።
፲፩ ወተሐርዶ ለላሕም በቅድመ እግዚአብሔር ኀበ ኆኅ
ተ ደብተራ ዘመርጡል ።
፲፪ ወትነሥእ እምደመ ላሕም ወትወዲ ዲበ አቅርንተ
ምሥዋዕ ዘቤተ መቅደስ በአጽባዕትከ ወዘተርፈ ኵሉ ደሞ
ትክዑ ጥቃ ቤተ መቅደስ ።
፲፫ ወትነሥእ ኵሎ ስብሐ ከርሡ ፡ ወከብዶ እንተ ትን
እስ ወከልኤተ ኵልያቶ ፡ ወስብሐ ዘላዕሌሆን ወታነ
ብር ውስተ ምሥዋዕ ።
፲፬ ወሥጋ ላሕም ወማእሰ ወጸፍዖ ታውዒ በእሳት ፡ አው
ጺአከ አፍአ እምትዕይንት ፡ እስመ ዘኀጢአት ውእቱ ።
፲፭ ወትነሥእ አሐደ በግዐ ወያነብሩ አሮን ወደቂቁ እደ
ዊሆሙ ላዕለ ርእሰ በግዕ ።
፲፮ ወተሐርዶ ለውእቱ በግዕ ፡ ወትነሥእ ደሞ ወትክዑ
ላዕለ ምሥዋዕ ፡ ወውስተ ኵሉ ዓውዱ ትነሰንስ ።
፲፯ ወትመትሮ በበመሌሊቱ ወተሐፅብ ንዋየ ውስጡ ወእ
ገሪሁ ወታነብር ኀበ ዘሌለዪከ ።
፲፰ ወታዐርግ ኵሎ በግዐ ላዕለ ምሥዋዕ ፡ ቍርባን ውእቱ
ለእግዚአብሔር ።
፲፱ ወትነሥእ ካልአ በግዐ ወያነብሩ አሮን ወደቂቁ እደ
ዊሆሙ ላዕለ ርእሱ ።

ምዕራፍ ፳፱ ።

፩ እንዲያገለግሉኝ አክብረህ በሾምኻቸው ጊዜ የምታደ
ርግላቸው ሥራ ይህ ነው ፡ (ለነሱ የምትሠዋላቸው) አንድ
ወይፈንና ሁለት ንጹሓን በጎችን አምጣ አለው ።
፪ በዘይት የታሸ የቂጣ እንጀራና በዘይት የታበቀ የሥ
ንዴ ድፎን ልጦ ጕርዶ ከወጣለት ሥንዴ ሥራላቸው ።
፫ ሁለቱን በጎችና ወይፈኑንም በመሶብ አድርገህ (ለመ
ሥዋዕት) አቅርባቸው ።
፬ አሮንና ልጆቹንም በውኃ አጥበህ ወደ ደብተራ ኦሪት
አቅርባቸው ። ዘሌዋ፡ ፹ ፲፪ ፡ ዕብ፡ ፲ ፳፪ ።
፭ ልብሶቹንም አምጥተህ ወንድምህ አሮንን አልብሰው
የምታለብሰውም ልብስ የነጭ ሐር ቀሚስ ሞሉጣ ግምጃ
ኤፉድንና ሎግዮን ነው ፡ እነዚህንም (በክበበ ጥውዮ) ሰን
ሰለት እሠራቸው ። ዘሌዋ፡ ፰ ፯ ።
፮ ኵፌቱን በራሱ ላይ ድፋለት ፡ በኵፌቱም ላይ የራስ
ወርቅ አድርግለት ። ዘኍ፡ ፴፰ ፳፰ ።
፯ ከበረከኸውም ዘይት አምጥተህ በራሱ ላይ አፍስስ
በት (ከእግር እስከ ራሱ አካሉን) ቅባው ።
፰ ልጆቹንም አቅርበህ የሚገባ ልብሳቸውን አልብሳቸው
የወርቅ ዝናራቸውንም አስታጥቃቸው ።
፱ ኵፌትንም በራሳቸው ድፋባቸው ፡ መሥዋዕት የሚ
ሠዉ ለዘለዓለሙ ለኔ አገልጋዮች ይሆኑኛል ፡ የአሮንንም
ቀኝ እጁን የልጆቹንም ቀኝ እጃቸውን ቅባ ።
፲ ወይፈኑን ወደ ደብተራ ኦሪት በር አቅርበው አሮንና
ልጆቹም በቤተ እግዚአብሔር ፊት ለፊት ቆመው እጃቸ
ውን በወይፈኑ ራስ ላይ ይጫኑ ። ዘሌ፡ ፰ ፲፬ ።
፲፩ ላሙንም በደብተራ ኦሪት ደጃፍ በእግዚአብሔር ፊት
አረደው አወራርደው ።
፲፪ ከላሙም ደም ከፍለህ በጣትህ እየጠለቅህ በቤተ መቅ
ደስ አጠገብ ባለ በአቅርንተ ምሥዋዑ ላይ አድርገው የተ
ረፈውን ደሙ ግን በቤተ መቅደስ አጠገብ ባለ በምሥ
ዋዑ ዙርያ አፍስሰው ። ዘፀ፡ ፴ ፪ ።
፲፫ የሆድ ዕቃውን ጕልገል ጕበቱን ግራ ቀኝ ኵላሊቱን
በነዚህ ላይ ያለውን ስብ ሁሉ አምጥተህ በምሥዋዑ ላይ
አኑረው ። ዘሌዋ፡ ፫ ፫ ።
፲፬ የላሙን ሥጋና ቈርበቱን ፈርሱን ግን አፍአ አውጥ
ተህ በእሳት አቃጥለው የኃጢአት ነውና ።
፲፭ ከሁለቱ በጎች አንዱን በግ አምጥተህ አሮንና ልጆቹ
በበጉ ራስ ላይ እጃቸውን ይጫኑበት ።
፲፮ ያንንም በግ አርደህ አወራርደህ ደሙን አምጥተህ
በምሥዋዑ ላይ አፍስሰው ፡ (የተረፈውንም) በመሠውያ
ዙርያ ረብርበው ።
፲፯ በየስልት በየስልቱ አርደህ አወራርደህ ሆድ ዕቃው
ንና እግሩን አጥበህ (የበጉን ሥጋ) ለይተህ ለይተህ በኖር
ክበት ላይ አኑረው ። ዘፍ፡ ፰ ፳፩ ።
፲፰ በጉንም በመላው በመሠውያው ላይ አድርገህ አቃጥ
ለው ይኸውም ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ቍርባን ነው ።
፲፱ ሁለተኛውንም በግ አምጥተህ አሮንና ልጆቹ እጃቸ
ውን በራሱ ላይ ይጫኑበት ።

፳ ወሕርዶ ወንሣእ እምደሙ ወአንብር ዲበ ከተማ ዕዝኑ ለአሮን እንተ የማን ፡ ወዲበ ከተማ አጽባዕተ እዴሁ ዘየማን ፡ ወዲበ ከተማ አጽባዕተ እግሩ ዘየማን ወዲበ ከተማ ዕዘኒሆሙ ለደቂቀ አሮን ዘየማን ፡ ወዲበ ከተማ አፃብዐ እደዊሆሙ ዘየማን ፡ ወዲበ ከተማ አጻብዐ እገሪሆሙ ዘየማን ።

በጉንም አርደህ አወራርደህ ከደሙ ቀድተህ አምጥተህ የአሮንን ቀኝ ጆሮውን ፡ ቀኝ እጁን ፡ ቀኝ እግሩን ቀበው ፡ የአሮንም ልጆች ቀኝ ቀኝ ጆሮአቸውን ፡ ቀኝ ቀኝ እጃቸውን ቀኝ ቀኝ እግራቸውን ቀባቸው ።

፳፩ ወትነሥእ እምደም ዘምሥዋዕት ፡ ወእምቅብዕ ቡሩክ ፡ ወትነሰንስ ላዕለ አሮን ወላዕለ አልባሲሁ ፡ ወእምድኅሬሁ ላዕለ ደቂቁ ወላዕለ አልባሲሆሙ ወይትቄደስ ውእቱ ወዓራዙ ወደቂቁ ወዓራዞሙ ምስሌሆሙ ።

ከመሥዋዕቱም ደም ቀድሰህ ከኖርኸው ከአራት ሽቱ ከአምስተኛ ዘይት አምጥተህ በአሮን ልብስ ላይ ርጨው ከሱም በኋላ በልጆቹና በልብሶቻቸው ላይ ርጭ ፡ እሱም ይከብራል ልብሱም ልጆቹም ይከብራሉ ልብሶቻቸውም ።

፳፪ ወደሞ ለውእቱ በግዕ ትክዑ ውስተ ቤተ መቅደስ በዓውዱ ፡ ወትነሥእ እምውእቱ በግዕ ስብሐ ዘይገለብብ ከርሦ ወከብዶ ፡ ወክልኤተ ኵልያቶ ወስብሐ ዘላዕሌሆን ፡ ወትነሥእ አገዳሁ ዘየማን ፡ እስመ በእንተ ዝንቱ ይትፌጸም ።

የዚያንም በግ ደም በቤተ መቅደሱ በመሠውያው ዙርያ አፍስሰው ፡ ከዚያም በግ ሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ስብ ግልገል ጉበቱን ሁለት ኵላሊቶቹን በላያቸው ላይ ያለውን ስብንንና የቀኝ ወርቹን ስብ አምጣ ፡ የአሮን የክህነቱ ሥራ በዚህ ይፈጸማልና ።

፳፫ ወኅብስተ አሐተ ወጸሪቀ አሐተ እምውስተ መሶብ ዘውኁቴቱ ንቡር ኵሉ ዘሜሙ ቅድመ እግዚአብሔር ።

(ሴዋውያን) በእግዚአብሔር ፊት አዘጋጅተው ካኖሩት በመሶብ ውስጥ ተቀምጦ ካለው አንድ እንጀራ አንድ ድፎ ቂጣ አምጣ ።

፳፬ ወታነብር ኵሎ ዘውስተ እዴሁ ለአሮን ፡ ወውስተ እደወ ደቂቁ ፡ ወትፈልጠ ፍልጣነ በቅድመ እግዚአብሔር ።

ይህን ሁሉ አምጥተህ በአሮን እጅና በልጆቹ እጅ አኑረው ሁሉንም በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ መሥዋዕት አድርገህ ለየው ።

፳፭ ወትትሜጠዎ እምእደዊሆሙ ፡ ወታነብር ዲበ ምሥዋዕ ለመዓዛ ሠናይ በቅድመ እግዚአብሔር ፡ መሥዋዕት ውእቱ ለእግዚአብሔር ።

ከሰጠኻቸውም በኋላ መልሰህ ከእጅ ከእጃቸው ተቀብለህ ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ ያለው መሥዋዕት ሊሆን በምሥዋው ላይ አቅርበው ይህም ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ ያለው መሥዋዕት ነው ። ዘሌዋ፡ ፰ ፳፰ ።

፳፮ ወትነሥእ ተላዖ ለበግዕ ዘፍጻሜ ለአሮን ፡ ወትፈልጠ ፍልጣነ በቅድመ እግዚአብሔር ወይኩን ለከ ክፍለ እምኔሁ ።

አሮን የተቀበበት የበጉንም ፍርንቢያ ወስደህ በእግዚአብሔር ፊት የተለየ መሥዋዕት አድርገው ፡ ከሱም ላንተ ዕድል ፈንታ ይሁንህ ። ዘኍ፡ ፲፰ ፲፩ ።

፳፯ ወመዝራዕቶኒ ትፈልጥ በከመ ፈለጥከ በግዐ ፍጻሜ እምኅበ አሮን ፡ ወእምኅበ ደቂቁ ።

አሮን ተቀብቶ የተሾመበት በጉን ከአሮንና ከልጆቹ እንደለየኸው ወርቹንም ከሥጋው ለየው ።

፳፰ ወይኩኖሙ ለአሮን ወለደቂቁ ሕገ ዘለዓለም በኅበ ውሉደ እስራኤል ፡ እስመ ፍልጣን ውእቱ ዝ ።

ይህ የተለየ መሥዋዕተ ኃጢአታቸው ነውና በእስራኤል ልጆች ዘንድ ለአሮንና ለልጆቹ ለዘለዓለሙ ሕግ (ሥርዓት) ይሁናቸው ። ዘሌ፡ ፲ ፲፫ ።

፳፱ ወፍልጣነ ይኩን በኅበ ውሉደ እስራኤል እምዝብኅት ዘይዘብሑ ለፍርቃኖሙ ፡ ፍልጣን ለእግዚአብሔር ።

ለእግዚአብሔር የተለየ መሥዋዕት ሁኖ ከመከራው ሊድኑበት ድኤል ከሚሠዉት መሥዋዕት ይልቅ በእስራኤል ልጆች ዘንድ ይህም ለአሮንና ለልጆቹ የተለየ መሥዋዕት ይሁናቸው ።

፴ ወልብሰ ቅድሳቱ ለአሮን ለይኩን ለውሉዱ እምድኅሬሁ ከመ ይትቀብዑ በቱ ፡ ወከመ ይፈጽሙ እደዊሆሙ ።

የአሮን ልጆች አራት ሽቱ አምስተኛ ዘይት አጣፍጠው እጆቻቸውን ተቀብተው ይከብሩበት ዘንድ ከሱ በኋላ አሮን የተሾመበት የአሮን ልብሰ ተክህኖ ለልጆቹ ይሁን ።

፴፩ ወሰቡዐ ዕለተ ለይልበሶ ካህን ዘህየንቴሁ እምደቂቁ ፡ ዘይበውእ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ፡ ከመ ይሠየም በቅድሳት ።

ይህንም አሮን የተሾመበትን ልብሰ ተክህኖ በቅድስተ ቅዱሳን ሊሾም ወደ ደብተራ ኦሪት የሚገባው ከልጆቹ ስለሱ ተተክቶ የሚሾመው ካህን ሰባት ቀን ይልበሰው ።

፴፪ ወበግዐ ዘፍጻሜ ትነሥእ ወታበስል ሥጋሁ በመካን ቅዱስ ።

አሮንና ልጆቹ ከደሙ የተቀቡበት በጉን አርደህ አወራርደህ ሥጋውን ወስደህ በከበረ ቦታ ቀቅለው ።

፴፫ ወይብልዑ አሮን ወደቂቁ ሥጋ በግዕ ወኅብስተ ዘውስተ መሶብ በኅበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ።

የበጉን ሥጋና በመሶብ ያለውን ድፎውን እምበሻውን አሮንና ልጆቹ በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ተቀምጠው ይብሉት

፴፬ ይብልዕዎ በኅበ ተቀደሰ በሀየ ከመ ይፈጽሙ እደዊሆሙ ፡ ለተቀድሶቶሙ ወውሉደ ባዕድ ኢይብልዖ እስመ

ሊከብሩበት ሊሾሙበት እጆቻቸውን እንዲቀቡ በዚያ በከበረ ቦታ ሁነው ይብሉት ፡ ነገር ግን የተቀደሰ ነውና

ቅዱስ ውእቱ ።

(ከነገደ ሌዊ ያልተወለደ) ባዕድ አይብላው ።

፴፬ ወለእመ ተርፈ እምሥጋ መሥዋዕት ዘፍጻሜ ወኅብስቲሁ እስከ ደግደግ ታውዕዮ በእሳት ለዘተርፈ ወኢይትበላዕ እስመ ቅዱስ ውእቱ ።

ደሙን ከተቀቡበት ከበጉ መሥዋዕት ሥጋ ከድፎውም ከእምባሻውም እስከ ነገው ቢያድር ተርፎ ያደረውን በእሳት አቃጥለው የከበረ ነውና ፤ (ተርፎ አድሮ አይበላ) ።

፴፭ ወግበር ለአሮን ወለደቂቁ ከመዝ ኵሎ ዘከመ አዘዝኩከ ፡ ሰቡዐ ዕለተ ከመ ትረድዖሙ አደዊሆሙ ።

እጆቻቸውን ትቀባቸው ዘንድ ቀባቸው ብዬ ያዘዝኩህን ሁሉ ለአሮንና ለልጆቹ ሰባት ቀን አድርግላቸው ።

፴፮ ወላሕመ ዘእንበይነ ኃጢአት ትገብር ለለዕለቱ በዘበቱ ታነጽሕ ምሥዋዐ ሶበ ትቄድሶ ቦቱ ።

ምሥዋዑን በምታከብርበት ደሙንም በምትቀባው ጊዜ ምሥዋዑን በምታነጻ ገንዘብ ስለ ኃጢአት የሚሠዋውን ላም ሰባት ቀን ዕለት ዕለት ሠዋው ።

፴፯ ወትቀብዖ ሰቡዐ ዕለተ ወታነጽሖ ለምሥዋዕ ወትቄድሶ ፡ ወይኩን ምሥዋዒከ ቅዱሰ ቅዱሳን ፤ ወኵሉ ዘለከፎ ለውእቱ ምሥዋዕ ለይትቀደስ ።

በመሥዋዕት ኃጢአቱም ምሥዋዑን ሰባት ቀን ቀብተህ አንጻው አክብረው መሠውያህም ከከበሩ የከበረ ይሁን ፤ ምሥዋዑንም የነካው ሰው ሁሉ ይከብራል ።

፴፰ ወዝ ውእቱ ዘይትገበር ለመሥዋዕት ዘዘልፍ ፤ አባግዐ ንጹሐነ እለ አሐቲ ዓመቶሙ ፤ ክልኤተ ለለዕለቱ ።

(ጧት ማታ) ዘወትር ለመሥዋዕት የምትሠራው ሥራ ይህ ነው ፤ ንጹሐን (ማለት ቀንዳቸው ያልከረከረ ጥፍራቸው ያልዘረዘረ ላታቸው ያላረረ) ዓመት የሆናቸው ሁለት በጎች ።

፴፱ ወአሐደ በግዐ ትገብር በጽባሕ ፤ ወአሐደ ፍና ሠርክ ፤ ወዓሥራታ ለኢፍ ሥንዳሌ ልሑጽ በቅብዕ ፤ ወልቱም በራብዕታ ለኢን ፤ ወሞጻሕተ ወይን ራብዕታ ለኢን ለአሐዱ በግዕ ።

አንዱን መሥዋዕተ ነግህ ፤ አንዱን መሥዋዕተ ሠርክ አድርገህ ሠዋቸው ፤ (ኢፍ አሥረ-ፊጅ ነው) ፤ ለመሥዋዕተ ነግህ የኢን መሥፈሪያ አራተኛ እጅ በሆነ ተወቅጦ በተንጣለለ ዘይት የተለወሰ ልዩ ጕርዶ የወጣለት የኢፍ አሥረኛውን ሥንዴ አቅርብ ፤ ለአንድ በግ ፍልቅ አድርገው ፤ የሚያፈሱት የኢን (የገንቦ) እርቦ ወይን ነው ።

፵ ወለካልእኒ በግዕ ዘትገብሮ ፍና ሠርክ በሐሳበ መሥዋዕትከ ዘነግህ ትገብሮ ።

በሠርክ የምታቀርበው ለሁለተኛውም በግ ፤ በነግህ በቀረብከው መሥዋዕት ልክ አድርገህ አቅርብለት ።

፵፩ ወከማሁ ሞጻሕቶኒ ትገብሮ ለመዓዛ ሠናይ ፤ መሥዋዕት ውእቱ ለእግዚአብሔር ።

እንደዚሁም ፍልቅ አድርገው የሚያፈሱት ወይኑንም የገንቦ እርቦ ወይን አቅርብለት ፤ ይኸውም በጎ መዓዛ ያለው ሁኖ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መሥዋዕት ነው ።

፵፪ ዘወትር ለትውልድክሙ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል በቅድመ እግዚአብሔር በዘእትኤመር ለከ በህየ ከመ እንብብከ ።

ይኸውም አንተን ልነጋገርህ በምገለጥበት በታ በደብተራ ኦሪት ደጃፍ በእግዚአብሔር ፊት ዘወትር ለልጅ ልጆቻችሁ ጧት ማታ የሚቀርብ ይሁን ።

፵፫ ወእኤዝዞሙ በህየ ለውሉደ እስራኤል ፤ ወእትቄደስ በክብርየ ።

በዚያም በታ ሁኜ የእስራኤልን ልጆች አዛቸዋለሁ ፤ እኔም በክብሬ እመሰገናለሁ ።

፵፬ ወእቄድሳ ለደብተራ መርጡል ወለምሥዋዒሃ ፤ ወእቄድሶሙ ለአሮን ወለደቂቁ ከመ ይሠዑ ሊተ ።

ደብተራ ኦሪትንና መሠውያዋንም አከብራቸዋለሁ ለኔም ጧት ማታ መሥዋዕት እንዲሠዉልኝ አሮንና ልጆቹን አከብራቸዋለሁ ። ዘሌ፡ ፰፩ ፲፩ ።

፵፭ ወእኀድር ማእከሌሆሙ ለውሉደ እስራኤል ወእከውኖሙ አምላኮሙ ።

(እኔም) በእስራኤል ልጆች (በረድኤት) አድሬባቸው እኖራለሁ የፍቅር አባትም እሆናቸዋለሁ ።

፵፮ ወየአምሩ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላኮሙ ዘአውጻእክዎሙ እምድረ ግብጽ ከመ እስመይ በላዕሌሆሙ ወእከውኖሙ አምላኮሙ ።

በነሱ እጠራባቸው ዘንድ ከግብጽ አገር ያወጣኋቸው ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር እንደሆንኩና ፤ (የፍቅር የሃይማኖት) አባታቸው እንደሆንኩም ያውቃሉ ።

ምዕራፍ ፴ ።

፩ ወግበር ሊተ ምሥዋዐ ዘዕጣን እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ዘእመት ኑኁ ፤ ወእመት ራኅቡ ፤ ርቡዐ ግበሮ ፤ ወክዕበ እመት ቆሙ ፤ ወእምኔሁ ይትገበሩ አቅርንቲሁ ።

(ሸምሸር ሰጢን ከሚባል) ከማይነቅዝ ዕንጨት የዕጣን መሠውያ (ማዕጠንት) ሥራልኝ ይህንንም አቈልቋዩን ክንድ ፤ ወርዱን ክንድ ፤ ምዕዘኑን አድርገህ ሥራው ፤ ቁመቱም ሁለት ክንድ ይሁን ፤ ቀንዶቹም ሥረ-ወዕ ይሁኑ ።

፪ ወትቀፍሎ ወርቀ ንጹሐ ምድሮ ወዓውደ አረፍቱ ፤ ወአቅርንቲሁ ወግበር ሎቱ ቀጸላ ዘወርቅ ።

ምድሩን የግድግዳውን ዙርያና ቀንዶቹንም የጸራ ወርቅ ለብጣቸው ፤ በዙርያውም የወርቅ ከንፈር (ክፈፍ) አድርግበት ። ዘፀ፡ ፴፯ ፳፭ ፡ ፵ ፭ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወግበር ሎቱ ክልኤተ አውቃፋተ ወርቅ መትሕተ ቀጸላሁ፤ ላዕለ ክልኤቱ ፍናሁ፤ ወትገብር ላዕለ ክልኤቱ ገበዋቲሁ። | ፫ | ከክንፈሩም በታች ሁለት የወርቅ አምበሮች አድርግ ለት፤ እነዚህንም በሁለት ጐኖቹ አድርጋቸው። ዘፀ፡ ፳፯ ፳፩፡ ፵ ፩። |
| ወይኩኑ አብያተ ለመሳውሪሁ ከመ ያንሥኡ በሙ ኪያሁ። | ፬ | እሱንም በእነሱ እንዲያነሡበቸው ለመሸከሚያዎቹ ቤት ይሁኑ። ራዕ ዮሐ፡ ፰ ፫። |
| ወግበር መሳውርተ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ፤ ወቅፍሎሙ ወርቀ። | ፭ | ከማይነቅዝ ዕንጨት አምጥተህ መሸከሚያዎችን አድ ርግለት ወርቅንም ለብጣቸው። |
| ወታነብሮ ቅድመ መንጦላዕት ዘሀሎ ኀበ ታቦት ዘመ ርጡል በዘእትኤመር ለከ በሀየ። | ፮ | ማዕጠንቱንም እኔ ላንተ በዚያ በምገለጥልህ በታ በደ ብተራ ኦሪት ካሉት ታቦት በላይ ባለ መጋረጃ አንጻር አኑረው። ፩ ነገ፡ ፳፫ ፲፫፤ ሉቃ፡ ፩ ፱። |
| ወይዕጥን በውስቴቱ አሮን ዕጣነ ዘቅታሬ ድቁቀ በበ ነግህ። | ፯ | አሮን በጎ መዓዛ ያለው የተፈጨ የደቀቀውን ዕጣን በነግህ በነግህ ይጠንበት። ፩ ሳሙ፡ ፪ ፳፰። |
| ወሰበ ይገብር መኀትወ በሠርክ ይዕጥን በውስቴቱ ዘዘልፍ በቅድመ እግዚአብሔር በትውልድክሙ። | ፰ | በዓልም ባደረገ ጊዜ በዋዜማው ለልጅ ልጃችሁ መጠ በቂያ ሊሆን በእግዚአብሔር ፊት ዘወትር በሠርክ በሠ ርክ ይጠንበት። ዘሌዋ፡ ፲ ፩። |
| ወኢትደምሩ ውስቴቱ ዕጣነ ዘካልእ ቅታሬሁ፤ ወመ ሥዋዕተ ወሞጻሕተ ኢታውጽሑ ዲቤሁ። | ፱ | ቅታሬ መዓዛው ልዩ የሆነ ሌላ ዕጣን አትጨምሩበት በማዕጠንቱም መሥዋዕት አትጠኑበት፤ ወይንንም ፍልቅ አድርጋችሁ በላዩ ላይ አታፍስሱበት። |
| ወይትመሐለል አሮን በአቅርንቲሁ ለለዓመት ምዕረ፤ ወይነሥእ እምደም ዘያነጽሕ ኃጢአተ ምዕረ ለለዓመት፤ ወይገብር ከመ ያንጽሕ ትውልዶሙ ወቅዱሰ ቅዱሳን ውእቱ ለእግዚአብሔር። | ፲ | አሮን ከዓመት አንድ ጊዜ አቅርንተ ምሥዋዑን ይዞ ይጸልይ፤ ከዚያም አስቀድሞ የሕዝቡን ኃጢአት ከሚያስ ተሠርየው ከመሥዋዕተ ደም ይዞ ከዓመት አንድ ጊዜ ይ ግባ፤ የጽኤል ነገዶቸው ከኃጢአታቸው ያነጻበት ዘንድ በዓ ለ አስተሥርዮን ያድርግ፤ ይኸውም ደሙ ዕጣኑ ለእግዚ አብሔር በጎ መዓዛ ያለው መሥዋዕት ሁኖ የሚቀርብ ከከበሩ የከበረ ነው። ዘሌዋ፡ ፳፫ ፳፯። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤ ለእመ ነሣእከ ሕሊናሆሙ ለውሉደ እስራኤል ከመ ትኊልቆሙ ለየሀብ አሐዱ አሐዱ ቤዛ ነፍሱ ለእግዚአብሔር። | ፲፩ | እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፤ የእ ስራኤልን ልጆች ልቡና ይዘኸው እንደሆነ እንዱም እንዱ ለእግዚአብሔር ገንዘቡን ለሰውነቱ ቤዛ አድርጎ ይስጥ። |
| ወኢይምጻእ ላዕሌሆሙ ድቀት አመ ትኄልቆሙ። | ፲፪ | ይህን ካደረጉ በኋላ በቈጠርኻቸው ጊዜ መቅሠፍቱ በነሱ ላይ አይመጣባቸውም። ፪ ሳሙ፡ ፳፬ ፪። |
| ወዝ ውእቱ ዘይሁቡ ኵሎሙ እለ የሐውሩ ከመ ይት ኌለቁ፤ መንፈቃ ለሰቅል በሰቅል ቅዱስ ዕሥራ አበሊ ሰቅል፤ ወመንፈቃ ለሰቅል ቍርባኑ ለእግዚአብሔር። | ፲፫ | ሊቈጠሩ የሚሄዱትም ሰዎች ሁሉ የሚሰጡት ይህ ነው እንደ መቅደሱ ሚዛን የሰቅል ግማሽ ነው፤ ይኸውም የሰቅል ግማሽ ሃያ አበሊ (አቦት) ነው፤ የሰቅሉም ግማሽ ለእግዚአብሔር የተወደደ ሁኖ የሚቀርብ ቍርባኑ ነው። |
| ወኵሉ ዘየሐውር ከመ ይትኌለቍ ዘእምዕሥራ ክራ ማቲሁ፤ ወፈድፋደ። | ፲፬ | ሊቈጠርም የሚሄደው ሁሉ ሃያ ዓመት የሆነው ከሃ ያም ዓመት በላይ የሆነው ነው። |
| ባዕል ኢይወስክ፤ ወነዳይ ኢያንትግ እመንፈቃ ለሰ ቅል፤ እለ ያበውኡ ቍርባኖሙ ለእግዚአብሔር ቤዛ ነፍ ሶሙ። | ፲፭ | ለሰውነታቸው መበዠ ሊሆን ለእግዚአብሔር ቍርባን አድርገው ከሚያገቡት ክድሬም (አቀመት) አትርፎ ባለጸ ጋም አይጨምር ድኻም አያጐድል። ኢዮብ ፴፬ ፲፱። |
| ወትነሥእ ብሩረ ዘአብኡ ቍርባኖሙ ውሉደ እስራ ኤል፤ ወትሁብ ለምግባረ ደብተራ ዘመርጡል፤ ወይኩኖሙ ተዝካሮሙ ቅድመ እግዚአብሔር ቤዛ ነፍሶሙ። | ፲፮ | የእስራኤልም ልጆች ቍርባን አድርገው ያገቡትን ብር ተቀብለህ ለደብተራ ኦሪት ሥራ ሊሆን (ለአሮን) ስጠ ው፤ ይኸውም በእግዚአብሔር ፊት መታሰቢያ ሊሆና ቸው ለሰውነታቸው ቤዛ ነው። ዘኍ፡ ፲፮ ፵። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤ ግበር መቅ ለደ ዘብርት፤ ወመንበሩሂ ዘብርት። | ፲፯ | እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው እንዲህም አለው፤ የብርት መታጠቢያ ሰን (ኵስኵስት) ሥራ መቀመጫውም ብርት ይሁን። |
| ወታነብሮ ማእከለ ደብተራ ዘመርጡል ወማእከለ ምሥዋዕ ወትሠውጥ ውስቴቱ ማየ። | ፲፰ | ይህንም በምሥዋዐ ብርቱና በደብተራ ኦሪት መካከል አኑረው ውኃም ጨምርበት። |
| ወይትሐፀቡ አሮን ወደቂቁ እምውስቴቱ እደዊሆሙ | ፲፱ | አሮንና ልጆቹም መሥዋዕትን ለመሠዋት ወደ ደብ |

ወእገሪሆሙ፣ ሶበ ይበውኡ ውስተ ደብተራ መርጡል ከመ ይሡዑ ።

፳ ወሶበ የዓርጉ ይሡዑ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ይትሐፀቡ እደዊሆሙ ወእገሪሆሙ ከመ ኢይሙቱ ።

፳፩ ወይኩኖሙ ሕገ ዘለዓለም ሎሙ ወለውሉዶሙ እምድኅሬሆሙ ።

፳፪ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣ አንተ ንሣእ አፈዋተ ጽጌ ዘከርቤ ቅድወ ኃምስተ ምእተ ሰቅሰ ።

፳፫ ወቀናንሞ ቅድወ በመንፈቁ ለቅዳሚ ክልኤተ ምእተ ወኃምሳ፣ ወቀጺመተ ቅድወ ክልኤተ ምእተ ወኃምሳ ።

፳፬ ወአበሚ ኃምስተ ምእተ በሰቅል ቅዱስ፣ ወቅብዐ ዘይት በመስፈርተ ኢን ።

፳፭ ወግበር ቅብዐ ቅዱሰ ጽውጠ ዘጸዓጢ ።

፳፮ ወትቀብዖ እምኔሁ ለደብተራ ዘመርጡል፣ ወለታቦተ መርጡል ።

፳፯ ወማእደ ወኵሉ ንዋዮ፣ ወለተቅዋመ ማኅቶት ወለኵሉ ንዋያ፣ ወለምሥዋዕኒ ዘዕጣን ።

፳፰ ወለምሥዋዕ ዘመሥዋዕት ወለኵሉ ንዋዩ፣ ወለመቅለድ ምስለ መንበሩ ።

፳፱ ወትቄድሶሙ ወይከውኑ ቅዱሳነ፣ ወዘኪያሆሙ ለከፈ ለይትቀደስ ።

፴ ወለአሮን ወለደቂቁ ቅብዖሙ ወቀድሶሙ፣ ከመ ይሡዑ ሊተ ።

፴፩ ወበሎሙ ለውሉደ እስራኤል፣ ዝ ቅብዕ ዘይትቀብዑ ቅዱስ ለይኩን ማእከሌክሙ ለትውልድክሙ ።

፴፪ ወባዕድ ሰብእ ኢይትቀባዕ እምኔሁ፣ ወከመ አምሳሊሁ ኢትግበሩ ለክሙ ከማሁ፤ እስመ ቅዱስ ውእቱ ዝ ቅብዕ አመ ትገብርዎ ።

፴፫ ወዘወሀበ እምኔሁ ለባዕድ ዘመድ ለይሠሮ እምሕዝብ ።

፴፬ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ፣ ንሣእ ለከ አፈዋተ ማየ ልብን ወቀንአተ ቅድወ ወስኂነ ዘያንጸበርቅ፣ ወኵሉ ዕሩየ ለይኩን ድልወቱ ።

፴፭ ወግበርዎ ዕጣነ ኪያሁ ግብረ ዕጣን ቅድወ ወግብረ ንጹሐ ወቅዱሰ ግበር ።

፴፮ ወተሐርጽ እምኔሁ ድቂቀ ወታነብሮ ቅድመ ደብተራ ዘመርጡል፣ በዘበቱ እትኤመር ለከ እምህየ ወቅዱሰ ቅዱሳን ለይኩንክሙ ዝ ዕጣን ።

፴፯ ወበዝ ግብረት ኢትግበሩ አርአያ ዝ ዕጣን ኀሩመ ለይኩንክሙ ዝንቱ፣ ወቅዱሰ ለእግዚአብሔር ።

ተራ ኦሪት በገቡ ጊዜ በብርት ካለው ውኃ እጃቸውንና እግራቸውን ይታጠቡ ። ኢሳ፡ ፵፪ ፲፩ ።

ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ለማሳረግ ወደ ደብተራ ኦሪት በገቡ ጊዜ እንዳይሞቱ (እንዳይቀሠፉ) እጃቸውንና እግራቸውን ይታጠቡ ። ዕብ፡ ፲ ፳፪ ።

ይህም ለጊዜው ለነሱ ከነሱም በኋላ ለልጅ ልጆቻቸው ለዘለዓለሙ ሕግ ሥርዓት ይሁናቸው ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፤ ከማረ ከተወደደ ከርቤ ከሚባል ሽቱ አበባ የጣፈጡ ሽቶዎችን አምስት መቶ ወቄት ምዝን አንተ ተቀበል ።

ያማረ የተወደደ ቀናንሞ የሚባል ሽቱንም በቀደመው ሽቱ እኩሌታ ሁለት መቶ አምሳ ወቄት ተቀበል ያማረ የተመረጠ ቀጺመት የሚባል ሽቱንም የሁለት መቶ አምሳ ወቄት ምዝን ተቀበል ።

አበሚ የሚባለውንም ሽቱ በቅዱስ ሰቅል ሚዛን አምስት መቶ ወቄት ምዝን ተቀበል፤ የወይራ ዘይትንም በማድጋ አከፋይ አንድ የኢን መሥፈርያ ተቀበል ።

ይኸነንም አዋቂ ያጣፈጠው የተቀደሰ ሽቱ አድርገው ።

ከዚህም ደብተራ ኦሪትን ቀባት፣ በደብተራ ኦሪት ውስጥ ያለች ታቦቷንም ። ዘኍ፣ ፯ ፩ ።

ገበታውንም የገበታውንም ዕቃ ሁሉ ፋና የሚበራበት መቅረዙንም ዕቃውንም ሁሉ ዕጣን የሚታጠንበት ማዕጠንቱንም ቀባ ። ዘሌዋ፡ ፰ ፲ ።

መሥዋዕቱ የሚሠዋበት መሠውያን ዕቃውንም ሁሉ የብርቱ ማስታጠቢያውን ሰን ከመቀመጫው ጋር ቅባው ።

በዚህ ሁሉ አክብራቸው እነሱም የተቀደሱ ይሁኑ እነሱንም የነካቸው የተቀደሰ ይሁን ።

አሮንና ልጆቹን ለኔ መሥዋዕት እንዲሠዉልኝ ቀብተህ አክብራቸው ።

የእስራኤልን ልጆች ይህ የሚቀቡት ሽቱ ለልጅ ልጆቻችሁ ዘመን በናንተ በሌዋውያን መካከል የተለየ ይሁን እናንተ አትቀቡት በላቸው ።

ይህንም ስታደርጉት ከእስራኤል ያልተወለደ ሌላ ሰውነቱ አይቀባ፤ እንደሱም አስመስላችሁ አሁን እንደተናገርኩት ለራሳችሁ አታድርጉ ይህ ሽቱ የተቀደሰ ነውና ።

ከዚህ ሽቱ ዘመዴ ነው ብሎ ለባዕድ ዘመድ የሰጠ ከወገኑ ተለይቶ ይጥፉ (በድንጋይ ተወግሮ) ይሙት ።

እግዚአብሔርም ሙሴን ልበንጃ ሽቱ ያማረ የተወደደ ቀንአት የተባለ ሽቱ የሚያበራ ነጭ ዕጣን ከእስራኤል ተቀበል፤ ሚዛኑም ሁሉ የተካከለ ይሁን ።

ይህንንም ያማረ የተወደደ የዕጣን ሥራ አድርጋችሁ ሠርታችሁ ዕጣን አድርጉት፣ የከበረና የጸራ ሥራ አድርገህም ሥራው ። ዘፀ፡ ፳፱ ፵፪ ።

ከዚህም ዕጣን ወስደህ ፈጭተህና አድቀቀህ ዱቄቱን ከዚያ ላንተ በምገለጥበት ቦታ በደብተራ ኦሪት ፊት አኑረው፤ ይህም ዕጣን ለናንተ ከክቡሩ የከበረ ይሁንላችሁ ።

የዚህንም ዕጣን አምሳያ በበታችሁ ሠርታችሁ አታድርጉ፣ ይህም ለናንተ እርም ይሁንባችሁ፣ ለእግዚአብሔር ግን የከበረ የተለየ ገንዘቡ ይሁን ።

፴፰ ወዘአግበረ እምኔሁ ከመ ያጼንዎ ፡ ለይማስን እም ሕዝቡ ።

ምዕራፍ ፴፩ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ ናሁ ተሰመይኩ በስሙ ለበስልኤል ወልደ ኡሬ ፡ ወልደ ሖር ዘእምነገደ ይሁዳ ።

፪ ወመላእክዎ መንፈሰ ቅዱሰ ፡ ወጥበበ ፡ ወአእምሮ ፡ ወአቁም በኵሉ ምግባር ከመ የሐሊ ።

፫ ወይኩን ሊቀ ጸረብት ፡ ወከመ ይግበር ወርቀ ወብሩረ ወብርተ ፡ ወኀብረ ያክንት ፡ ወኀብረ ሕብድ ፡ ወለይ ክዑብ ፡ ወቢሶስ ክዑብ ።

፬ ወግብረ እብንሂ ዘይትገበር ውስተ ምግባር ፡ ወዘይጸርብ እምዕፅ ፡ ከመ ይግበር እምኵሉ ግብር ።

፭ ወአነ ወሀብኩ ኤልያብሃ ወልደ አክሴምክ ፡ ዘእምነገደ ዳን ።

፮ ወለኵሉ ጠቢበ ልብ ወሀብኩ አእምሮ ወይግበር ኵሎ ዘአዘዝኩከ ።

፯ ደብተራ ዘመርጡል ፡ ወታቦተ ዘኅርመት ፡ ወምሕዋዐ ዘላዕሌሃ ፡ ወንዋየ ለደብተራ ።

፰ ወምሥዋዐ ዘዕጣን ወተቅዋመ ማኅቶት ንጽሕት ፡ ወኵሎ ንዋያ ፡ ወማእደ ወኵሎ ንዋዮ ፡ ወምሥዋዐ ዘመሥዋዕት ፡ ወኵሎ ንዋያቲሁ ወማእከከ ወመንበሮ ።

፱ ወአልባሲሆን ዘክብሩ ለአሮን ፡ ወአልባሰ ደቂቁ ብዘ በቱ ይገብሩ ሊተ ግብረ ።

፲ ወቅብአ ዘይትቀብኡ ፡ ወዕጣነ ዘየዓጥኑ ለመቅደስ ፡ ወኵሎ ዘአዘዝኩከ ይግበሩ ።

፲፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ አንተ አዝዞሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

፲፪ ወበሎሙ ዑቁ ከመ ትዕቀቡ ሰንበትየ ሕስመ ትእምርት ውእቱ በኀቤየ ወበኀቤክሙ ፡ ወበትውልድክሙ ከመ ታእምሩ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ዘእቄድሰክሙ ።

፲፫ ወዕቀቡ ሰንበትየ እስመ ቅድስት ይእቲ ለክሙ ፡ ወዘአርከሳ ሞተ ለይሙት ።

፲፬ ወኵሉ ዘይገብር በቲ ግብረ ለትሠሮ ይእቲ ነፍስ እም ሕዝባ ።

፲፭ ሰዱሰ ዕለተ ተገበር ግብረከ ፡ ወሳብዕት ዕለት ሰንበት ዕረፍት ወቅድስት ለእግዚአብሔር ፡ ወኵሉ ዘይገብር ግብረ በዕለተ ሰንበት ፡ ሞተ እመዊት ለይሙት ።

፲፮ ወይዕቀቡ ደቂቀ እስራኤል ሰንበተ ፡ ከመ ይግበሩ በትውልዶሙ ሥርዓት ይእቲ ለዓለም ሊተ ።

፲፯ ወለደቂቀ እስራኤል ትእምርት ውእቱ ዘለዓለም ፡ እስመ በሰዱስ ዕለት ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ወበሳብዕት ዕለት ፈጸመ ወአዕረፈ ።

ከዚህም ዕጣን በቤቱ ተድላ ደስታ ሊያደርግበት ሊያሸተው (እንደ ቤተ እግዚአብሔር አድርጎ) የሠራ ሰው ከወገኖቹ ተለይቶ ይጥፋ (በእሳት ተቃጥሎ) ።

ምዕራፍ ፴፩ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው ፤ እነሆ በበስልኤል ስም ተጠራሁ ፤ ይህም ከነገደ ይሁዳ የተወለደ የሖር የልጅ ልጅ የኡሬ ልጅ በስልኤል ነው ።

መንፈሰ ረድኤትን ጥበብን ዕውቀትን ሞላሁበት (አሳደርሁበት) እሱም በሥራው ሁሉ የተወሰነ ነው ።

ጠቢብ ጋበዝ አምበል (የአናጢዎች አለቃ) ተሹሞ ሕብረ ወርቁን ብሩን ብርቱን ሰማያዊ ሐሩን ብጫ ሐሩን ዕጽፍ ሁኖ የተፈተለ ቀይና ነጭ ሐሩን ይሠራ ዘንድ ነው ።

በሥራው ሁሉ ተጠርቦ ተለዝቦ የሚሠራ የዲንጋይም ሥራ ከዕንጨትም ወገን የሚጠርበውንና የሚያለዝበውን የዕንጨቱን ሥራ ከሥራ ሁሉ ለይቶ ይሠራ ዘንድ ነው ።

እኔም ከነገደ ዳን የሚሆን የአክሴምክ ልጅ ኤልያብን ሰጠሁ ። ፩ ነገ ፯ ፲፬ ። ኢሳ ፳፰ ፳፮ ።

ያዘዝኩህን ሁሉ ይሠሩ ዘንድ በልቡናቸው ጥበብን እውቀትን ላሳደርሁባቸው ሁሉ እውቀትን ሰጠኋቸው ።

ደብተራ ኦሪትን ሥርዓት ጽንቶበት የሚኖር ታቦቱን መክደኛዋን የደብተራ ኦሪትን ዕቃ ይሠሩ ዘንድ ዕውቀትን ሰጠኋቸው ። ዘፀ ፴፯ ፴፱ ።

ዕጣን የሚታጠንበት ማዕጠንትን ፋናው የሚበራበት የነጻውን መቅረዝ ዕቃውን ሁሉ ገበታውንና ዕቃውን ሁሉ መሥዋዕቱ የሚሠዋበት መሠዊያውንና ዕቃዎቹን ሁሉ መቀለጺንና መቀመጫውን ይሠሩ ዘንድ ።

አሮን የሚከብርባቸውን ልብሶች የኔን ሥራ በሚሠሩ ልጆ ገንዘብ የልጆቹንም ልብሶች ይሠሩ ዘንድ ።

የሚቀቡትን ቅብዐ ክህነት ለቤተ መቅደስ የሚያጥኑትን ዕጣን ሊሠሩትም ያዘዝሁትን ሁሉ ይሠሩ ዘንድ ዕውቀትን ሰጠኋቸው ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ፤ አንተ የእስራኤልን ልጆች (እንዲህ ብለህ) እዘዛቸው ።

የማከብራችሁ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ታውቁ ዘንድ በእኔና በናንተ ዘንድ ለልጅ ልጃችሁ ምልክት ነውና ሰንበቶቼን ፈጽማችሁ ጠብቁ በላቸው ።

ለናንተ የከበረች (በዓል) ስለሆነች ቅዳሜን አክብሯት የሻራትም ሰው ፈጽሞ ይሙት ።

ሥራውንም የሚሠራበት ሁሉ ያች ሰውነት ከወገኖቿ ተለይታ ትጥፋ ። ዘሌዋ ፳፫ ፪ ። ሕዝ ፵፬ ፳፬ ።

ስድስት ቀን ሥራህን ሥራ ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር የተቀደሰች በዓል ናትና ቅዳሜ ቀን ሥራን የሚሠራ ሁሉ ፈጽሞ ይሙት ።

በልጅ ልጆቻቸው ይሠሩት ዘንድ የእስራኤል ልጆች ቅዳሜን ያክብሩ ፤ ለኔም የዘለዓለም ሥርዓቴ ናት ።

ለእስራኤልም ልጆች ለዘለዓለም የገዥና የተገዥ ምልክታቸው ነው እግዚአብሔር በስድስተኛው ቀን ሰማይንና ምድርን ፈጥሮ በሰባተኛይቱ ቀን (ቅዳሜ) ሥራውን

ፈጽሞ ዐርርበታልና ።

፲፰ ወሰበ ፈጸመ ተናግሮ ምስሌሁ በደብረ ሲና ወሀበ ለ
ሙሴ ክልኤተ ጽላተ ዘትእዛዝ ፡ ጽላት ዘእብን ፡ ጽሑፋት
በአጽባዕተ እግዚአብሔር ።

በደብረ ሲና ከሱ ጋራ ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ ዐሥሩ
ቃላት የተጻፈበቸው ሁለቱን ጽላት ለሙሴ ሰጠው ፡ እነዚ
ህም በእግዚአብሔር ጣት በእብን በረድ የተጻፉ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፴፪ ።

፩ ወሰበ ርእዩ ሕዝብ ከመ ጐንደየ ሙሴ ወሪደ እምደ
ብር ተንሥኡ ላዕለ አሮን ወይቤልዎ ግበር ለነ አማልክተ
እለ የሐውሩ ቅድሜነ ፡ እስመ ዝኩ ብእሲ ሙሴ ዘአውጽ
አነ እምድረ ግብጽ ኢነአምር ምንተ ኮነ ።

ሕዝቡም ሙሴ ከደብረ ሲና መውረዱን እንደ ዘገየበ
ቸው በዩ ጊዜ ከግብጽ አገር ያወጣን ወንድምህ ሙሴ
ምን እንደ ሆነ አናውቅምና ፡ በፊታችን የሚሄዱልን ጣላ
ቶቻችንን የሚያጠፉልን አማልክትን ሥራልን ብለው በአ
ሮን ላይ (በጠላትነት) ተነሡበት ። ዘዳግ ፱ ፱ ።

፪ ወይቤሎሙ አሮን ንሥኡ ሠርጐ ወርቅ ዘውስተ አዕ
ዛነ አንስቲያክሙ ወአዋልዲክሙ ወአምጽኡ ኀቤየ ።

አሮንም በሚስቶቻችሁና በሴት ልጆቻችሁ ጆሮዎች
ያለ የወርቅ ጌጣ - ጌጥ ተቀብላችሁ ወደኔ አምጡ አላቸው ።

፫ ወነሥኡ ኵሉ ሕዝብ ሠርጐ ወርቅ ዘውስተ አዕዛነ
አንስቲያሆሙ ወአምጽኡ ኀበ አሮን ።

ሕዝቡም ሁሉ በሚስቶቻቸው ጆሮ የነበረውን የወርቅ
ጌጣ - ጌጥ ሰብረው ወደ አሮን አመጡ ።

፬ ወተመጠወ እምእደዊሆሙ ወመሰሎ በምሳሌ ወገ
ብሮ ላሕመ ዘስብክ ወይቤሎሙ እሉ አሙንቱ አማል
ክቲከ እስራኤል ዘአውጽኡከ እምድረ ግብጽ ።

(አሮንም) ከእጃቸው ተቀብሎ በመቀረጫ ቀረጸው ፡
ቀልጦ የተሠራ ጥጃም አድርጎ እስራኤል !! ከግብጽ አገር
ያወጡህ አማልክቶችህ እሊህ ናቸው አላቸው ።

፭ ወሰበ ርእየ አሮን ነደቀ ምሥዋዐ እንጻሮ ወአሰደ እን
ዘ ይብል በዓለ እግዚእ ጌሠም ።

አሮንም ወደው እንደተቀበሉት ባየ ጊዜ በጣዖቱ
ፊት ለፊት መሠውያን ጸፈጸፈ ፡ (ወድያውም) ነገ የጌታ
በዓል ነው ብሎ አዋጅ አስነገረ ። ፩ ነገ፡ ፲ ፴ ።

፮ ወጌሠ አሮን በጣኒታ ወአዕረገ መሥዋዕተ ወአብአ
ቍርባነ ዘመሥዋዕተ ፍርቃን ፡ ወነበሩ ሕዝብ ይበልዑ
ወይሰትዩ ወተንሥኡ ይዘፍኑ ወይትዋነዩ ።

አሮንም በነገታው ማለዳ ተነሥቶ መሥዋዕቱን አሰረገ
ከመከራ የሚድኑበት ቍርባንም አቀረበ ፡ ሕዝቡም
(በጣዖቱ አጠገብ ተቀምጠው) ተረፈ መሥዋዕቱን ሊበሉ
ሊጠጡ ሊዘፍኑ ሊጫወቱ ተነሡ ። ፩ ቆሮ፡ ፲ ፮ ።

፯ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ሑር ወአፍጥን
ወሪደ እምዝየ ፡ እስመ አበሱ ሕዝብከ ዘአውጻእከ እም
ድረ ግብጽ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው !
ከግብጽ አገር ያወጣኻቸው ወገኖችህ በድለዉኛልና ከዚህ
(ከደብረ ሲና) ፈጥነህ ወርደህ ሂድ ።

፰ ወወጽኡ እምፍኖት ዘአዘዝክዎሙ ወገብሩ ላሕመ
ወሰገዱ ወሦዑ ሎቱ ወይቤሉ ፡ እሉ አሙንቱ አማልክ
ቲከ እስራኤል ዘአውጽኡከ እምድረ ግብጽ ።

እኔ ካዘዝኋቸው ሕግ ሥርዓት ወጥተው በደሉ የላሙ
ንም ምስል ሠርተው አቁመው ሰገዱለት ፡ መሥዋዕቱንም
ሠዉለት ፡ እስራኤል ከግብጽ ያወጡህ አማልክቶችህም
እኒህ ናቸው አሉ ። ፩ ነገ፡ ፲፪ ፳፰ ።

፱ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ፡ ርኢኩ ዘንተ ሕዝበ
ወናሁ ዝንቱ ሕዝብ ግዙፈ ክሳድ ።

እግዚአብሔር ሙሴን ይህን ሕዝብ አየሁት እነሆም
አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው ። ኢሳ፡ ፵፰ ፬ ።

፲ ወይእዜኒ ኅድገኒ እጥፍኦሙ በመዓትየ ፡ ወእሠይመከ
ላዕለ ሕዝብ ክቡድ ወዓቢይ ።

አሁንም ተቈጥቼ ላጥፋቸው ተወኝ ከዚህ በሚበል
ጥና በሚበዛ ወገን ላይ እሾምኻለሁ አለው ።

፲፩ ወሰአለ ሙሴ ቅድመ እምላኩ ወይቤ ለምንት እግዚኦ
መዓተ ትትመዓዕ ላዕለ ሕዝብከ ዘአውጻእከ እምድረ ግብጽ
በኃይል ጽኑዕ ወበመዝራዕት ልዑል ወዐቢይ ።

ሙሴም በፈጣሪው ፊት ቁሞ ጸለየ (ለመነ) አቤቱ ከግ
ብጽ አገር በጽኑ ኃይል በልዑልና በታላቅ ሥልጣን ያወ
ጣኻቸው ወገኖችህን ለምን ተቈጥተህ ታጠፋቸዋለህ አለ ።

፲፪ ከመ ኢይበሉ ግብጽ በእኩይ አውጽኦሙ ከመ ይቅ
ትሎሙ በውስተ አድባር ወከመ ያጥፍኦሙ እምድር ፡ አቍ
ርር መዓተከ ዘተማዐከ ወመሐሬ ኵነ ላዕለ እከዮሙ ለሕ
ዝብከ ።

የግብጽ ሰዎች በተራራው ሊገድላቸው ከዚህ ዓለም
ሊያጠፋቸው (ወገኖቹ እስራኤልን) በክፉ ነገር አወጣቸው
እንዳይሉ የተቈጣህባቸውን ቁጣ አብርድላቸው የወገኖች
ህንም በደል ይቅር በይ ሁን (ይቅር በል) ።

፲፫ ተዘከር አብርሃምሃ ወይስሐቅሃ ወያዕቆብሃ አግብርቲከ
ዘመሐልከ ሎሙ በርእስከ ወትቤሎሙ ፡ ብዙኀ አበዝኀ
ለዘርእክሙ ከመ ከዋክብተ ሰማይ ብዙኀ ፡ ወኵሎ ዘንተ
እሁብ ለዘርእክሙ ወይመልክዋ ለዓለም ።

ከነዓንን ለዘለዓለሙ ሊገዟትና ሊወርሱዋት ዘራች
ሁን እንደ በዙ እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛዋለሁ ፡ ይህን
ንም ሁሉ ለልጆቻችሁ እሰጣቸዋለሁ (ሕያው የ አማንየ
ብለህ) በራስህ የማልክላቸው አገልጋዮችህ አብርሃም ይስ
ሐቅ ያዕቆብን አስብ ። ዕብ፡ ፲፮ ፲፫ ።

፲፬ ወሠረየ እግዚአብሔር በእንተ እኪት ዘይቤ ይግበር

እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ አደርጋታለሁ ብሎ የተ

ላዕለ ሕዝብ ።

፲፭ ወተመይጠ ሙሴ ወወረደ እምደብር ወክልኤ ጽላት ዘትእዛዝ ዘውስተ እደዊሁ ፤ ጽላት ዘእብን ወጽሑፋት እንተ ክልኤቱ ገበዋቲሆን እንተ ለፌኒ ወእንተ ለፌኒ ።

፲፮ ወግብረቶን ግብረተ እግዚእ ፤ ወጽሕፈቶን ጽሕፈተ እግዚአብሔር ውእቱ ፤ ወግሉፋት ላዕለ ጽላት ።

፲፯ ወሰሚዖ ሆሚዖ ቃለ ሕዝብ እንዘ ይጸርሑ ፤ ይቤሎ ለሙሴ ድምፀ ጸብኢት ውስተ ትዕይንት ።

፲፰ ወይቤሎ ሙሴ ኢኮነ ዝንቱ ድምፅ ዘመላእክት እለ ይትኄየሉ ፤ ወኢኮነ ድምፀ መላእክት ዘፀብዕ አላ ድምፀ መልእክቱ ለወይን እሰምዕ አንሰ ።

፲፱ ወሶበ ቀርበ ሙሴ ኀበ ትዕይንት ርእዮ ለውእቱ ላሕም ወተውኔት ወተምዐ ወገደፎን እምውስተ እደዊሁ ለእልክቱ ክልኤ ጽላት ወቀጥቀጦን በታሕተ ደብር ።

፳ ወነሥአ ለውእቱ ላሕም ዘገብሩ ወአውዓዮ በእሳት ወሐረዮ ወአድቀቆ ወዘረዎ ውስተ ማይ ወአስተዮሙ ኪያሁ ለደቂቀ እስራኤል ።

፳፩ ወይቤሎ ሙሴ ለአሮን ምንተ ረሰይከ ዘንተ ሕዝበ ፤ ከመ ታምጽእ ላዕሌሆሙ ኃጢአተ ዓቢየ ።

፳፪ ወይቤሎ አሮን ለሙሴ ኢትትመዓዕ እግዚእ ላዕሌየ ለሊከ ተአምር ግእዘሙ ለእሉ ሕዝብ ።

፳፫ ወሶበ ይቤሉኒ ግበር ለነ አማልክተ እለ የሐውሩ ቅድሜነ እስመ ዝንቱ ሙሴ ዘአውጽአነ እምድረ ግብጽ ኢነአምር ምንተ ኮነ ።

፳፬ ወእቤሎሙ ዘቦ እምኔክሙ ወርቀ አምጽኡ ፤ ወአምጽኡ ወወሀቡኒ ወወረውክዎ ውስተ እሳት ፤ ወወጽአ ዝንቱ ላሕም ።

፳፭ ወሶበ ርእየ ሙሴ ከመ ዓለወ ሕዝብ ፤ እስመ አዕለ ዎሙ አሮን ፤ ወኮኑ ሰሐቀ ለጸላእቶሙ ።

፳፮ ወቆመ ቅድመ ትዕይንት ወይቤ ዘኀረዮ እግዚአብሔር ይምጻእ ኀቤየ ፤ ወተጋብኡ ኀቤሁ ኵሉ ደቂቀ ሌዊ ።

፳፯ ወይቤሎሙ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል አሐዱ አሐዱ ይፁር ሰይፎ ፤ ወሑሩ ወዕግቱ እምአንቀጽ እስከ አንቀጸ ትዕይንት ፤ ወአሐዱ አሐዱ ይቅትል እኅዋሁ ፤ ወአሐዱ አሐዱ ይቅትል ከልአ ፤ ወአሐዱ አሐዱ ይቅትል ዘቅሩቦ ።

፳፰ ወገብሩ ደቂቀ ሌዊ በከመ ይቤሎሙ ሙሴ ፤ ወወድቀ እምሕዝብ ይእተ አሚረ ሠላሳ ምእት ብእሲ ።

፳፱ ወይቤሎሙ ሙሴ ፤ አንፈስክምዎ ዮም ለእግዚአብሔር በእደዊክሙ አሐዱ አሐዱ እምኔክሙ በወልዱ ወበእኁሁ ከመ ትትወሀብ ለክሙ በረከት ።

፴ ወኮነ በሣኒታ ይቤሎሙ ሙሴ ለሕዝብ ፤ አንትሙ ገገ ይክሙ ጌጋየ ዓቢየ ፤ ወይእዜኒ አዐርግ ኀበ እግዚአብሔር

ናገሬትን የከፋይቱን ነገር ይቅር አለ (ተወ) ።

ሙሴም ተመልሶ ከደብረ ሲና ወረደ ፤ ዐሠርቱ ቃላት የተጻፉበቸው ሁለቱም ጽላቶች በእጁ ተይዘው ነበር ፤ ጽላቶቹም የዕንቍ ናቸው እንዚህም በጐናቸው በሁለት ወገን ግራና ቀኝ ዐሠርቱ ቃላት የተጻፉባቸው ናቸው ።

አሠራራቸው የጌታ ሥራ ነው ፤ አጻጻፋቸውም የእግዚአብሔር አጻጻፍ ነው ፤ (ዐሠርቱ ቃላትም) በሁለቱ ጽላቶች ላይ ተቀርጸዋል ፤ (ተጽፈዋል) ።

ኢያሱም የሕዝቡን ጩኸት ሰምቶ ሙሴን በከተማው የሰልፍ ድምፅ አለ (እሰማለሁ) አለው ።

ሙሴም ይህ የምትሰማው ለሰልፍ የሚበረታቱ የአርበኞች ድምፅ አይደለም የተሸናፊዎች ድምፅም አይደለም ድምፀ ፋሕሮ ለወይን) እስራኤል ያልፈላ ፐሽ ጠጅ ጠጥተው የሆነውንና ያልሆነውን ይለፈልፋሉ እሰማለሁ እንጂ አለው ። ዘፀ ፴፩ ፲፰ ።

ሙሴም ወደ ከተማው በቀረበ ጊዜ ጥጃውንና ዘፈኑን አይቶ ተቈጣ ፤ እሊህ ሁለቱን ጽላቶች ከእጆቹ ጥሎ ከተራራው በታች ሰበራቸው ።

የሠሩትንም ጣዖት (ጥጃ) ወስዶ በእሳት አቃጠለው ፤ ፈጭቶም አደቀቀው ፤ ከፈሳሽ ውኃም በጥብጦ ለእስራኤል ልጆች ያኑን አጠጣቸው ።

ሙሴም አሮንን በነሱ ላይ ታላቅ ኃጢአት ልታመጣበቸው ይህን ሕዝብ ለምን እንዲበድል አደረግኸው አለው።

አሮንም ሙሴን እንዲህ አለው ፤ አቤቱ በኔ ላይ አት በሳጭብኝ የኒህ ወገኖች ሥራቸውን አንተው ቅሉ ታውቀዋለህ ።

ከግብጽ አገር ያወጣን ሰው ሙሴ ምን እንደ ሆነ እና ውቅምና በፊት በፊታችን የሚሄዱልን ጠላቶቻችንን የሚያጠፉልን አማልክት ሥራልን ቢሉኝ ።

እኔም ከናንተ ወርቅ ያለው አምጡ አልኳቸው እነሱም አምጥተው ሰጡኝ እኔም እሳት አስነድጄ በዚያ ላይ ጣልሁት ፤ ይህም ጥጃ ወጣ ።

ሙሴም አሮን አስወንጅሏቸዋልና ለጠላቶቻቸውም መዘባበቻ ሁነዋልና ሕዝቡ እንደ ወነጀሉ ፤ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር የወደደው የመረጠው ሰው ወደኔ ይምጣ አለ።

በከተማው መካከል ቆሞ እንዲህ የሌዊም ልጆች ወደሱ ተሰበሰቡ ።

የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር አንዱም አንዱም ሰይፉን በብብቱ ይሸከም ፤ (በወገቡ ይታጠቅ) ከበርም እስከ ከተማው በር ሂዱችሁ ክበቡ ፤ አንዱም አንዱም ወንድሙን ይግደል ፤ አንዱም አንዱም ባልንጀራውን ይግደል አንዱም አንዱም ጎረቤቱን ይግደለው ብሏል አለ ።

የሌዊም ልጆች ሙሴ እንዳላቸው አደረጉ ፤ ያን ጊዜም ከሕዝቡ ሦስት ሺህ ሰው ሞተ ። ፩ ቆሮ ፲ ፯ ።

ሙሴም የእግዚአብሔር በረከቱ ትሰጣችሁ ዘንድ በእጆቻችሁ ከናንተ አንዱም አንዱ ልጁን ወንድሙን በመግደላችሁ ዛሬ እግዚአብሔርን ደስ አሰኛችሁት አላቸው ።

በበነጋው እንዲህ ሆነ ሙሴ ወገኖቹን ታላቅ በደል በድላችኋል ፤ አሁንም አማልጄ ኃጢአታችሁን አስተሠር

ከመ አስተሥሪ ለክሙ ኃጢአትክሙ ።

ይላችሁ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር (ወደ ደብረ ሲና) እወጣለሁ አላቸው ። ፩ ሳሙ፡ ፲፪ ፳ ።

፴፩ ወገብአ ሙሴ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤ ፡ እስእለከ እግዚኦ ፡ ናሁ አበሱ እሉ ሕዝብ አበሳ ዓቢየ ፡ ወገብሩ ሎሙ አማልክተ ዘወርቅ ።

ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ አቤቱ እለምንሃለሁ እነሆ እኒህ ሕዝብ ታላቅ በደል በደሉ የወርቅ አማልክትን ለራሳቸው ሠሩ አለ ።

፴፪ ወይእዜኒ እመ ተኀድግ ሎሙ ዘንተ ኃጢአተ ኅድግ ፡ ወእመ አኮሰ ደምስስ ኪያየ እመጽሐፍከ ዘጸሐፍከኒ ።

አሁንም ይህን ጽኑ በደል (በቸርነትህ) ይቅር ብትላቸው ይቅር በላቸው ያለዚያ ግን ከጻፍከኝ መጽሐፍህ እኔን ደምስሰኝ ። መዝ፡ ፷፱ ፳፰፡ ሮሜ ፱ ፫ ።

፴፫ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ለዘንቱ ዘአበሰ በቅድሜየ እደመስሶ እመጽሐፍየ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው ፤ በፊቴ የበደለኝን ይህን ወገን ከመጽሐፌ አውጥቼ እደመስሰዋለሁ ። አለው ። ዘሌዋ፡ ፳፫ ፴፡ ሕዝ፡ ፲፰ ፬ ።

፴፬ ወይእዜኒ ሑር ወምርሖሙ ለሕዝብየ ውስተ መካን ዘእቤለከ ፡ ወናሁ መልአክየ የሐውር ቅድመ ገጽከ ፡ ወአመ ዕለተ እዋሕዮሙ አገብእ ላዕሌሆሙ ኃጢአቶሙ ።

አሁንም ሂድ እነዚህን ወገኖች መርተህ ወዳልኩህ ቦታ ውሰዳቸው ፡ እነሆም መልአኬ በፊትህ ይሄዳል ነገር ግን (በመዓት) በጐበኘኋቸው ቀን ኃጢአታቸውን በራሳቸው ላይ አመጣባቸዋለሁ ። ዘኍ፡ ፳ ፲፯ ።

፴፭ ወቀተለ እግዚአብሔር እምሕዝብ በእንተ ዘገብሩ ላሕመ ዘገብረ ሎሙ አሮን ።

አሮን ሠርቶ የሰጣቸውን ላም አምላክ አድርገው ስላመለኩ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ወገን ብዙ ሰው ገደለ (አጠፋ)።

## ምዕራፍ ፴፫ ።

፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ሑር ወዕርግ እምዝየ አንተ ወሕዝብከ ዘአውፃእከ እምድረ ግብጽ ፡ ውስተ ምድር ዘመሐልኩ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ እንዘ እብል ለዘርእክሙ እሁብ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው ፤ ለልጆቻችሁ እሰጣታለሁ ብዬ ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ ወደ ማልኩላቸው (ወደ ከነዓን) ከግብጽ አገር ከወጣኸቸው ወገኖችህ ጋር አንተ ከዚህ አገር ወጥተህ ሂድ ።

፪ ወእፌንዎ ለመልአክየ ቅድሜከ ወያወጽኦሙ ለከናኔዎን ወለአሞሬዎን ፡ ወለኬጤዎን ፡ ወለፌርዜዎን ፡ ወለጌርጌሴዎን ፡ ወለኤዌዎን ፡ ወለኢያቡሴዎን ።

መልእክተኛዬንም ከንተ አስቀድሜ ወደ ከነዓን እሰዳለሁ ፡ እሱም ሂዶ ከናኔዎንን አሞሬዎንን ኬጤዎንን ፌርዜዎንን ጌርጌሴዎንን ኤዌዎንና ኢያቡሴዎንን (ከከነዓን አገር) ያወጣቸዋል (ያጠፋቸዋል)።

፫ ወኢያበውአከ ውስተ ምድር እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ ፡ ወኢየዓርግ ምስሌከ በእንተ ሕዝብከ እለ ያገዝፉ ክሣዶሙ ከመ ኢያኅልቆሙ በፍኖት ።

እሱም እየመራ ወስዶ ወተትንና ማርን ወደምታፈሰው ምድር አላገባህም ፡ እኔ ግን የበደሉኝን በደል (አስቤ) በጕዳና እንዳላጠፋቸው ክሣደ ልቡናቸውን ስላጸኑ ወገኖችህ ከፋት ከንተ ጋር አብሬህ አልወጣም አለው ።

፬ ወሰቢ ሰምዑ ሕዝብ ዘንተ ነገረ እኩየ ለሀዉ ላሀ ዓቢየ ።

ሕዝቡም ይህን ክፉ ቃል በሰሙ ጊዜ ጽኑ ልቅሶ አለቀሱ ። ፪ ሳሙ፡ ፲፱ ፳፬ ።

፭ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በሎሙ አንትሙሰ ሕዝብ ዘያገዝፍ ክሣዶ አንትሙ ፡ ዑቁ ከልእተ መቅሠፍተ ኢያምጽእ ላዕሌክሙ ፡ ወአጠፍእክሙ ወይእዜኒ አሰስሉ አልባሰ ክብርክሙ ወሠርጕክሙ ወአርእየክሙ ዘእሬስየክሙ ።

እግዚአብሔር ሙሴን የእስራኤልን ልጆች እንዲህ በላቸው አለው እናንተስ ክሣደ ልቡናውን ያጸና ወገኖች ናችሁ ፡ ከዚህ ቀድሞ ከመጣሁት መቅሠፍት ሌላ መቅሠፍት አምጥቼ እንዳላጠፋችሁ ዕወቁ ተጠንቀቁ ፡ አሁንም ለጣዖቱ በዓል ከብራችሁበት አጊጻችሁበት የዋላችሁበትን ልብስ ከናንተ አስወግዱ ይህን ያደረጋችሁ እንደሆነ የማደርግላችሁን አሳያችኋለሁ ።

፮ ወአሰሰሉ ደቂቀ እስራኤል ሠርጓቲሆሙ ወአልባሲሆሙ በደብረ ኮሬብ ።

የእስራኤልም ልጆች ለጣዖቱ በዓል (ያጌጹበት) ልብሳቸውንና ጌጻቸውን በኮሬብ ተራራ አስወገዱ ፡ (አራቁ)።

፯ ወነሥአ ሙሴ ሐይመቶ ወተከለ አፍአ ርኁቀ እምትዕይንት ፡ ወተሰምየት ደብተራ ዘመርጡል ፡ ወከነ ኵሉ ዘየኀሥሥ ለእግዚአብሔር የሐውር ኀበ ይእቲ ደብተራ ዘአፍአ እምትዕይንት ።

ሙሴም ድንኳኑ ይዞ ከከተማ በአፍአ ራቅ አድርጎ ተከላት ይህችውም ደብተራ ኦሪት ተባለች ያን ጊዜ እግዚአብሔርን በሕግ በአምልኮት የሚሻው ሰው ሁሉ ከከተማ በአፍአ ወደ ተተከለች ወደዚያች ድንኳን ይሄድ ነበር ። ዘኍ፡ ፲፮ ፳፯ ።

፰ ወሰበ የሐውር ሙሴ ይበእ ውስተ ይእቲ ደብተራ ዘአፍአ እምትዕይንት ይቀውም ኵሉ ሕዝብ ወይኔጽር አሐዱ

ሙሴ ከከተማ በአፍአ ራቅ ብላ ወደ ተተከለች ድንኳን ሊገባ በሄደ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ይቆም ነበር እስኪገባም

እሐዱ ኀበ ኆኅተ ደብተራ፡ ወይሬእይዎ ለሙሴ ሶበ የሐ
ውር እስከ ይበውእ ውስተ ደብተራ ።
፱ ወእምከመ ቦአ ሙሴ ውስተ ደብተራ ይወርድ ዓምደ
ዘደመና እንዘ ይቀውም ኀበ ኆኅተ ደብተራ፡ ወይትናገር
እግዚአብሔር ለሙሴ ።
፲ ወይሬእዮ ኵሉ ሕዝብ ለውእቱ ዓምድ ዘደመና እንዘ
ይቀውም ኀበ ኆኅተ ደብተራ፡ ወይትናገር እግዚአ
ብሔር ምስለ ሙሴ፤ ወቀዊሞሙ ኵሉ ሕዝብ ኀበ ኆኅተ
ደብተራሆሙ ይሰግዱ ።
፲፩ ወይትናገር እግዚአብሔር ለሙሴ ገጸ በገጽ ከመ ይት
ናገር ብእሲ ምስለ ዓርኩ፡ ወይገብእ ውስተ ትዕይንት
ወጽሙድስ ሆሴዕ ወልደ ነዌ ወሬዛ ውእቱ ወኢይወጽእ
እምትዕይንት ።
፲፪ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር ናሁ ትቤለኒ ስዶ ለዝ
ንቱ ሕዝብ፡ ወበሕቱ ኢነገርከኒ ዘትፌኑ ምስሌየ፡ ወለሊከ
ትቤለኒ ኪያከ አእመርኩ እምኵሉ ፡ ወረከብከ ሞገሰ
በኀቤየ ።
፲፫ ወለእመሰኬ ረከብኩ ሞገሰ በኀቤከ አስተርእየኒ ገሃደ
ሊተ ወአእምር ወእርአይከ ከመ ይኩነኒ ረኪበ ሞገስ
በቅድሜከ ዮም፡ ወከመ አእምር ከመ ሕዝብከ ውእቱ ዝ
ንቱ ሕዝብ ዓቢይ ።
፲፬ ወይቤሎ እግዚአብሔር አነ አሐውር ቅድሜከ ወአዐ
ርፈከ ።
፲፭ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር እመ አንተ ለሊከ ኢተ
ሐውር ስሌነ ወኢታወጽአነ እምዝየ፡ በምንት ይትዓ
ወቅ ከመ አማን ረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ አነኒ ወሕዝብ
ከኒ ዘእንበለ ሶበ ሖርከ ምስሌነ ።
፲፮ ወንከብር አነኒ ወሕዝብከኒ በኀበ ኵሉ አሕዛብ ዘሀሎ
ውስተ ኵሉ ምድር ።
፲፯ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ዘንተኒ ነገረ ዘትቤለኒ
እገብር ለከ፡ ወረከብከ ሞገሰ በቅድሜየ ወአአምረከ እም
ኵሉ ።
፲፰ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር አርእየኒኬ ስብሐቲከ ።
፲፱ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ አነ አኀልፍ ቅድሜከ
በስብሐትየ ወእጼውዕ ስመ እግዚአብሔር በቅድሜከ ወእ
ምሕሮ ለዘመሐርክዎ፡ ወእምህሮ ለዘተሣሀልክዎ ።
፳ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ርእዮተ ገጽየሰ ኢት
ክል እስመ አልቦ ዘይሬኢ ገጽየ ወየሐዩ ።
፳፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ናሁ መካን ኀቤየ ሀሎ
ወትቀውም ውስተ ኰኵሕ፡ እስከ የኀልፍ ስብሐትየ ።
፳፪ ወአነብረከ ውስተ ስቍረተ ኰኵሕ ወእከድን እዴየ
በላዕሌከ እስከ አኀልፍ ።
፳፫ ወአሴስል እዴየ ወይእተ ጊዜ ትሬኢ ድኅሬየ፡ ወገጽ
የሰ ኢያስተርኢ ለከ ።

ድረስ በሚሄድበት ጊዜ አንዱም አንዱ በድንኳኑ ደጃፍ
ሁኖ ሙሴን ያየው ነበር ። መዝ፡ ፺፱ ፯ ።
ሙሴም ወደ ድንኳኑ ከገባ በኋላ ዓምደ ደመና ወርዶ
በድንኳኑ ደጃፍ ይቆም ነበር፡ እግዚአብሔርም ሙሴን
ቃል ለቃል ይነጋገረው ነበር ።
ያንንም ዓምደ ደመና በድንኳኑ ላይ ቆሞ ሕዝቡ ሁሉ
ያየው ነበር፡ እግዚአብሔርም ከሙሴ ጋር ቃል ለቃል
ይነጋገር ነበር፡ ሕዝቡም ሁሉ በየድንኳናቸው ቁመው
(ለጌታ) ይሰግዱለት ነበር ። ዘዳግ፡ ፭ ፳፬ ።
እግዚአብሔርም ሙሴን ሰው ከወዳጁ ጋር እንደሚነ
ጋገር ፊት ለፊት ይነጋገረው ነበር፡ (ከተነጋገረውም በኋላ)
ወደ ከተማው ይመለስ ነበር፡ አገልጋዩ የነዌ ልጅ ሆሴዕ
ግን ገና ሕፃን ነበርና ከከተማው አይወጣም ነበር ።
ሙሴም እግዚአብሔርን እነሆ ይህንን ሕዝብ አንተ
መርተህ ውሰደው አልከኝ፡ ነገር ግን አንተ ከኔ ጋር የም
ትልከውን ሰው አልነገርከኝም፡ አንተ ከሁሉ ይልቅ አን
ተን ወደድኩህ፡ በኔ ዘንድ በለሟልነትን አገኘህ አልከኝ
በንተም ዘንድ በልሟልነትን ካገኘሁ ፊትህን ገልጠህ አሳ
የኝ፡ ለኔም ዛሬ በንተ ዘንድ በልሟልነትን ማግኘት ይሆነኝ
ዘንድ ይህም ወገንህ በንተ ዘንድ የከበረ ወገን እንደሆነ ዐ
ውቅ ዘንድ ፊትህን አይህ ዘንድ ገልጠህ አሳየኝ አለው ።
እግዚአብሔርም እኔ በፊትህ እሄዳለሁ አሳርፍህ
ማለሁ አለው ። ዘፀ፡ ፴፬ ፱ ።
ሙሴም እግዚአብሔርን እንዲህ አለው አንተው ራስህ
ከኛ ጋራ ካልሄድክ ከዚህ ቦታም ካላወጣኸን አንተ ከኛ
ጋራ ብትሄድ ነው፡ እኛም በንተ ዘንድ በልሟልነትን ቁና
ገኘ ነው እንጂ እኔም ሆንኩ ወገኖችህ (እስራኤል) በንተ
ዘንድ በለሟልነትን እንዳገኘሁ በምን ይታወቅ፤ አለው ።
አንተ ከኛ ጋራ ከሄድክ ግን እኔም ወገኖችህ (እስራ
ኤል) በዚህ ዓለም ላይ ባሉ አሕዛብ ሁሉ ዘንድ እንከብራ
ለን አለው ።
እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፤ በኔ ዘንድ
በለሟልነትን አግኝተኻልና ከሁሉም ለይቼ ወድጄኻለሁና
ያነን ያልከኝን ነገር አደርግልኻለሁ አለው ።
ሙሴም እግዚአብሔርን ጌትነትህን (ገልጠህ) አሳየኝ
አለው ። ኤር፡ ፴፩ ፲፬ ። ሮሜ ፬ ፬፡ ፱ ፲፭ ።
እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ እኔ በፊትህ
የጌትነቴን ስም እየጠራሁ በፊትህ አልፋለሁ የምምረውን
እምረዋለሁ ይቅር የምለውንም ይቅር እለዋለሁ ።
እግዚአብሔርም ሙሴን ፊቴን አይቶ የሚድን የለምና
ፊቴንስ ማየት አትችልም አለው ።
እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው እነሆ በኔ ዘንድ
ቦታ አለ፡ የጌትነቴም ቃል ተነግሮ እስኪፈጸም ድረስ በአ
ለቱ ላይ ትቆመጣለህ ። ኢሳ፡ ፪ ፳፩ ።
በአለቱም ውስጥ አኖርኻለሁ፡ የጌትነቴንም ነገር ተና
ግሬ እስካልፍ ድረስ እጄን በላይህ እጋርዳለሁ (በሥልጣኔ
እሠውርኻለሁ) ።
(በዋሻው ውስጥ ሳለህ) እጄን ካንተ ላይ አነሣለሁ ያን
ጊዜ ኋላዬን ታያለህ፡ ፊቴን ግን አታየውም ዮሐ፡ ፩ ፲፰ ።

## ምዕራፍ ፴፬ ።

፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ቀርር ለከ ክልኤተ ጽላ
ተ ዘእብን በከመ ቀዳምያት ፡ ወዕርግ ኀቤየ ውስተ ደብር
ወእጽሕፍ ውስተ ውእቶን ጽላት ዝከተ ነገረ ዘሀሎ ውስተ
ቀዳምያት ጽላት ዘቀጥቀጥከን ።

፪ ወኩን ድልወ ለነግህ ፡ ወተዓርግ ውስተ ደብረ ሲና
ወቁም ህየ ላዕለ ርእሰ ደብር ።

፫ ወአልቦ ዘየዓርግ ምስሌከ ፡ ወአልቦ ዘይሄሉ ውስተ
ኵሉ ደብሩ ወአባግዕኒ ወአልሕምትኒ ኢይትረዐዩ ቅሩበ
ለውእቱ ደብር ።

፬ ወወቀረ ሙሴ ክልኤ ጽላተ ዘእብን በከመ ቀዳምያት ፡
ወነሥአ በእዴሁ ክልኤተ ክልኤ ጽላተ ዘእብን ፡ ወጌሠ
በጽባሕ ወዓርገ ሙሴ ውስተ ደብረ ሲና ፡ በከመ አዘዞ
እግዚአብሔር ።

፭ ወወረደ እግዚአብሔር በደመና ወቆመ ህየ ወጸውዐ
በስመ እግዚአብሔር ።

፮ ወኀለፈ እግዚእ ቅድመ ገጹ ፡ ወስምየ እግዚእ እግ
ዚአብሔር መሐሪ ወመስተሣህል ፡ ርኁቀ መዓት ወብዙኀ
ምሕረት ወጻድቅ ።

፯ ዘየዓቅብ ለጽድቅ ወይገብር ምሕረተ ለአእላፍ ወዘያሴ
ስል ዓመፃ ወጌጋየ ወኃጢአተ ፡ ወለመአብሰሰ ኢያነጽሖ ፡
ዘያገብእ ኃጢአተ አበው ላዕለ ውሉድ ወላዕለ ውሉደ ው
ሉድ እስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ ።

፰ ወጐጕአ ሙሴ ወደነነ ውስተ ምድር ወሰገደ ለእግዚ
ብሔር ።

፱ ለእመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ ይሑር እግዚእየ
ምስሌየ ፡ እስመ ዝንቱ ሕዝብ ጽኑዐ ክሣድ ውእቱ ፡ ወተ
ሣሃል ኃጣውአ ወአበሳሁ ለሕዝብከ ፡ ወንኩን ለከ ።

፲ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ናሁ አነ እሠይም ለከ
ኪዳነ በቅድመ ኵሉ ሕዝብከ ወእገብር ለከ ዓቢያተ ወክ
ቡራተ ዘኢኮነ ከማሁ ውስተ ኵሉ አሕዛብ ወውስተ ኵሉ
ምድር ፡ ወይሬኢ ኵሉ ሕዝብ እለ ውስቴቶሙ ሀሎከ ግ
ብሮ ለእግዚአብሔር ፡ እስመ መድምም ውእቱ ዘአነ እገ
ብር ለከ ።

፲፩ ወዑቅ አንተ ብሕቱ ኵሉ ዘአነ እኤዝዘከ ፡ ወናሁ አነ
አወጽአሙ እምቅድመ ገጽክሙ ለከናኔዎን ወለአሞሬዎን
ወለኬጢዎን ወለፌርዜዎን ወለኤዌዎን ወለኢያቡሴዎን ።

፲፪ ወዑቅ አንከ ርእሰከ ፡ ከመ ኢትትመሐል ምስለ እል
ከቱ ሰብእ እለ ይተርፉ ውስተ ይእቲ ምድር እንተ ውስ
ቴታ ትበውኡ ፡ ከመ ኢይኩን ጌጋይ ላዕሌክሙ ።

፲፫ ወምሥዋዓቲሆሙ ንሥቱ ፡ ወምስላቲሆሙ ስብሩ ፡
ወአእዋሞሙ ግዝሙ ፡ ወግልፎ አማልክቲሆሙ አውዕዩ

## ምዕራፍ ፴፬ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው ፤ እንደ ፊተኞቹ
ሁለት የእብን በረድ ጽላቶችን ቀርጸህ ወደ ደብረ ሲና
ወደኔ ውጣ ፡ በሰበርካቸው በቀደሙት ሁለት ጽላቶች
ተጽፎ የነበረውን ያን ዐሥርቱ ቃላትን በነዚያ ጽላቶች ላይ
እጽፋለሁ ። ዘዳግ፡ ፲ ፩ ።

ለነገም የተዘጋጀህ ሁን ነገ ይህን ጊዜ እኔ ወዳለሁበት
ወደ ደብረ ሲና ወጥተህ በተራራው ራስ ላይ ቁም ።

ካንተ ጋር የሚወጣ ሰው የለም (አይኑር) በተራራ
ውም ዙርያ ሁሉ የሚኖር ሰው አይኑር ፡ (ሰንኳን ሰው)
ላሞችና በጎች ስንኳ በተራራው አቅራቢያ አይሠማሩ
አሰው ።

ሙሴም እንደ ቀደሙት ሁለት የእብን በረድ ጽላቶች
ቀርጾ እነዚያን ሁለት የእብን በረድ ጽላቶች በእጁ ይዞ
እግዚአብሔር እንዳዘዘው ጧት ተነሥቶ ገስግሶ ወደ
ደብረ ሲና ወጣ ።

እግዚአብሔር በደመና ወርዶ በዚያ (በደብረ ሲና)
ቆመ ፡ ገዥ የሚሆን ስሙንም እግዚአብሔር ብሎ ጠራ ።

ያን ጊዜ ጌታ እግዚአብሔር ስሜ መሐሪ ፡ ይቅር ባይ
ከመዓት የራቀ ፡ ምሕረቱ የበዛ እውነተኛ ነው እያለ
በሙሴ ፊት አለፈ ። ኢዩ፡ ፪ ፲፫ ። ሮሜ ፪ ፬ ።

(እውነትን) የሚጠብቃት እሱ ነው ፡ ለብዙሰዎች ይቅ
ርታን፡ ግፍን በደልን ኃጢአትን ከሰው የሚያርቅ እሱ
ነው ፡ በደለኛውን ግን ከፍዳ አያነጻውም ፡ ያባቶችን ኃጢ
አት በልጆች ፡ የልጆችንም ኃጢአት በልጅ ልጆች ላይ
እስከ ሦስት እስከ አራት ትውልድ ድረስ የሚያመጣ
እሱ ነው ።

ሙሴም ይህን ሰምቶ ፈጥኖ ወደ ምድር ወድቆ ለእ
ግዚአብሔር ሰገደ ። ኤር፡ ፴፪ ፲፰ ።

ሙሴ እግዚአብሔርን እንዲህ አለው ፤ በፊትህ ባለሟ
ልነትን አግኝቼ እንደሆነ አንተ ጌታዬ ከኔ ጋር ሂድልኝ ፡
ይህ ወገን ክሣደ ልቡናውን ያጸና ነውና ፡ አንተ ግን የዚ
ህ ሕዝብ በደሉን ኃጢአቱን ይቅር በለው ፡ (ይህን) ያደረ
ግህለት እንደሆነ እኛም ላንተ እንሆናለን (እንገዛለን) ።

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው ፤ በወገኖችህ
ሁሉ ፊት እነሆ ቃል ኪዳን አደርግልኻለሁ (ብርሃኔን በፊ
ትህ እስልብኻለሁ) በዚህ ዓለም ሁሉ እንደሱ ተደርጎ የማ
ያውቅ በሕዝቡም በአሕዛቡም ዘንድ ተደርጎ የማያውቅ
ታላቅና ድንቅ ተአምራቱን አደርግልኻለሁ ይህም እኔ የማ
ደርግልህ ተአምራት ድንቅ ነውና አንተ ያለህበትም ሕዝ
ብ ሁሉ (የኔን) የእግዚአብሔርን ሥራ ያያል ።

ነገር ግን አንተ እኔ የማዝህን ሁሉ ዕወቅ ፡ እነሆ እኔ
አሞሬዎንን ኬጢዎንን ፌርዜዎንን ጌርጌሴዎንን ኤዌዎን
ንና ኢያቡሴዎንን ከፊታችሁ አውጥቼ እሰዳቸዋለሁ ።

እንግዲህም ወዲህ በናንተ ላይ ዕዳ በደል እንዳይሆን
በችሁ ወደ ምትገቡበት ወደዚያች አገር ከሞት ከቀሩ ሰ
ዎች ጋራ እንዳትማማል ራስህን ዕወቅ (ጠብቅ) ።

መሠውያዎቻቸውን አፍርሱ ምስሎቻቸውንም ስበሩ ፡
የሚያመልኩባቸው ዛፎቻቸውን ቍረጡ ፡ (ዓይን እጅ እግ

| | | |
|---|---|---|
| በእሳት ። | | ር) የተቀረጹባቸው ጣዖቶቻቸውን በእሳት አቃጥሉ ። |
| ወኢትስግዱ ለካልእ አምላክ ፡ እስመ እግዚአብሔር ቀናኢ ስሙ ፡ ወእግዚአብሔር ቀናኢ ውእቱ ። | ፲፬ | የእግዚአብሔር ስሙ ቀናተኛ ስለሆነ እግዚአብሔርም ለአምላክነቱ ቀናተኛ ነውና ለሌላ አምላክ አትስገዱ ። ዘፀ ፡ ፳ ፭ ፡ ኢሳ ፡ ፶፯ ፲፭ ። |
| ዮጊ ትትማሐሉ ምስለ እለ ይነብሩ ውስተ ይእቲ ምድር ወትዜምዉ ድኅረ አማልክቲሆሙ ፡ ወትሠውዑ ለአማልክቲሆሙ ፡ ወይጼውዑከ ወትበልዕ እመሥዋዕቶሙ ። | ፲፭ | በዚያች ምድር ከሚኖሩ ሰዎች ጋራ እኩ ትማማሉ ይሆናል ፡ አማልክቶቻቸውን ተከትላችሁ በጣዖት አሰክት ሰስኑ ለጣዖቶቻቸውም ትሠዉላቸው ይሆናል ፡ ወይም እኩ ለጣዖቱ በዓል ይጠሩህና ሂደህ ተረፈ ጣዖቱን ትበላ ይሆናል ። ፩ ቆሮ፡ ፰ ፩ ፡ ፲ ፴፯ ። |
| ወትነሥእ እምአዋልዲሆሙ ለደቂቅከ ፡ ወአዋልዲከ ትሁብ ለደቂቆሙ ፡ ወያዜምዋሆሙ ለደቂቅከ ድኅረ አማልክቲሆን ፡ ወይዜምዋ አዋልዲከ ድኅረ አማልክቲሆሙ ። | ፲፮ | ሂደህም ሴቶች ልጆቻቸውን አጭተህ ለወንዶች ልጆችህ ሴቶች ልጆችህን ወስደህ ለወንዶች ልጆቻቸው ታጋበለህ ፡ ያገቡዋቸውም የአሕዛብ ሴቶች ጣዖቶቻቸውን ተከትለው እንዲሰስኑ ያደርጓቸዋል ሴቶች ልጆችህም ጣዖቶቻቸውን ተከትለው እንዲሰስኑ ያደርጓቸዋል (እንዳያደርጓቸው ተጠንቀቅ) ። ዘኍ ፡ ፳፭ ፩ ፡ ዕዝ፡ ፱ ፪ ። |
| ወአማልክተ ዘስብክ ኢትግበር ለከ ። | ፲፯ | ተመትተው የተሠሩትን ጣዖቶች ላንተ አታድርግ ፡ (ሠርተህ አታምልክ) ። ዘፀ ፡ ፳፫ ፲፭ ። |
| ወሕገ ፍእት ዕቀብ ፡ ሰቡዐ መዋዕለ ብላዕ ናዕተ በከመ አዘዝኩከ በዘመኑ በወርኀ ሚያዝያ ፡ እስመ በወርኀ ሚያዝያ ወጻእከ እምድረ ግብጽ ። | ፲፰ | ቂጣ የምትበሉበት የበዓሉን ሕግ ጠብቅ ፡ ከግብጽ አገር በሚያዝያ ወር ወጥተኻልና በሚያዝያ ወር በዘመኑ ሥርዓቱን ጠብቅ ብዬ እንዳዘዝኩህ ሰባት ቀን ቂጣ ብላ ። |
| ወኵሉ ትበዕት ዘይፈትሕ ማኅፀነ ሊተ ውእቱ ፡ በኵሩ ለላሕም ፡ ወበኵሩ ለበግዕ ፡ ወበኵሩ ለአድግ ። | ፲፱ | መጀመሪያ የተወለደ ወንድ ወንዱ በኵር ልጅም ለኔ ነው ፡ የላሙም የበጉም የአህያውም በኵር የኔ ነው ። |
| ወለበኵረ አድግሰ ትቤዝዎ በበግዕ ፡ ወእመሰ ኢቤዘ ውክሁ ሤጠ ትሁብ ፡ ወኵሎ በኵረ ውሉድከ ትቤዙ ወኢታስተርኢ ቅድሜየ ዕራቀከ ። | ፳ | የአህያውን በኵር ግን በበግ ለውጠው ፡ በበግ ክልለ ወጥከውም ሽጠህ ዋጋውን ስጥ ፡ የበኵር ልጅህንም ሁሉ ዋጋውን ሰጥተህ ተበዥተህ አስቀረው በፊቴም ባዶ እጅህ አትታይ ፡ (መባእህን ይዘህ ግባ) ። |
| ሰዱሰ መዋዕለ ትገብር ግብረከ ፡ ወበሳብዕት ዕለት ተዓርፍ ፡ ወታዓርፍ ዘርአ ወዓፂደ ። | ፳፩ | ስድስት ቀን እረስ ቈፍር ፡ በሰባተኛው ቀን ግን ዕረፍ ፡ ከመዝራትም ከማጨድም ዕረፍ ። |
| ወበዓለ ሰንበት ትገብር ሊተ ፡ አመ ይቀድሙ ዓፂደ ሥርናይ ፡ ወበዓለ ምኵራብ ። | ፳፪ | (ሰዎች) አስቀድመው ሥንዴውን በሚያጭዱበት ወራት በሱባዔ በሚከብር በዓል እሸት ነዶውን ይዘህ መጥተህ ለኔ በዓል አድርግልኝ ፡ በዓለ መጸለትንም አድርግልኝ ። |
| ሠለስተ ጊዜያተ ማእከለ ዓመት ያስተርኢ ኵሉ ተባዕትከ ቅድመ ታቦተ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ። | ፳፫ | ወንድ ወንዱ ሁሉ ለገቢረ በዓል እየወጣ በእስራኤል ፈጣሪ በእግዚአብሔር ማደርያ ፊት በዓመት ሦስት ጊዜ ያክብር ። |
| ወአመ አወፅአሙ ለአሕዛብ እምቅድመ ገጽከ እሰፍሖን ለአድዋሊከ ፡ ወአልቦ ዘይፈትዋ መኑሂ ለምድርከ ። | ፳፬ | አሕዛብን ከፊትህ አስወጥቼ በሰደድኳቸው ጊዜ አውራጃዎችህን አሰፋቸዋለሁ ፡ አገርህንም የሚመኛት ማንም ማን የለም ። |
| ወሰበ ተዓርግ ሠለስተ ጊዜያተ በዓመት ታስተርኢ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ኢትዝባሕ ላዕለ ደም ብኁዕ መሥዋዕትየ ። | ፳፭ | በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታየት በዓመት ሦስት ጊዜ ስትወጣ መሥዋዕቴን በአደረ ደም አትሠዋ ። |
| ወኢይቢት ለነግህ መሥዋዕተ በዓል ዘፋሲካ ። | ፳፮ | የፋሲካው በዓል መሥዋዕትም ለነገ አይደር ። |
| ቀዳሜ እክለ ምድርከ ትወስድ ቤተ እግዚአብሔር አምላክከ ፡ ወኢታብስል በግዐ በሐሊበ እሙ (እንዘ ይጠቡ ሐሊበ እሙ) ። | ፳፯ | መጀመሪያ ከእርሻህ የተገኘውን እኽል ወደ ፈጣሪህ ወደ እግዚአብሔር ቤት ውሰድ ፡ በጉንም በናቱ ቅቤ አትቀቅል ። ዘዳግ፡ ፳ ፪ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ጸሐፍ ለከ ዘንተ ነገረ እስመ በዝንቱ ነገር አቀውም ኪዳነ ለከ ወለእስራኤል ። | ፳፰ | እግዚአብሔርም ሙሴን በዚህ ነገር ለአንተና ለእስራኤል ቃል ኪዳኔን አጸናለሁና ይህንን ነገር ጻፍ አለው ። |
| ወነበረ ሙሴ ቅድመ እግዚአብሔር አርብዐ መዓልተ ወአርብዓ ሌሊተ ኢበልዐ እክለ ፡ ወኢሰትየ ማየ ፡ ወጸሐፈ እግዚአብሔር ውስተ ጽላት ዘንተ ነገረ ዐሠርተ ቃላተ ። | ፳፱ | ሙሴም አርባ ቀን ፡ አርባ ሌሊት (በደብረ ሲና) ከእግዚአብሔር ጋር ኖረ ፡ እንጀራንም አልበላም ፡ ውኃንም አልጠጣም ፡ እግዚአብሔር ቀድሞ በሁለቱ ጽላቶች ተጽ |

፳፱ ወሶበ ወረደ ሙሴ እምደብረ ሲና ወሀለዋ ክልኤቲ ጽላት ውስተ እደዊሁ፤ ወእንዘ ይወርድ እምደብር ኢያእመረ ከመ ተሰብሐ ኅብረ ገጹ እንዘ ይትናገር ምስለ እግዚአብሔር ።

፴ ወሶበ ርእይዎ አሮን ወኵሉ ደቂቀ እስራኤል ለሙሴ ከመ ተሰብሐ ርእየተ ኅብረ ገጹ ፈርሁ ቀሪቦቶ ።

፴፩ ወጸውዖሙ ሙሴ ወገብኡ ኀቤሁ አሮን ወኵሉ መኳንንተ ትዕይንት ወተናገሮሙ ሙሴ ።

፴፪ ወእምድኅረ ዝንቱ ቀርቡ ኀቤሁ ኵሉ ደቂቀ እስራኤል ወአዘዞሙ ኵሎ ዘተናገሮ ለእግዚአብሔር በደብረ ሲና ።

፴፫ ወሶበ አኅለቀ ተናግሮቶሙ ወደየ ሳዕለ ገጹ ግልባቤ በዘይሜውር ገጾ ።

፴፬ ወሶበ የሐውር ሙሴ ቅድመ እግዚአብሔር ከመ ይትናገሮ ያሴስል ግልባቤሁ እስከ ይወጽእ፤ ወእምከመ ወጽአ ይነግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ኵሎ ዘአዘዞ እግዚአብሔር ።

፴፭ ወርእዩ ደቂቀ እስራኤል ከመ ተሰብሐ ገጹ ለሙሴ ወከመ ወደየ ግልባቤ በዘይሜውር ገጾ እንዘ ይወጽእ ከመ ይትናገሮሙ ።

## ምዕራፍ ፴፭ ።

፩ ወአስተጋብኦሙ ሙሴ ለኵሉ ማኅበረ ደቂቀ እስራኤል ወይቤሎሙ፤ ዝንቱ ውእቱ ነገር ዘይቤ እግዚአብሔር ከመ ትግበርዎ ።

፪ ሰዱስ መዋዕለ ትገብሩ ግብረክሙ ወበሳብዕት ዕለት ታዕርፉ ቅድስት ሰንበት፤ ዕረፍት ለእግዚአብሔር፤ ኵሉ ዘይገብር ባቲ ግብረ ለይሙት ።

፫ ወኢታንድዱ እሳተ በውስተ ኵሉ ማኅደርክሙ በዕለተ ሰንበትየ ።

፬ ወይቤሎሙ ሙሴ ለኵሉ ማኅበረ ደቂቀ እስራኤል እንዘ ይብል ዝንቱ ውእቱ ቃል ዘአዘዘ እግዚአብሔር እንዘ ይብል ።

፭ ንሥኡ እምኔሆሙ መባአ ለእግዚአብሔር፤ ኵሉ ዘሐለየ ልበሙ ያምጽኡ እምቀዳሚ ንዋዮሙ እምወርቅ ወእምብሩር ወእምብርት ።

፮ ወያክንት ወኅብረ ከብድ፤ ወለይ ክዑብ፤ ወቢሶስ ፍቱል፤ ወፀጕረ ጠሊ ።

፯ ወማእሰ በግዕ ግቡረ መሐን፤ ወመሐነ መጸጸት ወዕፀ ዘኢይነቅዝ ።

፰ ወቅብዐ ለማኅቶት፤ ወአፈዋተ ለተቀብዖ፤ ወዕጣነ ለማዕጠንት ።

፱ ወአእባነ መረግድ፤ ወአእባነ ዘይትኌረው ለኤፉድ ወለሎግዮ ።

፲ ወኵሎሙ ጠቢባነ ልብ ዘውስቴትክሙ ይምጽኡ ወይግበሩ ኵሎ ዘአዘዘ እግዚአብሔር ።

፲፩ ደብተራ፤ ወሥቃቲሃ፤ ወመክደና ወናፃፃቲሃ፤ ወአዕ

ፊው የነበሩ በሠርቱ ቃላትን ዳግመኛ በሁለቱ ጽላቶች ጻፈ፤ (በግብር አምላካዊ ጻፈለት)።

ሙሴም ከደብረ ሲና በወረደ ጊዜ ሁለቱ ጽላቶች በእጆቹ ተይዘው ነበር፤ ከደብረ ሲናም ሲወርድ በደብረ ሲና ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር በፊቱ ብርሃን እንደ ተሣለበት አላወቀም ነበር። ዘፀ፡ ፴፱ ፲፰ ።

አሮንና የእሥራኤልም ልጆች ሁሉ ሙሴን በፊቱ ኅብረ መልክዐ ብርሃን ተሥሎበት በዩት ጊዜ ወደሱ መቅረቡን ፈሩ።

ሙሴም ጠራቸው፤ አሮንና የከተማው መኳንንትም ሁሉ ወደሱ ተመለሱ፤ ሙሴም ተነጋገራቸው ።

ከዚህም በኋላ የእስራኤል ልጆች ሁሉ ወደርሱ ቀረቡ እግዚአብሔር በደብረ ሲና የተነጋገረውን ሁሉ (አድርጉ ብሎ) አዘዛቸው ። ዘፀ፡ ፳፬ ፫ ።

ይህንም ነግሯቸው ከጨረሰ በኋላ ፊቱን የሚሠውር በትን መሸፈኛ በፊቱ ላይ አደረገ። ፪ ቆሮ፡ ፫ ፲፫ ።

ሙሴ እግዚአብሔርን ሊነጋገረው በሄደ ጊዜ ከደብረ ሲና እስኪወጣ ድረስ (መሸፈኛውን) ከራሱ ላይ ያወርድ ነበር፤ ከወጣም በኋላ እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ ለእስራኤል ልጆች ይነግራቸው ነበር።

የእስራኤልም ልጆች የሙሴ ፊቱ እንደበራ ሊነግራቸውም (ከደብረ ሲና) ሲወጣ ፊቱም በሚሠውርበት መሸፈኛ እንደሠወረ አዩ።

## ምዕራፍ ፴፭ ።

ሙሴ የእስራኤልን ልጆች ማኅበር ሁሉ ሰብስቦ ልታደርጉት እግዚአብሔር የተናገረው ነገር ይህ ነው አላቸው።

ስድስቱን ቀን ሥራችሁን ሥሩበት፤ በሰባተኛው ቅዳሜ ቀን ግን ታርፉ ዘንድ ለእግዚአብሔር የተቀደሰች የዕረፍት በዓል ናት ሥራን የሚሠራበት ሁሉ ይሙት።

ቅዳሜ ቀን በየቤታችሁ ሁሉ (ዕንጨት ሰብራችሁ ፈልጣችሁ) እሳት አታንድዱ። ዘፀ፡ ፲፮ ፳፫ ።

ሙሴ የእስራኤልን ልጆች ወገኖች ሁሉ እንዲህ ሲል ነገራቸው፤ እግዚአብሔር አድርጉት ብሎ ያዘዘው ቃል ይህ ነው። ዘፀ፡ ፳፭ ፩-፪።

እናንተ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መባን ከነሱ ተቀበሉ፤ እነሱ ከደገኛው ገንዘባቸው ልቡናቸው ያሰበውን ሁሉ ከወርቅም ከብርም ከናስም ያምጡ።

ሰማያዊም ሐምራዊም ቀይ ግምጃም ጥሩ በፍታም የፍየል ጠጕር።

ቀለም የገባ የበግ ቁርበት (በሕረ ማሪብ) ሰማያዊ ቁርበት የማይነቅዝም ዕንጨት።

ዘይትም ለመብራት፤ ሽቱም ለመቀበት ለጣፋጭ ዕጣን ቅመም።

የመረግድ ዕንቆች ለኤፉድና ለደረት ኪስ የሚሆን የተበሳ እብነ በረድ (ፈርጥ) ያምጡ።

ከናንተም ዘንድ ያሉ በልባቸው ብልሃተኞች የሆኑ ሁሉ መጥተው እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ ያድርጉ።

ማደሪያው ድንኳኑን ማልበሻውን መክደኛውን መያ

| | | |
|---|---|---|
| ማዲሃ፡ ወመናሥግቲሆን ። | | ገሮዎቹን ምሰሶዎቹን መወርወሪያዎቹን ። |
| ወታቦተ ዘመርጡል፡ ወመፃውሪሃ፡ ወተድባበ ወመንጦላዕተ ዘምሥዋር ። | ፲፪ | ታቦቱን መሎጊያዎቹን የሥርየት መክደኛውን የሚጋርደው መጋረጃውን ። ዘፀ፡ ፴ ፪፡ ዕብ፡ ፱ ፪ ። |
| ወአዕማዲሃ፡ወምዕማዲሆን፡ወማእደ፡ወመፃውርቲሁ፤ | ፲፫ | አዕማዶቹን ምዕማዶቹን ገበታውን መሸከሚያዎቹን። |
| ወኵሎ ንዋያቲሁ፡ ወተቅዋመ ማኅቶት ። | ፲፬ | ዕቃውን ሁሉ መብራት የሚያበሩበት መቅረዙን ። |
| ወኵሎ ንዋያ፡ ወመኅትዊሃ፡ ወቅብዐ ማኅቶት ። | ፲፭ | ዕቃውን ሁሉ ቀንዲሎቹን የመብራቱንም ዘይት ። |
| ወምሥዋዐ ዘዕጣን፡ ወመፃውርቲሁ፡ ወቅብዐ ዘይት ቀብዕ፡ ወዕጣነ ዘየዓጥኑ፡ ወመክደነ ሞኅተ ዘደብተራ ። | ፲፮ | የዕጣኑን መሠውያ (ጽንሐሕ) መሎጊያዎቹን የሚቀቡትንም ዘይት የሚያጥኑትን ዕጣንም ለደብተራ ኦሪት ደጃፍ የሚሆን መጋረጃ ። ዘፀ፡ ፴ ፳፫ ። |
| ወምሥዋዐ ዘመሥዋዕት፡ ወሰቅሰቀ ዘብርት፡ ዘሎቱ መፃውርቲሁ፡ ወኵሎን ንዋያቲሁ፡ ወማእከከ ንዋያቲሁ፡ ወማእከከ ምስለ መንበሩ ። | ፲፯ | ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆን መሠውያውን የናሱንም መከታ መሸከሚያዎቹን ዕቃዎቹን ሁሉ የመታጠቢያው ሰኑን ዳካውን ከነ መቀመጫው ። |
| ወመንጦላዕተ ዓፀድ፡ ወአዕማዲሁ፡ ወምዕማዲሆን፡ ወመክደነ አንቀጸ ዓፀድ መታክሊሁ ለደብተራ፡ ወመታክለ ዓፀድ፡ ወአውታሪሆን ። | ፲፰ | የአደባባዩን መጋረጃ ምሰሶዎቹን እግሮቹንም የአደባባዩን ደጃፍ መጋረጃ የድንኳን ካስማዎች የአደባባዩን ካስማዎችና አውታሮቹንም ። |
| ወአልባሲሁ ለአሮን ካህን፡ ወአልባሰ ደቂቁ ዘክህነ ቶሙ፡ ወአልባሰ በዘይገብሩ በውስተ መቅደስ ። | ፲፱ | በመቅደስ ውስጥ ለማገልገል በብልሃት የተሠሩም የክህነ የአሮን ልብሶችን በክህነት ለማገልገል የተቀደሱ የልጆቹንም ልብሶች ። ዘፀ፡ ፴፩ ፲ ። |
| ወወፅኡ ኵሉ ማኅበሮሙ ለደቂቀ እስራኤል እምኅበ ሙሴ ። | ፳ | የእስራኤል ልጆች ማኅበሮችም ሁሉ ከሙሴ ፊት ወጡ ። |
| ወአምጽአ አሐዱ አሐዱ በከመ ሐለየ በልቡ፡ ወበከመ ፈቀደ በነፍሱ አምጽአ መበአ ለእግዚአብሔር ለኵሉ ግብረ ደብተራ ዘመርጡል፡ ወለኵሉ መፍቅዳ፡ ወለኵሉ አልባስ ዘመቅደስ ። | ፳፩ | አንዱ አንዱም ልቡ እንዳሰበውና መንፈሱም እንደ ወደደው ለእግዚአብሔር መባውን አመጣ፡ ለመገናኛው ድንኳን ሥራ ሁሉ ለሚያስፈልገው ሁሉ ለመቅደስም ልብሶች ሁሉ ። ዘፀ፡ ፴፱ ፩ - ፵፩፡ ዘኍ፡ ፬ ፭ - ፮ ። |
| ወአምጽኡ እደው ዘእምኅበ አንስትኒ ዘከመ ፈቀደ ልቦን ማኅተማተ ወአውጻበ፡ ወኅልቀታተ፡ ወሐብላታተ ወአውቃፈ፡ ወኵሎ ሠርጕ ዘወርቅ ። | ፳፪ | ወንዶችም ከሴቶች ዘንድ ልቡናቸው ያሰበውን ማርዳዎችን ንፎ መንደልቶን (ሎቲዎች) ቀለበቶችን ድሪዎችን አምባሮችን የወርቅ ጌጦችንም ሁሉ አመጡ ። |
| ወኵሎ አምጽኡ ወርቀ መበአ ለእግዚአብሔር፡ ወኵሉ ብእሲ ዘረከበ ያክንተ፡ ወኅብረ ከብድ፡ ወለየ ክዑበ ወቢሦስ ክዑበ፡ ወፀጕረ ጠሊ፡ ወማእሰ በግዕ ግቡረ መሐን፡ ወማእሰኒ ዘሥርየቱ ኅብረ ያክንት ። | ፳፫ | ሁሉም የወርቅን ስጦታ ሁሉ ለእግዚአብሔር አቀረቡ፡ ሰማያዊ ሐርን ሐምራዊ ሐርን ቀይ ግምጃን ዕጽፍ ሁኖ የተፈተለ ቢጫ ሐርን የፍየል ፀጕርም የበሕር ዓረብም ሰማያዊ ኅብረ ቀለም የገባ ብሕረ ዓረብም (የአስፋጣ ቄርበት) አመጡ ። |
| ወአብእ ኵሉ ዘበጽዐ ብጽዐተ፡ ብሩረ ወብርተ መበአ ለእግዚአብሔር ወእምኅበ ተረክበ ዕፀ ዘኢይነቅዝ ለኵሉ ምግባረ መፍቅዳ ለደብተራ አምጽኡ ። | ፳፬ | ስለት የተሳለ ሁሉ የብርን የነሐስን ስጦታ ሁሉ ለእግዚአብሔር መባ አድርጎ አቀረበ፡ የማይነቅዝ ዕንጨት ከተገኘ ዘንድ ለደብተራ ኦሪት ማገልገያ የሚያስፈልገውን ሁሉ አመጡ ። ፩ ዜና መዋ፡ ፳፱ ፰ ። |
| ወብእሲትኒ እንተ ትክል ፈቲለ በእደዊሃ አምጽአት ፈትለ ዘያክንት፡ ወኅብረ ከብድ፡ ወለይ፡ ወቢሦስ ። | ፳፭ | በእጅዋ መፍተልን የምትችል ሴትም የሰማያዊውን የሐምራዊውን የቀይና የቢጫውን ሐር ፈትል አመጣች ። |
| ወኵሎን አንስት እለ ሐለያ በልበን፡ ወበጥበብ ፈተላሁ ለፀጕረ ጠሊ ። | ፳፮ | (እንስጥ ብለው) በልቡናቸው ያሰቡ ሴቶችም ሁሉ አመጡ፡ የፍየሉንም ጠጕር በብልሀት በጥበብ ፈተሉት። |
| ወመላእክትኒ አምጽኡ አእባነ መረግድ፡ ወአእባነ ዘይትኄረው ለኤፉድ ዘላዕለ መትከፍት ወለሎግዮ ። | ፳፯ | አለቆችም የዕንቍ ደንጊያዎች (እብነ በረድ) ለኤፉድና ለደረት ኪስ የሚገቡት ፈርጦችን ። |
| ወቅብዐ ማኅቶት፡ ወቅብዐ ዘይትቀብዑ፡ ወዕጣነ ዘየዓጥኑ ። | ፳፰ | ለመብራት ዘይትን ለቅብዐት ሽቱን ለሚያጥኑት ጣፋጭ ዕጣንን አመጡ ። ፩ ዜና መዋ፡ ፳፱ ፮ ። |
| ወኵሉ ብእሲ ወብእሲት ዘፈቀደ ልበሙ ከመ ያብኡ ወይግበሩ ኵሎ ግብረ ዘአዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ አምጽኡ ደቂቀ እስራኤል መበአ ለእግዚአብሔር ። | ፳፱ | ወንዶችና ሴቶች ሁሉ ልቡናቸው የፈቀደውንና እግዚአብሔር በሙሴ ቃል ያዘዘውን ሥራ ሁሉ ይሠሩ ዘንድ የእስራኤል ልጆች ለእግዚአብሔር ስጦታን አመጡ ። |
| ወይቤሎሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል ናሁ ጸውዖ እግዚአብሔር በስሙ ለበስልኤል ወልደ ኡሬ ወልደ ሖር | ፴ | ሙሴም የእስራኤልን ልጆች እነሆ እግዚአብሔር ከነገደ ይሁዳ የሆነውን የሖር የልጅ ልጅ የኡሬ ልጅ ብስል |

ዘእምነገደ ይሁዳ ።

ኤልን በስሙ ጠራው አላቸው ። ፩ ዜና መዋ፡ ፳፪ ፱ ።

፴፩ ወመልአ መንፈሰ እግዚአብሔር፣ ወጥበበ፣ ወልቡና፣ ወአእምሮ፣ ከመ ይኩን ሊቀ ላዕለ ኵሉ ጸረብት ።

በሥራ ሁሉ በጥበብም በማስተዋልም በዕውቀትም የአናጢዎች ሁሉ አለቃ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔርን መንፈስ ተመላ ። ዘፀ፡ ፴፩ ፪ ።

፴፪ ወይግበር ኵሎ ምግባረ፣ ወይግበር ወርቀኒ ወብሩረኒ ወብርተኒ ።

ሥራውን ሁሉ ይሠራ ዘንድ በወርቅ በብርና በናስም ይሠራ ዘንድ ። ዘፍ፡ ፵፩ ፴፰፣ ኢዮብ ፴፪ ፰ ።

፴፫ ወይግበር ኪነ ዕንቍኒ ወዕፀኒ፣ ወይግበር ኵሎ ግብረ በጥበብ ወይምሀር ።

በፈርጥ የሚሆነውን የዕንቍ ድንጋይ ይቀርፅ ዘንድ ዕንጨቱንም ይጠርብ ዘንድ በብልሃት የሚሠራውን ሥራ ሁሉ ይሠራ ዘንድና ያስተምርም ዘንድ ።

፴፬ ወወደየ ውስተ ልቡ ሎቱኒ ወለኤልያብ ወልደ አክሴምክ ዘእምነገደ ዳን ።

እርሱና የነገደ ዳን የሆነው የአክሴምክ ልጅ ኤልያብን ያስተምሩ ዘንድ በልቡናቸው አሳደረባቸው ።

፴፭ ወመልአሙ ጥበበ ልብ፣ ከመ ያእምሩ ግቢረ ኵሎ ምግባረ መቅደስ፣ ዘይትአነም ከመ ይእንሙ በያክንት፣ ወበኅብረ ከብድ፣ ወበለይ ክዑብ፣ ወቢሦስ ወከመ ይግበሩ ኵሎ ግብረ ጽርበት ዘዘዚአሁ ።

የመቅደስን ሥራ ሁሉ መሥራትን ይሠሩ ዘንድ በሰማያዊ ሐር በሐምራዊ ሐር ዕጽፍ ሁኖ በተፈተለ ቀይ ሐር በብሩሕ ሐር የሚሠራውን ሥራ ሁሉ ያውቁ ዘንድ ልዩ ልዩ የአጠራረብም ሥራ ሁሉ ይሠሩ ዘንድ የማስተዋል ጥበብን መላባቸው ።

## ምዕራፍ ፴፮ ።

፩ ወገብሩ በስልኤል ወኤልያብ፣ ወኵሎሙ ጠቢባነ ልብ እለ ተውህበ ሎሙ ጥበብ ወአእምሮ፣ ከመ ይግበሩ ኵሎ ግብረ መቅደስ ዘይትፈቀድ፣ ኵሎ ዘአዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

የሚፈለገውን ለመቅደስ ማገልገያ ሥራ እንዲሠሩ ጥበብና ዕውቀት የተሰጣቸው በስልኤልና ኤልያብ የልብ ዕውቀት ያላቸውም ሁሉ እግዚአብሔር በሙሴ ቃል ያዘዘውን ሁሉ ሠሩ ። ዘፀ፡ ፳፰ ፫፣ ኢሳ፡ ፳፰ ፳፮ ።

፪ ወጸውዖሙ ሙሴ ለበስልኤል ወለኤልያብ ወለኵሎሙ እለ በሙ ጥበብ ዘወሀበሙ እግዚአብሔር አእምሮ ውስተ ልበሙ ወለኵሎሙ እለ በፈቃደ ልበሙ ይገብሩ፡ ከመ ይግበሩ ወከመ ይሑሩ ውስተ ዝንቱ ግብር ከመ ይፈጽምዎ ።

ሙሴም በስልኤልና ኤልያብን እግዚአብሔር በልባቸው ጥበብን ዕውቀትን የሰጣቸው ሁሉ ሥራውን ለመሥራት በልቡናቸው ፈቃድ የተነሣሡትን ሁሉ ሥራውን ሠርተው ይፈጽሙ ዘንድ ጠራቸው ።

፫ ወነሥኡ እምቅድመ ሙሴ መባአ ዘአብኡ ደቂቀ እስራኤል ለኵሉ ምግባረ መቅደስ ከመ ይግበሩ፣ ወእሙንቱሂ ይትዌከፉ ዓዲ ዘያበውኡ እምኀበ እለ ያመጽኡ ነግሀ ነግሀ ።

የእስራኤል ልጆች ይሠሩ ዘንድ ለመቅደስ ሥራ ያመጡትን ስጦታ ሁሉ ከሙሴ ፊት ተቀበሉ፣ እነሱም በፈቃዳቸው ያቀረቡትን ዕለት ዕለት ወደርሱ ያመጡ ነበር ።

፬ ወመጽኡ ኵሎሙ ጠቢባን እለ ይገብሩ ግብረ መቅደስ አሐዱ አሐዱ በበምግባሪሁ ዘይገብር፣ ይቤልዎ ለሙሴ ብዙኀ መባአ ዘያበውኡ ሕዝብ እምግብር ዘአዘዘ እግዚአብሔር ከመ ይትገበር ።

የመቅደሱንም ሥራ የሚሠሩ ጠቢባን ሁሉ አንዱም አንዱም እንደየሥራው በመሥራት መጥተው፣ እግዚአብሔር ይደረግ ዘንድ ካዘዘው ሥራ እጅግ የበዛ ስጦታ ሕዝቡ አመጡ ብለው ለሙሴ ነገሩት ።

፭ ወአዘዘ ሙሴ ወሰበከ ውስተ ትዕይንት ለእድኒ ወለአንስትኒ ወይቤ እምይእዜ ኢይግበሩ መባአ ዘመቅደስ ።

ሙሴም ወንድም ሴት ለመቅደስ ስጦታ ከዚህ የበለጠ የሚያመጣ አይኑር ብሎ በሰፈሩ አዘዘ፣ (አወጀም) ።

፮ ወተከልአ ሕዝብ እምአብኦ፣ እስመ አከሎሙ ለምግባር ዘይገብሩ፣ ወተርፎሙ ።

ሕዝቡም ስጦታን ከማቅረብ ተከለከለ፣ ያመጡት ነገር ሥራን ለመፈጸም በቅቶ ተርፏቸዋልና ።

፯ ወገብሩ ኵሎሙ ጠቢባነ ልብ፣ ምግባረ ደብተራ ዐሠርተ አዕፃደ እምቢሦስ ክዑብ፣ ወእምያክንት ወኅብረ ከብድ፣ ወለይ ክዑብ፣ ወኪሩቤነ ገብሩ በምግባረ ምእናም ።

በልባቸው ብልሃተኞች የሆኑ ሁሉ የድንኳኑን ሥራ ከተፈተለ ከጥሩ በፍታ ከሰማያዊና ከሐምራዊ ሐር ከቀይ ግምጃም ዓሥር መጋረጃዎችን ሠሩ፣ ከእነርሱም በላይ ብልሀ ሠራተኛ በሚሠራው አሠራር ኪሩቤልን አደረጉባቸው ። ዘፀ፡ ፳፮ ፩፣ ምሳ፡ ፲ ፰ ።

፰ ወኑኁ ለአሐዱ ዓፀድ ዕሥራ ወሰመንቱ በእመት፣ ወርኅቡ ርብዕ በእመት ለአሐዱ ዓፀድ፣ በመስፈርቱ ከማሁ ለኵሎሙ አዕፃድ ።

ያንዱም መጋረጃ ርዝመት ሃያ ስምንት ክንድ፣ ወርዱም አራት ክንድ ለአንዱ መጋረጃ ነው፣ የመጋረጃዎቹም ሁሉ እንዲሁ በዚያው ልክ ነው ።

፱ ወኀምስተ አዕፃደ አስተሳመኩ በበይናቲሆሙ አሐደ ምስለ ካልኡ፣ ወኀምስተ አዕፃደ አስተሳመኩ በበይናቲሆሙ ።

አምስቱንም መጋረጃዎች አንዱን ካንዱ ጋር እርስ በርሳቸው አጋጠሙ፣ ደግሞም አምስቱ መጋረጃዎች እንዲሁ አንዱን ካንዱ ጋር አገናኙ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወገብሩ ኀምሳ መማስጠ ዘያክንት ላዕለ ክንፈረ አሐዱ ዓፀድ፣ እምጽንፉ በዘየኃብር፣ ወከማሁ ኀምሳ መማስጠ ገብሩ በክንፈረ ዓፀድ ካልእ በዘየኃብሩ ። | ፲ | በአንዱ መጋረጃ ክፈፍ ላይ ከሰማያዊ ሐር አምሳ ቀለበቶችን ከመጋረጃው ጫፍ እንዲጋጠሙ አደረጉ፣ እንዲሁም በሁለተኛው መጋረጃ ክፈፍ አምሳ ቀለበቶች እንዲጋጠሙ አደረጉ ። |
| ወገብሩ ኀምሳ ሞፃዳተ ዘወርቅ ወአኀበሩ አዕፃዳተ አሐደ ምስለ ካልኡ በሞፃዳት፣ ወኮነ ደብተራሁ አሐደ ። | ፲፩ | አምሳ የወርቅ መያያዦችን ሠሩ፣ መጋረጃዎቹንም እርስ በርሳቸው በመያያዦች አያያዙዋቸው ድንኳኑም አንድ ሆነ ። |
| ወገብሩ ዐውርተ ወአሐደ አዕፃደ ዘሠቅ ዘይሜውሮ እምላዕሉ ለደብተራ ። | ፲፪ | ከድንኳኑም በላይ ዓሥራ አንድ መጋረጃዎችን ከፍየል ጠጕር አደረጉ ። |
| ወለለአሐዱ ዓፀድ ኑኁ ሠላሳ በእመት፣ ወርኅቡ ርብዕ በእመት፣ ለለአሐዱ ዓፀድ ከማሁ በአምጣኒሆሙ ። | ፲፫ | ለያንዳንዱም መጋረጃ ርዝመቱ ሠላሳ ክንድ ለያንዳንዱም መጋረጃ ወርዱ እንዲሁ አራት ክንድ ሁኖ መጠናቸው ትክክል ነው ። |
| ወአኀበሩ ኀምስተ አዕፃደ በበይናቲሆሙ፣ ወሰብዕተ አዕፃደ አኀበሩ በበይናቲሆሙ ። | ፲፬ | አምስቱንም መጋረጃች ርስ በርሳቸው ሰባቱንም መጋረጃች ርስ በርሳቸው አንድ አድርገው አጋጠሙዋቸው ። |
| ወገብሩ ኀምሳ መማስጠ ላዕለ ክንፈረ አሐዱ ዓፀድ በጽንፉ በዘየኀብሩ ። | ፲፭ | ከተጋጠሙትም መጋረጃች በአንደኛው መጋረጃ ዘርፍ ላይ አምሳ ቀለበቶችን አደረጉ ። |
| ወኀምሳ መማስጠ ገብሩ ላዕለ ክንፈረ ዓፀድ ካልእ በዘየኀብሩ ። | ፲፮ | ከተጋጠሙትም መጋረጃዎች በሁለተኛው መጋረጃ ዘርፍ ላይ አምሳ ቀለበቶችን አደረጉ ። |
| ወገብሩ ኀምሳ ሞፃዳተ ዘብርት በዘየኀብሩ ከመ ይኩን አሐደ ። | ፲፯ | ድንኳኑም አንድ እንዲሆን ያጋጥሙት ዘንድ አምሳ የናስ መያያዦችን ሠሩ ። |
| ወገብሩ ዘይከድኖ ሰውቀ ማእሰ በግዕ ሕሡየ፣ ወከማሁ ገብሩ ለሱሉ ። | ፲፰ | ለድንኳኑም መደረቢያ የለፋ የበግ ቁርበት አደረጉ፣ ከዚያም በላይ ሌላ መደረቢያ ከአስቆጣ ቁርበት አደረጉ ። |
| ወገብሩ አዕማደ ዘደብተራ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ዘዐሥር በእመት ቆሙ ለአሐዱ ዓምድ፣ ወርኅቡ እመት ወመንፈቀ እመት ። | ፲፱ | ለድንኳኑም ከማይነቅዝ ዕንጨት የሚቆሙትን ሳንቆች አደረጉ፣ ለአንዱም ሳንቃ ርዝመቱ አሥር ክንድ፣ ወርዱ አንድ ክንድ ተኩል ነው ። |
| ወመሰምከተ ሥረዊሁ ክልኤቱ ለአሐዱ ዓምድ፣ እንዘ ይሰመክ አሐዱ ምስለ ካልኡ፣ ወከማሁ ገብሩ ለሱሉ አዕማደ ደብተራ ። | ፳ | ለያንዳንዱም ሳንቃ አንዱን ከሌላው ጋር የሚያያይዙ ሁለት ማጋጠሚያዎች ነበሩ፣ ለድንኳኑም ሳንቆች ሁሉ እንዲሁ አደረጉ ። |
| ወገብሩ ዕሥራ አዕማደ እምገጸ አዜብ ። | ፳፩ | በደቡብም ወገን ሃያ ሳንቆችን አደረጉ ። |
| ወገብሩ ሎሙ ለዕሥራ አዕማድ አርብዐ ስከተታተ ዘብሩር፣ ክልኤቱ ስከተቱ ለአሐዱ ዓምድ በክልኤሆሙ ገጻቲሁ ወክልኤቱ ስከተቱ ለአሐዱ ዓምድ በክልኤሆሙ ገጻቲሁ ። | ፳፪ | ለሃያውም ሳንቆች አርባ የብር እግሮችን አደረጉ፣ ለአንድ ሳንቃ በሁለት ወገኑ ሁለት እግሮች በአንድ ወገኑም ሁለት እግሮች ነበሩት፣ ከያንዳንዱም ሳንቃ በታች ሁለት ማጋጠሚያዎች ሁለት እግሮች ነበሩ ። |
| ወእምክልእ ገጸ ደብተራ መንገለ ሰሜን ገብሩ ዕሥራ አዕማደ ። | ፳፫ | ለድንኳኑ በሁለተኛው ወገን በሰሜን በኩል ሃያ ሳንቆችን አደረጉ ። |
| ወስከተቶሙ አርብዓ ዘብሩር ለለአሐዱ ዓምድ፣ ወክልኤቱ ስከተቱ እምክልኤቱ ገጻቲሁ ። | ፳፬ | ለያንዳንዱም ሳንቃ አርባ የብር እግሮች አደረጉ፣ ከእያንዳንዱም ሳንቃ በታች ሁለት እግሮች አደረጉ ። |
| ወእምድኅር እምገጸ ደብተራ መንገለ ባሕር ገብሩ ሰብዓተ አዕማደ ። | ፳፭ | በምዕራብም በኩል በስተኋላ ከድንኳኑ ፊት ለፊት ሰባት ሳንቆችን አደረጉ ። |
| ወክልኤተ አዕማደ ገብሩ ዓዲ ለመዓዝነ ተብተራ እምድኅር ። | ፳፮ | ዳግመኛም ለማደሪያው ከሁለት ማዕዝን በስተኋላ ሁለት ሳንቆች አደረጉ ። |
| ወዕሩየ ኮኑ ወኀብሩ እምታሕቱ እስከ ላዕሉ፣ ወከማሁ ገብሩ ለክልኤሆን መዓዝን ። | ፳፯ | ትክክል የሆኑ ከታችም እስከ ላይ እስከ አንደኛው ቀለበት ድረስ አንድ ሳንቃ ድርብ ነበረ፣ ለሁለቱም ማዕዝን እንዲሁ አደረጉ ። |
| ወኮኑ ሰመንቱ አዕማድ ወምዕማዲሆሙ ዓሡሩ ወስሱ ዘብሩር፣ ወለለአሐዱ አሐዱ ዓምድ ክልኤቱ ክልኤቱ ምዕማዱ ። | ፳፰ | ስምንት ሳንቆችና ዓሥራ ስድስቱ የብር እግሮቻቸው ከእያንዳንዱ ሳንቃ በታች ሁለት ሁለት እግሮች ነበሩ ። |
| ወገብሩ መናሥግተ ለአዕማደ ደብተራ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ። | ፳፱ | ለድንኳኑ ሳንቆች ከማይነቅዝ ዕንጨት መወርወሪያዎችን አደረጉ ። |

፴ ኃምስተ መናሥግተ እምአሐዱ ገጽ ወኃምስተ መናሥ
ግተ እምክልኢ ገጽ፣ ወኃምስተ መናሥግተ ዘመንገለ ባሕር።

፴፩ ወገብሮ ለመንሥግ ዘማእከል ከመ ይዕዱ በማእከለ
ኢዕማድ እምጽንፍ ኀበ ጽንፍ ።
፴፪ ወለአዕማድ ወለመማስጡ ወለመናሥግቲሁ ቀፈል
ዎሙ ወርቀ ።
፴፫ ወገብሩ መንጦላዕተ ዘያክንት ወኅብረ ክብድ፣ ወለይ
ክዐብ፣ ወቢሦስ ፍቱል፣ ወገብሩ በግብረ ምእናም ኪሩቤነ።

፴፬ ወገብሩ ላቲ አርባዕተ አዕማደ ዕምዕዕ ዘኢይነቅዝ፣
ወቀፈልዎሙ ወርቀ ወአርእስቲሆሙኒ ዘወርቅ ።
፴፭ ወገብሩ ሎሙ አርባዕተ ምእማደ ዘብሩር ።
፴፮ ወገብሩ ላቲ መንጦላዕተ ዘይከድኖ ለኆኅተ ደብተራ፣
እምያክንት ወኅብረ ክብድ ወለይ ክዐብ፣ ወቢሦስ ፍቱል
በብዑድ ግብረት ።
፴፯ ወገብሩ ላቲ ለመንጦላዕት ኃምስተ አዕማደ እምዕዕ
ዘኢይነቅዝ፣ ወቀፈልዎሙ ወርቀ፣ ወአርእስቲሆሙኒ ዘወ
ርቅ፣ ወገብሩ ሎሙ ኃምስተ ምዕማደ ዘብርት ።

## ምዕራፍ ፴፯ ።

፩ ወገብረ ባስልኤል ታቦተ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ዘካዕበ
እመት ወመንፈቀ እመት ኑኃ፣ እመት ወመንፈቀ እመት
ራኅበ፣ እመት ወመንፈቀ አመት ቆሙ ።
፪ ወቀፈላ ወርቀ ንጹሐ እምውስጣ ወእምአፍአሃ፣ ወገ
ብረ ላቲ ቀጸላ ወርቅ በዓውዳ፣ ወገብረ በውስቴታ ማዕበለ
ዘወርቅ ዘኖፃዳት እምዓውዳ ።
፫ ወሰበከ ላቲ ዕበነ አርባዕተ ዘወርቅ ወአንበሮን ላዕለ
አርባዕቱ ምስማካቲሃ፣ ዕበነ ክልኤ ውስተ አሐዱ ምስ
ማክ፣ ወዕበነ ክልኤ ውስተ ዳግም ምስማክ ።
፬ ወገብረ ላቲ መፃውርተ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ወቀፈ
ሎሙ ወርቀ ።
፭ ወአብአ ድንባዛቲሃ ውስተ እልኩ ዕበን አርባዕ፣ እለ
ውስተ ምስማክ ዘታቦት፣ መሳክሚሃ ለታቦት በዘይሰክ
ምዋ በሙ ።
፮ ወገብረ ላቲ ተድባበ ዘወርቅ ንጹሕ፣ ዘካዕበ እመት
ወመንፈቀ እመት ኑኑ፣ እመት ወመንፈቀ እመት ራኅቡ ።
፯ ወገብረ ላቲ ክልኤተ ኪሩቤነ ዘወርቅ ፍሑቅ፣ ወገብሮሙ
እምክልኤቱ ምስማካቲሁ ለተድባብ አሐዱ ኪሩብ እም
ለፌ፣ ወአሐዱ ኪሩብ እምለፌ እምስማካቲሁ ለተድባብ ።

፰ ወኮኑ ኪሩቤን ይረብቡ ክነፊሆሙ እመልዕልት እንዘ
ይጼልሉ ክነፊሆሙ መልዕልተ ተድባብ፣ ወገጾሙ ይትና
ጸር በበይናቲሆሙ በዲበ ተድባብ ።
፱ ወገብረ ማእደ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ኑኑ ክዕበ እመት፣
ወራኅቡ እመት፣ ወቆሙ እመት ወመንፈቀ እመት ።

፲ ወቀፈሎ ወርቀ ንጹሐ፣ ወገብረ ሎቱ ቀጸላ ዘወርቅ
በዓውዱ ።

በማደሪያውም በአንደኛው ወገን አምስት መወር
ወርያዎች በሁለተኛውም ወገን አምስት መወርወርያዎች
በምዕራቡም ወገን አምስት መወርወርያዎችን አደረጉ ።
መካከለኛውንም መወርወርያ በሳንቆቹ መካከል ከዳር
እስከ ዳር እንዲያልፍ አደረገው ።
ሳንቆቹንም ቀለበቶቹንም መወርወርያዎቹንም በወርቅ
ለበጡዋቸው ።
መጋረጃውንም ከሰማያዊ ከሐምራዊ ከተፈተለ ቀይ
ሐርና ከብሩህ ሐር በርሱም ላይ በሽማኔነት አሠራር ኪሩ
ቤልን አደረጉበት ።
ከማይነቅዝም ዕንጨት አራት ምሰሶዎችን አደረጉላት
በወርቅም ለበጡዋቸው፣ ኵላቦቻቸውም የወርቅ ነበሩ ።
ለነሱም አራት የብር ምዕማዶች (እግሮች) አደረጉ ።
የድንኳኑንም ደጃፍ የሚሸፍን ከሰማያዊና ከሐምራዊ
ከቀይ ግምጃና ከተፈተለም ከጥሩ በፍታ በልዩ አሠራር
የተሠራ መጋረጃን አደረጉ ።
ለመጋረጃውም ከማይነቅዝ ዕንጨት አምስት ምሰሰ
ዎች አደረጉላት በወርቅም ለበጡዋቸው ኵላቦቻቸውም
የወርቅ ናቸው አምስት የናስ እግሮችንም አደረጉላቸው።

## ምዕራፍ ፴፯ ።

በስልኤል ከማይነቅዝ ዕንጨት (ግራር) ታቦትን ርዝ
መቱ ሁለት ክንድ ተኩል፣ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል
ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል ሠራ ።
በውስጥም በአፍአም በጥሩ ወርቅ ለበጣት፣ በዙርያ
ዋም የወርቅ አክሊል አደረገላት፣ በዙርያዋ ላሉ ቀለበ
ቶች መቋሚያ ሊሆን ለከንፈርዋ የወርቅ ፈሰስ አወጣላት ።
አራት የወርቅ ቀለበቶችንም አደረገላት፤ ባራት እግ
ሮቿም አኖራቸው፣ በአንድ ወገን ሁለት ቀለበቶች በሌላ
ውም ወገን ሁለት ቀለበቶች ።
መሎጊያዎቹንም ከማይነቅዝ ዕንጨት ሠርቶ በወርቅ
ለበጣቸው ። ዘኍ፣ ፬ ፯ ።
ታቦቷንም በነሱ ለመሸከም በታቦቱ አጠገብ ባሉቱ
አራት ቀለበቶች መሎጊያዎቹን አገባ ።

መክደኛውንም ከጽሩ ወርቅ ሠራ፣ ርዝመቱም ሁለት
ክንድ ተኩል፣ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል ነው ።
ሁለቱንም ኪሩቤል ከተመታ ወርቅ ሠራ፣ በመክደኛ
ውም ላይ በሁለት አደረጋቸው፣ ከሥርየት መክደኛውም
ጋር አንዱን ኪሩብ በአንድ ወገን ሁለተኛውን ኪሩብ በሌ
ላው ወገን አድርጎ በአንድ ላይ ሠራቸው ።
ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ወደ ላይ ዘርግተው የሥር
የት መክደኛውን በክንፎቻቸው ሸፈኑ፣ እርስ በርሳቸ
ውም በመክደኛው ላይ ፊት ለፊት ይተያዩ ።
ከማይነቅዝም ዕንጨት ርዝመቱ ሁለት ክንድ ወርዱም
አንድ ክንድ፣ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል የሆነ ገበ
ታን (ማእድን) ሠራ ። ሚል፣ ፩ ፯ - ፲፪ ።
በጥሩ ወርቅም ለበጠው በዙርያውም የወርቅ አክ
ሊል አደረገለት ።

፲፩ ወገብረ ማዕበለ ዘወርቅ በዓውዱ መጠነ አርባዕቱ አፃባዕ፥ ወገብረ ለቀጸላሁ ዕበነ አርባዕተ፥ ወገብረ ናፃዳተ ዘማዕበል ለቀጸላሁ ።

፲፪ ወገብረ አርባዕተ አውቃፋተ ዘወርቅ፥ ወአንበሮን ዲበ አዕባን ውስተ አርባዕቱ ፍና፥ ዘእገሪሁ መንገለ ቀጸላሁ ።

፲፫ ወከኑ አዕባኒሁ አብያተ ለመፃውሪሁ ዘያነሥእ ማእደ፤

፲፬ ወገብረ መፃውርቲሁ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ፥ ወቀፈሎሙ ወርቀ ንጹሐ ከመ ያንሥኡ በሙ ማእደ ።

፲፭ ወገብረ ንዋያተ ዘማእድ መጽብሐ፥ ወአጽሕልተ፥ ወመዳምሀ፥ ወመዋጽሐ በዘበቱ ያወጽሑ ዘወርቅ ።

፲፮ ወገብረ መራናተ እምወርቅ ንጹሕ ፍሑቅ፥ ገብራ ለመራናት ዓምዳ ወአብራዒሃ፥ ወመአኃዚሃ፥ ወክበበ ርእሳ፥ ወጽጌያቲሃ እምኔሃ ተገብሩ ።

፲፯ ሰብዓቱ አብራዕ እለ ይወጽኡ እምገበሃ ለተቀዋመ ማኅቶት፥ ሠለስቱ አብራዕ እምአሐዱ ፍናሃ፥ ወሠለስቱ አብራዕ እምክልኢ ፍናሃ ።

፲፰ ወሠለስቱ መአኃዚሃ እለ የኀብሩ ምሳሌ ለአሐዱ ክበበ ርእስ ጽጉይ፥ ከማሁ ለሰብዓቲሆሙ አብራዕ፥ እለ ይወጽኡ እምተቀዋመ ማኅቶት ።

፲፱ ወለተቀዋመ ማኅቶት መአኃዚሃ አርባዕቱ፥ ወጽጌያቲሃ ወክበበ ርእሳ ወክበብ መትሕተ ክልኤቱ ።

፳ ክበበ ርእሳ ወአብራዒሃ እምኔሃ ከኑ ኵሎሙ ፍሑቅ እምአሐዱ ወርቅ ንጹሕ ።

፳፩ ወገብረ መኃትዊሃ ሰብዓተ፥ ወገብረ ዕዋዓቲሃ ወበዘያሜንይዋ ዘወርቅ ወለኵሉ ንዋያቲሃ መክሊተ ወርቅ ገብራ ።

፳፪ ወገብረ ምሥዋዐ ዘዕጣን እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ዘእመት ኑኁ፥ ወእመት ራኅቡ፥ ርቡዐ ገብሮ ።

፳፫ ወክዕበ እመት ቆሙ፥ ወእምኔሁ ተገብሩ አቅርንቲሁ ።

፳፬ ወቀፈሎ ወርቀ ንጹሐ ምድሮ ወዓውደ አረፍቱ፥ ወአቅርንቲሁ ።

፳፭ ወገብረ ሎቱ ቀጸላ ዘወርቅ በዓውዱ፥ ወክልኤተ አውቃፋተ ወርቅ ገብረ ሎቱ መትሕተ ቀጸላሁ ላዕለ ክልኤቱ ገበዋቲሁ፥ ዘይከውኑ አብያተ ለመፃውሪሁ ከመ ያንሥኡ በሙ ኪያሁ ።

፳፮ ወገብረ መፃውርቲሁ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ፥ ወቀፈሎሙ ወርቀ ።

፳፯ ወገብረ ቅብዐ ዘይትቀብዑ እምዘይት፥ ወአፈዋተ ቅድወ፥ ጽሩጠ ዘጸዐጢ ።

ምዕራፍ ፴፰ ።

፩ ወገብረ ምሥዋዐ ለመሥዋዕት እምዕፅ ዘኢይነቅ ዘኀምስቱ በእመት ኑኁ፥ ወኀምስቱ በእመት ራኅቡ፥ ርቡዐ ክነ፥ ወሠልሰ በእመት ቆሙ ።

፲፩ በዙርያውም አንድ ጋት የሚያኽል የወርቅ ፈሰስ አዘረበት በክንፈሩም ዙርያ አራት ቀለበቶችን አደረገለት፥ ለክፈፉም መያዣዎችን ሠራለት ።

፲፪ ለእክሊሉም አራት ቀለበት አደረገለት፥ ቀለበቶቹንም አራቱ እግሮቹ ባሉበት በአራቱ ማዕዘኖች አኖራቸው ።

፲፫ ገበታውንም ለመሸከም መሎጊያዎቹ እንዲሸከሙባቸው ቀለበቶች በክፈፉ አጠገብ ነበሩ ።

፲፬ ገበታውን ይሸከሙባቸው ዘንድ መሎጊያዎቹንም ከማይነቅዝ ዕንጨት ሠርቶ በጥሩ ወርቅ ለበጣቸው ።

፲፭ ለማፍሰሻም ይሆኑ ዘንድ በገበታው ላይ የሚኖሩትን ዕቃዎች ወጭቶችን ጭልፋዎችን ጽዋዎችን መቅጃዎችን ከጥሩ ወርቅ ሠራቸው ።

፲፮ መቅረዞችንም ከተመታ ጥሩ ወርቅ አደረጋቸው መቅረዙንም ከእግሩና ከአገዳው ጋር ፅዋዎቹ ጕብጉቦቹና አበቦቹ ከዚያው ተሠሩ ።

፲፯ ለመብራቱም መቅረዝ በስተጐኑ ሰባት ቅርንጫፎች ወጡለት፥ ሦስቱ ቅርንጫፎች በአንድ ወገን ሦስቱም ቅርንጫፎች በአንድ ወገን ወጡ ።

፲፰ በአንደኛው ቅርንጫፍ ጕብጉቡንና አበባውን ሦስትም የለውዝ አበባ የሚመስሉትን ፅዋዎች በሁለተኛው ቅርንጫፍ ጕብጉቡንና አበባውን እንዲሁም ከመቅረዙ ለሚወጡ ለሰባቱ ቅርንጫፎች አደረገ ።

፲፱ በመቅረዙም ጕብጉቦቹንና አበቦቹን አራትም የለውዝ አበባ የሚመስሉትን ጽዋዎች አደረገ ።

፳ ጕብጉቦችና ቅርንጫፎቹም ከርሱ ጋር አንድ ነበሩ፥ ሁሉም አንድ ሁኖ ከተቀረፀ በጥሩ ወርቅ ተሠርቶ ነበር ።

፳፩ ሰባቱንም መብራቶች ፅዋዎችንም መኰስተሪያዎቹንም የኵስታሪ ማድረጊያዎቹንም ከጥሩ ወርቅ ሠራ መቅረዙንም ዕቃውንም ሁሉ ከአንድ መክሊት ጥሩ ወርቅ አደረገ ።

፳፪ ከማይነቅዝም ዕንጨት ርዝመቱ አንድ ክንድ ስፋቱ አንድ ክንድ አራት ማዕዝን የሆነ የዕጣን መሠውያን ሠራ ።

፳፫ ከፍታውም ሁለት ክንድ ነበረ፥ ቀንዶቹም ከሱ ጋር የተሠሩ ነበሩ ።

፳፬ ላይኛውንና የግድግዳውን ዙርያ ቀንዶቹንም በወርቅ ለበጠው ።

፳፭ በዙርያውም የወርቅ ክፈፍ አደረገለት፥ ከክፈፉም በታች ሁለት የወርቅ ቀለበቶች ሠርቶ በሁለት ጐኑ አደረጋቸው፥ እሱን ያነሡባቸው ዘንድ ለመሎጊያዎቹ ስራፍ ነበሩ ።

፳፮ መሎጊያዎቹንም ከማይነቅዝ ዕንጨት ሠርቶ በወርቅ ለበጣቸው ።

፳፯ የሚቀቡትንም ቅባት ከዘይት አደረገ፥ ጥሩውንም የጣፋጭ ሽቱ ዕጣን በቀማሚ ብልሃት የተቀመመ አደረገ።

ምዕራፍ ፴፰ ።

፩ ርዝመቱ አምስት ክንድ፥ ወርዱም አምስት ክንድ ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆን ከማይነቅዝ ዕንጨት ሠራ ከፍታውም ሦስት ክንድ ሆኖ አራት ማዕዝን ነበር ።

፪ ወገብረ አእጋሪሁ ውስተ አርባዕቱ መዓዝኒሁ ወእምኔሁ ይእቲ ምቅዋማቲሁ ።

እግሮቹንም በአራት ማዕዝኑ አደረገ፤ ማቆሚያዎቹም ከርሱ ጋር አብረው የተሠሩ ነበሩ ።

፫ ወገብረ ሎቱ አቅርንተ ዲበ አርባዕቱ መዓዝኒሁ፤ ወእምኔሁ ወጽኡ አቅርንቲሁ ወቀፈሎ ብርተ ።

ቀንዶችንም በአራት ማዕዝኑ አደረገለት፤ ቀንዶቹም ከርሱ ጋር በአንድነት የተሠሩ ናቸው፤ በናስም ለበጠው ።

፬ ወገብረ ኵሎ ንዋያተ ምሥዋዕ ምግኅሣተ፤ ወጸኅራተ ወፍያላተ ወመኆስሳተ ወመሳውደ እሳት ኵሎ ገብረ እምብርት ።

የመሠውያዎቹንም ዕቃዎች ሁሉ፤ ምንቸቶቹን መጫሪያዎቹን፤ ድስቶቹን፤ ሜንጦቹንና የእሳት ማንደጃዎቹን ሁሉ ከናስ አደረገ ።

፭ ወገብረ መጥበስተ ለመሥዋዕት ስቅሉቀ፤ ከመ መሥገርተ ዓሣ ዘብርት ።

እንደ ዓሣ መረብ ሁኖ የተሠራም ለመሠውያው መጥበሻ የናስ መከታ አደረገ ።

፮ ወገብረ ሎቱ ለመጥበስት አርባዕተ ኅልቀታተ ዘብርት ውስተ አርባዕቱ መዓዝኒሁ ።

ለመጥበሻውም አራት የናስ ቀለበቶችን በአራት ማዕዝኑ አደረገለት ።

፯ ወአንበሮ ለመጥበስት በቤተ መሥዋዕት ታሕተ ወከነ በመንፈቀ ቤተ መሥዋዕት ።

መከታውንም እስከ መሠውያው እኩሌታ ይደርስ ዘንድ ከመሠውያው ቤት በታች አኖረው ።

፰ ወሰበከ አርባዕተ አውቃፋተ ዘብርት ለአርባዕቱ መዓዝኒሁ ከመ ይኩኑ አብያተ ለመፃውርቲሁ ።

ለመሎጊያዎቹም ሥፍራ ይሆኑ ዘንድ ለአራቱ ማዕዝኖች አራት የናስ ቀለበቶችን ሠራ ።

፱ ወገብረ መፃውርተ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ፤ ወቀፈሎሙ ብርተ ወአብአ መፃውርቲሁ ውስተ አውቃፋት ዘላዕለ ገበዋቲ ምሥዋዕ ከመ ያንሥኡ በሙ ኪያሁ ፍሉግ ሰሌዳ ገብሮ ።

መሎጊያዎቹን ከማይነቅዝ ዕንጨት ሠርቶ በናስ ለበጣቸው፤ መሎጊያዎቹንም እሱን ይሸከሙባቸው ዘንድ በመሠውያው ጐን ላይ ባሉት ቀለበቶች ውስጥ አገባ፤ ከሳንቆቹም ሠርቶ ክፍት አደረገው ።

፲ ወገብረ ማእከከ ዘብርት ወመንበሩሂ ዘብርት፤ ወአንበሮ በአንጻረ አንስት እለ ይመጽኡ ከመ ይጸልዩ ኀበ አንቀጸ ደብተራ ዘመርጡል በዘይትሐፀቡ ቦቱ ።

መቅለዱንና እግር ዘቀኑውን ከናስ ሠርቶ (ሌዋውያን) በሚታጠቡበት በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ሊጸልዩ በሚመጡ ሴቶች አንጻር አኖረው ።

፲፩ ወገብረ ላቲ ዐፀደ ለደብተራ መንገለ አዜብ እንተ የማን ወመንጦላዕተ ዓፀድ እምቢሶስ ክዑብ ወኑኁ ምእት በእመት ።

ለደብተራ ኦሪት በስተደቡብ በቀኝ በኩል አደባባይ ሠራ፤ የአደባባዩም መጋረጃ ርዝመቱ መቶ ክንድ የሆነ፤ ዕፁፍ ሁኖ ከተፈተለ ብጫ ሐር የተሠራ ነው ።

፲፪ ወአዕማዲሁ ዕሥራ ዘብሩር ወምዕማዲሆሙ ዕሥራ ዘብርት ።

ሃያ የብር ምሰሶዎችንና ሃያ የብርት ምዕማዶችን ሠራ ።

ውኖፃዳቲሆሙ ወጥነፊሆሙ ለአዕማድ ዘብሩር ።

ለምሰሶዎቹም ኵላቦቻቸውንና ዘንጎቻቸውን ከብር አደረገ ።

፲፫ ወለመንገለ ሰሜን መንጦላዕቱ ምእት በእመት ኑኁ ።

በስተ ሰሜንም መቶ ክንድ ርዝመት ያለው መጋረጃን አደረገ ።

፲፬ ወአዕማዲሁ ዕሥራ ዘብሩር ወምዕማዲሆሙ ዕሥራ ዘብርት ውኖፃዳቲሆሙ ወጥነፊሆሙ ለአዕማድ ዘብሩር ።

ሃያ የብር ምሰሶዎችንና የናስ እግሮችንም ሠራ፤ ለምሰሶዎቹም የብር ኵላቦችንና ዘንጎችን አደረገ ።

፲፭ ወዘመንገለ ባሕር መንጦላዕቱ ኀምሳ በእመት ኑኁ፤ አዕማዲሆሙ ዐሠርቱ ዘብሩር ወምዕማዲሆሙ ዐሠርቱ ዘብርት ።

በስተ ምዕራብም ርዝመቱ አምሳ ክንድ ያለውን መጋረጃ ሠራ፤ ዓሥር ምሰሶዎቹ ከብር፤ ዓሥር እግሮቹ ከናስ የተሠሩ ነበሩ ።

፲፮ ውኖፃዳቲሆሙ ወጥነፊሆሙ ለአዕማድ ዘብሩር ።

የምሰሶዎቹም ኵላቦችና ዘንጎች የብር ነበሩ ።

፲፯ ወዘመንገለ ጽባሕ መንጦላዕቱ ኀምሳ በእመት ኑኁ፤ ወአዕማዲሁ ዐሠርቱ ዘብሩር፤ ወምዕማዲሆሙ ዐሠርቱ ዘብርት ።

በስተ ምሥራቅም ርዝመቱ አምሳ ክንድ ያለውን መጋረጃ ሠራ፤ ከብር የተሠሩ ምሰሶዎቹ ዓሥር ከናስ የተሠሩ እግሮቹም ዓሥር ነበሩ ።

፲፰ ዐሠርቱ ወኀምስቱ በእመት ኑኁ ለመንጦላዕት እምገጸ አሐዱ ምስማክ፤ አዕማዲሁ ሠለስቱ፤ ወምዕማዲሆሙ ሠለስቱ ።

በአንዱም ወገን ርዝመቱ ዓሥራ አምስት ክንድ ምሰሶዎቹም ሦስት ምዕማዶቹም ሦስት ነበሩ ። ፪ ዜና፡ ፫ ፲፬ ።

፲፱ ወእምከልእ ምስማክ፤ ዐሠርቱ ወኀምስቱ በእመት ኑኁ ለመንጦላዕት፡ አዕማዲሁ ሠለስቱ ወምዕማዲሆሙ ሠለስቱ፤ ወኵሉ መንጦላዕተ ዓፀድ ዘዓውድ እምቢሶስ ።

በሁለተኛውም ወገን ርዝመቱ ዓሥራ አምስት ክንድ ያለውን መጋረጃ አደረገ፤ ምሰሶዎቹም ሦስት የምሰሶዎቹ ምዕማድም ሦስት ነበሩ፤ በአደባባዩ ዙርያ ያለው መጋረጃ ሁሉ ከጥሩ በፍታ የተሠራ ነው ።

፳ ወኵሉ አዕማድ ዘዐፀድ ወአርእስቲሆሙ ቅፉላን በብሩር፤ ወምዕማዲሆሙ ዘብርት ።

የአደባባዩም ምሰሶች ሁሉና ክበሶቻቸው በብር የተለበጡ ነበሩ፤ ምዕማዶቻቸውም ከናስ የተሠሩ ናቸው ።

| | | |
|---|---|---|
| ወለአንቀጸ ዓፀድ መንጦላዕቱ ዕሥራ በእመት ኑኁ፤ በያክንት ወኅብረ ክብድ ወለይ ክዑብ ወቢሦስ ክዑብ ወብዑድ ኮነ በግብረ መርፍእ ። | ፳፪ | ሃያ ክንድ የሆነ የአደባባዩም ደጅ መጋረጃ ከሰማያዊና ከሐምራዊ ሐር፣ ከቀይ ግምጃ ከጥሩ በፍታም በልዩ ጥልፍ አሠራር የተሠራ ነበር ። |
| ወቆሙ ኆምስቱ በእመት እመንገለ ራኀቡ ከመ መንጦላዕተ ዐፀድ ። | ፳፫ | ርዝመቱ አምስት ክንድ፣ ቁመቱም እንደ አደባባዩ መጋረጃ አምስት ክንድ ነበር ። ዘፀ፡ ፴፩ ፩-፯ ። |
| ወአዕማዲሁ አርባዕቱ ዘብሩር ወምዕማዲሆሙ አርባዕቱ ዘብርት፡ ወኵሉ መኃክለ ደብተራ ዘዐውደ ዓፀድ ዘብርት ። | ፳፬ | አራት ምሰሶዎቹ ከብር አራት ምዕማዶቹም ከናስ የተሠሩ ነበሩ፤ በደብተራ አሪት ዙርያ ያሉ ካስማዎች ሁሉ የናስ ነበሩ ። |
| ወኪመዝ ሥርዓታ ለደብተራ መርጡል ዘከመ ተአዘዘ ሙሴ እምእግዚአብሔር ከመ ይኩኖሙ ግብሮሙ ለሌዋውያን በእደ ይታምር ወልደ አሮን ካህን ። | ፳፭ | ሙሴ ከእግዚአብሔር እንደ ታዘዘው ለሌዋውያን ማገልገያ እንዲሆናቸው በካህኑ በአሮን ልጅ በይታምር የተቈጠረው የደብተራ አሪት ዕቃ ድምር ይህ ነው ። ዘሌ ፭ ፲፩፤ |
| ወባስልኤል ወልደ ኡሪ ወልደ ሑር ዘእምነገደ ይሁዳ ገብረ ኵሎ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ። | ፳፮ | ከነገደ ይሁዳ ወገን የሆነ የሑር የልጅ ልጅ የኡሪ ልጅ ባስልኤል እግዚአብሔር ለሙሴ እንዳዘዘው ሁሉን ሠራ ። |
| ወምስሌሁ ኤልያብ ወልደ አክሴምክ ዘእምነገደ ዳን ዘከነ ሊቀ ኪነት ዘበምእናም ወዘበመርፍእ ወበዘአሥቅ፤ ከመ ይእንም በያክንት ወበኅብረ ክብድ ወበለይ ክዑብ ወቢሦስ ክዑብ ። | ፳፯ | በሽማኔነት በግብረ መርፌና በጥልፍ ሥራ የጥበብ አለቃ የሆነ የዳን ነገድ ወገን የአክሴምክ ልጅ ኤልያብም በሰማያዊ በሐምራዊ ዕፅፍ ሁኖ በተፈተለ ቀይ ግምጃና በብጫ ሐር ይሠራ ዘንድ ከርሱ ጋር ነበር ። |
| ወኵሉ ወርቅ ዘመበእ ዘተገብረ ለምግባረ ደብተራ፤ ኮነ ዕሥራ ወተስዓቱ መክልይ ወሰብዓቱ ምእት ወሠላሳ ሰቅል በሰቅል ቅዱስ ። | ፳፰ | የደብተራ አሪት ሥራ የተሠራበት የመባው ወርቅ ሁሉ በቤተ እግዚአብሔር አዋቂ ሚዛን ሃያ ዘጠኝ መክሊት ሰባት መቶ ሠላሳ ወቄት ሆነ ። ዘፀ፡ ፳፯ ፲፱-፳፩ ። |
| ወብሩርኒ ዘመበአ ዘአስተፋቀዱ እምትዕይንት፤ ምእት መክልይ፡ ወዓሠርቱ ምእት ወሰብዓቱ ምእት ሰብዓ ወኀምስቱ ሰቅል በሰቅል ቅዱስ ። | ፳፱ | ከከተማው አቆጣጠረው ያመጡት እስራኤል መባ አድርገው ያቀረቡት ብርም በመቅደሱ ሰቅል ሚዛን መቶ መክሊት፣ ሺሕ ሰባት መቶ አምስት ወቄት ሆነ ። |
| ዘአስተዋጽኡ በበርእሶሙ አሐተ አሐተ ዲድርክመ፤ ወአሐቲ ዲድርክም መንፈቁ ለሰቅል ። | ፴ | በየራሳቸው ያዋጡትም ገንዘብ አንድ አንድ ወቄት ነው ይኸውም አንድ ድሪም አቀመት የሰቅል ግማሽ ነው ። |
| ወኵሉ ዘሖረ ውስተ ፍቅድ ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ስሳ እልፍ ወሠላሳ ምእት ወኀምስቱ ምእት ወኀምሳ ። | ፴፩ | ይህንም ገንዘብ ለመስጠት ሊቈጠር የሄደው ሰው ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ የሆነው ስሳ እልፍ ከሦስት ሺሕ አምስት መቶ አምሳ ነበር ። |
| ወተገብረ ኀክቱ ምእት መክልይ ዘብሩር ለምዕማደ አዕማድ ዘደብተራ፤ ወለምዕማደ አዕማድ ዘመንጦላዕት ። | ፴፪ | ይኸውም መቶው የብር መክሊት ለደብተራ አሪት ምሰሶዎች ከባስ ለመጋረጃው ምሰሶዎችም እግር ተሠራላቸው ። ዕዝ፡ ፱ ፰፤ ኢሳ፡ ፳፪ ፳፬። |
| ምእት መክልይ ለምእት ምዕማድ፤ በበሐቲ መክሊት ለለሐቲ ርእስ ። | ፴፫ | ይህም መቶው መክሊት ለመቶው ከባሶች ለያንዳንዲቱ መክሊት በያንዳንዲቱ ራስ ላይ ነው ። |
| ወለኀክቱ ዐሠርቱ ምእት ወሰብዐቱ ምእት ወሰብዓ ወኀምስቱ ሰቅል ገብርዎ ለአዕማደ ዓፀድ ። | ፴፬ | ይህንም ሺሕ ከሰባት መቶ ሰባ አምስቱን ወቄት ለዙርያ ቅጥሩ አዕማድ ከባስ አድርገው ሠሩት ። |
| ወከነ ብርት ዘመበእ አርባዕቱ ምእት ወሰብዓ መክልይ ወዕሥራ ምእት ወአርባዕቱ ምእት ሰቅል ። | ፴፭ | ለእግዚአብሔር መባ ሆኖ የገባው ብርቱም አራት መቶ ወቄት ሁለት ሺሕ አራት መቶ ሰቅል ነው ። |
| ወገብረ እምኔሁ መንበረ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወምሥዋዐ ዘመሥዋዕት ። | ፴፮ | ሙሴም ከዚህ ብረት ለደብተራ አሪት ደጃፍ መድረክ መሥዋዕት የሚሠዋበትን መሠውያን አደረገ ። |
| ወመጥበስተ ወኵሎ ንዋየ ምሥዋዕ ወመንበረ ዓፀድ ዘዓውድ ። | ፴፯ | መሥዋዕቱ የሚጠበስበት መጥበስትን፣ የምሥዋዑን ሥራ ሁሉ ሠራበት ። |
| ወመንበረ አንቀጸ ዓፀድ ወኵሎ መታክለ ደብተራ ወመታክለ ዓፀድ ዘዓውድ ። | ፴፰ | በዙርያው ላለውም ቅጥር አዕማድ፣ ለዙርያ ቅጥሩም በር መድረክ፣ ለደብተራ አሪትም ካስማ በዙርያ ላለው ሽማ ቅጥርም ካስማ ሠራለት ። |
| ምዕራፍ ፴፱ ። | | ምዕራፍ ፴፱ ። |
| ወዘተርፈ ወርቅ ዘመበእ ተገብረ ንዋየ በዘይገብሩ ቅድመ እግዚአብሔር። | ፩ | ለመባ ከገባው ወርቅ የተረፈው ወርቅ ግን በእግዚአብሔር ፊት በሚሠሩበት ገንዘብ ሌላ ዕቃ ተሠራበት። |

፪ ወእምነ ያክንት ወኅብረ ክብድ ወለይ ወቢሦስ ተገብረ አልባስ ለመልእክተ መቅደስ ።

ከሰማያዊ ከሐምራዊና ከቀይ ሐር ከብጫ ሐርም በመቅደስ ለማገልገል ልብስ ተሠራ ።

፫ ወገብሩ አልባሰ ቅዱሰ ለአሮን በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘውም የተቀደሰውን ልብስ ለአሮን ሠሩለት ።

፬ ወገብሩ ኤፉደ በወርቅ ወበያክንት ወበኅብረ ክብድ ወበለይ ክዐብ፡ ወቢሦስ ክዐብ ።

ኤፉድንም በወርቅ በሰማያዊ ሐር፥ በሐምራዊ ሐር ዕፅፍ ሁኖ ከተፈተለ ከብጫ ሐርና ከቀይ ግምጃ አደረጉ።

፭ ወገብሩ ቈጽለ ዘወርቅ ወሰጠቅዎ ወገብርዎ ከመ ይትፈተል ምስለ ያክንት ወምስለ ኅብረ ክብድ ወምስለ ለይ ክዐብ ወምስለ ቢሦስ ክዐብ ።

ወርቁንም እንደ ቅጠል አሳስተው እየሰነጠቁ ከሰማያዊ ከሐምራዊ ከቀይና ከብጫ ሐር ጋር እየተሸረበ እንዲፈተል አደረጉት ።

፮ ወገብርዎ ልብሰ መትከፍት ዘይወርድ ውስተ ክልኤሆን መታክፈሁ ወአነሙ ክልኤተ ኤጲሞሳተ እምኔሆሙ እለ ይትላጸቁ በክልኤቱ ገበዋቲሁ ።

በሁለቱ ጫንቃዎቹ የሚወርድ ልብሰ መትከፍትን ሠሩ፥ ከአራቱ ኅብርም በሁለት ወገኖቹ የሚገናኙ ሁለት ቀሚሶችን ሠሩ ። ኢሳ፡ ፲፩ ፭፡ ራዕ፡ ዮሐ፡ ፩ ፲፫ ።

፯ ወለትብልያሰ ዘልብሰ መትከፍት አነምዎ እምኔሆሙ በከመ አነሙ ኪያሃ በወርቅ ወበያክንት ወበኅረ ክብድ ወበለይ ክዐብ ወቢሦስ ክዐብ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ኤፉን በወርቅ በሐምራዊ በሰማያዊ በብጫና በቀይ ግምጃ እንደሠሩ የልብሰ መትከፉን መታጠቂያ አድርገው ሠሩት ።

፰ ወገብሩ እእባነ መረግድ ወአውደድዎሙ ምስለ ወርቅ ወገለፍዎሙ ከመ ግልፈተ ማኅተም በበአስማቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

የመረግድ (ዕንቊ) ድንጊያዎችንም ሠርተው ከወርቅ ጋር አስማምተው እንደ ማኅተም ቅርጽ አድርገው የእስራኤል ልጆች ስም ቀረፁባቸው ። ኢያ፡ ፬ ፯፡ ነህ፡ ፪ ፳።

፱ ወአንበርዎሙ ዲበ ኤጲሞስቲሃ ለልብሰ መትከፍት ለአዕናቍ ዘተዝካሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ዘከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

ለእስራኤል ልጆች የመታሰቢያ ድንጋዮች ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው አድርገው ዕንቆቹን በኤፉዱ ጫንቃ ቀሚሶች ላይ አኖሩዋቸው ።

፲ ወገብሩ ልብሰ ሎግዮ ግብረ ምእናም እሡቅ ከመ ግብረተ ልብሰ መትከፍት በወርቅ ወበያክንት ወበኅብረ ክብድ ወበለይ ክዐብ ወቢሦስ ክዐብ ርቡዕ ወውጡሕ ውእቱ ።

የደረቱን ኪስ እንደ ኤፉድ አሠራር ብልሃት ሥራ በወርቅ በሰማያዊ በሐምራዊ በቀይና በብጫ ሐር ሠሩት፥ ምዕዙንና ድርብም አደረጉት ። ሕዝ፡ ፳፰ ፲፫ ።

፲፩ ወልብሰ ሎግዮ እመት ኑኁ ወእመት ራኅቡ፥ እንዘ ውጡሕ ውእቱ ወተአንመ ውስቴቱ አርባዕቱ ሶታ እንመት ዘአዕናቍ ።

የደረቱን ኪስ (ልብሰ ሎግዮ) ድርብ ሁኖ ርዝመቱ ክንድ ወርዱም ክንድ ነበረ፥ በርሱም አራት ተራ የአዕናቊ ፈርጥ አደረጉበት ።

፲፪ አሐዱ ሶታ በሰርድዮን ወበጳዝዮን ወበመረግድ ።

አንደኛው ተራ ሰርድዮን፥ ጳዝዮን መረግድ ።

፲፫ ወካልእ ሶታ ዘኅብሩ ከመ ፍሕም ወሰንፔር ወኢያሰጲድ ።

ሁለተኛው ተራ እንደ ፍም መልክ ያለ ዕንቊ ሰንፔር ኢያሰጲድ ።

፲፬ ወሣልስ ሶታ በለግርዮን ወበአካጥስ ወበአሜቴስጢኖስ።

ሦስተኛው ተራ በለግርዮን (ያክንት) ኬልቄዶን አሜቴስጢኖስ ።

፲፭ ወራብዕ ሶታ በዕንቍ ዘኅብረ ወርቅ ወቢረሌ ወበሦም፥ ወዓውዶሙ በወርቅ እሱር ።

አራተኛው ተራ ወርቅማ ዕንቊ ቢረሌ ሦም ሲሆኑ እሊህ ሁሉ በወርቅ ፈርጥ የተያዙ ናቸው ።

፲፮ ወውእቶሙ አዕናቍ በበአስማቲሆሙ ለዐሠርቱ ወክልኤቱ ደቂቀ እስራኤል ወግሉፋን ከመ ግልፈተ ማኅተም ለለአሐዱ በበስሞሙ ።

እነዚህም ዕንቆች በዓሥራ ሁለቱ የእስራኤል ልጆች ስም ለያንዳንዱም በየስማቸው እንደ ማኅተም አቀራረፅ የተቀረፁ ናቸው ።

፲፯ ወገብሩ ሎቱ ለልብሰ ሎግዮ ሰናስለ ጽፉረ በግብረት ፍቱል ወበወርቅ ንጹሕ ።

ለደረቱም ኪስ የተጐነጐኑትን ድሪዎች እንደ ገመድ አድርገው ከጥሩ ወርቅ ሠሩለት ።

፲፰ ወገብሩ ክልኤተ ክበበ ጥውዮ ዘወርቅ፥ ወክልኤተ ኅልቀታተ ወርቅ ወወደይዎን ለውእቶን ኅልቀታት ውስተ ክልኤሆን ጽንፈሁ ለልብሰ ሎግዮ ።

ሁለት የወርቅ ፈርጦችን ሁለት የወርቅ ቀለበቶችንም ሠርተው እሊያን ሁለት ቀለበቶች በሁለት የደረት ኪስ ጫፎች አደረጉዋቸው ።

፲፱ ወወደይዎ ለዝክቱ ጽፍሮ ወርቅ ላዕለ እልክቱ ኅልቀታት እልክቱ ኅልቀታት እምክልኤሆሙ ገበዋቲሁ ለልብሰ ሎግዮ ወውስተ ክልኤሆሙ ማኅበርቱ ወክልኤቱ ጽፍሮ ።

ሁለቱንም የተጐነጐኑትን የወርቅ ድሪዎች በደረቱ ኪስ ወገኖች ወዳሉት ወደ ሁለቱ ቀለበቶች አደረጉ (አገቡ) ።

፳ ወአንበርዎን ላዕለ እልክቱ ክልኤ ክበበ ጥውዮ ወወደይዎን ማእከለ መታክፍቲሁ ለልብሰ መትከፍት አንጻረ ገጹ፤

ሁለቱንም የድሪ ጫፎች በሁለቱ ፈርጦች ውስጥ አግብተው በኤፉድ ጫንቃዎች ላይ ፊት ለፊት አደረጉዋቸው ።

፳፩ ወገብሩ ኅልቀታተ ወርቅ ወአንበርዎሙ ላዕለ ክልኤቱ

ሁለቱንም የወርቅ ቀለበቶች ሠርተው በኤፉዱ ፊት

ጽንፈሁ ለኤፉድ እምታሕቱ መንገለ ገጹ ኀበ ማኅበርቱ መልዕልተ እንመቱ ለልብሰ መትከፍት ።

ሐሬት ባለው በደረቱ ኪስ በሁለቱ ጫፎቹ ላይ አደረጉዋቸው ።

፳፪ ወአስተአኀዝዎ ለልብሰ ሎግዮ እምኀልቀታቲሁ ኀበ ኀልቀታተ ኤፉድ በረትለ ያክንት ከመ ይኩን ሳዕለ እንመተ ኤፉድ ፡ ከመ ኢያንጠልልል ልብሰ ሎግዮ እምልብሰ መትከፍት ዘከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

የደረቱን ኪስ በብልሃት ከተጠለፈው ከኤፉድ ቋድ በላይ እንዲሆን ፡ ከኤፉዱም እንዳይለይ የደረቱን ኪስ ከቀለበቶቹ ጋር ወደ ኤፉዱ ቀለበቶች በሰማያዊ ፈትል አያያዙት እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ።

፳፫ ወገብሩ ጸዴሬ በግብረ ምእናም ዘኵለንታሁ በያክንት ክዑብ ፡ ወአፈ መልበስቱ እምኔሁ በዓውዱ ወድማሬሁ እንዋ ከመ ኢይትበተክ ።

ኤፉዱን ቀሚስ ሁለንትናው በሸማኔ ሥራ አሠራር በሰማያዊ ሐር ሠሩት ፡ እንዳይቀደድም እንደ ጥሩር የተሠራ ጥልፍ በአንገትጌው ዙርያ ነበር ።

፳፬ ወገብሩ መልዕልተ ዓውዱ በልብሰ ጸዴሬ መትሕቴሁ ከመ ፍሬያተ ሮማን ሰበ ይጸጊ እምያክንት ወኀብረ ክቡድ ወለይ ክዑብ ወቢሶስ ክዑብ ።

በቀሚሱም ታችኛው ዘርፍ ከሰማያዊ ከሐምራዊ ከቀይ ግምጃና ከጥሩ ሐር እንደ ሮማን ፍሬዎች በዙርያው ላይ አደረጉ ።

፳፭ ወገብሩ ጸናጽላተ እምወርቅ ንጹሕ ወአንበርዎን ለጸናጽላት ማእከለ ሮማናት ዲበ ጽንፉ ለጸዴሬ እንተ ዓውዱ ።

ከጥሩ ወርቅም ጸናጽሎችን (ቃጭሎችን) ሠርተው ቃጭሎቹን በቀሚሱ ዙርያ ዘርፍ ላይ በሮማኖቹ መካከል አደረጉዋቸው ።

፳፮ ወበውስተ ሮማናት ጸናጽል አሐዱ ወሮማን አሐዱ ጸናጽል አሐዱ ወሮማን አሐዱ ፡ ጸናጽል አሐዱ ወሮማን አሐዱ በዘበቱ ይገብሩ ዘከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው የሚያገለግሉበትን አንድ ጸናጽል አንድ ሮማን ፡ አንድ ሮማን አንድ ጸናጽል አከታትለው በሮማኖቹ ውስጥ አደረጉ ።

፳፯ ወገብሩ አልባሰ ዘቢሶስ ግብረ ምእናም ለአሮን ወለደቂቁ ወአክሊለ ዘቢሶስ ፡ ወቆብዐ ዘቢሶስ ፡ ወድርማንቀ ዘቢሶስ ።

ለአሮንና ለልጆቹ እንደ ሸማኔ አሠራር ከነጭ ሐር መጠምጠሚያን ከነጭ ሐርም ቆብን ከነጭ የተልባ እግር ሰናፊልን ሠሩላቸው ። ኢሳ ፡ ፷፩ ፲ ፡ ሮሜ ፫ ፳፪ ።

፳፰ ወቅናታተ ዘቢሶስ ፡ ወዘያክንት ወዘኀብረ ክቡድ ወዘለይ ክዑብ ወእሡቅ ግብሩ ዘከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ከነጭ ሐር ፡ ከሰማያዊ ከሐምራዊ ከቀይ ግምጃ በጥሩ አሠራር የተሠሩ መታጠቂያዎችን ሠሩ ። ዘፀ ፡ ፳፰ ፬ ፴፱ ፡ ሕዝ ፵፬ ፲፰ ።

፳፱ ወገብሩ ቈጽለ ወርቅ ፍሉጠ እምወርቅ ንጹሕ ወጸሐፉ ላዕሌሁ መጽሐፈ በቅርፀተ ማኅተም ቅዱስ ለእግዚአብሔር ።

ከጥሩ ወርቅ የተለየ (የተቀደሰ) አሳስተው ሠርተው በላዩ ላይ እንደ ማኅተም ቅርፅ ለእግዚአብሔር ቅዱስ መባል ይገባል የሚል ጻፉበት ። ዘፀ ፡ ፳፰ ፴፪ ።

፴ ወወደዩ ሎቱ ነጽፈ ዘያክንት ከመ ይንበር መልዕልተ አክሊል ዘከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው በመጠምጠሚያው ላይ ያንጠለጥሉት ዘንድ ሰማያዊ ሐር አሠሩበት ።

፴፩ ወተፈጸመ ኵሉ ምግባረ ደብተራ ወገብሩ ደቂቀ እስራኤል ኵሉ ዘከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

የደብተራ ኦሪት ሥራ ሁሉ ተፈጸመ ፡ የእስራኤል ልጆችም እግዚአብሔር ለሙሴ ያዘዘውን ሁሉ ሠርተው ፈጸሙ ።

፴፪ ወአምጽእዋ ለደብተራ ኀበ ሙሴ ወለሠቃቲሃ ወለኵሉ ንዋያቲሃ ወለአዕማዲሃ ወለዐምዳቲሃ ወለመናሥግቲሆን ወለመከየዲሆን ።

ድንኳኒቱንም ዕቃዎቿን ሁሉ መደረቢያዎቿን ምሰሶዎቿን መያዣዎቿን መወርወሪያዎቿን የምሰሶዎቹን እግሮች ሁሉ ወደ ሙሴ አመጡ ። ዘፀ ፡ ፳፭ ፶ ።

፴፫ ወመክደንታቲሃ ዘአምእስተ በግዕ ወአምእስተ መጸጺት ወመንጦላዕተ ምክዳን ወታቦተ ስምዕ ።

ከአውራ በግ ቁርበት የተሠሩ መደረቢያዎች ከአስቆጣ ቁርበት የተሠሩ ማእሰ መጸጺቶች የሚሸፍነውንም መጋረጃ የምስክሩንም ታቦት ። ዕብ ፡ ፱ ።

፴፬ ወመፃውርቲሃ ወምስሐለ ወማእደ ምስለ ኵሉ ንዋያቲሁ ወኅብስተኒ ዘይሠርዑ ።

መሎጊያዎቿን የሥርየት መክደኛውን ገበታውን ከነ ዕቃዎቹ ሁሉ የሚያቀርቡትንም ኅብስት ።

፴፭ ወተቅዋመ ማኅቶት ንጽሕተ ወመኃትዊሃ ዘየኃትዉ በሙ ወኵሎ ንዋያቲሃ ።

የጸራውን መቅረዝ የሚያበሩባቸው ቀንዲሎቿን ዕቃዎቿን ሁሉ ።

፴፮ ወቅብዐ ማኅቶት ወምሥዋዐ ዘወርቅ ወቅብዐ ቡዘይት ቀብዑ ወዕጣነ ዘየዓጥኑ ።

የመብራቱን ዘይት የወርቅ መሠውያን የሚቀቡትንም ቅብዓ ቅዱስ የሚያጥኑትን ጥሩ ዕጣን ።

፴፯ ወመክደኒ ኆኅተ ደብተራ ወምሥዋዐ ዘብርት ወመጥበሰ ዘብርት ዘሎቱ ወለመፃውርቲሁ ወኵሎ ንዋያቲሁ ።

የደብተራ ኦሪትን ደጃፍ መጋረጃ የናሱን መሠውያ የናሱን መከታ (መጥበሻ) መሎጊያዎቹንና ዕቃውን ሁሉ ።

፴፰ ወማእከከ ምስለ መንበሩ ወመንጦላዕተ ዓፀድ ወአዕ

መታጠቢያን ከነመቀመጫው የአደባባዩን መጋረጃ ምሰ

ማዲሁ ወመከየዲሆን ።
፴፱ ወመክደኒ አንቀጸ ዓፀድ ወሐብላቲሁ ወመቻግሪሁ
ወመታክሊሁ ወኵሎ ንዋያተ ምግባረ ደብተራ ዘመርጡል ፤
፵ ወአልባሰ ቅድሳት ዘአሮን ወአልባሰ ደቂቁኒ ዘክህነ
ቶሙ ወዘተርፉ አልባሳተ ለምግባረ ደብተራ፣ ወመክደንተ
በሰድኒ ።

፵፩ በከመ ኵሉ ዘአዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ፣ ከማሁ
ገብሩ ደቂቀ እስራኤል ኵሎ ሥርዓቶ ።
፵፪ ወርእየ ኵሎ ዘተገብረ ዘገብሩ ዘከመ አዘዘ እግዚአብ
ሔር ከማሁ ተገብረ፣ ወባረኮሙ ሙሴ ።

ምዕራፍ ፵ ።

፩ ወተናገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ አመ ርእሰ
ሠርቅ ቀዳሚ ወርኅ ትተክላ ለደብተራ መርጡል ።

፪ ወታነብር ውስቴታ ታቦተ ዘስምዕ ወትከድና ለታቦት
በመንጦላዕት ።
፫ ወታበውእ ማእደ ወትሠርዕ በሥርዓቱ ወታበውእ
መራናተ ወትሠርዕ መኃትዊሃ ።

፬ ወታነብር ማዕጠንተ ዘወርቅ ቅድመ ታቦት ዘስምዕ
ወታነብር መንጦላዕተ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ።

፭ ወታነብሮ ለምሥዋዕ ዘመሥዋዕት በቅድመ ኆኅተ
ደብተራ ዘመርጡል ወታነብር ማእከከ ማእከለ ደብተራ
ወማእከለ ምሥዋዕ፣ ወትወዲ ውስቴቱ ማየ።

፮ ወትተክል ዓፀደ ዓውዱ ወታነብር መክደኒ አንቀጸ
ዐፀድ ።
፯ ወትነሥእ ቅብዐ ዘበቱ ይትቀበኡ ወትቀብዓ ለደብ
ተራ ወለኵሉ ዘውስቴታ ወትቄድሶ ኪያሃ ወኵሉ ንዋያ
ቲሃ ወትከውን ቅድስተ ።
፰ ወትቀብኦ ለምሥዋዕ ዘመሥዋዕት ወለኵሉ ንዋያቲሁ
ወትቄድሶ ለምሥዋዕ ወይከውን ውእቱ ምሥዋዕ ቅዱሰ
ቅዱሳን ወትቀብኦ ለማእከከ ወለመንበሩ ወትቄድሶ ።

፱ ወታቀርቦሙ ለአሮን ወለደቂቁ ኀበ ኆኅተ ደብተራ
ዘመርጡል ወተሐጽቦሙ በማይ ።
፲ ወታለብሶ ለአሮን አልባሰ ቅድሳት ወትቀብኦ ወትቄ
ድሶ ወይከውነኒ ክህነ ።
፲፩ ወታቀርቦሙ ለደቂቁኒ ወታለብሶሙ አልባሲሆሙ
ወትቀብኦሙ በከመ ቀባዕኮ አባሆሙ ወይከውኑኒ ካህናተ ።

፲፪ ወይከውኖሙ ዝንቱ ቅብዓት ዘክህነት ዘለዓለም ለት
ውልዶሙ ።
፲፫ ወገብረ ሙሴ ኵሎ ዘአዘዘ እግዚአብሔር ከማሁ ገብረ ።

፲፬ ወኮነ በቀዳሚ ወርኅ በካልእት ዓመት እምዘወጽኡ

ሰዎቹንና እግሮቻቸውን ።
የአደባባዩን ደጃፍ መጋረጃ ለስንሰሎቶቹን አውታሮቹን
ካስማዎቹን ለደብተራ ኦሪት የሚሆኑ ዕቃዎችን ሁሉ ።
በመቅደሱ ውስጥ ለማገልገል የተቀደሱትን የክህኑ
የአሮንን ልብሶች በክህነት ሊያገለግሉት የልጆቹንም ልብ
ሶች የቀሩትንም ለደብተራ ኦሪት ሥራ የሚሆኑ ልብሶችን
ሌላውን የሚሸፍኑባቸውንም፣ ወደ ሙሴ አመጡ ።
እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ሁሉ የእስራኤል
ልጆች ሥራውን ሁሉ እንዲሁ አደረጉ ።
ሙሴም የተሠራውን ሁሉ አየ፣ እነሆም እግዚአብሔር
እንዳዘዘው እንዲሁ እንደተደረገ አይቶ ባረካቸው ።

ምዕራፍ ፵ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፣ ከመ
ጀመሪያው ወር በፊተኛው ቀን የመገናኛውን ድንኳን
ትተክላለህ ። ዘፀ፡ ፲፪ ፪፣ ግብ፡ ሐዋ፡ ፯ ፴፬ ፵፫ ።
በርሷም ውስጥ የምስክሩን ታቦት ታኖራለህ ታቦቱ
ንም በመጋረጃ ትጋርዳለህ ። ዘኍ፣ ፬ ፭ ።
ገበታውንም አግብተህ በርሱ ላይ የሚኖረውን ዕቃ
ታሰናዳለህ መቅረዙንም አግብተህ ቀንዲሎቹን ትለኰ
ሳለህ ።
በምስክሩም ታቦት ፊት የወርቅ ማዕጠንትን ታኖራ
ለህ፣ በደብተራ ኦሪትም ደጃፍ ፊት መጋረጃውን ትጋ
ርዳለህ ።
ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆነውንም መሠውያ በመ
ገናኛው ድንኳን በማደሪያው ደጅ ፊት ታኖረዋለህ፣ የመ
ታጠቢያውንም ሰን በመገናኛው ድንኳንና በመሠውያው
መካከል አኑረህ ውኃ ትጨምርበታለህ ።
በዙርያውም አደባባዩን ትተክላለህ፣ የአደባባዩንም
(ወትተክል) ደጃፍ መጋረጃ ትዘረጋለህ ።
የሚቀቡትን ቅብዐ ቅዱስ ወስደህ ድንኳኑን በውስጧ
ያለውንም ሁሉ ቀባ፣ እርሱንም ዕቃዎቹንም ሁሉ ትቀድ
ሰዋለህ፣ ቅዱስም ይሆናል ። ዘፀ፡ ፴ ፳፫ - ፳፮ ።
ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆነውንም መሠውያና ዕቃ
ውንም ሁሉ ትቀብዋለህ፣ መሠውያውንም ትቀድሰዋለህ፣
መሠውያውም ቅዱስ ቅዱሳን ይሆናል፣ የመታጠቢያውን
ሰን መቀመጫውንም ቀብተህ ቀድሰው ። ዘፀ፡ ፳፱ ፴፮ ።
አሮንንና ልጆቹን ወደ መገናኛው ድንኳን አቅርበህ
በውኃ እጠባቸው ። ሌዋ፡ ፰ ፩ - ፲፫ ።
የተቀደሰውን ልብስ ለአሮን አልብሰው ቀብተህም
ቀድሰው እንዲገለግልም ይሆነኛል ። ዘፀ፡ ፳፰ ፵፩ ።
ልጆቹንም አቅርበህ ልብሶቻቸውን አልብሳቸው፣ አባ
ታቸውንም እንደ ቀባህ ቀባቸው፣ እነሱም አገልጋዮች
ይሆኑኛል ። መዝ፡ ፻፴፫ ፪፣ ዕብ፡ ፯ ፳፫ ።
ይህም የክህነት ቅብዓት ለልጅ ልጆቻቸው ለዘለዓለም
ይሆንላቸዋል ። ዘኍ፡ ፳፭ ፲፫ ፣ ዕብ፡ ፯ ፲፩ ።
ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሁሉ እንዲሁ
አደረገ ።
ከግብጽ አገር በወጡ በሁለተኛው ዓመት በመጀመ

| | | |
|---|---|---|
| እምድረ ግብጽ አመ ርእሰ ሠርቀ ወርኅ ተከልዋ ለደብተራ ፤ | | ርያው ወር ድንኳኒቱን ተከሏት ። |
| ወተከላ ሙሴ ለደብተራ ወአስተናበረ ምዕማዲሃ ወአቀመ አዕማዲሃ ወወደየ መናሥግቲሆን ። | ፲፭ | ሙሴ ድንኳኒቱን ተከላት፤ ምዕማዶቿንም አኖረ፤ ሳንቆቹን አቆመ፤ መወርወሪያዎቹንም አገባባቸው ። |
| ወአቀመ አዕማዲሃ ወሰፍሐ አዕፃዲሃ ለደብተራ ወአንበረ ሠቃተ ዲበ ደብተራ ። | ፲፮ | ምሰሶዎቹን አቆመ፤ የድንኳኑንም ፈርጅ ዘረጋ፤ መደረቢያዎቹም በድንኳኑ ላይ አደረገ ። |
| ወአንበረ መክደነ መልዕልተ ሠቅ ዘከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ። | ፲፯ | እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው በመደረቢያው ላይ መሸፈኛውን አኖረ ። |
| ወነሥአ ሙሴ ለመጻሕፍተ ትእዛዝ ወወደዮን ውስተ ታቦት ወአንበሮን ለመግውርት ውስተ አውታፋተ ታቦት ። | ፲፰ | ሙሴ የትእዛዛቱን መጻሕፍትን ወስዶ በታቦቱ ውስጥ አገባቸው፤ መሎጊያዎቹንም በታቦቱ ቀለበቶች አገባቸው ። |
| ወአንበሮ ለምስሐል መልዕልተ ታቦት ወአብአ ለታቦት ውስተ ደብተራ ። | ፲፱ | የሥርየት መክደኛውንም በታቦቱ ላይ አኖረው፤ ታቦቱንም ወደ ድንኳኑ ውስጥ አገባት ። |
| ወወደየ መክደና መንጦላዕተ ወሠወራ ለታቦተ መርጡል ዘከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ። | ፳ | እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው መክደኛዋን መጋረጃ አድርጎ ታቦቱን ሸፈናት ። ዘፀ፡ ፴፭ ፲፪ ። |
| ወአንበሮ ለማእድ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል መንገለ ገቦሃ ዘመስእ ለደብተራ እምአፍአሁ ለመንጦላዕት ። | ፳፩ | ገበታውን በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ከመጋረጃው ውጭ በደብተራ ኦሪት በሰሜን በኩል አኖረው ። |
| ወሠርዐ ውስቴታ ኅብስተ ቍርባን ቅድመ እግዚአብሔር ዘከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ። | ፳፪ | እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው የቍርባኑን ኅብስት በውስጧ በእግዚአብሔር ፊት አሰናዳ ። ዘፀ፡ ፳፭ ፴፯ ። |
| ወአንበራ ለመራናት ውስተ ደብተራ መርጡል አንጻረ ማእድ መንገለ አዜብ ለደብተራ ። | ፳፫ | መቅረዙንም በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ፊት ለፊት በድንኳኑ በስተ ደቡብ በኩል አኖረው ። |
| ወሠርዐ መኅትዊሃ ቅድመ እግዚአብሔር በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ። | ፳፬ | እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ቀንዲሎቹን በእግዚአብሔር ፊት አዘጋጀ ። ዘፀ፡ ፴ ፯ ። |
| ወአንበረ ማዕጠንተ ዘወርቅ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ቅድመ መንጦላዕት ። | ፳፭ | የወርቁንም ማዕጠንት በደብተራ ኦሪት ውስጥ ከመጋረጃው ፊት አኖረ ። ዘፀ ፳፯ ፴፯ ። |
| ወዐጠነ ውስቴቱ ዕጣነ ዘኀብረ ዘከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ። | ፳፮ | እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ያቀረበውን ዕጣን በውስጥ አጠነበት ። ዘፀ፡ ፳፱ ፴፰ ። |
| ወአንበሮ ለመክደነ ኆኅተ ደብተራ ወለምሥሥዋዕ ዘመሥዋዕት አንበሮ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ። | ፳፯ | በድንኳኑም ደጃፍ ፊት መጋረጃውን ዘረጋ፤ ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆነውን መሠውያ በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ፊት አኖረው ። |
| ወአዕረገ ላዕሌሁ መሥዋዕተ ወቍርባነ ዘከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ወአንበሮ ለማእከክ ማእከለ ደብተራ ወማእከለ ምሥዋዕ ። | ፳፰ | እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው በላዩ ላይ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ሠዋበት መታጠቢያውንም በድንኳኑና በመሠውያው መካከል አኖረው ። |
| ወወደየ ውስቴቱ ማየ ከመ ይትሐፀቡ ቦቱ አሮን ወደቂቁ እደዊሆሙ ወእገሪሆሙ ሶበ ይበውኡ ውስተ ደብተራ ወሶበ ይቀርቡ ኀበ ምሥዋዕ ዘከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ። | ፳፱ | እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው አሮንና ልጆቹ ወደ ደብተራ ኦሪት በሚገቡበትና ወደ መሠውያው በሚቀርቡበት ጊዜ እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን በርሱ ይታጠቡ ዘንድ ውኃን ጨመረበት ። ዘፀ፡ ፴ ፲፱ ። |
| ወአቀመ ዐፀደ በዐውደ ደብተራ ወምሥዋዕ ወአንበሮ ለምክዳነ አንቀጸ ዘዐፀድ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ | ፴ | ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው በድንኳኑና በመሠውያው ዙርያ አደባባይን አቆመ፤ (ተከለ) በአደባባዩም ደጃፍ መጋረጃ ዘረጋበት ። |
| ወፈጸመ ሙሴ ኵሉ ግብሮ ወከደና ደመና ለደብተራ መርጡል ወሰብሐተ እግዚአብሔር ተመልአት ደብተራ ። | ፴፩ | ሙሴ ሥራውን ሁሉ ሠርቶ እንደፈጸመ ደብተራ ኦሪትን የእግዚአብሔር ብርሃን ወርዶ ሸፈናት፤ ደብተራ ኦሪትም የእግዚአብሔር ክብር (ብርሃን) ተመላች ። |
| ወስእነ ሙሴ በዊአ ውስተ ደብተራ መርጡል እስመ ጸለላ ደመና ወሰብሐተ እግዚአብሔር ተመልአት ደብተራ ። | ፴፪ | ደብተራ ኦሪት ደመና ብርሃን ጋርዷታልና የእግዚአብሔርንም ብርሃን ተመልታለችና ሙሴ ወደ ደብተራ ኦሪት መግባት ተሳነው ። ዘኍ፡ ፲ ፲፩ ሰሎ፡ ፱ ፲፱ ። |
| ወአምከመ ሰሰለ ደመና እምላዕለ ደብተራ ይግዕዙ ደቂቀ እስራኤል በበነገዶሙ ። | ፴፫ | የደመናው ብርሃንም ከደብተራ ኦሪት በተነሣ ጊዜ የእስራኤል ልጆች በየነገዳቸው ይጓዙ ነበር ። |

ወእመሰ ኢተሰለ ደመና ኢይግዕዙ እስከ አመ ይሴሰል ደመና እስመ ደመና ይነብር ላዕለ ደብተራ መንፈቅ ።

ወእሳተ ይከውን ላዕሌሃ ሌሊተ ቅድመ ኵሉ እስራ ኤል በኵለሄ ኀበ ገዕዙ ።

፴፬ ደመናው ብርሃን ተነሥቶ ከልሄደ ግን ደመናው እስ ኪነሣላቸው ድረስ አይጓዙም ነበር፤ ደመናው ቀን በድ ንኳኑ ላይ ነበርና ። ዘፀ፡ ፲፫ ፳፩ ።

፴፭ ሌሊትም እስራኤል ሁሉ በተጓዙበት በታ ፊት በድ ንኳኑ ላይ እሳት ሁኖ ሰፍሮበት ይውል ነበርና ።

ተፈጸመ ኦሪት ዘፀአት፤
ወለእግዚአብሔር ክብር ወስብሐት፤
አሜን ።

የእስራኤልን መውጣት የሚናገር መጽሐፍ ተፈጸመ
ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ለዘለዓለሙ
አሜን ።

## ኦሪት ዘሌዋውያን

ስለ እስራኤል መውጣት ነገር ተናግሮ፤ የደብረ ሲናን የ፲ቱ ቃላትን የደብተራ ኦሪትን ሲገልጽ መጥቶ ነበርና፤ አሁን ደግሞ የክህናቱንና የመሥዋዕቱን ሕግና ወግ ለመናገር ያመጣዋል ። የሌዋውያንን የክህናቱን ሕግና ወግ የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው ።

አባቶቻችን ሠለስቱ ምእት ሊቃውንት ለመጻሕፍት ሁሉ አርእስት ሲሰጡ ለዚህም ይህን አርእስት ሰጥተውታል ። እርሱ ግን ነገሩን "ወጸውዖ እግዚአብሔር ለሙሴ„ ብሎ ይጀምራል ።